# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

## ዐሥራ አንደኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ጥር
፳፻፮ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዱ ፳፻፮ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

## ዐሥራ አንደኛ ክፍል

አድራሽ፡-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website;-www.zeorthodox.org

*የኮምፒዩተር ሌይ አውት ዲዛይን፡- ልደት አስፋው*
*0911-350439*

www.zeorthodox.org

### ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል፡፡

# መታሰቢያነቱ



በማይለዋወጥ አቋም ለአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊና መንፈሳዊ አገልግሎት መቃናት ፈር ለቀደዱ ለአባ ገብረ ትንሣኤ አብርሃ ይሁንልኝ።

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ። በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም።

www.zeorthodox.org

# ማውጫ


| ተ.ቁ | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም (አንድ) | 1 | | | |
| 2. | የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም (ሁለት) | 5 | | | |
| 3. | ወደ ሮሜ(አንድ) | 11 | | | |
| 4. | ወደ ሮሜ(ሁለት) | 16 | | | |
| 5. | ወደ ሮሜ(ሦስት) | 21 | | | |
| 6. | ወደ ሮሜ(አራት) | 26 | | | |
| 7. | ወደ ሮሜ(አምስት) | 31 | | | |
| 8. | ወደ ሮሜ(ስድስት) | 37 | | | |
| 9. | ወደ ሮሜ(ሰባት) | 41 | | | |
| 10. | ወደ ሮሜ(ስምንት) | 44 | | | |
| 11. | የቤ.ክ ታሪክ በ፩ኛው መ.ክ.ዘ(አንድ) | 47 | | | |
| 12. | የቤ.ክ ታሪክ በ፩ኛው መ.ክ ዘ(ሁለት) | 53 | | | |
| 13. | የቤ.ክ ታሪክ በ፩ኛው መ.ክ ዘ(ሦስት) | 59 | | | |
| 14. | የቤ.ክ ታሪክ በዓለም ከ፫-፮ኛ መ.ክ ዘ (አራት) | 65 | | | |
| 15. | የኢ.ቤ.ታ ከ፲፮-፳ኛ መ.ክ.ዘ (አንድ) | 69 | | | |
| 16. | የኢ.ቤ.ታ ከ፲፮-፳ኛ መ.ክ.ዘ (ሁለት) | 75 | | | |
| 17. | የኢ.ቤ.ታ ከ፲፮-፳ኛ መ.ክ.ዘ (ሦስት) | 80 | | | |
| 18. | የኢ.ቤ.ታ ከ፲፮-፳ኛ መ.ክ.ዘ (አራት) | 85 | | | |
| 19. | ካቶሊክ እና ክፍፍሎቹ (አንድ) | 89 | | | |
| 20. | ካቶሊክ እና ክፍፍሎቹ (ሁለት) | 98 | | | |
| 21. | ጥንታዊ ኦርቶዶክሳውያን (አንድ) | 104 | | | |
| 22. | ጥንታዊ ኦርቶዶክሳውያን (ሁለት) | 108 | | | |
| 23. | ጥንታዊ ኦርቶዶክሳውያን (ሦስት) | 112 | | | |
| 24. | ቅንዓት | 117 | | | |
| 25. | ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ | 122 | | | |
| 26. | አባ ባሕርይ (መዝሙረ ክርስቶስ) | 129 | | | |
| 27. | አዋልድ መጻሕፍት | 134 | | | |


www.zeorthodox.org

## ዐሥራ አንደኛ ክፍል


| ተ.ቁ | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | ወግ፣ባህል፣ ትውፊት በመጽሐፍ ቅዱስ (አንድ) | 137 | | | |
| 29. | ወግ፣ባህል፣ ትውፊት በመጽሐፍ ቅዱስ (ሁለት) | 140 | | | |
| 30. | መንፈሳዊው ትውፊት በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ (ሦስት) | 144 | | | |
| 31. | እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም | 147 | | | |
| 32. | ክብረ ቅዱሳን | 153 | | | |
| 33. | ደብረ ዘይት- ዳግም የመምጣቱ መታሰቢያ | 158 | | | |
| 34. | እኔ የማን ነኝ ? | 164 | | | |
| 35. | ሰው ምንድነው ? | 169 | | | |
| 36. | መንፈሳዊው ሰው | 173 | | | |
| 37. | መንፈሳዊ እድገት(አንድ) | 177 | | | |
| 38. | መንፈሳዊ እድገት(ሁለት) | 181 | | | |
| 39. | ቅዱስ ቁርባን | 185 | | | |
| 40. | ጾታዊ ቀጠሮ….. | 189 | | | |
| 41. | ቁማር | 192 | | | |
| 42. | የሕይወት ምርጫ(አንድ) | 196 | | | |
| 43. | የሕይወት ምርጫ(ሁለት) | 199 | | | |
| 44. | የሕይወት ምርጫ(ሦስት) | 203 | | | |
| 45. | የሕይወት ምርጫ(አራት) | 206 | | | |
| 46. | ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት | 210 | | | |
| 47. | ትዕግሥት | 213 | | | |
| 48. | ትሕትና | 216 | | | |
| 49. | በደብረ ታቦር ክብሩን ገለጠ | 219 | | | |
| 50. | ሥርዓተ ማኅሌት | 222 | | | |
| 51. | በንጽሕና መኖር ይቻላል..? | 225 | | | |
| 52. | በንጽሕና ያሉ ወጣቶች መገለጫ | 229 | | | |


www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል። ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው።

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው። ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል።

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራቅ መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ። ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ። በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ። አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ። በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው።

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር። በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት

www.zeorthodox.org

እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ፡፡

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለንትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

***"እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፡፡" ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው። በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

www.zeorthodox.org

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል። ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና። ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል። በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው። ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል። መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ። ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ።

www.zeorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም(አንድ)

## አንደኛ ሳምንት

**የትምህርት ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እና ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ስለተተረጎመበት ሂደት ይገነዘባሉ፤መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"የተጻፈው ሁሉ ለእኛ ተጻፈ"* ሮሜ.፲፭፥፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት››፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ››፤ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻(2000) ዓ.ም

## የትምህርቱ መግቢያ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ዓይነት ይተረጐማል፡-

- የመጀመሪያው ከቋንቋ ወደ ቋንቋ የሚደረግ ሲሆን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማዳረስ የሚደረግ ትርጓሜ ነው፡፡
- ሁለተኛው የመጽሐፍ ቅዱስን ምስጢር ለመረዳት የሚያስችለን ትርጓሜ ነው፡፡

ይህንንም በግእዝ፡- ‹‹ትርጉም›› እና ‹‹ፍካሬ›› ብለው ሲለዩት፤ በእንግሊዝኛ፡- (Translation and Interpretation) የሚሉ ገላጭ ቃላት አሉት፡፡ በዚህ ትምህርታችንም ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ለሚደረገው ትርጓሜ ‹‹ትርጉም›› (Translation) ለምስጢራዊው ፍቺም ‹‹ፍካሬ›› (intertpretation) የሚሉትን የግእዝ ቃላት እንጠቀማለን፡፡

በመላው ዓለም በብዛት በመታተም እና በመሠራጨት መጽሐፍ ቅዱስን የሚያህለው መጽሐፍ የለም፡፡ ከ2200 ቋንቋዎች በላይ በመተርጎም ተወዳዳሪ የለውም ፤ በብዙ ቅጂዎች (copies) ብዛትም ቀዳሚው ነው፡፡ ከ፲፱፻፸(1970)ዎቹ እስከ ፲፱፻፺(1990)ዎቹ ዓመታት ታትሞ የተሠራጨው ብቻ ከአራት ቢልየን በላይ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ለአብዛኛው የዓለም ክፍል (99 በመቶ) መድረስ ችሏል፡፡

www.zeorthodox.org

በሌላ በኩልም መጽሐፍ ቅዱስ ምስጢራዊ መጽሐፍ ስለሆነ ምስጢሩን ለመረዳት የሚያስችል ትርጓሜ ያስፈልገዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ***"እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ፤"*** ቈላ.፬፥፫ እንዳለ የእግዚአብሔር ቃል የተዘጋ ደጅ ነውና መክፈቻ ያስፈልገዋል፡፡ መክፈቻውም ፍካሬ መጻሕፍት (Interpretation) ይባላል፡፡

በዛሬው ትምህርታችንም ሁለቱንም የትርጉም ዓይነቶች ምንነት እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**፩.የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም** (Translation)፡-

መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራይስጥ፣ በግሪክና በአረማይክ ቋንቋዎች የተጻፈ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ከ2200 በላይ ቋንቋዎች ተተርጉሟል፡፡ ለዘመናት በተደረገው ትርጉም ሥራ መጽሐፍ ቅዱስ በመላው ዓለም በሚገኙ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች በየቤቱ፤ እንዲዳረስ አስችሎታል፡፡

### 1.1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚተረጎምበት መንገድ፡-

መጽሐፍ ቅዱስን ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ለመተርጎም፡- የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እና ረድኤት ፤ የቋንቋ ክህሎት እና ዕውቀት፤ የገንዘብ አቅም፣ ጊዜ እና ጽናት ያስፈልጋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የሚተረጎምበት መርሖዎች አሉ፡፡ እነርሱም፡- **ትክክለኛነት፣ ግልጽነት፣ ታማኝነት፣ ሕያውነት፣ የቋንቋ ወጥነት፣ ተነባቢነት እና የቋንቋ ክቡርነት** ናቸው፡፡

**ስልቶች**፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች በተናጠል ወይም በተለያየ አገባብ የሚከተሉትን ስልቶች ይጠቀማሉ፡፡

1. **ቃል በቃል** (word by word)፡- ቃላቱን በተመሳሳይ ሁኔታ ወደሌላ ቋንቋ ቃላት መተርጎም ነው፡፡
2. **መስመራዊ**(linear)፡- በሐረግ እና በዐረፍተ ነገር የተገለጠውን ሐሳብ ዋና ጭብጥ መተርጎም ላይ ያተኩራል፡፡
3. **ቀጥተኛ** (Literal)፡- ከአቀባይ ቋንቋ ወደ ተቀባይ ቋንቋ በቀጥታ የመተርጐም ስልት ሲሆን ከተነባቢነት እና የቋንቋ ውበት ይልቅ ቃል በቃል ለመተርጐም ትኩረት ይሰጣል፡፡
4. **ገላጭ** (Dynamic)፡- በተቀባይ ቋንቋ ሐሳብን በመግለጽ እና ተነባቢነት ላይ ያተኩራል፡፡ አብዛኛዎቹ ***"ቀለል ባለ ....."*** የሚሰኙት የዘመናችን ትርጓሜዎች ይህን ስልት ይከተላሉ፡፡

በእነኚህ መርሖዎች እና ስልቶች መሠረትም መጽሐፍ ቅዱስ ሲተረጎም ኖሯል ይተረጎማልም፡፡

**1.2 ጥንታውያን ትርጓሜዎች**፡- መጽሐፍ ቅዱስን እንከተላለን በሚሉና በእውነትና በሐሰት ወዳጅነት የተሰለፉ ብዙ ክፍሎች አሉ፡፡ እነዚህ ክፍፍሎች ሳይፈጠሩ በፊት የተደረጉ ትርጓሜዎች ወይም መጽሐፍ ቅዱስ በጥንቱ ዘመን የተተረጐመባቸው ቋንቋዎች እና የትርጉም ሥራዎች **ጥንታውያን ትርጓሜዎች** ተብለው ይታወቃሉ፡፡ እነዚህም፡-

www.zeorthodox.org

**በኢትዮጵያው ግእዝ**፡- ግእዝ በዓለማችን ቀድሞ መጽሐፍ ቅዱስ ከተተረጎመባቸው ቋንቋዎች አንዱ ነው፡፡ ብሉይ ኪዳን ከዕብራይስጥ እና ከግሪክ ቋንቋዎች አስቀድሞ ወደ ግእዝ ቋንቋ የተተረጐመ ሲሆን፤ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም ከ፬ኛ-፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአቡነ ሰላማ እና በዘጠኙ ቅዱሳን አማካኝነት ከግሪክ ፣ ሱርስት እና ዕብራይስጥ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ ተተርጉሟል፡፡

**በጥንቱ ሶሪያ (ሱርስት)፡-** የሮሃው ራቡላ፣ የመንበጉ ፊልክስዮስ እና ቶማስ ዘሄራክል ከሁለተኛው እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ሱርስት (ሲርያክ)ቋንቋ ተርጉመዋል፡፡

**በግብጹ ኮፕቲክ፡-** ከሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሦስት የአነጋገር ስልቶች (Dialectic) መጽሐፍ ቅዱስ ተተርጉሟል፡፡

**በአርመንያ፡-** በቅዱስ ሜስሮኘ እና ቅዱስ ስህክ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአርመኖቹ አርማኒያ መጽሐፍ ቅዱስን አግኝቶአል፡፡

**በጥንቱ ላቲን፡-** አባ ጀሮም በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ጥንቱ ላቲን መጽሐፍ ቅዱስን ሲተረጉም ትርጓሜውም ቩልጌት ይባላል፡፡

**ገት፡-** በአሁኑዋ ሮማንያ ይኖሩ የነበሩት ገቶች መጽሐፍ ቅዱስን ውልፊላ የተባለ ሰው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተርጉሞላቸው ነበር፡፡

በዚህ መሠረትም እነዚህ ከላይ ባየናቸው ቋንቋዎች እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመባቸው ናቸው፡፡

በኋላኛው ዘመንም ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መጽሐፍ ቅዱስ ተተርጉሟል፡፡ ከእነዚህም፡-

- ወደ እንግሊዝኛ ዊልያም ቴንዳየል በ፲፭፻፳፭(1525) ዓ.ም
- ወደ ጀርመንኛ ሉተር በ፲፭፻፵፭(1545) ዓ.ም ተርጉመዋል፡፡
- የንጉሥ ጀምስ ትርጉም (King James Version) በ፲፮፻፲፩(1611) ዓ.ም ተተርጉሞአል፡፡
- በዚህ ሒደት ነው በአሁኑ ወቅት ከ2200 በሚበልጡ ቋንቋዎች መጽሐፍ ቅዱስ በመላው ዓለም የተተረጎመው፡፡

በሀገር ውስጥም፡-

- አባ አብርሃም ከ፲፰፻(1800)-፲፰፻፲(1810) ዓ.ም ገደማ ወደ አማርኛ፤
- አናሲሞስ ነሲቡ ወደ ኦሮምኛ በ፲፰፻፺፪(1892) ዓ.ም፤
- አለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩ ወደ ትግርኛ በ፲፱፻፵፰(1948) ዓ.ም ተርጉመዋል፡፡
- ጉራግኛ እና ወላይትኛ ቋንቋዎችም መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጐመባቸው የሀገራችን ቋንቋዎች ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

መጽሐፍ ቅዱስ በክፍል በክፍል የተተረጐመባቸው ከሃያ በላይ የሀገራችን ቋንቋዎችም አሉ፡፡

**ማጠቃለያ፡-** በምድራችን በብዙ ቋንቋዎች፣ ለረጅም ዘመናት በመተርጎም አቻ የሌለው መጽሐፍ ቅዱስ ከ2,200 ቋንቋዎች በላይ የተተረጐመ ለአብዛኛው (98%) የዓለም ሕዝብ የተዳረሰ መጽሐፍ ነው፡፡

**ተግባር፡-** ወደ ኢትዩጵያ ቋንቋዎች (ግእዝ፣ ኦሮምኛ፣ አማርኛ...) የተረጐሙ አባቶችንም ታሪክ ጠይቃችሁ ለሳምንት አቅርቡ።

***ጥያቄዎች፡-***

1. መጽሐፍ ቅዱስ በስንት ዓይነት መንገዶች ይተረጎማል? አብራሩ።
2. መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥንታውያን ትርጉሞች የሚባሉት በምን ቋንቋ የተተረጎሙ ናቸው? እስከ ስንተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ተተረጎመ?
4. የኋለኛው (ቅርብ ጊዜ) መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመባቸው ቋንቋዎች እና ተርጓሚዎችን ከነ ዘመኑ ጥቀሱ?
5. መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ውስጥ ከስንት በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል?

www.zeorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም (ሁለት)

## ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርት ዓላማ፡-** ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምስጢራዊ የትርጉም ስልት ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደለትም "*** *፪ኛ ጴጥ.፩፥፳*

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻(2000) ዓ.ም›› ገጽ 174-209፤ ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ›› በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ

**የትምህርቱ መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የመጀመሪያ ክፍል አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ስለ ፍካሬ መጻሕፍት ( የመጽሐፍ ቅዱስ ምስጢራዊ ትርጉም ) እንማራለን፡፡

### 2. ፍካሬ መጻሕፍት (Bible Interpretation)

መጽሐፍ ቅዱስ ምስጢራዊ መጽሐፍ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የተዘጋ ደጅ ከፋች እና መክፈቻ ያስፈልገዋል፡፡ ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በተዘጋ ደጅ የመሰለው፡፡ ***" እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ"*** ቈላ.፬፥፫ ጌታችንም በምሳሌ ሲያስተምር ደቀ መዛሙርቱ ‹‹ስለምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ?›› በማለት ጠይቀውታል፡፡ እርሱም ***ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም፡፡*** በማለት ለሁሉም ያልተሰጠውን ምስጢር ነግሯቸዋል፡፡ የጠርሴሱ ጳውሎስም በኤፌሶን መልእክቱ ***"የወንጌልን ምስጢር"*** ሲል እናነባለን፡፡

ይህንን ምስጢር ለመረዳት በዘመነ ብሉይ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች መጽሐፍ ቅዱስን ይተረጉሙ ነበረ፡፡ ***" ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ "*** ማቴ.፲፫፥፴፭ መዝ.፸፰(፸፯)፥፪ የተባለው ይፈጸም ዘንድ የቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ትርጓሜ የተገለጠውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በእርሱ የማያምኑ ምስጢሩን አይረዱም፡፡ ***"እርሱም የላከውን እናንተ አታምኑምና በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ የላችሁም፤ እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም፡፡"*** ዮሐ.፭፥፴፱

www.zeorthodox.org

በጌታችን እውነተኛ እምነት ያላቸውና እርሱም ሊገልጥላቸው የመረጣቸው የእግዚአብሔርን ምስጢር ያውቃሉ፡፡ ***"ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፡፡ ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ? አሉት፡፡ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም"*** ማቴ.፲፫፥፲፩ ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ ***"የወንጌልን ምስጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤"*** ኤፌ.፮፥፲፱ ያለው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ሐዋርያዊ ትርጓሜ አቆይታለች፡፡

**2.1 አስፈላጊነቱ፡-** በዘመናችንም መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አያስፈልገውም የሚሉ እንዳሉ ሁሉ ፤ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትም መጽሐፍ ቅዱስ ይተረጐማል ብለው ያምናሉ፡፡ ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ፤ በዚህ ትምህርታችን የሚከተሉትን ምክንያቶች ማየት ይበቃናል፡፡

- የሰው ልብ በኃጢአት ስለታወረ የእግዚአብሔርን መልእክት መረዳት አልቻለምና የቃሉን ትርጎሜ የሚያስረዱ አስፈለጉ፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈበት ቋንቋ ፣ ባሕል እና የአጻጻፍ ስልት አንጻር ለማወቅ፡፡
- በምሳሌዊ አቀራራብ የተጻፉትን ለመረዳት ትርጎሜ ያስፈጋል፡፡

**2.2 ፍካሬ በመጽሐፍ ቅዱስ፡-** መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም ያስተማረን ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ለምሳሌም የሚከተሉትን ተመልከቱ፡-

***"መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም፡፡"*** ፩ኛ. ቆሮ.፪፥፲፫ በዚህ መንገድም መጽሐፍ ቅዱስ ይተረጎማል፡፡ ከላይ እንዳየነውም ጌታችን በብሉይ ኪዳን የተጻፉት ትንቢቶችን እና ምስጢሮችን በተግባር እና በቃል ተርጉሞልናል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም ብሉያትን የተረጎመበት መንገድ ነበር፡፡ ሁለት ምሳሌዎችን እንይ፡-

***"እናንተ ከሕግ በታች ልትኖሩ የምትወዱ ሕጉን አትሰሙምን? እስኪ ንገሩኝ፡፡ አንዱ ከባሪያይቱ አንዱ ከጨዋይቱ የሆኑ ሁለት ልጆች ለአብርሃም እንደነበሩት ተጽፎአልና፡፡ ነገር ግን የባሪያይቱ ልጅ እንደ ሥጋ ተወልዶአል የጨዋይቱ ግን በተስፋው ቃል ተወልዶአል፡፡ ይህም ነገር ምሳሌ ነው እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ኪዳኖች ናቸውና፡፡"*** ገላትያ.፬፥፳፩-፳፬ ይህንን ጥቅስ የሚያነብ በዘፍ.፲፮፥፲፰፣፳፩ የተጻፈውን የአብርሃምን ታሪክ ያስታውሳል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም በዚህ መንገድ ተርጉሞታል፡፡

***"ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፡፡ አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ፡፡ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፤ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ***

www.zeorthodox.org

***ድንጋይ ጠጥተዋልና ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበር፡፡"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፥፩-፭ ይህም በዘጸአት እና ዘኁልቁ የሚገኝ ታሪክ ነው፤ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ተርጉሞታል፡፡

**2.2 ፍካሬ በቤተ አይሁድ፡-** በዘመነ ብሉይ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚተረጉሙ ነበሩ፡፡ ነህ.፰፥፰ በጌታችን ዘመን የነበሩት አይሁድም በተለያየ ዓይነት ትርጓሜ የሚመሩ ክፍሎች ነበሩዋቸው፡፡ ፈሪሳውያን ለፊደል፣ ኤስያውያን ለመንፈሳዊ ትርጉም ትኩረት ይሰጡ ነበር፡፡

**2.3 ፍካሬ መጻሕፍት በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን፡-** ከጥንት እስከ ዛሬ የተለያየ የአተረጓጐም ስልት የሚከተሉ የትርጓሜ ትምህርት ቤቶች እና መምህራን ነበሩ፡፡ በመጀመሪያዎቹ አራት መቶ ዓመታት የእስክንድርያው ትምህርት ቤት ለመጽሐፍ ቅዱስ ምስጢራዊ እና ምሳሌዊ ትርጓሜ ትኩረት ሲሰጥ፤ የአንፆኪያው ትምህርት ቤት ለቀጥተኛ ትርጉም ትኩረት ይሠጥ ነበር፡፡

**3. የፍካሬ ዓይነቶች**

3.1. ***መሠረታዊ የትርጓሜ ዘዴዎች***፡፡ የተለያዩ የትርጓሜ ዘዴዎች ያሉ ሲሆን፤ በሁለት ይጠቃለላሉ፡፡

***ሀ.ቀጥተኛ የትርጓሜ ዘዴ፡-*** ይህ የትርጓሜ ዘዴ ቃል በቃል የመጽሐፍን ቃል መተርጐም አለብን የሚል ሲሆን፥ ቃሉን በንባቡ ብቻ ይተረጉማል፡፡ በዚህ ትርጓሜ የአንፆኪያ ትርጓሜ ትምህርት ቤት በዋናነት በታሪክ ይታወቃል፡፡ መንገዳቸው ከአንፆኪያ ቢለይም ፈሪሳውያን እና የዘመናችን ፕሮቴስታንቶች ቀጥተኛ ትርጓሜን ይጠቀማሉ፡፡

**ለ.ኀብረ ምሳሌያዊ /ውስጠ ወይራዊ/፡-** ይህ ትርጓሜ የመጽሐፉን መንፈስ የምንረዳበትና ምስጢሩን የምንመረምርበት የትርጓሜ ስልት ነው፡፡ (፪ኛ ቆሮ ፫፥፯) በመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና ትምህርት ለሚነሡ ጥያቄዎችም መልስ ይሰጣል፡፡ ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ ***"ፊደል ይገድላል መንፈስ ሕይወት ይሰጣል፡፡"*** ያለው፡፡ በዚህ ትርጓሜ ከኤስያውያን ብዙዎቹ ወደ ክርስቶስ መጥተዋል፤ የእስክንድርያን ትምህርት ቤት ሃይማኖትም አጽንቷል፣ ቤተ ክርስቲያናችንም በተለያዩ ስልቶች ትጠቀምበታለች፡፡

www.zeorthodox.org

3.2 የቤተ ክርስቲያናችን የትርጉም ስልቶች የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጉሙባቸው በተለያዩ አድባራት እና ገዳማት የተመሠረቱ የመጻሕፍት ቤቶች የሚባሉ ትምህርት ቤቶች አሉ፡፡ አንድ ተማሪ ወደ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ከመግባቱ በፊት ቅኔ ቤት ገብቶ የቋንቋ እና ትርጓሜ ስልቶችን ይማራል፡፡ ከዚያም በአራት መደብ (ሐዲሳት፣ ብሉያት፣ ሊቃውንት እና መነኮሳት) የተባሉትን መጻሕፍት እንደ አቅሙ እና በተሰጠው ጊዜ መሠረት በጥልቀት

እየተነተኑ ይማራል። እነዚህን ትንታኔዎች የያዙ መጻሕፍትም የትርጓሜ መጻሕፍት ይባላሉ። በትምህርት ቤቶቹ የሚሰጠውና በየመጻሕፍቱ ከምናገኛቸው የትርጉም ስልቶች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ፦

1.) **ዘይቤያዊ**፦ይህ ሁለት ዓይነት ሲሆን ቀጥታ በቋንቋው አማራጭ ቃላትና አገባብ (vocabulary) የሚያስረዳ እና ከቋንቋ ወደ ቋንቋ በተደረገ ትርጉም የተከሠተን የቋንቋ ስሕተት ለማረም የሚጠቀሙበት ስልት ነው።

2.) **ምሳሌያዊ**፦በምሳሌነት የተቀመጡትን በአማናዊ ፍቺያቸው መተርጐም ነው። ለምሳሌ፦ የፋሲካው በግ (ዘጸ.፲፪፥፳፩-፳፰) ምሳሌነቱ ለክርስቶስ መሆኑን መተንተን ፤ ***"ባለመቶ ባለ ስድሳ እና ባለ ሠላሳ "*** (ማቴ.፲፫፥፩-፳፫) ብሎ ጌታችን የመሰለውን ባለመቶ እነ እገሌ፣ ባለስድሳ እነ እገሌ ወዘተ.....ብሎ መተርጎም ነው።

3.) **ምስጢራዊ**፦ በኃይለ ቃሉ ውስጥ ያለውን መንፈሳዊ ምስጢር ለማወቅ የሚረዳ የትርጉም መንገድ ሲሆን በምሳሌ፣ በታሪክ፣ በአንድምታ፣ በሐተታ እና በመሳሰሉት... መንገዶች ማመስጠር ነው። በዚህም ወርቅና ሰሙን እንለይበታለን።

4.) **እርቅ**፦የሚጋጩ የሚመስሉንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በመንፈሳዊ ትርጉም የምንረዳበት ነው። ለምሳሌ፦ጌታችን በደብረ ታቦር ሦስቱን ደቀ መዛሙርቱን ይዞ የወጣበትን ቀን ***"ከስድስት ቀንም በኋላ"*** ማቴ.፲፯፥፩ እና ***"ስምንት ቀን ያህል ቆይቶ"*** ሉቃ.፱፥፳፰ ብለው ሁለቱ ወንጌላውያን የጠቀሱትን በማቴዎስ በኋላ የተባለችው ቃል ስምንተኛ ቀንን እንደምታመለክት ማስረዳት ነው።

5.) **አንድም**፦ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉልንን ነቢያትንና ሐዋርያትን የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ያስተላለፈልን መልእክት፡፦ በተለያየ ጊዜ የሚፈጸም እና የሚተረጐም፣ ለዓለም በሙሉ የሚሆን ቃል ነው። በዚህ መሠረትም ተመሳሳይ ትርጉም የያዘውን ቃል ፩,፪,፫, ሳይሉ፤ አንድም እንዲህ ማለት ነው፤ አንድም ይሄን ለማለት ነው እያሉ እስከ ዐሥር የሚደርሱ ትርጉሞች የሚብራሩበት ስልት ነው።

6.) **ሐተታ**፦ ለእያንዳንዱ ጥቅስ እና ቃል ፤ ከቃል ትርጉም እስከ አገባቡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃልና ከታሪክ ጋር እያነፃፀሩ ሐተታ በመስጠት መተርጎም ነው።

www.zeorthodox.org

7.) **ንጽጽር**፦ ተመሳሳይ ጥቅሶችንና የቀደምት አባቶችን ትርጓሜ በአብነት በመጠቀምና በማነጻጸር "እገሌ" እንዲህ ብሎታል እያሉ መተርጎም ነው።

3.3 **ሌሎች የትርጉም ዓይነቶች** እነዚህ የትርጓሜ መንገዶች አብዛኛዎቹ ከላይ በጠቀስናቸው የትርጓሜ መንገዶች ይካተታሉ። ሆኖም በዘመናዊዎቹ የነገረ መለኮት ምሁራን የሚተነተኑትንና በምዕራባውያን የሚዘወተሩትን ለማወቅ እናየዋለን።

1. **ባለ አምስቱ ጥያቄያዊ ዘዴ** (The five w's. Method):- በቀላሉ ለማስታወስ የሚረዳ ስልት ነው ይሉታል፡፡ Where(የት)፣ when(መቼ )፣ who(ማን)፣ To whom(ለማን)፣ why (ለምን) የሚሉትን በመመለስ የሚደረግ ትርጓሜ ነው፡፡
2. **ክፋፍሎ ማጥናት** (Sectioning):- አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በቁጥር፣ በአንቀጽና በታሪክ እየከፋፈሉ የማጥናት ዘዴ ነው፡፡
3. **ንጽጽራዊ ጥናት** (Comparative Study):- መጻሕፍትን፣ ጥቅሶችን፣ ትንቢትና ፍጻሜን … በማነጻጸር ማጥናት ነው፡፡
4. **መሠረታዊ የአጠናን ዘዴ** (Basic method) ወይም Exegetical method በመባልም ይጠራል፡፡ ይህም የሚከተሉት ክፍሎች አሉት፡-
   - **መዋቅር**(structure) በቡድን፣ በክፍል ወይም በተመሳሳይ ነገሮች መድቦ በማዋቀር ማጥናት ነው፡፡
   - **ሐተታ** (comment) ፍቺ ለሚያስፈልገው ቃልና ሐሳብ ከተለያዩ የመጻሕፍት ትርጓሜ ማየት ነው፡፡
   - **ዓውደ ንባብ** (context) ሙሉ ሐሳቡን ከዓውደ ንባቡ በመውሰድ ማጥናት ነው፡፡
   - **ማገናዘቢያ /ትግበራ** (Application) ከራስ ሕይወት ጋር እያገናዘቡ÷በመተግበር ማጥናት ናቸው፡፡

በማገናዘብ ለመተግበር እና በዚህ ጥናት ውጤታማ ለመሆን የሚከተለውን ባለ ዐሥር ደረጃዎች ቅደም ተከተል መጠቀም ይመክራሉ፡፡

1. ከቃሉ ጋር መነጋገር ፣
2. ዓውደ ንባቡን ማስተዋል ፣
3. ምክንያተ ጽሑፉን ማጥናት ፣
4. የተለያዩ እትሞችን ማገናዘብ ፣
5. ማመሳከሪያ መጻሕፍት መጠቀም ፣
6. የጽሑፉን ዓይነት መለየት ፣
7. ቁልፍ ቃላትን መፍታት ፣
8. ከሌሎች ትርጓሜዎች ጋር ማመሳከር ፣
9. በርእስና ማውጫ መዘርዘር እና
10. እነዚህን ዘጠኝ ሂደቶች መከለስና መጻፍ ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ ፡-

- መጽሐፍ ቅዱስ ምስጢራዊ መጽሐፍ ነውና ለመረዳትም ምስጢራዊ ትርጉሙን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የመጽሐፍቅ ቅዱስን ምሥጢር የመተርጎም ስልት በመጽሐፍ ቅዱስ ያለ ነው፡፡ በቤተ አይሁድ እና በቀደመችዋ ቤተ ክርስቲያንም ነበር፡፡
- ቀጥተኛ እና ኀብረ አምሳላዊ የተባሉ ሁለት ዋና ዋና የትርጉም ስልቶች አሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በእነዚህ ስልቶች ተመሥርታ መጽሐፍ ቅዱስን የምትተረጉምበት መንገዶች አሏት፡፡

- መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን የሚሉ የዓለማችን ክፍሎችም ለዘመናት የተንዙባቸው ትርጎሜዎች አሉ፡፡
- የቀደሙት አባቶች በጥንቃቄ ሲመረምሩት ኖረው፤ ረቂቁ ገዝፎ ስውሩ ጎልቶ ተገልጾላቸዋል፡፡ እኛም ***አባቶቻቸውም ለመረመሩት ነገር በመትጋት፤*** ኢዮ.፰፥፰-፱ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ለማወቅ እንጣር፡፡

## ተግባር፡-

- **የማቴዎስ ወንጌል ምዕ.፲፩፣፲፪ እና የዮሐንስ ወንጌል ምዕ.፩፥፩-፲፫** የቃላቱን ፍቺ ከቤተ ክርስቲያናችን ትርጓሜ ወንጌል ተመልክታችሁ አጭር ማስታወሻ ጽፉችሁ ሳምንት ለመምህር አስገቡ፡፡
- መምህር፡- በተሰጡት ጥቅሶች፡- ግፈኞች፣ ይናጠቅዋታል፣ ከዮሐንስ እስከ አሁን፣ በመጀመሪያ፣ ቃል፣ ሁሉ በእርሱ ሆነ … ወዘተርፈ በሚሉ ቃላት አሉ፡፡ የእነዚህ ቃላት ትርጓሜ እና በዓውዱ ያላቸውን አገባብ ተማሪዎችን ከፋፍለው በቡድን እና በግል እንዲሠሩ ይመዱቡዋቸው፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም አስፈላጊነት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ቢያንስ ሦስቱን ግለጹ፡፡
2. መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም ያስተማረው ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ይህንን አባባል በምሳሌ አብራሩ፡፡
3. የቤተ ክርስቲያናችን የትርጉም ስልቶች ምን ምን ናቸው? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች(አንድ)

## መግቢያ

## ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡- ተማሪዎች የሮሜ መልእክት ለማን? የት? እንደ ተጻፈ እንዲሁም የመልእክቲቱን ዋና ዓላማ ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡- ***"ስለዚህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ።"*** ሮሜ.፩፥፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ‹‹የቅዱስ ጳውሎስ ትርጓሜ››፣‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት››፣ ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት›› መማሪያ ሞጅሎች፡፡

**መግቢያ፡-**ይህ በተከታታይ የምንማረው የሮሜ መልእክት የመግቢያ ጥናታችን የመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡ ዛሬ ስለ ሮሜ ከተማ፣ ስለ ሮሜ ቤተ ክርስቲያን እና የመልእክቲቱን መግቢያ (ለምን ተጻፈ?፣ ዋና መልእክቱ ምንድ ነው? የት? እና በማን? ተጻፈ) የሚሉትን እንማራለን፡፡

**የሳምንቱ ትምህርት፡-**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከጻፋቸው ዐሥራ አራት መልእክታት አንዱ የሮሜ መልእክት ነው፡፡ ወደ መልእክቲቱ ከመግባታችን በፊትም የሚከተሉትን ማጥናት ስለ መልእክቲቱ የተሻለ ግንዛቤ ይሰጠናልና እነዚህን እናስቀድማለን፡፡

1. **ሮሜ**፡- በ753 ዓ.ዓ ከክርስቶስ ልደት በፊት በመንታ ወንድማማቾቹ ሮሙለስ እና ሙለስ የተቋቋመች ከተማ ነች፡፡ በ509 የሮም ሪፐብሊክ ማዕከል ሆና ተሠራች፡፡ በ፷፫(63) ዓ.ም ሮም ልዕለ ኃያል ሆና አካባቢውን ተቆጣጠረች ፤ በኋላም ከግዛቱ ክፍሎች ጋር የሚያገናኝ መንገድ ተሠራላት፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ በተመላለሰበት ዘመን የሮም ግዛት ከዛሬዋ እንግሊዝ እስከ ዐረቢያ ምድር ያለውን ያጠቃልል ነበር፡፡ በ፷፫(63) ዓ.ም የነበረው የሮም መንግሥት ምድረ ፍልስጥኤምን በቁጥጥር ሥር ሲያደርግ እስራኤል የግዛቱ አካል ሆነች፡፡ የተወሰኑትን አይሁድም በምርኮ ሌሎቹም በንግድና በሥራ ወደ ሮም ገቡ ፡፡ እነኚህ አይሁድም በሮም ከተማ ምኩራቦቻቸውን በመሥራት ሥርዓተ ኦሪትን እየፈጸሙና ከአሕዛብ አንዳንዶቹን ወደ ይሁዲነት እያስገቡ ተስፋፉ፡፡

www.zeorthodox.org

2. **የሮሜ ቤተ ክርስቲያን፡-** ሐዋርያት በበዓለ ሃምሳ ሲያስተምሩ ከሮሜ የመጡ እና ወደ ይሁዲነት የገቡም እንደነበሩበት ሉቃስ በግብረ ሐዋርያት ጽፎአል፡፡ የሐዋ.ሥ ፪÷፲ እነዚህም ወደ ሮሜ ተመልሰው ክርስትና መስበክ እንደ ጀመሩ ይታመናል፡፡ በኋላም ሐዋርያት ተመላልሰው አስተምረዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ቤተ ክርስቲያን የሄደው በእስራቱ ወቅት ነው፡፡ በቁም እስር ሁለት ዓመት ሲኖርም ወንጌልን በሮም አስፋፍቷል፡፡ ከቅዱስ ጳውሎስ ቀድሞ ቅዱስ ጴጥሮስ በሮም አስተምሮ ነበር፡፡

3. **የሮሜ ቤተክርስቲያን ፈተና፡-** በሮሜ ቤተ ክርስቲያን ከይሁዲነት የመጡ እና ከአረማዊነት የተመለሱ ክርስቲያኖች በኅብረት ይኖሩ ነበር፡፡ በኋላም በአንፆኪያ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረውን ዓይነት ልዩነት ተፈጠረ፡፡ (የሐዋ.ሥ ፲፭÷፩-፭) ልዩነቱ አድጎም አንዱ በሌላው ይታበይበት ጀመር፣ የልዩነቶቻቸው ዋና ዋና ሐሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**አይሁድ፡-** አሕዛብን ሕገ ሙሴን፣ ሥርዓተ ኦሪትን  ልማደ ረበናትን ካልጠበቃችሁ ተስፋ ክርስቶስን አታገኙም ከማለት አልፈው፤  ከአብርሃም ዘርዕ የተገኙ ግዙራን እንደ ሆኑና ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር የታወቀው በይሁዳ መሆኑን ለማስረዳት፤ ከግብጽ ተአምራት እስከ ክርስቶስ መመላለስ ያለውን እየተረኩ ተስፋው ለእኛ ነው፡፡ ወደ እናንተ ነቢያት አልተላኩም፤ ክርስቶስም በእናንተ አልተወለደም፡፡ እንዲያውም ውሾች አላችሁ እንጂ ሰዎች አላላችሁም፤ ከተፈጠራችሁ ጀምሮ ለጣዖት ተገዢዎች የነበራችሁ እናንተ በክብር ከእኛ ጋር አትተካከሉም አሉ፡፡

**አሕዛብም** ፡- አይሁድ ለእግዚአብሔር ቸርነት የመለሱት መልስ ክህደት እንደ ነበር አንሥተው ፤ በሲና ሙሴ ታቦት ሲቀበል ጣዖት ሲያመልኩ፣ ነቢያትን ሲገድሉ እንደነበር ተረኩ፡፡ ***በኋላም ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ ሲወለድ ተመቅኝታችሁት ፣ ሰቅላችሁ ገደላችሁት*** አሉ፡፡ እኛ ግን ዜናውን ከሰማን ጀምሮ አምነናል ፣ እርሱም እኛን መርጦናል እናንተን አልፈለገም አሉ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም ከሁለቱም ወገን ምክንያት ሲያጠፋ ይህችን መልእክት ላከላቸው፡፡

4. **ምክንያተ ጽሒፍ፡-** ሐዋርያው የሮሜን መልእክት የጻፈበትንም ምክንያት በዋናነት መልእክቱ ይነግረናል ፡፡ በዚህ መሠረትም የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት እና አጥኝዎች በይዘቱና በታሪካዊ ዳሰሳዎች ተመርኩዘው የሚከተሉትን ምክንያቶች ያስቀምጣሉ ፡፡

www.zeorthodox.org

4.1 ***መከፋፈሉን ለማጥፋት እና ፍቅር ለማምጣት፡-*** በሮም ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ፍቅር ለመመለስ እና ሰላም ለማውረድ መልእክቱን ጽፏል፡፡ ከሁለቱም የትምክህታቸውን ምክንያት ሲያጠፋ ሁለቱም የእግዚአብሔርን ክብር ትተው መበደላቸውን አስረዳ፡፡ (፩÷፲፰ ፣ ፪÷፳፱) ነገር ግን ሁለቱም ለሰው ያልተቻለውን የእግዚአብሔርን ጽድቅ - ***"ምሕረተ ክርስቶስን እንዳገኙ"*** ም ሰበከ፡፡

በክርስቶስ የተሰጠን የልጅነት ሥልጣንና ጥሪ ሁለቱንም ማስተካከሉንም በእግዚአብሔር ፊት በእኩልነት መጠራታቸውን ከመጻሕፍት አስረዳ ፤ ጸብን አጥፍቶ የሰላምን ሕንፃ ለመመሥረትም ጻፈ። (የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው ገጽ 7-10)

4.2 **አገልግሎቱን በጽሑፍ ለመስጠት፡-** ይህንን የሚሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት በሮሜ.፩፥፱-፲፫ ያለውን መሠረት አድርገው፤ ሐዋርያው ወደ ሮም በአካል ባይሄድም ለአሕዛብ ሐዋርያነት ስለተሾመ አገልግሎቱን በጽሑፍ ለመስጠት የጻፈው ነው ይላሉ። (Pulpet Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN intr. pp. ii)

## 5. የተጻፈበት ዘመን ፣ ቦታና ቋንቋ ፡-

ቅዱስ ጳውሎስ በሦስተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው፥ በኤፌሶን የአርጤምስ ጣዖት ነጋድያንና አምላኪያን ሁከት ካነሡበት በኋላ በመቄዶንያ በኩል ወደ ግሪክ ገባ። በግሪኳ የቆሮንቶስ ከተማም ሦስት ወር ተቀመጠ። የሐዋ.ሥ ፳፥፩-፫። ይህ የሆነውም በ57 ወይም በ58 ዓ.ም እንደ ሆነ የታሪክ አጥኝዎች አርጋግጠዋል።

በዚህ ጊዜ ኢየሩሳሌም በረኃብ ስለተጠቃች ክርስቲያኖችም በአይሁድ ስለተገለሉ አይሁዳዊ ክርስቲያኖች ተቸግረው ነበር ። ቅዱስ ጳውሎስ በአሕዛብ ከተሞች ካሉ አብያተ ክርስቲያናት በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ክርስቲያኖች እርዳታ አሰባስቦ ነበር። ይህንንም በመልእክቱ አንሥቶታል። ሮሜ.፲፭፥፳፭-፳፯

በእነዚህ ታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች መሠረት፡- ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቲቱን የጻፈው በቆሮንቶስ ከተማ፣በ፶፰(58) ዓ.ም ገደማ፣ በወቅቱ የሮም ነዋሪዎች እና የሮም ግዛት ዋና የመግባቢያ ቋንቋ የነበረውን ግሪክኛ ተጠቅሟል። ያደረሰችለትም ፌበን የተባለች እናት ናት። ሮሜ. ፲፮፥፩-፪

## 6. የመልእክቲቱ ዋና ዓላማ፡-

1. ***የእግዚአብሔርን ጽድቅ ማስተማር ነው።*** የእግዚአብሔርን ሕግ አውቀው መጠበቅ ያልቻሉትን እስራኤልንና በጣዖት አምልኮ የተያዙትን አሕዛብን መሐሪው ልዑል እግዚአብሔር ለዘላለማዊ ድኅነት መጥራቱን በዋናነት እንዲህ በማለት አስተምሮአል። የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለመፈጸምና ለማግኘት፡- ማመን ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ፣ በመንፈስ ቅዱስ መመራት እና ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል።
2. ***ክርስቲያናዊ አኗኗርን ማስተማር።*** ይህም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት በቤተ ክርስቲያንና በዓለም የሚኖራቸውን የፍቅርና የመከባበርን ሕይወት ይዟል።

www.zeorthodox.org

**7. የመልእክቱ አከፋፈል -**

የሮሜ መልእክትን ለማጥናት እንዲመች በሚከተለው ሁኔታ ይከፋፈላል፡፡

1. ***መግቢያ*** (፩፥፩-፲፯) ሰላምታ፣ ምሥጋናና ሕዝብ እና አሕዛብ ለመዳን መጠራታቸውን የሚገልጸው - የመልእክቱ ዋና ሓሳብ፤
2. ***ሁሉም የእግዚአብሔር ክብር ጐድሎታል፡፡*** (፩፥፲፰-፫፥፳፫)፡- እስራኤል የተሰጣቸውን ሕግ ባለመጠበቅ፤ አሕዛብም እግዚአብሔርን ባለማወቃቸው የእግዚአብሔር ክብር ጐድሎአቸዋል ፡፡
3. ***መሠረታዊ ትምህርት-ጽድቅ እና ቅድስናን ስለማግኘት፡፡*** (፫፥፳፬ - ፰፥፴፱) የእግዚአብሔርን ክብር ለመጎናጸፍ (ጽድቅ እና ቅድስናን ለማግኘት) የተቻለው :- በክርስቶስ ቤዛነት ነው፡፡ ይህንንም በማመን እና ከመጠመቅ ከመንፈስ ቅዱስ እንቀበለዋለን፤ የጽድቅ ፍሬም በዚያ አለ ፡፡
4. ***የእስራኤል አለመታዘዝ እና የአሕዛብ መጠራት፡፡***(፱፥፲፩-፴፮) እስራኤል በአባቶች በኩል በእግዚአብሔር ምርጫ ቢጠሩም ለእግዚአብሔር አልታዘዙም፤ አሕዛብም በወንጌል በእምነት ተጠሩ፡፡
5. ***ተግባራዊው ክርስቲያናዊ ሕይወት*** (፲፪፥፩-፲፬፥፳፫) በዚህም የተለወጠ ክርስቲያናዊ ሕይወት፣በጸጋ መሰማራት፣የሌሎችን ሸክም መሸከም እና በማያምኑ መሐል የሚኖረን ኑሮ ተገልጦአል፡፡
6. ***ማጠቃለያና የስንብት ሰላምታ*** (፲፭፥፩-፲፮፥፳፯) የሌሎችን ሸክም በመሸከም በአንድ ሐሳብ መሆንን ፣ ሕዝብና አሕዛብ በተሰጣቸው ተስፋ እንዲጸኑ አሳስቧል፡፡ አሕዛብን ለማስተማር የደከመው ጳውሎስ ወደ ሮም መሄድ አልተሳካለትም፡፡

በይሁዳ ያሉትን ድሆች እንዲያግዙ በመጠየቅም ማጠቃለያ ሰጥቷል፡፡ (፲፭፥፩ እስከ ፍጻሜ ምዕራፍ) ሲያጠቃልልም በአደራ ሰላምታ እና ከስሕተት እንዲጠበቁ በተሰጠ ማስጠንቀቂያ ዘግቶታል፡፡ (፲፯፥፩-ፍ/ም)

## ማጠቃለያ፡-

- የሮም ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አንዷዋ ናት፡፡ በዚያም ከአሕዛብና ከአይሁድ ያመኑ ይኖሩባት ነበር፡፡ በንቀትና በትዕቢት የተነሣውን ዕውቀት የጎደለውን ልዩነት በማጥበብ ሰላም እና እርቅ ለማምጣት ሐዋርያው መልእክቱን ጽፏል፡፡
- በቆሮንቶስ በ፶፰(58) ዓ.ም ገደማ የተጻፈችው መልእክት ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን ጽድቅና ክርስቲያናዊ ኑሮን ማስተማር ነው፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

1. ሰውን ሁሉ አክብሩ፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው በእኩል ፈጥሮታል በአንድነትም ለዘላለማዊ ሕይወት ጠርቶናልና በንቀት፣ በስድብ እና ባልተሟላ ዕውቀት ክፉ መነጋገር አይገባም፡፡
2. ከዛሬ ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት (ለ፲፮ ቀናት) የሮሜን መልእክት በቀን አንድ ምዕራፍ አንብቡ፡፡

***ይቆየን...***

***ጥያቄዎች፡-***

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጻፋቸው መልእክታት ስንት ናቸው?
2. የጥንቷ ሮሜ አሁን የት የምትገኝ ከተማ ናት? መቼ? እና በማን? ተመሠረተች በወቅቱ የነበራት ግዛት ከየት እስከ የት ነበር? አይሁድ ወደ ሮም የሔዱበት ምክንያት ለምን ነበር?
3. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮም የሔደው መቼ? እና በምን ምክንያት ነበር?
4. በወቅቱ የሮሜ ቤተ ክርስቲያን ፈተና ምን ነበር? አብራሩ፡፡
5. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሮሜን መልእክት የጻፈበት ምክንያት ምንድነው? ዓላማውስ?

www.zeorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች(ሁለት)

## አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- እግዚአብሔር ሁሉንም ለድኅነት እንደጠራ መማር የትምህርቱ ዋና ዓላማ ነው፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡- ***"ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና ፡፡"*** ሮሜ.፩፥፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ሮሜ.፩፥፩-፲፯፣ ‹‹ቅዱስ ጳውሎስ ትርጓሜ›› በመሐሪ ትርፌ፣ ‹‹The Epistle of Saint Paul to the Romans››: Father Tadros Yakob Malaty: 2007-2008

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን የሮሜ መልእክትን የጥናት መግቢያ አይተናል፤ መልእክቲቱ በሰባት ዐበይት ክፍሎች እንደምትከፈልም ተምረናል፡፡ በዛሬው ጥናታችንም የመልእክቲቱን የመግቢያ (ሮሜ.፩÷፩-፲፯) ክፍል እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

***ሀ. የመልእክቲቱ የመግቢያ ክፍል፡-*** ይህ የሮሜ መልእክት የመግቢያ ክፍል የወንጌልን ጥሪ ምንነት ፣ ሰላምታ ፣ ምሥጋና እና የመልእክቲቱ ዋና ሐሳብ የሆነውን የሁሉም መዳንን ይዟል፡፡

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ‹‹ዋና ዓላማ›› የሁሉም መዳን ነው፡፡

1. የወንጌል ጥሪ እና መልሱ (፩÷፩-፯)፡-

**ቅዱስ ጳውሎስ ለወንጌል ሐዋርያነት የተጠራ ነው፡፡** ቅዱስ ጳውሎስ ጥሪውን በማስቀደም ራሱን ያስተዋውቃል፡፡ ይህንንም ***ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ*** በማለት ገልጦታል፡፡

**ጌታችን ጸጋንና ሐዋርያነትን በመስጠት ዓለሙን ጠርቷል፡፡** ዓለም ለመዳን የተጠራበት አገልግሎት የተፈጸመው ክርስቶስ ጸጋንና ሐዋርያነትን በመስጠቱ ነው፡፡ ***‹‹ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን፤››*** ሐዋ.፩፥፭ ይህንን ጸጋና ሐዋርያዊ ተልእኮ ቤተ ክርስቲያን በትውልድ ሁሉ ስታስተላልፍ ኖራለች፡፡

**የወንጌል ጥሪ ለሚታዘዙ ሁሉ ነው፡፡** የወንጌልን ጥሪና ዓላማ ‹‹***በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ለእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ***›› ፩፥፭ እንዳለ በእምነት ለሚታዘዙ የሚተላለፍ ጥሪ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥሪው ቅድስናን ለመስጠት*** ነው፡፡*የወንጌል ዓላማ ሰዎች **የኢየሱስ ክርስቶስ*** ወይም ***ቅዱሳን*** እንዲሆኑ ነው፡፡ ‹‹***የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ፡፡ በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ፡፡***›› ሮሜ.፩፥፮-፯ ሆኖም ***የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና፡፡*** ማቴ.፳፪፥፲፬ ከጥቂቶቹ የተመረጡት ጋር ለመቆጠር ለጠሪው ራስን መስጠትና ለጥሪው ከማይሆኑት ነገሮች መለየት ያስፈልጋል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ራሱን ለእግዚአብሔር ፈጽሞ የሰጠ ነው፡፡ ሰዎች ክርስቲያን መሆን በሚያፍሩበት ዘመን፤ እርሱ ***"የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ"*** ሮሜ.፩፥፩ ብሎ ራሱን ለሰጠለት ታመነ፡፡ ሐዋርያው ራሱን የሰጠበት መጠን የበለጠ የተገለጠው በገላትያ መልእክቱ ነው፡፡ ***"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው፡፡"*** ገላ.፪፥፳ ቅዱሳን ለታላቅ ክብር የበቁት ራሳቸውን በመስጠታቸው ነው፡፡ ሆኖም ብዙዎቻችን ኃጢአትና የዓለም ልምምዶቻችን ራሳችን ለእግዚአብሔር ባርያ (አገልጋይ) እንዳንሆን ይይዙናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ እንደ መፍትሔ የሚያመለክተን ***መለየትን*** ነው፡፡

***ወጣቶች ሆይ*** ውጤታማ ስፖርተኛ የአልኮል መጠጥ፣ የአደንዛዥ *ዕፅ* ሱሰኛ መሆን አይችልም፡፡ ከሱሱ ሊለይ ይገባዋል፡፡ የወንጌል ጥሪም ከኃጢአትና ከዓለም ፍቅር መለየትን ትፈልጋለች፡፡ ‹‹***አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል፤***›› *ያዕ*.፬፥፬ ከጥቂት የተመረጡት ጋር ለመቆጠር ከሚያስፈልጉት አንዱና ቀዳሚው ከኃጢአትና ከዓለም ፍቅር መለየት ነው፡፡ ይህም በቀጣይነት በ*ዕ*ለታዊ ሕይወት መገለጥ አለበት:: ሐዋርያው መንፈሳዊ ልምምዱን ***"ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ"*** በማለት አስተምሮናል፡፡ (ሮሜ.፩፥፩-፪) በመሆኑም ለወንጌል ያለን መልስ ዉጫዊ ሳይሆን ከልብና በሕይወት የሚገለጥ መሆን አለበት፡፡ እመቤታችን ስትበሰር ‹‹እንደቃልህ ይደረግልኝ›› አለች፤ እንደቃሉ ኖረች፡፡

***ወንጌል ምንድናት***? ሐዋርያው ወንጌል ምን እንደሆነች አብራርቶልናል፡፡

***ወንጌል አስቀድሞ በነቢያት ተነግሮላታል፡፡ ታሪካዊ አጋጣሚ አይደለችም*** ፡፡***"በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ፡፡"*** ሮሜ.፩፥፩-፪

www.zeorthodox.org

***ወንጌል*** በእግዚአብሔር ልጅ ***መገለጥ ተመሠረተች፡፡ ዓላማዋም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ*** ማብሰር ነው፡፡***"የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ"*** ፩ኛ. ዮሐ.፫፥፱

***ወንጌል*** የክርስቶስን ሰው ***የመሆን ምስጢር መረዳት*** ነው፡፡ ሐዋርያው ***"በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ"*** (ከድንግል ማርያም)***"እንደ ቅድስና መንፈስ ግን.....የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ***

***ስለ ልጁ ነው ”*** ካለ በኋላ ***“እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።”*** (፩÷፫-፬) ይላል። ኢየሱስ ክርስቶስ የተዋሕዶ ስም ነው። ለዚህ ነው ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ ከአምላካዊው ክብሩ ሳይጎድል፣ በሥጋ መገለጡን ማመን፣ መረዳትና ማስተላለፍ ነው፤ የምንለው። ተዋሕዶ ከሁለት አካል (የሰው እና የአምላክ አካላት) አንድ አካል ነው፤ ከሁለት ባሕርይ የሰው እና የአምላክ ባሕርያት አንድ ባሕርይ ነው፤ (በተዋሕዶ) ብሎ የልጁን መገለጥ ማመን ነው። ሐዋርያው በዚህ ክፍል ያስተማረንም ይህንኑ የወንጌልን መሠረታዊ እምነት ነው።

በተጨማሪም ***ከዳዊት ዘር*** (ከድንግል ማርያም) ***የተወለደ*** እና ***የእግዚአብሔር ልጅ***፤ በማለት ***ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ*** ሁለት ልደታት እንዳሉት ገልጧል።

2. ሰላምታ እና ምሥጋና። (፩÷፯-፰)

በዚህ ክፍል የተደራሾቹን ማንነት ***“በሮሜ ላላችሁት ሁሉ”*** በማለት ይገልጣል። አባታዊ ቡራኬውን ከሰላምታ ጋር ሲያስተላልፍ ***“ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።”*** ቁጥር ፯ ይላል። ይህም በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት የምናገኘው የተለመደ ሰላምታ ነው።

ከዚያም የተመሰከረላትን እምነታቸውን ያመሰግናል። ***“እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ።”*** (፩÷፰) በማለት በጎውን በማመስገን ጀመሯል።

**የቅዱስ ጳውሎስ ተልእኮ። (ሮሜ.፩÷፱-፲፮)**

የቅዱስ ጳውሎስን መንፈሳዊ ተልእኮ ጌታችን ለሐናንያ ገልጦለት ነበር። ‹‹***በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው።*** የሐዋ.፱÷፲፭ ሐዋርያው ይህንን በእግዚአብሔር የተመሰከረለትን መንፈሳዊ ሓላፊነት ሲወጣ ኖሯል።

ሐዋርያው በዚያን ዘመን አሕዛብ ዋና ከተማ በነበረችውና ከ1.2 ሚልዮን በላይ ሕዝብ በነበረባት በሮሜ ተልእኮውን ለመፈጸም እንዲችል ይናፍቃል። በሮሜ ያሉትን ክርስቲያኖችንም ለማየት ጓጉቷል። (ቁ.፲፩ እና ፲፪) ይህንን ፍላጎቱንም በጸሎት አሳስቧል።***“በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና፤ ምናልባት ብዙ ቆይቼ ወደ እናንተ አሁን እንድመጣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀናልኝ እየለመንሁ ሁልጊዜ ስጸልይ ስለ እናንተ ሳላቋርጥ አሳስባለሁ።”*** ቁ. ፱-፲ ሆኖም በሮሜ በአካል ተገኝቶ ተልእኮውን መፈጸም አልቻለም፤***“ወንድሞች ሆይ፥ በሌሎቹ አሕዛብ ደግሞ እንደ ሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደ እናንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።”*** ሮሜ.፩÷፲፫።

www.zeorthodox.org

በአካል ለመገኘት ያልተቻለውን በመልእክት ለማስተላለፍ ተዘጋጀ።***“ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም ፥ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ፤ስለዚህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ***

***ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ።"*** ሮሜ.፩፥፲፬-፲፭ ልጆች እግዚአብሔር ለሁሉም ምክንያት አለው። ይህች መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ በአካል ተገኝቶ የተፈጠረውን ችግር መፍታት ባይችልም በመልእክት ለመፍታት በመፈለጉ የተጻፈች ናት። በአካል ቢገኝ መልእክቲቱን ላናገኛት እንችል ነበር። እግዚአብሔር ይህ ትምህርት ለትውልድ ሁሉ በጽሑፍ እንዲዳረስ ስለ ፈቀደ ይህን አደረገ።

ሌላው መንፈሳዊ ሓላፊነት በጥቃቅን ምክንያቶች፣ በቦታ እና በምድራዊ ኃይል አይገታም። እኛም ከሐዋርያው በአገልግሎታችን በጸሎት ከመትጋት ጋር በአጋጣሚው ሁሉ መበርታትን እንማራለን።

### 4. የሁሉም መዳን - የመልእክቲቱ ዋና ጭብጥ ነው። (ሮሜ.፩፥፲፮-፲፯)

ይህን በመልእክቲቱ ተከታይ ክፍሎች የምናየው ሲሆን፤ አሁን ዋና ሐሳብ መሆኑን በማንሣት እናልፈዋለን። ***"በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።"*** ፩፥፲፮ ክርስትና የዓለማችን ትልቁ እና ብዙ ተከታይ ያለው ሃይማኖት ሳይሆን በፊት፤ ክርስቲያን መሆን ለአንዳንዶች ወንጀል ለሌሎችም አዕምሮን ማጣት ነበር። በዚህ ምክንያት ብዙዎች የወንጌልን ቃል መመስከርና ክርስቲያን ነኝ ማለትን ይፈሩ ነበር። ጳውሎስም ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት እንዲሁ ነበር። የሐዋ.ሥ.፳፮፥፱-፳፱ አሁን ግን በወንጌል የተሰበከው የመስቀል ኃይል የሰው ልጆች የሚድኑበት ኃይል እንደሆነ ተረድቷልና፤ ከራሱ አልፎ ለሌሎችም አርዓያ በመሆን ***"በወንጌል አላፍርም"*** ሲል ያስተምራል።

***የሚያድነው የእግዚአብሔር ኃይል።*** ሐዋርያው በዚህ የእግዚአብሔር ኃይል ተጠቅሟል። ሌሎችም እንዲጠቀሙ ይተጋል። ***"አስቀድሞ ለአይሁድ ደግሞም ለግሪክ ሰው...የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው።"*** ሮሜ.፩÷፲፮ ይህ የእግዚአብሔር ማዳን በዘርና በድንበር ሳይወሰን ***"ለሚያምኑ ሁሉ"*** ነው።

***ሁሉ።*** በሮሜ መልእክት ከስልሣ ጊዜ በላይ የምናገኘው ቃል ነው። ይህ ቃል አይሁድንና አሕዛብን (የሰው ዘርን ሁሉ) ልዩነት ሳይኖር መበደላቸውንና ለመዳን መጠራታቸውን ለመወከል ተገልጧል።

ስናምን የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል እናገኛለን። በነቢያቱ ***ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ፤*** ክርስትና ***"የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት።"*** የሚገለጥበት ነው። ሮሜ.፩÷፲፯

www.zeorthodox.org

አይሁድ በሕግ እየተመኩ ሕግን አለመፈጸማቸውና መተላለፋቸው ፣ አሕዛብም እግዚአብሔርን አለማወቃቸው ከእግዚአብሔር ጽድቅ አርቋቸው ነበር። አሁን ግን ሰዎችን ሁሉ ለማዳን የተዘረጋ የእግዚአብሔር ኃይል አለ። እርሱም በክርስቶስ ቤዛነት የተገኘ ጽድቅ ነው። አሕዛብ እና አይሁድ በልዩነት ይኖሩ ነበር ፤ አሁን ግን ሁለቱም በእግዚአብሔር ኃይል ለመዳን ተጠሩ። መሠረቱም እምነት ነው። የሰው ልጆች መዳን የሚችሉት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምኑ ነው።

**ማጠቃለያ፡-** የሮሜ መልእክት ከምዕ.፩÷፩-፲፯ የወንጌል ጥሪ ሁሉንም ለመዳን መሆኑን ያስተምረናል፡፡

**ተግባር፡-** የተማርነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ፡፡

***መዝሙር***

አቀድም አዕኩቶቶ ለእግዚአብሔር

በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

***ጥያቄዎች፡-***

1. የወንጌል ጥሪ እና መልስ ምንድ ነው? ዓለም ለመዳን የተጠራበት አገልግሎት የተፈጸመው እንዴት ነው? የወንጌል ጥሪ ለማን ነው? ለምን? እንዴት? ምሳሌ በመጥቀስ አብራሩ፡፡
2. ‹‹ወንጌል›› ምንድን ናት? እንዴት ተመሠረተች? አብራሩ፡፡
3. ኢየሱስ ክርስቶስ የተዋሕዶ ስም ነው ሲባል ምን ማለት ነው? ጌታችን ስንት ልደታት አለው?
4. የሮሜ መልእክት ዋና ዓላማ እና ጭብጥ ምንድነው?
5. የሮሜ ክርስቲያኖች የተመሰገኑት ለምንድነው?

www.zeorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች(ሦስት)

## አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በእግዚአብሔር ቸርነት(ጸጋ) ለበደለኞች ሁሉ የተከፈተውን የጽድቅን በር ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል"*** ሮሜ. ፫÷፳፪-፳፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**ሮሜ.፪÷፲፰-፫÷፳፬፣ ‹‹ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው›› 1988 ዓ.ም፣ The Epistle of Saint Paul to the Romans:Father Tadros Yakob Malaty:2007-2008

**መግቢያ፡-** ባለፉት ሁለት የትምህርት ክፍሎች፤ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች መግቢያ ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም አሕዛብ እና አይሁድ ያጡት ጽድቅ ፤ በክርስቶስ ቤዛነት እንደተሰጣቸው እንማራለን፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ.፩÷፲፰-፫÷፳፬ ሁሉም የእግዚአብሔር ክብር እንደጎደላቸው አስተምሯል፡፡ ምክንያቱም በኃጢአት መከሰሳቸው ነበር፡፡ በክሱም በሁሉም ተፈረደባቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. ሁሉም የእግዚአብሔር ክብር ጐድሎአቸዋል፡፡(፩÷፲፰-፫÷፳፫)

አይሁድም ሆኑ አሕዛብ በኃጢአት ስለወደቁ፣ጽድቅን መፈጸምና ማግኘት አልቻሉም፡፡ ‹‹***ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል"*** ሮሜ.፫÷፳፪ ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ክፍል፤በአሕዛብ ጀምሮ የአይሁድን መንፈሳዊ ክብር ማጣት ያብራራል፡-

www.zeorthodox.org

አሕዛብ፡- የጽሑፍ ሕግ አልተቀበሉም ሆኖም፤ ***ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸው፡፡ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ፡፡››*** ሮሜ.፪÷፲፬-፲፭ እግዚአብሔር ለሁሉም አዕምሮ ሰጥቷል ፣ እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ለማምለክ

ተፈጥሮም አስተማሪ ናት፡፡ አሕዛብም ጥበብ አለን እንደማለታቸው ከሕሊናቸውና ከተፈጥሮ ተረድተው አምላካቸውን አላወቁትም፣ አላመለኩትምም፡፡ ሮሜ.፩፥፲፰-፳ ይልቁንም በእንስሳትና በፍጥረታት ምስል ያዘጋጇቸውን፣ የእጆቻቸውንም ሥራ አመለኩ፡፡ ሮሜ.፩፥፳፩-፳፭ እግዚአብሔርም ለአምላክነቱ ስለሚቀና ተዋቸው፡፡ ይህም አሳዛኝ መንፈሳዊ ውድቀት አስከተለባቸው፡- የማይረባ ሰይጣናዊ አእምሮ ሠልጥኖባቸው፣ በአመጽ ኖሩ፡፡ ከተፈጥሮ ፍቃድ ውጪም በተመሳሳይ ጾታ ዝሙት ወደቁ፡፡ ክፉ እና አመጽ የሆነው ሁሉ ሠለጠነባቸው፡፡ ይህም እግዚአብሔርን ባልወደዱት መጠን ለማይረባ አዕምሮ ተላልፈው ስለተሰጡ ነው፡፡ ሮሜ.፩፥፳፭-፳፰

አይሁድ ኃጢአትን ***ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል፤*** ሮሜ.፩፥፴፪ የሚለውን እያወቁ፤ በመሥራትና ከሠሪዎቹ ጋር በመስማማት ፍርድ የተገባቸው ሆነው ተገኙ፡፡ ይህን ሆኖ በሌላው በመፍረድ ኃጢአትም ወደቁ፡፡ ***አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፥ የምታመካኘው የለህም፤ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና፡፡ … እንደዚህ በሚያደርጉትም እውነተኛ የእግዚአብሔር ፍርድ አለ፡፡… እርሱ ለእያንዳንዱ እንደሥራው ያስረክበዋል፡፡*** ሮሜ ፪፥፩-፮ ሐዋርያው በዚህ መልእክቱ ይህንኑ የአይሁድን ግብዝነት ሲያብራራ፡- ‹‹ ***አንተ ግን አይሁዳዊ ብትባል በሕግም ብትደገፍ በእግዚአብሔርም ብትመካ ፣ ፈቃዱንም ብታውቅ ከሕግም ተምረህ የሚሻለውን ፈትነህ ብትወድ ፤ በሕግም የእውቀትና የእውነት መልክ ስላለህ፥ የዕውሮች መሪ፥ በጨለማም ላሉ ብርሃን፥ የሰነፎችም አስተማሪ፥ የሕፃናትም መምህር እንደ ሆንህ በራስህ ብትታመን፤እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን ? አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን? አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን ? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን? በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን ? በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡››*** ሮሜ.፪፥፲፯-፳፬

የአይሁድ ብልጫ፡- አይሁድ በአባቶችና የቃሉን አደራ በመቀበል ብልጫ (ቅድሚያ) ነበራቸው፡፡***“እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው ? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው፡፡ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው፡፡”*** ሮሜ.፫፥፩-፪ ሕይወት የሚገኝበትን ቃል ቢረከቡም፣ አይሁድ የዘላለምን ሕይወት አላገኙም፤ ምክንያቱም ኦሪት እና ነቢያት ወደ ተናገሩለት እውነት ወደ ክርስቶስ መምጣት እና ማመን አለመቻላቸው ነበር፡፡ (ዮሐ.፭፥፴፰-፵፯) ጥላውን (ኦሪትንና የነቢያትን ትንቢት) ይዘው አካል ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ አልደረሱምና ብልጫቸው እንደ ዔሳው ብኵርና ሆናባቸው አልተጠቀሙባትም፡፡

www.zeorthodox.org

ሁሉም በደለኞች ሆነው እግዚአብሔር የሚታገሰው ለንስሐ እንዲበቁ ነው፡፡ እርስ በርስ እየተካሰሱ መመጻደቃቸው ግን የባሰው በደል ነበር፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ***የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?*** ሮሜ.፪፥፬ ያለው፡፡

***ሁሉም ተከሰዋል፡-*** በመሆኑም የጽሑፍ ሕግ የተቀበሉት አይሁድም ሆኑ ፣ በተፈጥሮ ሕግ (ሕገ ሕሊና ወይም ሕገ ልቦና) የነበሩት አሕዛብ ወድቀዋልና ፍርድ ነበረባቸው፡፡ ***ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋልና፡፡*** ሮሜ.፩÷፲፪ ማንም መመካት አይችልም፡፡ ጠላታችን ሰይጣን አሳሳችና እና ከሳሽ ነው፡፡ (ዘካ.፫÷፩፣ ኢዮ.፩÷፮-፲፩፣ ራእ.፲፪÷፲) ሁሉንም በኃጢአት አሰናክሎ፣ ራሱ ስለከሰሳቸው ኩነኔ ነበረባቸው፡፡ ***አይሁድም የግሪክ ሰዎችም ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋልና፡፡*** ሮሜ.፫÷፱ ***ጻድቅ የለም አስተዋይም የለም ፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም ሁሉ ተሳስተዋል በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤*** ሮሜ.፫÷፲፩-፲፰ እግዚአብሔርም ***ሰው እንደሌለ አየ ፥ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም፤*** ኢሳ.፶፱÷፲፫ ***ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፡፡*** ሮሜ.፫÷፳፫

***ሁሉ*** - የሚለው ቃል ቅዱሳንን ያካትታል? ***"ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል"*** ሮሜ ፫÷፳፪ የሚለውን ክፍል ስናነብ፤ ከዓውደ ምንባቡ የምንረዳው በሮሜ ቤተ ክርስቲያን በትእቢት የተለያዩትንና በእነርሱ የተወከሉትን አይሁድን እና አሕዛብን ነው ፤ ሁለቱም ጽድቅን ማምጣት አልተቻላቸውምና፡፡

ሆኖም ጻድቅ የተባሉና በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኙ ቅዱሳን ከጌታ ልደት በፊት ነበሩ ለምሳሌ፡- አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው - ሔኖክ፤ ዘፍ.፭÷፳፬፣ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘውና ***ጻድቅ ፍጹምም ነበር*** የተባለው - ኖኅ፤ ዘፍ.፮÷፰-፱ ፣ የተባረከው አብርሃም፤ ዘፍ.፲፪÷፩-፫ ፣ ***ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ሰው፤*** ኢዮ.፩÷፰ ብሎ እግዚአብሔር የመሰከረለት - ኢዮብ ፣ በቅድስና ከሴቶች ከተወለዱት ***የሚበልጥ*** የተባለው - ዮሐንስ (ማቴ.፲፩÷፲፩) እና ሌሎችም ቅዱሳን ክርስቶስ በሥጋ ከመገለጡ ቀድመው ነበሩ፡፡ ሆኖም ***እነዚህ ሁሉ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም፥ ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበርና ፤*** ዕብ.፲፩÷፴፱-፵ የዘላለም ሕይወት ማግኘት ገነት መግባት አልቻሉም፤ ለዚህ ነው ኢሳይያስ፤ ***ጽድቃችንም እንደ መርገም ጨርቅ ነው*** ያለው፡፡ ኢሳ.፷፬÷፮

www.zeorthodox.org

በሌላም በኩል በሰው እና በሕግ ፊት የነጻ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ***መንጻት*** አልተቻለውም፡፡ ***‹‹በሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ፥ ያለ ነቀፋ ነበርሁ››*** ፊልጵ.፫÷፮ ***ያለው*** ጳውሎስ በሌላ ቦታ ***‹‹ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ››*** ፩ኛ ጢሞ.፩÷፲፭ ብሎ ነበር፡፡ ምንም በሕግ ያለ ነቀፋ ቢኖርም በኃጢአት የተያዘበት ምክንያትም ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም እንዲህ ይላል፡- ***በእግዚአብሔር የጽድቅ ብርሃን ፊት ሁሉም ኃጢአተኛ ነው፣ በሕግ ፊት ንጹሕ የሆኑት እንኳን ንጹሐን***

***አይደሉም። ይህም በድሆች ፊት ባለጸጋ ሆኖ በነገሥታት ሀብት ፊት ምስኪን ደሃ ወይም የድሆች አለቃ የሆነን ሰው ይመስላል።*** (ser.on N.T lesson 30:4 / Malaty comm.on epi. To.Raman p.63) ***ያዕቆብም ‹‹ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ። አትግደል ብሎአልና፤››*** ያዕ.፬÷፲ ያለው ለዚህ ነው።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን፤ ***ከሁሉ ተለይታ የተባረከች፤*** ሉቃ.፩÷፳፰ ናት። ይህም እግዚአብሔር አስቀድሞ ላቀደው ማዳን ያዘጋጃት እና ከኃጢአት የተረፈች ዘር በመሆንዋ ነው። ኢሳ.፩÷፱ እርስዋም አንጽቶ የጠበቃትን ***መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤*** ሉቃ.፩÷፵፯ ስትል አመስግናዋለች።

### 2. የእግዚአብሔር ማዳን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ጭንቅ ስለሆነችው ጽድቅ ሲያስተምር፤ ***እንግዲህ ማን ሊድን ይችላል?*** ተብሎ ሲጠየቅ፤ ***በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አለ*** ። ሉቃ.፲፰÷፳፮-፳፯ የሰው ልጅ ጠላቱን ዲያብሎስን ማሸነፍ ፣ ኃጢአትን ድል በመንሳት መቆምና ጽድቅን በራሱ ማምጣት አልቻለም። የሰውን ድካም የሚያውቀው ሰማያዊው አባትም የሰውን ልጅ እንዲሁ አልተወውም። ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይላል፡-***ርጉም በሆነ ከይሲ ምክር ትእዛዙን ባፈረስን ጊዜ ከተድላ ገነት ወደ ጥፋት፣ ከሕይወት ወደ ሞት፣ ከነጻነት ወደ መገዛት ወጣን ፤ ለኃጢአት ቀንበር ተገዛን፤ እርሱ ግን ፍጥረቶቹን አልተወንም ቸልም አላለንም፤ እርሱን እንደበደልነው መጠን ፈጽመን እንጠፋ ዘንድ በኃጢአታችን አልተቀየመንም፤ ወደደን እንጂ ማረን ይቅርም አለን ከሚገዛንም እጅ አዳነን።(ቅዳሴ ቁ.15)***

እናም ልዑል እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ጽድቅ እና መዳን ሊሰጥ ወደደ። ***ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት ፥ ጽድቁም አገዘው፤*** ኢሳ.፶፱÷፲፮ ተብሎ ***"በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገለጠ"*** ሮሜ. ፫÷፳፩ ይህም ማለት ሰዎች የተፈጥሮን እና የመጽሐፍን ሕግ በመጠበቃቸው ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ባቀደው ዕቅድ በነቢያት እንዳናገረው ጽድቅ ተሰጠን። (እነዚህን ጥቅሶች አንብቡ ኢሳ.፵፮÷፲፪-፲፫፣ ፶፩÷፭-፣፶፮÷፩) ***"እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው"*** ሮሜ. ፫÷፳፪

በሌላም ቦታ የእምነት የማዳን ኃይል ተጠቅሷል። የእስር ቤቱ አለቃ፤ ***እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?*** ሲል ጳውሎስ እና ሲላስ የመለሱለት ‹‹***በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ***›› ብለው ነው። የሐዋ.፲፮÷፴፩ ፊልጶስም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ፤ ‹‹***እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማነው?***›› ሲለው፤ ***በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል፤*** አለው። እርሱም፤‹‹***ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ*** ›› አለ። ተጠመቀ የሐዋ.፰÷፴፯

**እምነት ብቻ ለምን ተጠቀሰ?**

www.zoorthodox.org

እምነት መሠረት ነው፡፡ያላመነ ሌላ ሥራ ቢታዘዝ አይጠቀምበትም፤ ***ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና፡፡*** ዕብ.፲፩፥፮፡፡ ያመነ፦ ይጠመቃል፣የመልካም እምነቱ ፍሬ የሆነ መልካም ሥራም አለው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኝ ጽድቅ ሲልም የክርስትናውን መሠረት እየነገረን ነው፡፡

## ማጠቃለያ

አሕዛብ በጣዖት አምልኮ እና በማይረባ አዕምሮ ተይዘው ከጽድቅ ሲወጡ፤ አይሁድ አውቀው አጥፊዎች በመሆን ከፍርድ አልዳኑም፡፡ ሮሜ.፩፥፲፰-፫-፳፬ አለማመንም ሆነ ኃጢአትን መሥራት ከእግዚአብሔር ክብር ያጎድላል፡፡ የእግዚአብሔር የማዳን ኃይል ያስፈለገውም ለዚህ ነው፡፡ ***እግዚአብሔር ጽድቃችን ነው፡፡*** ኤር.፳፫፥፮ ተብሎ እንደተጻፈ በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን ጽድቅ ሰጠን፡፡

ጠላታችን ሰይጣን ለማሳት እና ለመክሰስ የቆመ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ሲያድነን በእምነት ሁሉንም ድል የማድረግ ኃይል ሰጥቶናል፡፡ በከይሲ ምክር ሳንታለል ፣ ኃጢአትን በእምነት ድል አድረገን በጽድቅ እንኑር፡፡ ‹‹***ለሚያምን ሁሉ ይቻላልና***›› ማር.፱፥፳፫

አይሁድ የቃሉን አደራ በመቀበል ፣ ብልጫ ቢኖራቸውም የሁሉ ፍጻሜ በሆነው በክርስቶስ አላመኑምና አልተጠቀሙበትም፡፡ እኛም ‹‹***ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን፡፡***›› ያዕ.፩፥፲፰ ተብሎ እንደተጻፈ የቃሉ አደራ ተሰጥቶናል፣ የእግዚአብሔርን ልጅነትም ተቀብለናልና በቃሉ መኖርና በእምነት መታዘዝ ይጠበቅብናል፡፡

## ተግባር፦

በተፈጥሯዊም ሆነ፣ በጽሑፍ ከእግዚአብሔር ለተሰጠን መታዘዝ አለብን፡፡ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ማመን እና መልካም መሆን ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ቃል እና ለሕሊናችሁ ታማኝ ሁኑ፡፡

### ጥያቄዎች፦

1. ሁሉም የእግዚአብሔር ክብር የጎደላቸው ለምንድነው? አሕዛብ እና አይሁድ ያጎደሉት ምንድነው? አብራሩ፡፡?
2. የእግዚአብሔር ጽድቅ የሚገኘው በምንድነው?
3. የአይሁድ ብልጫ በምን ነበር? ያልተጠቀሙበትስ ለምንድን ነው?
4. ሰዎች የተከሰሱት ለምንድን ነው? ማነው ከሳሻቸው?
5. ‹‹ሁሉ የእግዚብሔር ክብር ጎድሎአቸዋል›› ሮሜ.፫፥፳፪ የሚለውን ኃይለ ቃል በምሳሌና በጥቅስ አብራሩ፡፡
6. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ‹‹ከሁሉ ተለይታ የተባረከች›› ሉቃ.፩፥፳፫ የሚለውን በምሳሌ አብራሩ፡፡
7. መዳን በእምነት ነው፤ ሲባል ምን ማለት ነው? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች(አራት)

## ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡- ተማሪዎች ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ እና ስለ ቅድስና ምንነት እና ኑሮ ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች አብራርተው ይመልሳሉ።

**የሚጠኑ ጥቅሶች**፡-*"በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።"* ሮሜ ፫፥፳፬ *"እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን ? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ።"* ሮሜ.፫፥፴፩

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ሮሜ.3፡24-8፡39; ‹‹ ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው›› 1988 ዓ.ም፤ The Epistle of Saint Paul to the Romans: Father Tadros Yakob Malaty:2007-2008

**መግቢያ፡-** ይህ የሮሜ መልእክት ጥናታችን ቀጣይ ክፍል ነው። ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ቅዱስ ጳውሎስ በዚሁ መልእክቱ ከምዕ.፩፥፲፰-፫፥፳፬ ሁሉም የእግዚአብሔር ክብር እንደጎደለው ማስተማሩን፣ ምክንያቱም አሕዛብ እና አይሁድ በኃጢአት መከሰሳቸው እንደነበር ፣ የጎደላቸውን የእግዚአብሔር ጽድቅ፤ በክርስቶስ በማመን እንደተሰጣቸውም ተምረናል። በዛሬው ትምህርታችንም የጽድቅ ሥራ መግቢያ ስለሆኑት እምነትና ጥምቀት በሮሜ መልእክት መሠረት እናያለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

**ጽድቅ የተገኘው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት** ነው። በጌታችን እስከ ሞት በተከፈለልን ቤዛነት የጽድቅ በር ተከፍቶልናል። አይሁድ የጽሑፍ ፣ አሕዛብ የተፈጥሮን ሕግ መጠበቅ ስላልቻሉ የእግዚአብሔር ክብር ቢጎድላቸውም፡- " ***በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።"*** ሮሜ.፫፥፳፬ እንዲያው ሲል ዋጋ ያልከፈሉበት መሆኑን ያሳያል ፤ ጸጋ ማለትም ስጦታ ማለት ነውና። በእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታ ይጸድቃሉ ማለት ነው።

www.zeorthodox.org

**ጽድቅ በእምነት ይገኛል**። እምነት መሠረት ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ የጌታችንን ማዳን፡-*"በእምነት የሚገኝ"* ሮሜ.፫፥፳፭ ያለው። ምክንያቱም፡-

- ያመኑ ተነሳሕያን ናቸው። በኃጢአታቸው ተጸጽተው ንስሐ ይገባሉ። እውነተኛው ንስሐ ስርየት ያሰጣል። እግዚአብሔር ***በደሙ የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤*** በተባለው በወልድ ቤዛነት ስርየት ያገኛሉ። ለዚህ ነው ዮሐንስ፤ ‹‹***የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።*** ፩ኛ ዮሐ. ፩፥፯-፱ ያለው። እናም ኃጢአታችንን አምነን በእግዚአብሔርና በካህኑ ፊት በመናዘዝ ፣ በእምነት እና በእውነተኛ ንስሐ የሚገኘውን አዲስ ሕይወት መጓዝ እንጀምር።“ ***ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ..መተው ...ነው፥*** ” ሮሜ.፫፥፳፭
- መዳንና ጽድቅ የሚገኘው አይሁድ መፈጸም ሳይችሉ በሚመኩበት በሕግ ሥራ ሳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በማመን ነው።***ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው ? እርሱ ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፥ በእምነት ሕግ ነው እንጂ። ...*** ይህ ማለት ሕግን መሻር ሳይሆን፤ ሕግን በእምነት ማጽናት ነው።“ ***እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን ? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ*** ” ሮሜ.፫፥፴-፴፩
- ሕግ በእምነት ሲጸና ጌታችን በተራራው ስብከት እንዳስተማረን ከጻፎችና ከፈሪሳውያን በሚበልጥ ጽድቅ መገኘት ነው።ማቴ.፭፥፳። ለምሳሌ፡- የሚያምኑ አትግደል የሚለውን ሕገ እግዚአብሔር ያከብራሉ። እንዲሁም ለመግደል ምክንያት ከሆነውና ከመግደል በማይተናነሰው በስድብ ፣ በቂምና በቁጣ ተግባር አይገኙም። በሥጋ አለማመንዘር ብቻ ሳይሆን በኃልዮ እና በርእይም አለመውደቅ ነው። ... እነዚህንና ሌሎችን ሕጎች ማጽናት ከባድ ቢሆንም ለሚያምን ሁሉም ይቻላልና ሕግ በእምነት ይጸናል። ማቴ.፭፥፲፯-፵፱

**የእምነት አባት እና አርዓያ አባታችን አብርሃም (ምዕ.፬)፡-** ከላይ ለተነሣው ትምህርት (ስለ እምነት) የአብርሃም ሕይወት እና የዳዊት ትምህርት (በምዕራፍ ፬) በአስረጂነት ቀርበዋል፡-

1. የአብርሐም እምነት ጽድቅ የተቆጠረለት በእምነት ነው።(፬፥፩-፰) ***“አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም። መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።”*** ሮሜ.፬፥፪-፫
   ***ዳዊትም*** በእምነት ሥርየተ ኃጢአት ስላገኘው ሰው መስክሯል። ***“ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል ፤ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፤”*** ሮሜ.፬፥፮-፰ (፬፥፩-፰)
2. አብርሃም የአማንያን ሁሉ (የእምነት) አባት ነው። አብርሃም አመነ ጽድቅ ሆኖም

www.zeorthodox.org

ተቆጠረለት የተባለው ሳይገረዝ ነው። በኋላም ለእምነቱ ምልክት ተገረዘ። ***"የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።"*** ዘፍ.፲፪፥፫ እንደተባለ ለአይሁድና ለአሕዛብ የእምነት አባት ሆነ። በመሆኑም አባታችን አብርሃም የሁላችንም የእምነት አባትና በእምነት ለሚገኘው ጽድቅ አርዓያ ነው። (፬፥፱-፲፮)

3. አብርሃም እና እኛ በተስፋ እግዚአብሔርን በማመን አንድ ነን።(፬፥፲፯-፳፭) አብርሃም ልጅ ሳይኖረው ዘርህ ይበዛል የተባለውን ተስፋ ይዞ አመነ። (ቁ.፲፰) እንደምውት ከሆኑት ከእርሱና ከሳራ ማኅፀን በእምነት ፍሬ ጠበቀ። (ቁ.፲፱) ይህም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። (፳-፳፫)። ***"ነገር ግን። ተቈጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም፥ ስለ እኛም ነው እንጂ ፤ ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው።"*** ቁ.፳፫-፳፭

## ሁሉም በአዳም ሞተው በክርስቶስ ሕይወት ተሰጥቷቸዋል።(ምዕ.፭)፡-

አይሁድም ሆነ አሕዛብ የአንዱ አዳም ልጆች ናቸው። ይህ ምዕራፍ ስለ አዳምና ክርስቶስ ይነግረናል። ሁሉም በክርስቶስ በማመን ጽድቅና ሰላምን ያገኛሉ። ጸጋና ዘላለማዊ ክብርም ተሰጥቷል። በመከራ መጽናትና ማለፍም እንችላለን። ጸጋን የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ ፍቅር አድሎናል። ኃጢአተኞች ሳለን በክርስቶስ መስቀል ታርቀናል። (፭፥፮-፲፮) ሁሉም በቀዳሚው አዳም ሞተው (፭፥፲፪-፲፬) ፣ በዳግማዊው አዳም - በክርስቶስ ሕይወትና ጸጋን አግኝተዋል። (፭፥፲፭-፳፩)

ኃጢአት በበዛበት ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ። ሰዎች ጽድቅን መፈጸምና የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ብቃት እንዲኖራቸው ጸጋ ከመጠን ይልቅ በዝቶ ተሰጠ። ***"በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ።"*** ሮሜ.፭፥፳-፳፩

## ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። (ምዕ.፮)፡-

www.zeorthodox.org

ሐዋርያው በምዕራፍ አምስት ያነሣውን፤ በዚህ ምዕራፍ ይቀጥላል። በተለመደው በጥያቄና መልስ የማስተማር መንገዱም ያስረዳል። ***"እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?"*** ፮፥፩-፪

በእምነት የአብርሃም ልጆች መሆናችንን የነገረን ቅዱስ ጳውሎስ፣ በጥምቀት ወደሚገኘው የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ከፍ ያደርገናል። ይህም ያመኑ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ክርስቲያን

ሲሆኑ የተቀበሉት ነው፡፡ *"ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?"* ቁ.፫ አማንያን በጥምቀት የክርስቶስን የትንሣኤ ድል በሕይወታቸው ያገኛሉ፡፡ ይህም፡-

- ለኃጢአት ሞቶ ለጽድቅ መነሣት ነው፡፡ ቁ.፬-፲፩
- ከዓመጻ እቃነት ወደ ጽድቅ ጦር እቃነት ማደግ ነው፡፡ቁ.፲፪-፲፱

በክርስቶስ የሚገኘው ነጻነትም ይኸው ነው፡፡ ከአብርሃም ጋር አንድ የሚያደርገንም ሥጋዊ ዝምድና አይደለም፤ በቅድስና ሕይወት መለኮታዊ ጸጋና ልጅነትን መቀበል ነው፡፡ ቁ.፳-፳፫ በመሆኑም ይህ ምዕራፍ በሁለት ዐበይት ነገሮች ላይ ያተኩራል፡፡

1. በጥምቀት የሚገኝ አዲስ ሕይወት፡፡ (ምዕ.፮፥፩-፲፬)
2. ክርስቶስን ለመምሰል ፤ በክርስቶስ የተገኘው ነጻነት ናቸው፡፡ (ምዕ.፮፥፲፭-፳፫)

**ማጠቃለያ፡-** በዚህ ሳምንት ትምህርታችን እግዚአብሔር የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች አስተምሮናል፡፡

1. ዘላለማዊ ጽድቅ በክርስቶስ ቤዛነት የተገኘ ነው፡፡*" በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ፡፡"* ሮሜ.፫፥፳፬
2. መዳን፡-*"በእምነት የሚገኝ"* ሮሜ.፫፥፳፰ ነው፡፡ ይህም የመልካም ሥራ ፍሬ አለው፡፡
3. በእምነት ለመኖር አባታችን አብርሃም አብነታችን ነው፡፡ (ሮሜ.፬) የአዳም ልጆች ሁሉ የክርስቶስን የትንሣኤ ድል እንዲያገኙ በጥምቀት ሊመስሉት ይገባል፡፡ (ሮሜ.፭ እና ፮)

**ተግባር፡-** የተማራችሁትን አንብቡ ፣ በጥቂት በጥቂቱ ለመተግበር ሞክሩ፡፡

**አባሪ**

በሮሜ መልእክት፡- ***ቤዛነት*** ፣ ***እንዲያው*** ፣ ***ጸጋ*** እና ***ጽድቅ*** የሚሉትን ቃላት በተደጋጋሚ እናነባለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜያቸውን መረዳት ያስፈልጋልና አሁን እናያቸዋለን፡፡

ቤዛ፡- በእዳ የተያዘን ወይም የተወሰደን ለማስመለስ የሚከፈል ዋጋ ወይም ካሳ ነው፡፡ ይህም መቤዠት፣ መዋጀት በሚሉ አማራጭ ቃላት ተገልጾ በመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን፡፡ ዘሌ.፳፭፥፳፬፣ ዘጸ.፲፫፥፲፫፣ ገላ. ፬፥፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታችንን በመስቀል ተሸክሞ ስለ እኛ ሞቷል፣ ከተያዝንበት የሞት እዳም በደሙ ነጻ ያወጣን ቤዛችን እርሱ ነው፡፡ ማር.፲፥፵፭፣፩ኛ.ጢሞ.፪፥፮ ኤፌ.፩፥፯፡፡

***በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት*** ሲባልም እርሱ ስለ እኛ ኃጢአት በከፈለው መሥዋዕትነት ማለት ነው፡፡ ይህ ለማንም ያልተቻለና በእርሱ ብቻ የተደረገ ነው፡፡ ራእ.፭፥፬-፲ ፣ ገላ.፫፥፲፫

www.zeorthodox.org

## ዐሥራ አንደኛ  ክፍል

**እንዲያው፡-** በነጻ የሚገኝ ወይም የተሰጠን ነገር የሚገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው፡፡ ኤር.፳፬÷፲፫፣ ፪ኛ ተሰሎ.፫÷፰፣ ፩ኛ ቆሮ.፪÷፲፪፣ ራእ.፳፩÷፮፣፳፪÷፲፯ በክርስቶስ የተከፈለንን ዋጋ እና ያገኘነው መዳን ፤ እኛ ዋጋ ሳንከፍልበት እንዲያው በነጻ የተሰጠን መሆኑን ያመለክታል፡፡

**ጸጋ፡-** ስጦታ ማለት ነው፡፡ በዚህ መልእክት ከሃያ ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡ እንደአገባቡም እግዚአብሔር እንዲያው ስለወደደን የተሠጠን መዳን በእኛ ጽድቅ ሳይሆን በእርሱ ስጦታ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም የተሰጠን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ተሰጥዖዎችም (ማስተማር፣ ትንቢት መናገር፣ መፈወስ፣ ማስተዳደር… ) ጸጋ ይባላሉ፡፡

**እንዲያው** ያለዋጋ ማግኘትን ፤ **ጸጋ** ያለዋጋ የተገኘውን ስጦታ ያመለክታል፡፡

**ጽድቅ፡-** ቀጥተኛ ትርጉሙ እውነት ማለት ነው፡፡ በዚህ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ከሠላሳ ጊዜ በላይ የተነገረ ቃል ነው፡፡ በእምነት እና በቅድስና መኖር ጽድቅ ነው፡፡ ክፉውን መተው በጎውን መሥራት ጽድቅ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር መታዘዝም ጽድቅ ነው፡፡

ኢዮብ፡- ‹‹***በእውነት እንዲህ እንደ ሆነ አወቅሁ ሰውስ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን እንዴት ይችላል?***›› ኢዮብ.፱÷፪ እንዳለ፤ ኢሳይያስም ‹‹***በጽድቅ የሚጠራ በእውነትም የሚፈርድ የለም፡፡***›› ኢሳ.፶፱÷፬ ብሏል፡፡ ጳውሎስም ‹‹***አንዳች ጻድቅ የለም***›› በማለት የሰው ልጅ ያጣውን ጽድቅ ገልጠዋል፡፡ በመሆኑም እግዚአብሔር ለአዳም ልጆች ጽድቅን ሊያጎናጽፍ ፈቀደ፡፡ ኢሳ.፵፯÷፲፪-፲፫፣፶፩÷፭ በዚህ መሠረትም የሰው ልጆች ያጣነውን ጽድቅ በክርስቶስ ቤዛነት አገኘን፡፡***"አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን፡፡"*** ሮሜ.፭÷፱ ጽድቅን የሰጠ እግዚአብሔር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ጽድቅ በክርስቶስ ያመኑ ይቀበሉታል፣ይፈጽሙታልም፡፡ ኤር.፱÷፳፫-፳፬

***ጥያቄዎች፡-***

1. ጽድቅ እንዴት ተገኘ ?
2. አብርሃም ጽድቅ በሮሜ መልእክት መሠረት አብራሩ፡፡
3. የመጀመሪያው አዳምና ሁለተኛው አዳም በምን ይለያያሉ፡፡
4. ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አንድ የሚያደርገን ምንድነው ?
5. ቅድስና ማግኘት ምንድነው ?
6. *"ኃጢአት በበዛበት ፤… ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ፡፡"* ማለት ምን ማለት ነው። እንዴት ይገኛል ?
7. ሕግ ምንድነው ? ለምን ተሰጠ ?

www.zeorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች(አምስት) - ነፃነትና ቅድስና

## ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ከእርግማንና ከኃጢአት ቀንበር ነጻ ስለመውጣት፤ በቅድስና ስለ መኖር ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *" እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።"* ሮሜ.፯፥፳፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሮሜ.7፡1-8፡39; ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው›› 1988 ዓ.ም፤ The epistle of Saint Paul to the Romans:Father Tadros Yakob Malaty:2007-2008

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ለሰው ያልተቻለው ጽድቅ በክርስቶስ ቤዛነት እንደተገኘ እኛም ስናምን ጽድቅን እንደምናገኝ ፣ ለዚህ መሠረት ስለሆኑት እምነት እና ጥምቀትም ተምረናል። የአባታችንን የአብርሃምን እምነት፣ መታዘዝና ስለ ሁለተኛው አዳምም አይተናል።

በዛሬው ትምህርታችንም ዓለምን ስለገዛው እርግማን፣ ስለ ሕግና ከሕግ እርግማን ነጻ ስለመሆን እንማራለን። የትምህርታችን ዋና ክፍል የሆነውን ቅድስናን ገንዘብ ማድረግንም በሮሜ መልእክት መሠረት እናያለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. ቅድስቲቱ ሕግና ከእርግማን ነጻ መሆን። (ምዕ.፯፥፩-፳፥፲፯)

የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት በሕግ እየተመኩ ሌላውን የሚንቁትን አይሁድ ፤ በሕግ እርግማን መያዛቸውን ትኩረት ሰጥቶ ያስተምራል። በምዕራፉ መጀመሪያ *"ወንድሞች ሆይ፥ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና።"* ያለውም ለዚህ ነው። ፯፥፩ *"ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት።"* ቁ.፲፪ ሰዎች ግን ከኃጢአት በታች ሆኑ። *"ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና ፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ።"* ቁ.፲፬ በመሆኑም ሕግን በመተላለፍ የሚመጣው እርግማን ወደቀባቸው *"እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን ? አይደለም፥ ነገር ግን*

www.zeorthodox.org

*ኃጢአት ሆነ፤ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር።"* ፯፥፲፫ በመሆኑም ይህ ምዕራፍ ሦስት ዋና ነገሮችን ያነሣል።

1. ከሕግ እርግማን ነጻ መሆን (፩-፯) - ባል ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት እያለ የታሰረች ናት ፤ ባልዋ ቢሞት ነጻ ትሆናለች ፤ እኛም በክርስቶስ ከሕግ እርግማን ነጻ ወጣን።
2. በሕግ የታወቀው ኃጢአትና የሕግ ኃይል (፯-፲፫) - ሐዋርያው በዚህ ክፍል ኃጢአት እንዴት በሕግ እንደተገለጠች ያብራራል፤*"በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር። ሕጉ። አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና። ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ ፤ ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና።"* ፰-፱
3. የእግዚአብሔር ሕግና የኃጢአት ሕግ (፯፥፲፬-፳፬) ቅዱስ ጳውሎስ ሕግን የሚያውቀውን አይሁዳዊ ማንነት በራሱ መስሎ አስተምሯል። ይህ ሰው ሕግን ያውቃል፤ ሆኖም ኃጢአት በምኞት ሞት የሠራበት ሰው ነው። የማይወደውን ኃጢአት ያደርጋል ፣ የሚወደውን ሕግ ግን አይፈጽምም። እናም ይህ ሰው ራሱን ለኃጢአት ከተሸጠው ማንነት ነጻ የሚያወጣው ይፈልጋል።

➢ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***ምርጥ ዕቃ*** ያለው ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ ሰው ሁለት መልሶችን ሰጥቷል።

***ሀ.በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን ድልና ቅድስና ማመን።*** ይህ በቀጣዩ ምዕራፍ በስፋት ይብራራል። በዚህ ምዕራፍ መደምደሚያም ***"እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።"*** ሮሜ.፯፥፳፭ ብሏል።

በቆሮንቶስ መልእክቱም ይህንኑ አረጋግጦልናል።***"የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው። የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።"*** ፩ኛ. ቆሮ.፲፭፥፶፮-፶፯። ኃጢአትና እርግማን፤ ዲያብሎስና ኃይሉ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድል ተደርገዋል። እኛም በእርሱ ስናምን በኃጢአት ከተጎሳቆለ ሕይወት በቅድስና እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ክብር ይመልሰናል። በማንኛውም የቅድስና ድልም በሁሉ ማመስገን ይገባል። እንዴት ለሚለውም ቀጣዩ ምዕራፍ ምላሽ ይሰጠናል።

www.zeorthodox.org

***ለ.በፈተና መልካም ፍቃድን ለእግዚአብሔር ሕግ ማስገዛት።*** ጠላት በሥጋ ምኞት ፣ በዐይን አምሮት ያለማቋረጥ ይዋጋናል። በዚህ ውጊያ እግዚአብሔር የተወን ለክፉ ምኞት ተላልፈን የተሰጠን መስሎን ተስፋ ልንቆርጥ እንችላለን። የጠላት ዓላማውም ተስፋ ቆርጠን መንፈሳዊውን ጉዞ እንድንተው ለማድረግ ነው። በዚህ ወቅት የምንችለውን በማድረግ፤ እግዚአብሔር ለታላቁ ክብር እንደሚያበቃን ማመንና መጽናት ይጠበቅብናል። ሐዋርያው ለዚህ ፈተና የሚሰጠውን መልስ

*“በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ።”* ፯፥፳፭ በማለት ገልጦታል። ነብዩ ሚክያስም *“ጠላቴሆይ፥ ብወድቅ እነሣለሁና፥ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ።”* ሚክ.፯፥፰ እንዳለ በእግዚአብሔር ማዳን ተስፋ በማድረግ መኖር የማታ ማታ መንፈሳዊ ድል ያመጣል። ቅዱሳንም በዚህ ተስፋ ጸንተው በመጋደላቸው ኃጢአትን ድል ነስተዋል። ለምሳሌም ድል ካደረገችው እናት ታሪክ እንማር፤ ይህች ቅድስት ሴት ማርያም ግብጻዊት ትባላለች። ማርያም ግብጻዊት ለዐሥራ ሰባት ዓመታት በዝሙት ኖረች። በኋላም በንስሐ ተመለሰች። ለአርባ ሰባት ዓመታት በበረሓ በተጋድሎ አሳለፈች። ለቅድስናም በቃች። ለቅድስና ከመድረስዋ በፊት የነበረባትን ፈተና ዞሲማስ ለተባለው አባት እንዲህ ገልጣለት ነበር።*“...ያለፈ ሕይወቴንና ያሳለፍኩትን ደስታ በማሰብ እፈተን ነበር።... ያለፈ ሕይወቴ ትዝታ ደጋግሞ ባሰቃየኝ ጊዜ ደረቴን እየደቃሁ ወደ በረሐው ስገባ የገባሁትን ቃል ለራሴ አስታውሰው ነበር። ጌታዬም እንዲረዳኝ እለምነው ነበር።...እያስጨነቁኝ የነበሩትን ነገሮች እንዴት ልገልጽልህ እችላለሁ? ይፈትነኝ ስለ ነበረው የዝሙት አሳብስ እንዴት አድርጌ ላስረዳህ እችላለሁ? እንዲህ ፈተናው አብዝቶ ያስጨንቀኝ ነበር። በሠራሁት ኃጢአት ምስክር ሆኖ የሚያስፈርድብኝና የሚያስቀጣኝ ሆኖም ይታየኝ ነበር። እኔም መሬት ላይ ወድቄ እያለቀስኩ በእንባ እታጠብ ነበር።.... የሚያረጋጋና ደስ የሚል ብርሃን መጥቶ እስኪያበረታታኝና የሚያስጨንቁኝን አሳቦች ሁሉ እስኪያባርራቸው ከመሬት አልነሣም ነበር። አንዳንዳዴም አንድ ቀንና ሌሊት ሙሉ መሬት ላይ እንደ ወደቅሁ እቆያለሁ።... ብዙ ካለቀስኩና ደረቴን ከደቃሁ በኋላ ከሁሉም አቅጣጫ በእኔ ላይ የሚያበራ የሚመስል ብርሃን እመለከት ነበር። ከአስጨናቂው ማዕበል በኋላ ዘላቂ የሆነ ሰላም ይሰፍን ነበር።”* ገድለ ቅድስት ማርያም ግብጻዊት ገጽ 77-78 (በሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ አንድነት ገዳም፤ሰኔ 1999 ዓ.ም፤ የታተመ)

የሰውን ልጅ ውድቀት በምዕ.፯ የተረከልን ቅዱስ ጳውሎስ ፤ በምዕራፍ ፰. በክርስቶስ ያገኘውን ክብርና ድል ያበስራል። ለዚህ ነው አንዳንድ ሊቃውንት የሮሜን መልእክት ታላቅ ቤተ መቅደስ ብለው ምዕ. ፰ ቅድስተ ቅዱሳን ወይም መሠዊያና የድል ዓምድ የሚሉት።

www.zeorthodox.org

## ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን ፤ በመንፈስ ሕግ መመራት።(፰፥፩-፲፯)

ሰው የሥጋ ክፉ ምኞት ሠለጠነበት (፯፥፲፬፣፩፥፲፰-፴፪) የኃጢአት ባርያ ሆኖ ተዋረደ። ይህም በሥጋና በነፍስ ፍርድ (ኵነኔን) አመጣበት። ሆኖም ክርስቶስ ኵነኔውን ሻረ። (ቁ.፩-፬) ከባርነት አውጥቶም አርነት እና ሕይወትን ሰጠን።(ቁ.፪)

በእርሱ የሚያምኑም *በሥጋ ፈቃድ* ሳይሆን *በመንፈስ ፍቃድ* እንዲኖሩ ኃይልን ሰጣቸው። (ቁ.፭-፰)

በዚህ ሰው ወደ ሙሉ መንፈሳዊ ሰውነቱ ተመለሰ። ሰውም መንፈሳዊ ዝንባሌንም አገኘ። ክርስቶስ የሰውን ልጅ ባርያ ያደረገውን የኃጢአትን ሕግ ደምስሶ፤ ነጻ የሚያወጣውን የመንፈስ ሕግ መሠረተ። ቅዱስ መንፈሱን አሳደረብን፣ ከእርሱ ጋር እንድንሆን ፈቀደልን፤ ከእርሱ ጋር ስንሆንም በጽድቅ ሕያዋን ሆነን ፤ ለኃጢአት እንሞታለን። (ቁ. ፱-፲፩)

ክርስቲያኖች የክርስቶስ እዳ እንዳለብን እንረዳለን። በመሆኑም በመንፈስ የሥጋን ሥራ እንገድላለን።(ቁ.፲፪-፲፬) ይህንንም በጸሎት እንድናገኝ አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ሰጥቶናል። (ቁ.፲፭-፲፮) ልጆች በመሆንም የእግዚአብሔርን መንግሥት ወራሽነት ሥልጣን አገኘን።(ቁ.፲፯)

## 2. እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ቅድስናና የእኛ መልስ

***የእግዚአብሔር ልጆች ክብር*።፲፰-፳፭**

ይህ ክብር የፍጥረታት ሁሉ ናፍቆት ነው። እኛም በተስፋ እንጠብቀዋለን። ከምናገኘው ክብር አንጻር የዚህ ዓለም መከራ ምንም እንዳልሆነ እንቆጥራለን። በመሆኑም መከራን እንታገሳለን። የማናየውንም በእምነት ተስፋ አድርገን እንጠባበቃለን።

***መንፈስ ድካማችንን ያግዛል*። ፳፮-፳፯**

ለተዘጋጀው የእግዚአብሔር ልጆች ክብር እንዳንበቃ የሚያደርገን ድካም አለ። በዚህ የተነሣ ምንና እንዴት መጸለይ እንዳለብን አናውቅም። መንፈስ ቅዱስ ጸሎታችንን በማረም በድካማችንም በማበርታት ያግዘናል።

***የተጠራነው ለቅድስና ነው*። ፳፰-፴**

ጠሪው እግዚአብሔር ነው። ቁ.፳፰ ጥሪውም ልጁን ለመምሰል ነው። ቁ.፳፱ እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም እርሱን መከተል ይገባል። ቁ.፴

***የእግዚአብሔር ምርጦች ኩነኔ የለባቸውም*።(፰፥፴፩-፴፬)**

ሆኖም በቅድስና መኖራችንን የማይወደው ጠላት ሊያሰናክለንና ሊከሰን ይመጣል። ዘካ.፫፥፩-፲ ኢዮ.፩፥፮-፲፪ ሆኖም የሰይጣን ክስ አይሠራም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው። ቁ.፴፩ የሚጸድቅ እርሱ ነውና ማንም ሊቃወመን አይችልም። ቁ.፴፪-፴፫ እርሱ ያጸደቃቸውን ማንም አይከሳቸውም። ፈራጁ (የሚኮንነውም) ክርስቶስ ነው። ቁ.፴፬ እርሱ ካጸደቀ የከሳሹ ክስ ኩነኔ አያመጣብንም። እርሱ ደግሞ ሊያጸድቀንና ቅድስናን ሊሰጠን ፈቃዱ ነው።

***ለክርስቶስ ያለን ፍጹም ፍቅር*።፴፭-፴፱**

ለወደደንና ምሕረቱን ላበዛልን ለአምላካችን የሚኖረን ፍቅር በፍጹም ልብ በመውደድ እና እስከ

www.zeorthodox.org

ሞት በመታመንም የሚገለጥ ነው፡፡ በመሆኑም ከክርስቶስ ፍቅር መከራ አይለየንም፡፡ቁ.፴፭ ፍጥረታትም ሆኑ፣ ከፍታና ዝቅታ አይለዩንም፡፡ ቁ.፴፰-፴፱ እርሱም ከአሸናፊዎች የበለጠ ድል ይሰጠናል፡፡ ቁ.፴፮-፴፯ አጋንንት በመከራ፣ ገዳዮችን በማሰማራት ወይም የኃጠአትንና የሥጋ ምኞትን በማበርታት ድል ሊነሱን ይሞክራሉ፡፡ የሥጋና የነፍስ መከራም ያጸኑብናል፡፡ ***"በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፡፡"*** ቁ.፴፯ በሞቱ ሞትን ድል የነሳው ጌታ የጽድቅን ድል ይሰጠናል፡፡ የሕይወትን አክሊልም ያቀዳጀናል፡፡ ከአሸናፊዎች ያስበልጠናል፡፡ ለዚህ ነው ቅዱሳን የዚህ ዓለም መከራና ክብሩን ማጣት ምንም ያልመሰላቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ይህንኑ የቅዱሳን መንፈሳዊ እውቀት እና እስከ ሞት ራሳቸውን የሰጡበትን ምስጢር እንዲህ ገልጾታል፡፡ ***"ክፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ፡፡"*** ሮሜ.፰፥፴፱ ይህ ፍቅርና ስጦታ ለእኛም ነው፡፡ ፍቅሩን በምን ያህል መታመን መልሰንለታል? ሁላችንም ለእየራሳችን የምንመልሰው ይሆናል፡፡

## ማጠቃለያ

- ሕግን የሚያውቁት አይሁድ በሕግ የታዘዘውን ለመፈጸም በመፈለግና ለምኞት በመታዘዝ መሐል ነበሩ፡፡ ይህም ሕግን በመተላለፍ የሚመጣውን እርግማን አወረደባቸው፡፡
- ለዚህ ለኃጢአት ሕግ ከመገዛት የሚያድነው፤ በክርስቶስ ቤዛነት ማመን ነው፡፡ በጌታችን ያመኑ በመንፈስ ሕግ መመራት ፣ በቅድስና መኖርና ከኩነኔ መዳን ይችላሉ፡፡
- የሕግ ሁሉ ፍጻሜ የሆነው ፍቅርን በመያዝ ይህንን የእግዚአብሔርን ፍቅር ያስተዋሉ ቅዱሳን ራሳቸውን በመስጠት በመከራ ሁሉ ታገሱ፡፡

## ተግባር

- ክርስትና ድካማችንን በትክክል የምንረዳበት ሃይማኖት ነው፡፡ እናንተም ድካማችሁን ተረድታችሁ ጉድለታችሁን ሊሞላላችሁ በሚችለው ጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ፡፡
- ፍጹም እምነት ካለን በመንፈስ ሕግ በመመራታችን ይታወቃልና በመንፈስ ለመመራት የሥጋን ክፉ መሻት ለማሸነፍ ቁረጡ፡፡
- መልካም ለዋለላችሁ አምላክ የምትችሉትን ሁሉ ለመስጠት አትቆጠቡ፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች፡-***

1. ቅድስቲቱ ሕግ ለምን እርግማን አመጣች ?
2. ከእርግማን እንዴት ይዳናል? በተማራችሁት መሠረት አብራሩ።
3. በመንፈስ መመራትና መኖር ማለት ምንድ ነው?
4. ያለብንን ድካም የሚያግዘን ማነው? እንዴት ?
5. ከጠላታችን ክስ ነጻ የሚያደርገን ማነው ?
6. ***"በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።"*** ማለት ምን ማለት ነው? አብራሩ።

www.zeorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች(ስድስት)
# የእግዚአብሔር ጥሪ (የእስራኤልና የአሕዛብ አጠራር)
## ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች እግዚአብሔር ዓለምን የጠራበትን መንገድ ያውቃሉ፤ ለጥሪው ሊኖረን ስለሚገባው መልስ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው፤"* ያለው፡፡፲፥፲፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሮሜ. ፱-፲፩ ፣ ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጎሜው 1988 ዓ.ም ፣ The epistle of Saint Paul to the Romans:Father Tadros Yakob Malaty:2007-2008

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ስለ ቅድስቲቱ ሕግ፤ ሕግን ባለመጠበቅ ስለሚደርሰው እርግማን፣ ከእርግማን ስለ ዳንበት የክርስቶስ ቤዛነትና የመንፈስ ኑሮ፤ በዚህ ስለሚገኘውም ቅድስና፤ ለወደደን አምላክ ስለሚኖርን ፍጹም ፍቅር ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ቀድመው በአባቶች ስለተጠሩት እስራኤልና በኋላ በወንጌል ስለተጠሩት አሕዛብ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### ሀ. የእስራኤል ውድቀት

የእስራኤል ዘሥጋ ዋናና መሠረታዊ ችግር ራሳቸውን በእግዚአብሔር የተመረጡ ብቸኛ ሕዝቦች አድርገው መቁጠራቸው ነበር፡፡ ይህ ሐሳብ የአብርሃም ዘር ነን በሚል ትምክህት እንዲሁም ሕግ የተሰጠንና የጠበቅን ብቸኛ ሕዝቦች ነን በሚል ትምክህት ይገለጥ ነበር፡፡ ሐዋርያው ይህን አስተሳሰብ ተጋፍጦ አስተማረ፡፡ በአስደናቂ ጥበብም እውነታውን ከስሕተት አስተሳሰብ ለይቶ አስተማረ፡፡ እስራኤል ቀድመው መመረጣቸውን አላስተባበለም፤ እንዲያውም እውነቱን በሚገባ ገለጠው፤ ሆኖም ሁሉን ሊምር የወደደው ሕያው እግዚአብሔር አሕዛብንም በምሕረቱ ብዛት ጠርቷቸዋል፡፡

www.zeorthodox.org

1. **ሐዋርያው ስለ እስራኤል ያለው በጎ ምኞትና ክብር**፡፡፱÷፩-፭ ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ምሥክርነት ፣ በክርስቶስ ሆኖ ይህንን ሐሳብ ይነግረናል፡፡ በብዙ ኃዘን በማያቋርጥም ጭንቀት እስራኤል እንዲድኑ ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር፡፡፱÷፩-፫ ለእስራኤል የነበረው ክብር የሥጋ ወገኖቹ ስለነበሩ ብቻ አይደለም፡፡ ልጅነት፣ ክብር፣ የመቅደስ ሥርዓት ለእነርሱ ነበር፡፡ አባቶችም ከእነርሱ ነበሩ፡፡ ለዘላለምም የተባረከው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስም ከእስራኤል አባቶች ተወለደ፡፡ ቁ.፬-፭ ሆኖም እስራኤል ከተስፋው ተለይተው በመውደቃቸው ጳውሎስ አዝኖ ወደ አምላኩ ለመነ፡፡
2. **እግዚአብሔር አባቶችን መረጠ**፡፡ ፱÷፮-፲፫ አብርሃምንና አባቶችን የመረጠው እግዚአብሔር ነበር፡፡ አይሁድ ይህንን አልተረዱም፡፡ የይስሐቅ መወለድ፤ ያዕቆብ ተወዶ ኤሳው መጠላቱ፤ ምርጫው ከእግዚአብሔር እንደ ነበር ያስረዳናል፡፡
3. **እግዚአብሔር አሕዛብንም መርጧል**፡፡፱÷፲፬-፳፱ ቅዱስ ጳውሎስ እንደ እስራኤል አሕዛብም መጠራታቸውን ለማስረዳት ብዙ ምሳሌዎችንና አስረጅዎችን ጠቅሶአል፡፡ እግዚአብሔር ዓመጸኛ አይደለም፡፡ የሚምረውንም ይምራል፡፡ ማንምም ይህንን አደረግክ ብሎ እግዚአብሔርን ሊወቅስ አይችልም፡፡ አይሁድ ራሳቸውን የምሕረት ብቸኛ እቃ አድርገው መቁጠራቸው ስሕተት ስለሆነ ***"የምሕረቱ ዕቃዎችም ከአይሁድ ብቻ አይደሉም፥ ነገር ግን ከአሕዛብ ደግሞ የጠራን እኛ ነን"*** ይላል፡፡ ፱÷፳፬ በተጨማሪም የአሕዛብን መጠራት ትንቢት ከተናገሩት ነቢያት ሆሴዕን (ሆሴ.፪÷፳፪-፳፫፣፩÷፲) እና ኢሳይያስን (ኢሳ.፲÷፳፪-፳፫፣ ፩÷፱) ጠቅሷል፡፡ ሮሜ.፱÷፳፭-፳፱ ***"ሕዝቤም ያልሆነውን፦ አንተ ሕዝቤ ነህ እለዋለሁ እርሱም፦አንተ አምላኬ ነህ ይለኛል፡፡"*** ሆሴ.፪÷፳፫ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን የአሕዛብ መጠራት ‹‹***እንግዲህ ምን እንላለን ? ጽድቅን ያልተከተሉት አሕዛብ ጽድቅን አገኙ፤***›› ቁ.፴ ብሎ ያደንቃል፡፡ ይህ ጽድቅ በእምነት የተገኘ ጽድቅ ነው፡፡
4. **የእስራኤል መሰናከል**፡፡ ፱÷፴፩-፴፫ ጽድቅን ያልተከተሉት አሕዛብ በክርስቶስ በማመናቸው ጽድቅን አገኙ፡፡ ***"እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም፡፡"*** ቁ.፴፩ ለምን? ለሚለው ሐዋርያው በቁ.፴፪ እና ፴፫ ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶችን ገልጾአል፡፡ አንደኛው በሥራ እየተመኩ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ሲሆን ፤ ሁለተኛው በክርስቶስ ስለተሰናከሉ ነው፡፡ ***"ይህስ ስለ ምንድር ነው? በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው፤ እነሆ፥ በጽዮን የእንቅፋት ድንጋይና የማሰናከያ ዓለት አኖራለሁ፤ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ እንደ ተጻፈ በእንቅፋት ድንጋይ ተሰናከሉ፡፡"*** ፱÷፴፪-፴፫

በተመረጠው የማዕዘን ድንጋይ በኢየሱስ ክርስቶስ አይሁድ ተሰናከሉ፡፡ እርሱ ግን ላመኑበት

የተመረጠና ድንቅ የማዕዘን ራስ ነው፡፡ (መዝ.፻፲፯(፻፲፰)÷፳፪-፳፫፣ ፩ኛ.ጴጥ.፪÷፯-፰) ቀጣዩ ምዕራፍ (፲) አይሁድ የተጣሉበትን ምክንያት በስፋት ያብራራል፡፡ እነዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

5. ***ዕውቀት የሌለው ቅንዓት፡፡*** ፲÷፩-፫ የእስራኤል መዳን ፍላጎቱና ልመናው የሆነው ቅዱስ ጳውሎስ የውደቀታቸውን ምክንያት በቀጣይነት አብራራ፡፡ በዚህ ክፍልም፡- የእስራኤልን ቅናት መስክሮ ችግራቸው ዕውቀት የጎደለው ቅናት እንደነበር ያስተምራል፡፡ ***"በእውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና፡፡"*** ፲÷፪ ያላወቁት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ነው፡፡ ***የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም*** ፤ማንም በራሱ ጽድቅ የለውም፤ በራሱ ጻደቅ የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ አይሁድ ባያምኑበትም ***"የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው፡፡"*** ሮሜ.፩÷፬
6. ***የእምነት መሠረታውያንን ጥለዋል፡፡*** ፲÷፮-፲፫ የክርስቶስን ጌትነት ማመንና መመስከር (፮-፲፫ እና ፲፮-፲፫)፣ሌላውንም መውደድ (፲፪-፲፫) የሚያድን መሰረታዊ እምነት ነው፡፡ ***"ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና፡፡ ... በእርሱ የሚያምንም አያፍርም፡፡"*** ፲÷፱-፲፩ አይሁድ ግን አፈሩበት ጠሉትም፡፡ ከዚያም አልፈው የሰውን ልጆች ይንቁና ይጠሉ ነበር፡፡ ለዚህ ነው ***"በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው፤"*** ያለው፡፡ ፲÷፲፪
7. ***ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙም፡፡*** ፲÷፲፬-፳፩ ለማመንና ለመመስከር መማር ይቀድማል፡፡ እናም ሐዋርያት በመጀመሪያ የተላኩት ለእነርሱ ነበር፡፡ ሆኖም አልሰሙም ለምሥራቹም ቃል አልታዘዙም፡፡ ፲÷፲፬ በመሆኑም እግዚአብሔር ሕዝብ ያልነበረውን ጠርቶ እስራኤልን አስቀና፡፡ ፲÷፲፱-፳ ምክንያቱም እስራኤል እግዚአብሔር የማዳን እጁን ቢዘረጋለትም የማይሰማ ሕዝብ ነበር፡፡ ***"ቀኑን ሁሉ ወደማይታዘዝና ወደሚቃወም ሕዝብ እጆቼን ዘረጋሁ"*** ቁ.፳፩

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እኛ ብቻ የተመረጥን ነን የሚለውን የእስራኤልን ትምክህት ቅዱስ ጳውሎስ ተቃውሟል፡፡ ሆኖም በጥበብና በአድናቆት በመጀመር ችግራቸውን እንዲረዱ አድርጓል፡፡

ከክርስትናው ኑሮና እምነት ውጪ የሆኑት ወገኖቹ ጉዳይ አሳስቦት በእግዚአብሔር ፊት ቆመ፡፡ እኛም የወገኖቻችን ከእምነት፣ ከመልካም ምግባርና ከበረከት መራቅ ሊያሳዝነን ይገባል፡፡ ስለ ቤተሰብ

እምነት እና መልካም ማግኘትስ ታሳስባላችሁ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ አይሁድ ቢያሳድዱትም ስለ እነርሱ ይጸልይ ነበር፡፡ እኛም ለወገኖቻችን በእውነት የሚሰማን ልንሆን ይገባል፡፡

እግዚአብሔር እስራኤልንና አሕዛብን ጠርቷል፡፡ እነኛ በአባቶች እነኚህም በእምነት፡፡ ፍጻሜውም በክስቶስ ማመን ነበር፡፡ እስራኤል ግን ለወንጌል ምሥራች አልታዘዙም፡፡ እኛም መንፈሳዊ ቅናታችን በዕውቀት እና በእምነት ይሁን፡፡ ለእግዚአብሔር ቃል የምትታዘዙ ሁኑ፡፡

## ተግባር

- በትምህርቱ መሠረት ተወያዩ፡፡
- መንፈሳዊ ቅናታችሁን አዳብሩ ሆኖም ከእውቀት ጋር ይሁን፡፡ ለዚህ እንዲረዳችሁም ጠያቂና አንባቢ ሁኑ፡፡
- የእግዚአብሔርን ቃል መስማት አታስታጎግሉ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. የእስራኤል ጥሪ እንዴት ነበር ?
2. እስራኤላውያን ከሕይወት ትምህርት እንዴት ሳቱ ? ለውድቀት ያደረሳቸው ችግር ምን ነበር? አብራሩ፡፡
3. አሕዛብ በምን ተጠሩ ?
4. በሮሜ ምዕ.፲ የተጠቀሰው፤ የእስራኤል ዘሥጋ መንፈሳዊ ውድቀት ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? አብራሩ፡፡
5. የእስራኤል ዘሥጋ ሃይማኖታዊ ፍጻሜ ምን ይመስላችኋል ?

www.zeorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች(ሰባት) - የእስራኤል መዳን ትንቢት

# ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች እግዚአብሔር የሁሉንም መዳን እንደሚፈልግ መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትምና፡፡"*** ሮሜ.፲፩፥፳፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሮሜ.11፡1-36 ፤ ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው›› 1988 ዓ.ም፤ The Epistle of Saint Paul to the Romans: Father Tadros Yakob Malaty:2007-2008

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን የእስራኤልን መጣልና የአሕዛብን መጠራት ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ሁሉንም ሊምር የወደደው እግዚአብሔር ***"ቀኑን ሁሉ ወደ ማይታዘዝና ወደሚቃወም ሕዝብ "*** የተባሉትን እስራኤልን ሊያድንና እና ዓለሙን በሙሉ ሊምር እንደወደደ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

**ለ.እስራኤል ይድናሉ፡፡**

ሕያው እግዚአብሔር እስራኤልን ባለመታዘዛቸው ሊተዋቸው አልወደደም፡፡ አይሁድ (እስራኤል) በንስሐና በእምነት ወደ ክርስቶስ የሚመለሱበት ጊዜ አለ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በምዕራፍ ፲፩ በዋናነት የሚያነሳውም ይህንኑ ነው፡፡ በተጨማሪም አሕዛብ በመመካት ወንድሞቻቸው በአይሁድ ላይ እንዳይፈርዱና እንዳይወድቁ ይመክራል፡፡

1. **እግዚአብሔር ሕዝቡን ፈጽሞ አልጣለም፡፡** (፲፩፥፩-፲) አይሁድ ባላመታዘዛቸው ቢወድቁም ***"እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ አልጣላቸውም፡፡"*** ቁ.፲፩፥፪ ለዚህም ራሱን ***"እኔ ደግሞ እስራኤላዊና ከአብርሃም ዘር ከብንያምም ወገን ነኝና"*** ቁ.፲፩፥፩ በማለት፤ በኤልያስ ዘመን ***"ለበኣል ያልሰገዱትን ሰባት ሺሕ ሰዎች ለእኔ አስቀርቼአለሁ፡፡"*** ፲፩፥፬ እንደተባሉትም በክርስትና ዘመን ከቀሩ ክርስቲያን አይሁድ ጋር አሉ ፡፡

2. **ንስሐ ሲገቡ ይቀበላቸዋል፡፡**(፲፩-፲፯) ሌሎቹን አይሁድ ሊያስቀናለአሕዛብ መዳን ሆነ፡፡ ፲፩፥፲፩ ይልቁንም መሙላታቸው የበለጠ ስለሆነ አይሁድ ንስሐ ሲገቡ እግዚአብሔር ይቀበላቸዋል፡፡

www.zeorthodox.org

፲፩፥፲፪ በመሆኑም ሐዋርያው ወገኖቹን ለማዳን ጥሯል። ፲፩፥፲፫ እስራኤል በንስሐ ይመለሳሉ ***"የእነርሱ መጣል ለዓለም መታረቅ ከሆነ ከሙታን ከሚመጣ ሕይወት በቀር መመለሳቸው ምን ይሆን?"*** ፲፩፥፲፬ በሥራቸው በአባቶች ቅድስናን የማግኘትና የንስሐ ዕድል አላቸው። ፲፩፥፲፭

3. **አሕዛብ እንዳይመኩ የተሰጠ ምክር**።(፲፯-፳፬) ቅዱሳን አባቶችን አብርሐምና ሌሎችን ነቢያት በወይራ ዘይት መስሏቸዋል። የቀሩትን አይሁድም በቅርንጫፍ። አሕዛብንም በበረሓ የወይራ ዛፍ መሰለ። ሆኖም አይሁድ ከግንዳቸው ተቆርጠው አሕዛብ ገቡ። ማለትም በእነ አብርሃም እምነት አምነው የተሰጠውን ተስፋ አገኙ። አሕዛብ በዚህ ተመክተው እንዳይወድቁ ***"እነርሱ ከአለማመን የተነሣ ተሰበሩ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል። ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ።"*** ቁ.፳ በማለት ይመክራል።

4. **የአይሁድ ንስሐ ይጠበቃል**። (፳፭-፳፰) ነቢያትን በማሳደድ፣ ጌታችንንም ለሞት አሳልፈው በመስጠት አይሁድን የሚከሱ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች ነበሩ። እነዚህንም ***"ወንድሞች ሆይ፥ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ"*** ሲል ይመክራል። ቀጥሎም ***"ይህን ምስጢር ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፤ የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው፤ እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል፤"*** ሮሜ.፲፩፥፳፭

ምስጢር በሁሉም የማይታወቅ ነው። ሐዋርያውም ለአማንያን ይህንን ምስጢር አብራርቷል። ከዚህ ቦታ ሦስት ነጥቦች በምስጢር አካልነት ተገልጠዋል እነርሱም፦

*ሀ. እግዚአብሔር **"የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ"** ይጠብቃል።*

*ለ. እስራኤል በሙሉ ከጸጋው ተለይተው አልወደቁም። ሐዋርያትን ጨምሮ የተረፉ አሉ።" **ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው፤"** የሚለው ቃል ይህን ያስረዳል።*

*ሐ. ዋናው ምስጢርም " **እስራኤል ሁሉ ይድናል፤"** የሚለው ቃል ትንቢት ነው።*

እግዚአብሔር ቀድሞ በነቢያቱ ተናገሮ ነበር። ሮሜ.፲፩፥፳፮-፳፯፣ ኢሳ. ፶፭፥፲፯፣፶፱፥፳፣ ፳፯፥፱፣ ኤርም. ፴፩፥፴፬፤ የእስራኤል መጠራት በአባቶች በኩል ተወዳጅ ስለሆኑ ነው። ቁ.፳፰

5. **የላቀውና ታላቁ የእግዚአብሔር ዕቅድ ሁሉንም (የሰውን ልጅ ሁሉ) ይምር ዘንድ ነው**። ***"እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትምና።"*** ፲፩፥፳፱ ቀድሞ የወደዳቸውን እስራኤልን ለማዳን ጠራቸው። አሕዛብ ባልታዘዙበት ዘመን እስራኤል ታዘዙ፤ እስራኤል በወንጌል ባልታዘዙበት ዘመንም አሕዛብ ታዘዙ። ቁ.፴ አሕዛብ ያገኙትን ምሕረት እስራኤልም ያገኛሉ። የዚህ ዓላማውም ***"እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ"*** ነው። ሮሜ.፲፩፥፴፩-፴፪

6. **ምሥጋና**። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ድንቅ የእግዚአብሔር ምስጢር ተረድቶ ፣ ካስረዳ በኋላ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እንዲህ ሲል ያደንቃል። ***"የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ***

www.zoorthodox.org

*ዕውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም። የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው ? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።"* ፲፩፥፴፫-፴፮

## ማጠቃለያ

1. እግዚአብሔር ቀድሞ የጠራቸውን ሕዝቡን ፈጽሞ አልተዋቸውም። ሊያድናቸውም መልካም ሐሳብ አስቦላቸዋል። ከእስራኤል ዘሥጋ ከተወለዱት እነ ቅዱስ ጳውሎስ ንስሐ ሲገቡ ክብር እንዳገኙ፤ እስራኤልም ንስሐ ሲገቡ ይድናሉ። ልጆች እግዚአብሔር የሚታገሰን በንስሐ እንድንመለስ ነው። ይህንን አጋጣሚ ከተጠቀምንበት እንድናለን።
2. በእስራኤል መውደቅ አሕዛብ እንዳይመኩ ተመክረዋል። እኛም በሌላው ከመፍረድና ከመመካት ወጥተን እንደ ክርስቲያን ውድቀታቸው ሊያሳዝነን ይገባል።
3. አይሁድ ንስሐ እንደሚገቡ ነቢያት ተንብየዋል። ቅዱስ ጳውሎስም አስተምሮናል። እኛም ትጉታንና የሌሎቹ መዳን የሚያስደስተን ልንሆን ይገባል።
4. ከእስራኤል መዳንና ዳግም መጠራት ጋር ያለው፤ የዓለም የአሕዛብ ሙላትና ሁሉንም ይምር ዘንድ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ማዳን አለ። እናንተስ ምን ያህል ለዚህ የወንጌል ዓላማ ተዘጋጅታችኋል። ራሳችሁን በመመርመር ለታላቁ የመለኮት ዓላማ ተዘጋጁ።
5. ሁሉንም ማድረግ የሚችለውንም ጌታ አመስግኑት።

## ተግባር

- እግዚአብሔር ፈጽሞ እንደማይጥለን እንመን። *"አንተ ከምድር ዳርቻ የያዝሁህ ከማዕዘንዋም የጠራሁህና። አንተ ባሪያዬ ነህ፥ መርጬሃለሁ አልጥልህም ያልሁህ ሆይ፥ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ አበረታሃለሁ፥ እረዳሀማለሁ፥ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ። "* ፵፩፥፱-፲
- ለንስሓ እና እግዚአብሔር ለዓለም በሙሉ ላዘጋጀው አገልግሎት ተዘጋጁ።

www.zeorthodox.org

***ጥያቄ፡-***

1. ሕዝበ እስራኤል (አይሁድ) የሚድኑት እንዴት ነው? በትምህርቱ የተረዳችሁትን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እና ምሳሌ በማብራራት ግለጹ።

# የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች(ስምንት) - ተግባራዊ የክርስትና ትምህርቶች

## ዐሥረኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ክርስቲያናዊ ስለሆኑት መልካም ምግባራት፣ በፍቅር ስለመኖር፣ ደካሞችን ስለማገዝ፣ ራስን ለእግዚአብሔር ስለመስጠት ይገነዘባሉ። መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው›› ሮሜ.፲፪፥፩*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሮሜ. ከምዕራፍ ፲፪ እስከ ምዕራፍ ፲፮፣ ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው 1988 ዓ.ም፣ The epistle of Saint Paul to the Romans:Father Tadros Yakob Malaty:2007-2008

**መግቢያ፡-** ባለፉት ሳምንታት ተከታታይ ትምህርታችን ሰዎች ሁሉ ስለሚድኑበት፣ ስለ እምነት ተምረናል። የእምነትንና የፍቅርን ሕይወት በዓለም አቀፍ ደረጃ አስተምሮናል። እስራኤል ዘሥጋና ዘነፍስን ሊያድንና አንድ ሊያደርግ የፈቀደውን መለኮታዊ ፍቅርና ሥራም አይተናል። በቀጣዮቹ ምዕራፎችም እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊኖረው ስለሚገባ የእምነት ፍሬ እና የተግባር ክርስትና እንማራለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

1. **ክርስቲያንና ዕለታዊ ኑሮው።** ምዕ.፲፪፥፩-፳፩ ከእግዚአብሔር ያገኘነውን ጸጋና ቸርነት የነገረን ቅዱስ ጳውሎስ ውሳጣዊና አፍአዊ ኑሮአችን ምን መምሰል እንዳለበት በዚህ ምዕራፍ አስተምሯል።

www.zeorthodox.org

*ራሳችንን መሥዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔር ማቅረብ።* (ሮሜ.፲፪፥፩) የክርስትና የመጀመሪያው ደረጃና በሒደትም የምናሳድገው ራሳችንን ለእግዚአብሔር በማቅረብ ነው።

የልብ እና ውጫዊ ለውጥ። (፲፪፥፪) በልቡ የተለወጠ ሰው ይህንን ዓለም አይመስልም፤ በዓለማዊው ኑሮ ተጠምዶ ለሥጋ ፍላጎት ከማድላት ይልቅ፤ መንፈሳዊውን ሕይወት በማጠንከር መልካም የሆነውን ክርስቲያናዊ ተግባር ለመፈጸም ይተጋል። ወይም ውጫዊ ለውጥም ይታይበታል።

በመጠን ማሰብና መታገል፡፡ (ሮሜ. ፲፪፥፫) ሁላችንም በመጠናችን ልናስብና ልንኖር ይገባል፡፡ ከአቅም በላይ ማሰብ ትእቢት ነው፡፡ ጌታችን ጠላትን ያሸነፈው በትኅትና ነበር፡፡ ሉቃ. ፬፥፱-፲፪

በተሰጠን ጸጋ ማገልገል ይገባል፡፡(ሮሜ. ፲፪፥፬-፰) ለአንዱ ትምህርት፣ ለሌላው ማገልገል፣ አንዳንዶቻችንም ልግስና ልዩ ልዩ ጸጋ ተሰጥቶናል፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው በተሰጠን ጸጋ መልካም የሆነውን ሁሉ ክርስቲያናዊ ተግባር ለመፈጸም መሰማራት ነው፡፡ ጌታም የሰጠንን መክሊት ይጠይቀናል፡፡ ማቴ. ፳፭፥፲፭-፴

ግብዝነት በሌለበት ፍቅር መኖር፡፡ (ሮሜ. ፲፪፥፱-፳፩) ይህ ፍቅር ለበጎ የሚተባበር፣ ክፉን የሚጸየፍ የሌላቸውን የሚረዳ፣ ትጉት፣ ሰላማዊ፣ ለጠላቶች ምሕረት የሚያደርግና ክፉን በመልካም የሚያሸንፍ ነው፡፡ ክርስቶስ በተግባር አድርጎ ያሳየን ሲሆን ፍለጋውን እንከተል ዘንድ ምሳሌ ትቶልናል፤ ኃይልም ሰጥቶናል፡፡

❖ ክርስቲያን እነዚህን በዕለታዊ ኑሮው ሁሉ ይገልጣቸዋል፡፡

2. **ክርስቲያንና ምድራዊ መንግሥት**፡- (፲፫፥፩-፯) ክርስቲያን የሥልጣን ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ያምናል፤ ባለሥልጣናት ክፉውን በመቅጣት መልካሙን ሊያመሰግኑ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ክርስቲያኖች መልካም እያደረጉ ለባለሥልጣናት ይገዛሉ፡፡ የሚገባቸውን ክብር ይሰጣሉ፡፡ የሚጠበቅባቸውን ግብርም ይከፍላሉ፡፡

3. **ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው**፡፡(ሮሜ. ፲፫፥፰-፲) ማንም የቂም ዕዳ ሊኖርበት አይገባም፡፡ዐሥርቱ ትእዛዛት ባልንጀራህን ውደድ በሚለው ተጠቅልለዋል፡፡

4. **ለሰማያዊው ሀገር መዘጋጀት**፡፡(ሮሜ. ፲፫፥፲፩-፲፬) ክርስቲያን መዳኑን እየፈጸመ የሚኖር ነው፡፡ ***"ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ወደ እኛ ቀርቦአልና"*** የጨለማን ሥራ ዝሙት፣ ክርክር፣ ዘፈን፣ ስካር ምቀኝነት፣ ስርቆት ወዘተ እየፈጸምን መኖርን ትተን በአገባብ ለመመላለስ ክርስቶስን መልበስ ይገባናል፡፡

5. **ክርስቲያንና ባልንጀሮቹ**፡፡ (ሮሜ. ፲፬፥፩-፳፫) ክርስቲያን የደከሙትን አይንቅም፤ ይሸከማል፡፡ ሮሜ.፲፬፥፩-፱ በደካማው መፍረድ አይገባም፡፡ ከቁጥር ፲-፲፫ ***የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት፡፡*** ቁ.፲፯ በመብል ወንድምን ማሳዘንና ማሰናከል የለብንም፡፡ የሚያደርጉም በእምነትም ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነውና፡፡ ቁጥር ፲፬-፳፫ ሁሉንም በእምነት ማድረግ ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

6. **በእምነት ከደከሙት ጋር ያለው ግንኙነት** (ሮሜ. ፲፭፥፩-፴፫) ኃይለኞች ደካሞችን ማገዝ እና ደስ ማሰኘት አለባቸው፡፡ ይህም የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ያመጣል፡፡ ከጌታችን የተማርነውም ይህንኑ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን ሲደመድም ወደ ሮም ለመምጣት መከልከሉን ጠቅሶ፤

በቅርቡ እንደሚያያቸው ተናግሯል፡፡ የወደፊት ዕቅዱንም ስብከትና ድሆችን መርዳት መሆኑን ይገልጣል፡፡

7. የመልእክቱ መዝጊያ (ሮሜ. ፲፮) በዚህ ምዕራፍ ማስጠንቀቂያ፣ ስንብትና ሰላምታ ሰጥቶ ፈጸመ፡፡

## ማጠቃለያ

ሐዋርያው በዚህ ክፍል በዕለታዊ ሕይወታችን የሚገለጡ፣ ተግባራዊ ኑሮዎችን አስተምሮናል፡፡ ከእነዚህም፡- በፍቅር መኖር፣ የደካማውን ሐሳብ መቻል ማገዝ፣ ራስን ለእግዚአብሔር መስጠትና ከሌሎች ጋር ያለንን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና መንፈሳዊ ግንኙነታችንን እንድናሻሽል ይመክራል፡፡

**ተግባር፡-** የተማራችሁት ተለማመዱ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

መምህር ተማሪዎቹን በአራት ቡድን በመከፋፈል ይመድቢቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ የመወያያ ርእስ በመስጠት በተሰጣቸው ርእስ ላይ መጽሐፍ ቅዱስን እና በክፍል ውስጥ የተማሩትን መሠረት በማድረግ እንዲሁም ሌሎች አጋዥ መጻሕፍትን አንብበው አገናዝበው፣ መምህራንን ጠይቀው፤ በተሰጣቸው ርእስ ማብራሪያ ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ እና በክፍል ውስጥ ገለጻ እንዲያደርጉ ይሁን፡፡

ቡድን 1፡- ክርስቲያን እና ዕለታዊ ኑሮው ምን መምሰል አለበት?

ቡድን 2፡- ‹‹ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው›› የሚለውን ኃይለ ቃል ‹‹ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል፡፡ ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው›› ሮሜ.፲፫፥፱-፲

ቡድን 3፡- ‹‹ለሰማያዊው ሀገር መዘጋጀት›› ሲባል እንዴትና በምን ይገለጻል?

ቡድን 4፡- ክርስቲያን በእምነት ከደከሙት ጋር ያለው ግንኙነት ምን መምሰል አለበት?

www.zeorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን - የቤተ ክርስቲያን ነጻነት(አንድ)

# ዐሥራ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የቤተ ክርስቲያንን የመከራ ጉዞ እና ነጻነቱን ያውቃሉ። መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"አባቶችህ ለመረመሩት ነገር ትጋ"*

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› በዲያቆን መብራቱ ኪሮስ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መማሪያ ፤

**መግቢያ፡-** ይህ በተከታታይ የምንማረው *"የቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመን"* ታሪክ የመጀመሪያው ክፍል ነው። በዛሬው ትምህርታችንም የቤተ ክርስቲያንን መከራና በዐዋጅ የተሰጣትን የአምልኮ ነጻነት እንማራለን።

**የሳምንቱ ትምህርት፡-** ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተመሠረተች ጊዜ ጀምሮ ፈተና ነበረባት። የጌታችንን ትምህርትና ተአምራት ተመቅኝተው የተቃወሙት አይሁድ ትንሣኤውን ሊያስክዱ ሞክረዋል። ሆኖም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታላላቅ ተግባራትን የፈጸሙት እና ያስተማሩት ሐዋርያት በመጽሐፍ፣ በቃል እና በድንቆች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እውነቱን ገለጡ። አይሁድም ቅዱስ እስጢፋኖስን በድንጋይ ወግረው በመግደል፣ ሐዋርያትን በማሳሰር እና በማስገረፍ ለማስቆም ሞክረዋል። ቅዱሳን ሐዋርያት ግን በአገልግሎታቸው ስለጸኑ ከኢየሩሳሌም ውጪ ባሉ የእስራኤል ምድሮች እና በአሕዛብ ከተሞች የምሥራቹ ተስፋፋ። በኢየሩሳሌም ካመነው ስምንት ሺሕ ሕዝብ በላይ በተለያዩ ከተሞች አማንያን በዙ። የወቅቱ ልዕለ ኃያል በነበረችው የሮም ዋና ዋና ከተሞችም የወንጌል ትምህርት ተዳረሰ፤ አብያተ ክርስቲያናትም ተመሠረቱባቸው።

www.zeorthodox.org

ይህም ከአይሁድ ብቻ የነበረው ተቃውሞ አድጎ ከጣዖት አምላኪያን፣ ከሮም ቄሳሮች እና የተሳሳተ የሕይወት ግንዛቤ ከነበረባቸው የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች የክርስትና ጠላት ሆነው እንዲነሡ ምክንያት ሆነ። ክርስትና የእውነት እና የፍቅር ሃይማኖት ነውና ክርስቲያኖች

ሰማያዊውን እውነት በፍቅር እስከ ሞት በሚታመን ጽናት ገለጹ፡፡ ይህን ተከትሎም የሮም መንግሥት ቄሳሮች እና ሀገረ ገዢዎች ከዚያም በታች ያሉ ሹማምንት በዐዋጅ ቤተ ክርስቲያንን ሲያሳድዱ፤ ጣዖት አምላኪያኑ ለትምህርተ ክርስትና የኃይል መልስ በመስጠት ብዙ ክርስትያኖችን ገደሉ፤ አሳደዱ፡፡ በዚህ ሂደት የተሻለ የነበረው የፍልስፍናው ዓለም ለመወያየት ቢሞክርም የሮምን መንግሥት ኃይልና የውስጥ ጠላቶችን በመጠቀም ክርስትናን የማፍረስ ተንኮልን እንደ ጥበብ ተጠቀመ፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ከመጀመሪያው ዘመን ጀምሮ እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ በሮም መንግሥት የዐዋጅ እና የኃይል ጥቃት፤ በአይሁድ የአድማ ተቃውሞ በመከራና በስደት ኖራለች፡፡ የሮም ቄሳሮች እንደ አማልክት ይቆጠሩና ይመለኩ ነበር፡፡ ክርስትና ደግሞ የሐሰት አማልክትን ይቃወማል፡፡ አይሁድም የእግዚአብሔርን ጽድቅ ትተው የራሳቸውን ጽድቅ ለማቆም ሲጥሩ ከአምላክ ሰማይ ወምድር ፈቃድና ማዳን መውጣታቸው በክርስትና መስታወትነት ተገለጠባቸው፡፡ ለወትሮው ጠላቶች የነበሩት የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው፤ ሆኖባቸው ከቄሳሮችና ጣዖት አምላኪዎች ጋር ተባብረው ክርስቲያኖችን በግፍ እየገደሉ፣ ቅዱሳን መጻሕፍትንና አብያተ ክርስቲያናትን እያቃጠሉና እየዘጉ ሰብአዊ መብቶችን ለክርስቲያኖች ነፈጉ፡፡ በዚህ ምክንያትም ክርስቲያኖች ከማኅበረሰቡ እንዲገለሉ፣ በግፍ እንዲገደሉም ተደረገ፡፡

ይህ የመከራ ዘመን ***"ዘመነ ሰማዕታት"*** ሲባል፤ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ኃይል፣በፍቅር ክርስቶስን እየሰበኩ በጽናት ሰማዕትነትን ይቀበሉ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን በሰማዕትነት የሞቱ ክርስቲያኖች ብዙ ሲሆኑ የመጀመሪያው የክርስትና ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ቀዳሚ ሰማዕት ነው፡፡ የመጨረሻው ሰማዕት ሊቀ ጳጳስ ጴጥሮስ - ተፍጻሜተ ሰማዕት ይባላል፡፡ ሁሉም ብዙ መከራ ቢቀበሉም ከ 20-27 ዓመት ባለው የወጣትነት ዘመኑ በዓይነትና በተከታታይነት ብዙ መከራ የተቀበለው ቅዱስ ጊዮርጊስም ሊቀ ሰማዕት (የሰማዕታት አለቃ)ይባላል፡፡

***"እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎቹ ባልንጀሮቻቸውና የወንድሞቻቸው ቁጥር እስኪፈጸም ድረስ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው፡፡ "*** ራዕ ፮÷፱-፲፩ ***ጥቂት ዘመን*** የተባለው ያ የመከራ ዘመን የሚቆምበት እግዚአብሔርም ለቅዱሳን ጸሎት መልስ የሚሰጥበትና የሚፈርድበት ዘመን ደረሰና ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ነጻነትዋን አገኘች፡፡

www.zeorthodox.org

***ታሪካዊ ሂደቱ*** ፡- እግዚአብሔር በሰው ይሠራል፡፡ በዚህ መሠረት አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹና ክርስቲያኖች ነጻነት እንዲያገኙ አምላካችንና መድኃኒታችን ስለፈቀደ በሮም መንግሥት የሚከተለው ታሪክ ተፈጸመ፡፡

### ከንጋት በፊት ያለው ከባድ ጨለማ።

በተፈጥሮ ሂደት ከሰርክ እስከ ነግህ ፀሐይ የምትጠልቅበት ጨለማ የሚነግሥበት ቢሆንም ሊነጋ ሲል ያለው ጨለማ ግን ይበረታል። ቤተ ክርስቲያንም በአዋጅ ነጻነትዋን ከማግኘትዋ በፊት ከሰላሣ (30) ዓመታት ቀደም ብሎ በተነሣው በዲዩቅልጥያኖስ እና በጓደኛው መክስምያኖስ አመራር ከባዱ የቤተ ክርስቲያን የመከራ ዘመን ሆኖ በታሪክ ተመዝግቦዋል።

ንጉሥ ጋሊያኖን ከ፪፻፷-፪፻፷፰(260-268 ዓ.ም) በክርስቲያኖች ላይ ይደርስ የነበረውን መከራ ፣ እንግልትና ግድያ አስቆመ። በዚህ ዘመን ክርስቲያኖች በትምህርት፣ ምስጢራትን በመሳተፍ እና አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ ክርስትናን አስፋፉ። ነገር ግን ይህ እድገትና እፎይታ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ወደ አስደንጋጭ መከራ ተለወጠ። የዚህ ምክንያቱም ዲዮቅልጥያኖስ እና መክስምያኖስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያስነሡት ስደት ነው። በዚህ ዘመን ለተነሣው መከራ ዋናው ምክንያት የክርስቲያኖች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት መጨመሩ ነው። ቤተ ክርስቲያን ለአሕዛብ ቤተ ጣዖታትና ለሮማ መንግሥት ስጋት እንደ ሆነች በማሰብ፤ የክርስቲያኖችን ጥንካሬ መስበርና ለንጉሡ ማስገዛት የዘመኑ የሮም መሪዎች ፍልስፍና እና ውሳኔ ነበር።

**የዲዮቅልጢያኖስ እና መክስምያኖስ ዘመን** ፡- ከሮም መንግሥት ባላንጣ ከፋርስ ጋር በተደረገ ጦርነት በፈጸመው ጀብድ ለታላቅ ወታደራዊ መዓርግ የደረሰው ዲዮቅልጥያኖስ ከድሃ ቤተሰብ የተወለደ ሰው ነበር። በኋላም በ፪፻፹፬(284) ዓ.ም በሰፊው የሮም ግዛት ንጉሠ ነገሥት ሆነ። በጣም ተለጥጦ ሊወድቅ በነበረው የሮም ግዛት የመልሶ ማደራጀት ሥራን ሠራ። ግዛቱን ለሁለት ከፍሎ ምዕራቡን ለጓደኛው ለመክስምያኖስ ሰጥቶ እርሱ ምሥራቁን ክፍል ያዘ። ከዚያም ሁለቱም ***አውግስጦስ*** ተብለው ተሾሙ ። በምሥራቅ የዲዮቅልጥያኖስ አማች ጋሊሪዮስ በምዕራብ ኮንታንዲዮስ ክሎሪን ***ቄሳር*** በሚል ማዕረግ በእንደራሴነት ተሾሙ።

በተከታታይም ዲዮቅልጢያኖስ አራት አዋጆችን ከ፫፻፪-፫፻፬(302-304ዓ.ም) አወጣ። የመጀመሪያው በፌብሩዋሪ ፫፻፫(303) ዓ.ም የወጣው ሲሆን፤ የክርስቲያኖችን የአምልኮ ሥፍራዎች (አብያተ ክርስቲያናትን) መፍረስ እና ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲቃጠሉ፤ የሚያዝዝ ነበር። ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን መምህራንን ማጥፋት እና መንጋውን መበተን ነው። ሦስተኛውም ከሁለተኛው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የቤተ ክርስቲያን ካህናትን የሚመለከት ዝርዝር መመሪያ የያዘ ነው። አራተኛውና የመጨረሻው በ፫፻፬(304) ዓ.ም መጀመሪያ የወጣው ሲሆን ሁሉም አንድ እንኳን ሳይቀር ንጉሡ ባዘዘው መሠረት ለጣዖታት እንዲሰግዱና መሥዋዕት እንዲሠው የሚያዝ ዐዋጅ ነበር።

ከዲዮቅልጢያኖስ ጋር በቄሳር መዓርግ ምሥራቁን የሚያስተዳድረው ጋሌሪዮስም የከረረ ፀረ ክርስቲያን አቋም ስለ ነበረው፤ በምሥራቅ የሮም ክፍል የነበረው መከራ በደም የተሞላ ነበር።

www.zeorthodox.org

ታዋቂና ባለ ሥልጣን ክርስቲያኖች ሥልጣንና ጥቅማቸውን እንዲያጡና በግዛቱ ያሉ ክርስቲያኖችም ሕጋዊ መብታቸውን እንዲያጡ ተደረገ። ዋናውና በገሀድ የነበረው መከራ ቅዱሳት መጻሕፍቱን እንዲያስረክቡ የሚያዝዘውን ዐዋጅ ባልፈጸሙ ካህናት ላይ ነበር። ይህን ተጋፍጠው መጻሕፍቱን በመደበቅ ሰማዕትነት የከፈሉ፣ በድብቅ የተሰደዱና በየዋሻው ተቀምጠው መጻሐፍትን ባባዙት ካህናት እና ምእመናን ጥረት መጽሐፍ ቅዱስ ለዘመናችን እንዲደርስ ረድቶናል። በተቃራኒው በዚህ ፈተና የወደቁ አንዳንድ ካህናት በሮም እና በሰሜን አፍሪካ እንደ ነበሩም ታሪክ ይነግረናል። እነዚህም በኋላ ***"የተሸነፉ"*** የሚል ስያሜ ተሰጥቶአቸዋል።

በምዕራቡም ንጉሥ መክስምያኖስ በግሉ ፀረ ክርስቲያን አቋም ይዞ ማሳደዱን ቢገፋበትም ቄሳሩ ኮንታንዲዮስ ዐዋጁን ስላላመነበት መከራው የተሻለ ነበር። ለምሳሌ አብያተ ክርስቲያናት ቢቃጠሉም ክርስቲያኖችን ማሠር እና መግደል የምሥራቁን ያህል አልነበርም።

## የነጻነት ምክንያቶች

1. **ግፈኞች ደከማቸው።** በዕድሜ የገፋው ዲዮቅልጢያኖስ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ብዙ ታግሎ በሕመም እና ድካም በ፫፻፭(305) ዓ.ም ሥልጣኑን ሲለቅ መክስምያኖስም ሥልጣኑን አስረከበ። ጋሌርዮስና ኮንስታንድዮስ ከቄሳር ወደ አውግስጦስ መዓርግ አደጉ። ማክስምያስ እና ሰቨረስ የተባሉ የጦር መሪዎችም በቄሳር መዓርግ ተተኩ።

ምዕራባዊውን ሮም የያዙት ኮንስታዲዮስ እና ሰቨረስ ዐዋጁን ተቃወሙው መከራው በምዕራብ ቆመ። በምሥራቁ ግን በአውግስጦስ ጋሌርዮስ ምክንያት በስፋት ቀጠለ። ክርስቲያኖች የቀኝ ዓይናቸው እየወጣ የግራ እግራቸው በጋለ ብረት እየተተኮሰ አካለ ጐደሎ እንዲሆኑ ተደረገ። መከራውን የታገሡት ክርስቲያኖች ጸሎትና ጽናት ከእግዚአብሔር መልስ አስገኘና ጋሌርዩስ በጠና ታመመ። ይህም መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት (ፍትሕ) ጋሌርዮስን ወደ እውነት የመመለስ ዕድል ሰጠው። እርሱም በክርስቲያኖች ላይ የደረሰው መከራ እና ዐዋጅ ስሕተት እንደ ነበር አምኖ የክርስትናን የአምልኮት ነጻነት ***"የመቀበል አዋጅ"*** በ፫፻፲፩(311) ዓ.ም አወጣ። ክርስቲያኖች ለአምላካቸው ስለ ንጉሡ እንዲጸልዩም ጠየቀ። ይህም የሮም መንግሥት ከሁለት መቶ ዓመታት ክርስትናን የማሳደድ ጉዞው በኋላ የሰጠው የመጀመሪያው የአምልኮ ነጻነት ነበር። ይህም ለሮም መንግሥትና ለገዢዎቻቸውም ሰላም የሰጠ ሆነ።

www.zeorthodox.org

2. **የነጻነት ጮራ ታየ።** እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ሜይ 311 ዓ.ም ጋሌርዮስ ሲሞት አራት ተፎካካሪዎች የሮምን ግዛት ተቆጣጠሩ። እነርሱም የኮንስታንድዮስ ልጅ ቆስጠንጢኖስ ፣ ሊሲኒስ ፣ ማክስሚነስ ዳያ እና ማክሰንትዮስ ናቸው። ማክስሚነስ ዳያ የ311ዱን የአምልኮ ነፃነት

***የመቀበል አዋጅ*** በኀቡዕ ሲቃወም ቆይቶ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ጀመረ። ሦስቱም ግን ለክርስቲያኖች መሠረታዊ ነጻነት ሰጡ።

3. **የሕልም እና የእውን ድል**። በምዕራባዊው የሮም ግዛት በ፫፻፮(306) ዓ.ም ኮንስታዲዮስ ሞተና ልጁ ቆስጠንጢኖስ ተተካ። በዚህ ጊዜም፡- ብዙ ጦርነቶች በሰሜን ጣልያን ተደርገዋል። ከእነዚህም አንዱ እና ወሳኙ ቆስጠንጢኖስ ከማክስንትዩስ ጋር በሳክሳ ሩብራ ያደረገው ጦርነት ነበር ። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ለቀጣዩ ቀን ጦርነት እየተዘጋጀ በነበረበት ሌሊት ሕልም አየ። ሕልሙም የክርስቶስ ስም የመጀመሪያ ፊደላት በግሪክ ፊደል ተመሳቅለው አየ። በመስቀሉ ምልክት ድል እንደሚያደርግም ተነገረው። እርሱም ይህን ምልክት በሄልሜትና በወታደሮቹ ልብስ ላይ አድርጐ ጥቅምት 20 ቀን 312 ዓ.ም በሚል ቪያን ድልድይ በተደረገው ጦርነት ድል ተቀዳጅቶ፣ ምዕራባዊውን ሮም ጠቅልሎ ማስተዳደር ጀመረ። በምሥራቅ የነበረውና ክርስቲያኖችን የሚያሰቃየው ንጉሥ ማክሲንትዮስም በሊሲንየስ በ፫፻፲፫(313) ዓ.ም ተተካ።

4. **የነጻነት አዋጅ**። በ፫፻፲፫(313) ዓ.ም ቈስጠንጢኖስና ሊሲንየስ በሚላን ተገናኝተው የግዛት ውል ሲያደርጉ ለክርስትና ሙሉ ነጻነት ሰጡ። ይህም ***"የሚላኑ ዐዋጅ"*** የሚባለው ነው። ከዚህ በኋላ አብያተ ክርስቲያናት ታነፁ፤ ክርስትና ነጻነቱን ሲያገኝ በአስደናቂ ፍጥነት ተስፋፋ።

ይህ እድገት ያላስደሰተው እና ያልጠበቀው የሆነበት ሊሲንየስ የሚላኑን ዐዋጅ መጣስ ጀመረ። በዚህ ምክንያት በ፫፻፲፬(314) ዓ.ም በአድያናፖል ቆስጠንጢኖስ ድል ሲያደርገው ያደገበት ጥላቻ ክርስቲያኖች ላይ የሚያደርሰውን ግፍ አባሰው። በምሥራቁ የሮም ግዛት ክርስቲያኖችን አሳደደ ፣ ክርስቲያን ባሮችን ለአሕዛብ ሸጠ ፣ ክርስቲያን ሹማምንትን ሻረ ፣ ጳጳሳት እርስ በርስ እንዳይገናኙ እግድ ጣለ ፣ የአደባባይ ሥርዓተ አምልኮቶች ተከለከሉ ፣ ክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው የታሰሩትን ወንድሞቻቸውን እንዳይጠይቁም አገደ። ይህም ከ ፫፻፲፬-፫፻፳፫(314-323) ዓ.ም ቀጠለ።

በ፫፻፳፫(323) ዓ.ም ቆስጠንጢኖስ ሊሲንየስን በክራስፖሊስ አሸንፎ ብቸኛው የሰፊው ሮም ግዛት ንጉሥ ሆነ። ይህም ለቤተ ክርስቲያን ሙሉ የነፃነትና ከመንግሥት ጋር መግባቢያ ጊዜ ሆነላት። ቆስጠንጢኖስ በ፫፻፴(330) ዓ.ም ቁስጥንጥንያ የተባለችውን ከተማ መሥርቶ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ቤተ ክርስቲያን ሐግያ ሶፊያ (ቅድስት ጥበብ) ብሎ አሳነፀ። በርካታ አብያተ ክርስቲያናትም በየከተሞቹ ታነፁ።

www.zeorthodox.org

**ማጠቃለያ፡-** ቤተ ክርስቲያን የሦስት መቶ ዓመታት ስደት እና መከራ አሳልፋ በእውነት ትምህርት፣ በፍቅር እና በመሥዋዕትነት ነጻነት አገኘች።

## ተግባር፡-

1. ከቤተ ክርስቲያን የመከራ ጉዞ መልካም እያደረግን መከራ ስንቀበል መጽናትን እንማራለን። *‹‹ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፤ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱም ኃጢአት አላደረገም፤ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም። ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ...”* ፩ኛ ጴጥ.፪፥፳-፳፬ ስለዚህም መልካም በማድረግ መከራ ሲኖር የክርስቶስን አርዓያት እንደተከተሉት አበው በመኖር እግዚአብሔርን ደስ እናሰኘው።
2. *መንፈሳዊ ጽናት በፍቅር በጸሎትና ለእውነት በመቆም ይፈጸማል።* ይህም ዘላለማዊ ደስታን፣ *ዓመጸኞችን በፍቅር ለእግዚአብሔር መማረክንና ሰማያዊ ዋጋንም እንደሚያስገኝ* ከትምህርቱ ተረድተናል። በተረዳነው *መሠረት* ሌሎችን የእግዚአብሔር ለማድረግ በጸሎት እና በአርዓነት ምሳሌ *በመሆንም* የክርስትና የክብር *ዕቃ ለመሆን ራሳችሁን* ከኃጢአት አንጹ።›› ፪ኛ ጢሞ.፪፥፳-፳፪።

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ‹‹ዘመነ ሰማዕታት›› የተባለበት ምክንያት ምንድነው? ዘመኑስ መቼ ነበር?
2. የመጀመሪያው የክርስትና ሰማዕት ማን ነው? የመጨረሻው ሰማዕትስ ማን ይባላል? የሰማዕታት አለቃ የማባው (ሊቀ ሰማዕት) ማነው?
3. ከባዱ የቤተ ክርስቲያን የመከራ ዘመን ተብሎ በታሪክ የተመዘገበው ዘመን የሮም መንግሥት መሪዎች እነማን ነበሩ?
4. ዲዮቅልጥያኖስ ከ302-304 ዓ.ም በተከታታይ ያወጣቸው ዓዋጆች ምን ምን ናቸው?
5. የ‹‹ሚላኑ ዓዋጅ›› የሚባለውን ለክርስትና ሙሉ ነጻነት የሰጠ ዓዋጅ ያወጁት ንጉሦች እነማን ናቸው? መቼ?
6. ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በ330 ዓ.ም የመሠረታት ከተማ ማን ትባላለች? ዛሬ በየት ሀገር ትገኛለች? በዚህች ከተማ ያሳነፃት ልዩ ቤተ ክርስቲያን ማን ትባላለች?

www.zoorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን - የነጻነቱ ውጤቶች(ሁለት)

## ዐሥራ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ነጻነትን በዓዋጅ ማግኘትዋ ያስገኘውን ክፉና መልካም ውጤት ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚያቀር ቡላቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና፡፡ እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ፡፡"* ዮሐ.፬፥፴፯-፴፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ›› በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› በዲያቆን መብራቱ ኪሮስ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መማሪያ፡፡

**መግቢያ፡-** ክርስትና እንደ ዱላ ቅብብል ከአባት ወደ ልጅ ሲተላለፍ የኖረ ሕይወት ነው፡፡ ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን እንዳየነው በዘመነ ሰማዕታት የሰው ልጅ አእምሮ ከሚያስበው በላይ አሳዝኝ መከራዎች አልፈው፤ ቤተ ክርስቲያን ነጻነትዋን አገኘች፡፡ ዓለም ለቤተ ክርስቲያን የሰጠችው ነጻነት በዋናነት ዓለምን ከዚያም ቤተ ክርስቲያንን በብዙ የጠቀመ ሲሆን በተቃራኒው ነጻነቱን ተከትሎ የመጣ የቤተ ክርስቲያን ያልሆኑና አሉታዊ ውጤቶችም ነበሩ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን እነዚህን እናያለን፡፡

### ነጻነቱ ያስገኛቸው በጎና ክፉ ውጤቶች

www.zeorthodox.org

በጎ ውጤቶች፡- ለቤተ ክርስቲያን የተገኙ በጎ ውጤቶች የምንላቸው፡-

1. ለሦስት መቶ ዓመታት ያሳለፈችው መከራ ተቋጨ፡፡
2. አብያተ ክርስቲያናት ታነፁ፡፡ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በአዲሲቱ ከተማው በቁስጥንጥንያ ያሳነፃት ‹‹ሐባያ ሶፊያ›› (ቅድስት ጥበብ) በመባል የምትታወቀው ቤተ ክርስቲያን አንዷ ናት፡፡
3. በገሀድ የሚደረግ የጣዖት መሥዋዕት ቀረ፡፡ ከሰው ሰብእና የወረዱ አስጸያፊ መሥዋዕቶች ከቤተ ጣዖታቱ ባዶ መሆን ጋር ቀሩ፡፡

4. **ከቤተ ጣዖት ወደ ቤተ ክርስቲያን**፡፡ በከተማና በቅርብ ቦታዎች የነበሩ አብያተ ጣዖታት ተለውጠው አብያተ ክርስቲያናት ሆኑ፡፡
5. **ድጎማ** ፡፡ በግዛቱ ለነበሩት ጣዖታት ይሰጥ የነበረው የመንግሥት ድጎማ ቀርቶ ለቤተ ክርስቲያንና ለአገልጋዬችዋ ሆነ፡፡
6. **ለካህናት ልዩ መብት ተሰጠ**፡፡ የዜጐች የሥራ ግዴታዎች ፣ ግብር… ለካህናት ቀረ፡፡ በካህናት ላይ ክስ ቢኖር በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ፍርድ ቤቶች መታየት ጀመረ፡፡ ይህም አገልጋዮች ከሀገሪቱ ሕግ በላይ እንዲሆኑ አስቻለ፡፡
7. **ሰንበት መከበር ጀመረች**፡፡ የዕረፍትና የአምልኮ ቀን እንድትሆን ቆስጠንጢኖስ ሲያውጅ ለወታደሮቹ በሰንበት ዕረፍት ሰጠ፡፡ ዕለቲቱ የበለጠ በበዓልነት እንድትከበርም ሕዝባዊ ጨዋታዎች በሰንበት ተፈቀዱ፡፡

***ለመንግሥት እና ለሕዝብ የተገኙ መልካም ውጤቶች***

1. **ስቅላት ቀረ**፡፡ ሮማዊ ያልሆኑ የሚገደሉበት የስቅላት ቅጣት ቀርቶ፤ መስቀል የሰላምና ድል ምልክት ሆነ፡፡
2. **የአካል ጉዳተኞች ግድያ ቀረ**፡፡ ከአረማዊነት የተወሰደው አካል ጉዳተኞችን በገደ ቢስነት እየፈረጁ መግደል ቆመ፡፡
3. **የባሪያ ንግድ ተሻሻለ**፡፡ ባሪያን እንደ እንስሳ ቆጥሮ ማሰቃየትና ግድያ ቀርቶ ሰብአዊ ክብር እንዲጠበቅላቸው ተደረገ፡፡
4. **የግላዲያተሮች ግፈኛ ጨዋታ ተከለከለ**፡፡ ሰውና አራዊትን እያታገሉ በዘግናኝ ሞት መዝናናት ተከለከለ፡፡

## አሳዛኝ ክስተቶች፡-

ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት እውቅና ማግኘትዋን ተከትሎ፤ ክርስቲያኖች የበለጠ በአገልግሎታቸው እና በሕይወታቸው ሲበረቱ አብዛኛው ሕዝብ ክርስቲያን ሆነ፡፡ በቤተ መንግሥት እና በባለ ጸጐች አካባቢ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች የተሰጠው ክብርም የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የነበሩና ጥቅም ፈላጊዎችም በማስመሰል ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ አጋጣሚ ከፈተላቸው፡፡

www.zoorthodox.org

እነዚህም የአሕዛብ ጣዖታት ልማድን፣ የዓለምን የሐሰት ፍልስፍናና ለክርስቲያን ያልተገባ ሕይወትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው ገቡ፡፡ ይህም መልካም የሆኑት ትሕትና፣ የቅድስና ሕይወት ለክርስትና ዋጋ መክፈል ወዘተ እየቀሩ፡፡ በፍቅረ ነዋይ፣ በክፉ ምኞት፣ በሥልጣን ግብግብ፣ በአካባቢያዊነት እና በንቀት እንዲተኩ አደረገ፡፡ ስለዚህም አለመግባባቶች ወደ ነገሥታት ፍርድ

ወንበር፣ ቀላል ጉዳዮች ወደለየለት ልዩነት እንዲያድጉ ሲያደረግ ቀይቶ ቤተ ክርስቲያንን የከፋፈለ አደጋ ለመሆን በቃ፡፡ ከእነኚህ መከፋፈሎች በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የታዩት የሚከተሉት ልዩነቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

1. **የመላጥዬስ ሐሳብ፡-** በዲዮቅልጢያኖስ ዘመን የካዱና ለጣዖት መሥዋዕት የሠው፣ ያጤሱ ንስሓ ቢገቡም መቀበል የለብንም፤ በሚል ከተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስና ከተከታዩቹ ጋር የተፈጠረው ክርክር መወጋገዝ አስከትሎ ነበር፡፡

2. **የዶናቲስቶች ያልተገባ አክራሪነት፡-** በካርቴጁ ዶናቲስት መሪነት ጥንቃቄንና ቅድስናን በቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ ተነሥተው በሐሰተኛ መረጃዎች ምእመናኑን ግራ ማጋባትና ክርስቲያኖችን ማሳደድ ጀመሩ፡፡ በኋላም ቅዱስ ቁርባን የሚለወጠው ካህኑ ቅድስና ካለው ብቻ ነው፤ ብለው በማስተማራቸው የተወገዙ እና ለአንድ ክፍለ ዘመን የቆየ መለያየት የፈጠሩ ነበሩ፡፡

3. **ጽርስቅላውያን፡-** ጽርስቅላና ተከታዮቹ ጥንቆላንና ፍልስፍናን ከክርስትና ጋር ቀላቅለው እያስተማሩ፤ አስከፊ ሁከት ፈጥረው ነበሩ፡፡

4. **አርዮሳውያን፡-** በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአርዮስ የተጀመረ አዲስ ትምህርት ነው፡፡ አርዮስ በግሪካውያን ፍልስፍና (በተለይም በፕሌቶ) ትምህርት ሁለት አማልክት (ትልቅ እና ትንሽ) የሚለውን በመጽሐፍ ቅድስ ሽፋን ያስተማረ ሰው ነው፡፡ በዚህ ትምህርቱም የክርስቶስን አምላክነት ክዶ ፍጡር ነው አለ፡፡ በድምፁ ማማርና ለሕዝቡ በቀረበ አቀራረቡ በአጭር ጊዜ ተከታዮች አፈራ፡፡ ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ከስሕተቱ እንዲመለስ ቢመክረውም አልሰማም፡፡ ከመላጥዩስአውያን ጋር በመተባበሩ ቢወገዝም ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስን የተካው አኪላስ ከግዝቱ ፈታው፡፡ አኪላስ በመንበረ ማርቆስ በተሾመ በስድስተኛው ወር ሞተና ፫፻፲፪(312) ዓ.ም እለ እስክንድሮስ ተተካ፡፡ እለ እስክንድሮስ አርዮስ ከስሕተቱ እንዲታረም ቢመክረውም አልሰማም፡፡ ይባስ ብሎም እለ እስክንድሮስን በሰባልዮሳዊነት (እግዚአብሔር አንድ ገጽ ነው በማለት) ሊከሰው ሞከረ፡፡ እለ እስክንድሮስ የአርዮስን ክህደት አንድ መቶ ጳጳሳትን ይዞ ይህን ትምህርት ቢያወግዘውም በትምህርቱ የተሳሳቱ *"አባቶችን"* እና ተከታዩቹን ይዞ በስሕተቱ ቀጠለበት፡፡

እነዚህና የመሳሰሉት ክህደቶችና መከፋፈሎችን ለመግታትም አካባቢያዊ (local) እና ዓለም አቀፋዊ (Universal) ጉባኤያት ተካሂደዋል፡፡ የሮም መንግሥት ክርስቲያን መንግሥት ስለሆነም ነገሥታቱ በሕግና በአስተዳደር ለመፍታት ሞክረዋል፤ ብዙ ጊዜም ተሳስተዋል፡፡ አባቶችም መጻሕፍት በመጻፍ፣ በማስተማር እና በመንፈሳዊ ተጋድሎ በጾምና በጸሎት ለመፍታት ደክመዋል፡፡ ከዚህ በማስከተልም እነዚህን ሂደቶች እናያለን፡-

www.zeorthodox.org

## ጉባኤያት

የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሐዋርያት በኢየሩሳሌም በሃምሳ ዓ.ም የሰበሰቡት ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ለቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች መልስ የሚሰጡ የተለያዩ ጉባኤያት ተደረገዋል፡፡ ከእነዚህም የመጀመሪያው ዓለም አቀፋዊ ጉባኤ የኒቅያው ጉባኤ ነበር፡፡

1. **ጉባኤ ኒቅያ፡-** በአርዮስ የተሳሳተ ትምህርት ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ስትታመስ የተጠራ የመጀመሪያው ዓለም አቀፋዊ ጉባኤ ነው፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ነጻነት የሰጠው የመጀመሪያው ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የክፍፍሉን አደገኛነት ፈርቶ የጠራው ስብሰባ ሲሆን፤ ጉባኤው በኮርዶቫው ሊቀ ጳጳስ በሆስዩስና በአሌክሳንድርያው ሊቀ ጳጳስ በእለ እስክንድሮስ ተመራ፡፡

አርዮስ ***"አብ ወልድን ከወለደው የጊዜ መቀዳደም አለና አብ ይበልጣል ወልድ ያልነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ አምላክ የተባለው በስም ብቻ ነው፡፡"*** አለ፡፡ ከዚህም ጋር ***"ክርስቶስ ከፍጥረታት የሚልቅና በአብ ተፈጥሮ ሌሎችን ፍጥረታት የፈጠረበት ነው፡፡"*** ሲል አስተማረ፡፡

ነገር ግን ***"ልጅ"*** ሰው በሚገባበት ቃል የተቀመጠ እንጂ በተለምዶ እንደሚቀዳደሙት የሰውና የእንስሳት ልደት አልነበረም፤ እንዲያውም ከሻማ ብርሃን ሌላ ሻማ ቢለኮስ የትኛውም ብርሃን ይቀድማል እንደማይባለው ነው፡፡ በማለት ቅዱስ አትናቴዎስ የአብና የወልድን እኩልነት አስረዳ፡፡ በመጨረሻም ጉባኤው ***"ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ÷ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ የተወለደ እንጂ የተፈጠረ ያይደል፡፡"*** ሲል ውሳኔ አስተላለፈ፡፡ ከዚሁም ጋር የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችንና ሥርዓታት ላይ ውሳኔ ሠጥቶ ተጠናቀቀ፡፡ አርዩስ እና ትምህርቱም ተወገዙ፡፡ ብዙም ሳይቆይ እለ እስክንድሮስ ዐረፈ እና ቅዱስ አትናቴዎስ ተተካ፡፡

በዚህ ወቅት ነው ኢትዮጵያን በወንጌል ብርሃን ያበራት፤ ሶርያዊው ፍሬምናጦስ ከኢትዮጵያ ወደ እስክንድርያ ሄዶ በቅዱስ አትናቴዎስ ***"አቡነ ሰላማ የአክሱም እና የመላዋ ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ"*** በሚል መዐርገ ክህነት ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው፡፡

በሌላ በኩል በጉባኤው የተሸነፉት አርዮሳውያን በኒቆምዲያው አውሳብዮስ መሪነት መንግሥትንና የተከታዮቻቸውን ሁከት እየተጠቀሙ ኦርቶዶክሳውያኑን በተለይም ቅዱስ አትናቴዎስን ማሳደድና ማሳሰር ጀመሩ፡፡ ባይሳካላቸውም በተለያዩ ጉባኤያት ኦርቶዶክሳውያኑን ለማውገዝ ሞክረዋል፤ በኋላም ተዳከሙ፡፡ አርዮሳውያኑ ብዙ ተከታዮችን፤ሊቃነ ጳጳሳት እና ነገሥታቱንም እስከ ማሰለፍ ደረሱ፡፡

www.zoorthodox.org

እውነተኞቹም በትምህርት፣ በቃል እና በኑሮ ለመንጋው ምሳሌ በመሆንና በመከራው በመጽናት የእውነት ሃይማኖትን ጠብቀው አስተላላፉ፡፡ የኒቅያን ጉባኤ ውሳኔና የሐዋርያትን ትምህርት ለማስተላለፍ ከሐሰተኛ መምህራን ከስሑታንና ከዲያብሎስ ተንኮል ቤተ ክርስቲያንን ጠበቁ፡፡ ይህ ሒደት አርዮሳውያኑን ጸረ ኒቂያውያን፤ ኦርቶዶክሳውያኑን ኒቅያውያን የሚል ስያሜ አሰጣቸው፡፡

## 2. ጉባኤ ቁስጥንጥንያ፡-

**የጉባኤው ምክንያት፡-** በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከአርዮሳውያን ሌላ በሎዶቂያው አቡሊናርዩስ የሚመራውና፤ ‹‹ቃል ሥጋን እንጂ ነፍስን አልነሳም መለኮት ለሥጋ ነፍስ ሆነው›› የሚል አዲስና የተሳሳተ ትምህርት ተነሣ፡፡ ይህም ጌታችን ***"ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጥሀለሁ"*** ሉቃ.፳፪÷ ካለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የወጣ ነበር፡፡ የቁስጥንጥንያው ጳጳስ መቅዶንዮስም **"መንፈስ ቅዱስ አምላክ አይደለም"** ብሎ ተነሣ፣ የዚህ ትምህርት ተከታዮችም (Pneunatomachi) ተባሉ፡፡

**የጉባኤው መጠራት፡-** ጎርጎርዩስ ዘእንዚናዙ ንጉሥ ቴዎዶስዩስ አንደኛ ጉባኤ እንዲጠራ፤ ቤተ ክርስቲያንን እያዳከመና እየከፋፈለ ያለውን ኑፋቄና ክርክሩን እንዲያስቆም ጠየቀው፡፡ በዚህ መሠረት በግንቦት(may) ፫፻፹፩(381) ዓ.ም በቁስጥንጥንያ ከተማ ጉባኤ ተጠራ፡፡ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት አባቶች በሙሉ ሲገኙ በምዕራቡ የሮም ግዛት ካሉት ማንም አልተገኘም ነበር፡፡ ጉባኤው መጀመሪያ በሊቀ ጳጳሳት መላጥዩስ ተመራ፡፡ እርሱ በመሞቱም ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ተተካ፡፡ በኋላም የእስክንድርያው ጢሞቴዎስ ዘአልቦ ጥሪት ጉባኤውን መራ፡፡ የመቅዶንዮስ ትምህርት ተወገዘ፡፡ በኒቅያው ጉባኤ ሙሉ ውሳኔ ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ዛሬ በጸሎተ ሃይማኖት የምንደግመው ቃል ተጨመረበት፡፡ ***"በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፤ እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብ የሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለንም፤ እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረው ነው፡፡"*** ከዚህም ጋር ጌታችን ፍጹም ሰው ሲሆን(ሥጋን) ሲነሣ ነፍስንም እንደነሣ በማጽደቅ የአቡሊናርዮስን ትምህርት እና ሌሎች ሠላሳ ስድስት መናፍቃንን አውግዘው ጉባኤው ተጠናቀቀ፡፡

**ማጠቃለያ፡-** የክርስትና ነጻነት በርካታ መልካም እና አሳዛኝ ውጤቶችን አሳይቶናል፡፡ ነገር ግን አሁንም እውነተኛ ክርስቲያኖች መልካሙን ሲያጸኑ ክፉን በእምነት ድል አድርገውታል፡፡

**ተግባር**፡- መልካም አጋጣሚዎችንና ድሎችን ከመልካም አስተሳሰብ ጋር በማስተዋል መያዝ እና መጠቀም ያስፈልገናል፡፡ ግዴለሽነት እና ማስመሰል የሌሎችን ድካም ከንቱ ማድረግና ቅጣትንም ያስከትላልና፡፡ ***"ንቁ በሃይማኖት ጎልምሱ"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፮፥፲፫

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች፡-***

1. ቤተክርስቲያን በዘመነ ሰማዕታት ካሳለፈችው መከራ ነጻ ከወጣች በኋላ የተገኙት መልካም ውጤቶች ምን ምን ናቸው?
2. በመንግሥትና በሕዝብ በኩል መልካም ውጤቶች ናቸው የሚባሉትስ ምንድን ናቸው?

3. ቤተክርስቲያን በመንግሥት እውቅና ማግኘቷን ተከትሎ የተፈጠሩ አሳዛኝ ክሥተቶች ምን ምን ናቸው? በዝርዝር አብራሩ፡፡
4. የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጉባኤ መቼ እና የት ተካሔደ? ተሰብሳቢዎቹ እነማን ነበሩ?
5. የመጀመሪያው ዓለም አቀፋዊ ጉባኤ ማን በመባል ይታወቃል? የት ተካሔደ? መቼ ተደረገ?
6. ይህ ጉባኤ የተደረገበት (የተጠራበት) ዋናው ምክንያት ምንድነው? ጉባኤውን የጠራው (የሰበሰበው) ማን ነው? ጉባኤውን የመሩት ማን ይባላሉ? በጉባኤው የተላለፈው ውሳኔ ምን ነበር?
7. ‹‹አቡነ ሰላማ የአክሱም እና የመላዋ ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ›› በሚል መዓርገ ክህነት ተሾሞ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ማን ይባላል? የየት ሀገር ሰው ነው? ሾሞ የላከው አባት ማን ይባላል? የየት ሀገር ሰው ነው?
8. ‹‹ጉባኤ ቁስጥንጥንያ›› መቼ ተካሔደ? የተጠራበት (ጉባኤው የተካሔደበት) ምክንያት ምን ነበር? ጉባኤውን የመሩት አባቶች ማን ይባላሉ? በጉባኤው የተላለፈው ውሳኔስ ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን - የውስጥ መከራው መልካም ውጤቶች(ሦስት)

# ዐሥራ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የውስጥ ፈተናን በመልካም ስለ ማሸነፍ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን፡፡"*** ሮሜ.፰፥፳፰፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-**

**መግቢያ፡-** ቤተ ክርስቲያን በውጭ ጠላቶቿ ከተፈተነችው በላይ የውስጦቹ ፈተናዎች አውከዋታል፡፡ ነገር ሁሉ ለበጎ ሆኖ ፈተናዎቹ አስደናቂ በረከቶችን ለቤተ ክርስቲያን አስገኝተው አልፈዋል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ከእነዚህ መልካም ውጤቶች ሦስቱን እናያለን፡፡

1. **ክርስትና - *የመንግሥታት ሃይማኖት ሆነ*፡-** በ፫፻፹፯(387) ዓ.ም የምዕራቡን ሮም ንጉሥ አሸንፎ ቴዎዶስዮስ አንደኛ ብቸኛው የሮም ንጉሥ ሆነ፡፡ ይህ ንጉሥ በኦርቶዶክሳውያን አበው የተጠመቀ እና የሮም መንግሥት ሃይማኖት ክርስትና መሆኑን ያወጀ የመጀመሪያው ንጉሥ ነው፡፡

በሀገራችን የነበሩት እና ኢትዮጵያን ለሁለት ያስተዳድርዋት የነበሩት ነገሥታት አብርሃ እና አፅብሃም በቅዱስ አትናቴዎስ ተሹሞ በመጣው በአቡነ ሰላማ ፫፻፴(330) ዓ.ም ተጠመቁ ፤ ከሃያ ዓመታት የአቡነ ሰላማ፣ ሌሎች ኢትዮጵያውያንና የነገሥታቱም አገልግሎት በኋላ በእግዚአብሔር ፍቃድ እና ኃይል በ፫፻፶(350) ዓ.ም ክርስትና በኢትዮጵያ የመንግሥት እና ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ ታወጀ፡፡

www.zoorthodox.org

2. **የምንኩስና *መጀመር*፡-** ዓለማውያን ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባታቸውና ክርስትና በሮም መንግሥት እውቅና በማግኘቱ በሥልጣን እና በአካባቢያዊነት የተጀመረው መከፋፈል መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የረበሸባቸው ክርስቲያኖች ተለይተው መኖር ጀመሩ፡፡ ይህ ሂደትም ከጀማሪዎቹ አባቶች በአንዱ በመቃርዮስ ስም" ***የመቃርዮስ ንቅናቄ*** " (Moritorious Movement) ተባለ፡፡ ይህ የምንኩስና ዓይነት ኑሮ ሲሆን በቡድንና በግል ከዓለም ተለይተው መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በመንከባከብ ፤ በተመስጦ ፤ በጸሎት እና በተባሕትዎ የሚኖሩት መንፈሳዊ ኑሮ ነበር፡፡ ይህ ዓይነት

የገዳማዊነት ኑሮ በሔኖክ ፣ በኤልያስ እና በዮሐንስ መጥምቅ የታየ ነው፡፡ ጌታችንም አርባ ቀንና ሌሊት በቆሮንቶስ በረሐ በመኖር ያሳየው እና ባርኮ የሰጠው መንፈሳዊ አኑዋኑዋር ነው፡፡(፩ኛ ነገሥ.፲፱÷፬-፲፬፣ ማቴ.፫÷፩-፲፫፣ ማቴ.፬÷፩-፲፩) በዚህ አርዓያነት በግብጽ የተጀመረው ገዳማዊ ኑሮ በአጭር ጊዜ በበረሐና በዋሻዎች ተስፋፋ፡፡

ከእነዚህም በምንኩስና ሕይወትና ሥርዓተ ማኅበር ወጣኒነቱ የሚታወቀው ቅዱስ እንጦንስ ነው፡፡ ከ፪፻፶-፫፻፶፮(250-356) ዓ.ም አባ እንጦንስ ***"ፍጹም ልትሆን ብትወድ ያለህን ለድሆች ሰጥተህ ተከተለኝ ይህን በማድረግህ በሰማይ መዝገብ ይኖርልሃል"*** ማቴ ፲፱÷፳፩ የሚለው ቃል ሲነበብ ሰምቶ፤ ያለውን ሁሉ ለድሆች ሰጥቶ ወደ በረሓ ወጣ፡፡ በዚያም በአንድ ዋሻ ለሠላሳ ስድስት ዓመታት ኖረ፤ አርዓያውን የተከተሉት መነኮሳት ስለበዙ በአንድነት ገዳም መሥርቶ መኖር ጀመረ፡፡ አባታችን አንድ መቶ አምስት ዓመታት በዚህች ምድር ኑሮ ፣ ብዙ ተከታዮችንም አፍርቶ ዐርፈ፡፡

**የምንኩስና መስፋፋት፡-** ብዙዎቹ የአባ እንጦንስ ተከታዮች ምንኩስናን አስፋፍተዋል፡፡ በዋናነት ታላቁ መቃርስ ገዳመ አስቄጥስን በመገደም ገዳማዊ ኑሮን ሲያስፋፋ፤ አባ ጳኩሚስ ሥርዓተ ምንኩስናን ሠርቶአል፡፡ በኋላም እነቅዱስ ባስልዮስ ገዳማትንና ገዳማዊ ኑሮን አጠናክረው የሥርዓተ ምንኩስና መጻሕፍትን አዘጋጁ፡፡ ይህም **በተለያዩ አካባቢዎች ምንኩስና እንዲስፋፋ አድርጎአል፡፡** በግብጽ በረሐዎችና በሮም ምሥራቅ ግዛት በተለይም በሶርያ የተስፋፋው ምንኩስና በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ ገባ፡፡ ምዕራባውያኑም በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ገዳማትና ገዳማዊ ሕይወትን በአካባቢዎቻቸው አስፋፉ፡፡

### 3. የትርጓሜ ትምህርት ቤቶቹ መስፋፋት

የእስክንድርያ ፣ የአንጾኪያ ፣ የቂሣርያ ፣ የኤዴሳ እና የኢትዮጵያው በአክሱም ትምህርት ቤቶች ተስፋፉ፡፡ ዓለምን የለወጡ የነገረ መለኮት ምሁራንንም አፈሩ፡፡ ይህም ክርስትና ነጻነት ማግኘቱ እና ሕጋዊ ሃይማኖት መሆኑ ያስገኘው በጎ ፍሬ ነበር፡፡ በእስክንድርያ በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን እና በአንጾኪያ በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተቋቋሙት የቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ ትምህርት ቤቶች ፤ በቀጥተኛና ምስጢራዊ የትርጉም ስልት ሲለያዩ፤ ከሁለቱም አንዳንድ መናፍቃን የወጡ ቢሆንም ሂደቱ ትምህርት ሆኖ ከሁለቱም የተመሰከረላቸው አባቶች ወጥተዋል፤ የቅዱሳን ሊቃውንት መገኛም ሆነዋል፡፡

www.zeorthodox.org

የቂሣርያው ትምህርት ቤት በ፪፻፴፪(232) ዓ.ም ገደማ የተመሠረተ፣ ታላለቅ አባቶችን ያፈራ እና ትልቅ የክርስቲያን ቤተ መጻሕፍት የነበረው ነው፡፡ ከእዚህ የወጡት ፡- ታላቁ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ፣ ሁለቱ ቅዱሳን ጎርጎርዮሶች፣ የእነ ቅዱስ ኤፍሬም የኤዴሳው ትምህርት ቤትና የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የትርጉም ስልቶችም ሁለቱን ስልቶች ያስታረቁ ነበሩ፡፡

## 4. የመንፈሳዊ ጽሑፎች መስፋፋት

የአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሌላው በረከት የመጻሕፍት በብዛት መጻፍ ነው፡፡ ክርስትና በመንግሥት እውቅና ማግኘቱን ተከትሎ በርካታ ምሁራን ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው አስተዋጽኦ አበረከቱ፡፡ ይህም ቤተ ክርስቲያን፡- ምሁራን፣ ተናጋሪዎችና በኅብረተሰቡ የተከበሩ ሰዎችንም እንድታፈራ ምክንያት ሆነ፡፡ እነርሱም ጥልቅና የተጠኑ ሥራዎችን ለቤተ ክርስቲያን አበረከቱ፡፡

የመናፍቃኑም መነሣት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርታዊ መልስ የሚሰጡ በርካታ መጻሕፍትን እንዲጽፉ አነሣሣቸው፡፡ በተጨማሪም የምንኩስና ሕይወት የጸጥታ፣ የብቸኝነትና የጸሎት ሕይወት ጥልቀት ያላቸው መጻሕፍት በአባቶች እንዲጻፉ አደረገ፡፡ በዚህ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ በርካታ መጻሕፍት ተጽፈው ነበር፡፡ ከመጻሕፍቱና ከጸሐፊዎቹም የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡-

1. **አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ፪፻፶፮-፫፻፵**(256-340 **ዓ.ም**)፡- በቂሣርያ ተወልዶ ያደገውና ክርስትናን የተማረው አውሳብዮስ በቤተ ክርስቲያን ላይ በተነሣው ስደት ወደ ፍልስጥኤም እና ግብጽ መሰደዱ እውቀት እና ልምድ ጨምሮለታል፡፡ የቂሣርያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ሲሾም በኒቂያ ጉባኤ ተግኝተው አርዮስን ከተቃወሙት አንዱ ነበር፡፡ የተለያዩ ታሪካዊ ጽሑፎችን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት ያሰኘውን እስከ ዘመኑ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሌሎችንም ጽፎአል፡፡

2. **ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ፫፻፳፱-፫፻፺** (329-390 ዓ.ም)፡- የእንዚናዙ ሊቀ ጳጳስ ከነበረው አባቱ እና ኖና ከተባለች ጠንካራ ክርስቲያን እናቱ የተወለደው እና ክስትናን የተማረው ጎርጎርዮስ በዘመኑ የነበረውን ትምህርት በፍልስጥኤም፣ በግሪክ እና በአሌክሳንድርያ ተማረ፡፡ በእንዚናዙ፣ በሳሲማ እና በቁስጥንጥንያ የተሾመ ሲሆን የታወቀበት አገልግሎቱ ግን በእንዚናንዙ ነበር፡፡ የቁስጥንጥንያ ጉባኤ እንዲካሄድ ንጉሡን ያማከረው እና ምስጢረ ሥላሴን በጉባኤው ቀድሞ ያስተማረውም እርሱ ነበር፡፡ በመጨረሻም በእንዚናዙ አገልግሎ ዐርፎአል፡፡ ጎርጎርዮስ በርካታ ጽሑፎችን ያስተላለፈ አባት ሲሆን የነገረ መለኮት አባት ያሰኙት አምስት ትምህርቶች፣ ወደ ጽሑፍ የተቀየሩ አርባ አምስት የጽሑፍ ንግግሮች፣ 245 መልእክታት፣ ከ200 በላይ ግጥሞች አበርክቶአል፡፡

www.zeorthodox.org

3. **ቅዱስ አትናቴዎስ ከ፪፻፺፭-፫፻፸፫**(295-373)**ዓ.ም**፡- ከአረማውያን ቤተሰብ የተወለደውና በልጅነቱ ክርስቲያን የሆነው ቅዱስ አትናትዮስ በወቅቱ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ከነበረው ከእለ እስክንድሮስ ተምሮ ዲቁና ተሾመ፡፡ በኒቅያ ጉባዔም አርዮስን ረታው፡፡ ከእለ እስክንድሮስ በኋላ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖአል፡፡ በአርዮሳውያን ተንኮል ብዙ ጊዜ ከመንበሩ የተሳደደና መከራ የተቀበለ አባት ነው፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ከስደት እና ከመንፈሳዊ ሓላፊነት ጋር ሆኖ በርካታ

መጻሕፍትን ጽፎልናል፡፡ እነዚህም፡- **የመሠረተ እምነት መጻሕፍት** (የአርዮስን ትምህርት የተቃወመበት ሲሆን የወልድን አምላክነት እና የአካላትን ሕልውና ያብራራባቸው አራት መጻሕፍት እና ለሰራጵየኑ ጳጳስ የክርስቶስን አምላክነትና የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ያብራራባቸው መጻሕፍት ናቸው፡፡) **የጥብቅና መጻሕፍት፡፡** (ስለ ቤተ ክርስቲያን ጥብቅና የቆመባቸው ከአሕዛብ ጣዖታት ጋር ክርስትናው እንደሚለይ እና ስለ እግዚአብሔር ቃል ሰው መሆን ያስተማረበት ለመናፍቃን ምላሽ የተሰጠባቸው መጻሕፍት ናቸው፡፡) **የተለያዩ መልእክታት፡፡** (ለፋሲካ እና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ለአባቶች የተላኩ መልእክታት) **ከትርጓሜ መጻሕፍት፡፡** (መዝሙረ ዳዊትን የተረጎመበት በዋናነት ይታወቃል) **ስለ ምንኩስና፡፡** (በቅዱስ እንጦንስ ሕይወት ተመርኩዞ ምንኩስናን የገለጠበት) መጻሕፍት ናቸው፡፡

4. **የኢየሩሳሌሙ ቄርሎስ(ከ፫፻፳-፫፻፹፮(320-386)ዓ.ም)፡-** በጥያቄና መልስ (catechesies) የተዘጋጁ ሃያ አራት ትምህርቶች ነበሩት፡፡

5. **ባስልዮስ ዘቂሣርያ (ከ ፫፻፳፱-፫፻፸፱(329-379 ዓ.ም)** ከክርስቲያን እና ባለጠጋ ቤተሰብ የተወለደውና በቂሣሪያ ሊቀ ጳጳሳት የነበረው ባስልዮስ፤ ከካህን አባቱ ከመነኩሲት አኅቱ እና ከሁለቱ ጳጳሳት ወንድሞቹ ጋር ቤተ ክርስቲያንን ያገለገለ አባት ነው፡፡ ለክህደት እና የመናፍቃን ትምህርት እውነተኛውን መልስ የሰጠ፣ የተመሰከረለት ገዳማዊ፣ የተደነቀ መምህር እና ሰባኪ ነበር፡፡ የተጣሉትን በተለይም የእስክንድርያንና የአንጾኪያን ክርስቲያኖች ለማስታረቅ የተጋ የበቃ እና የነቃ አባት እንደነበር መጻሕፍት ይመሰክሩለታል፡፡ ከጻፋቸው መጻሕፍትም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡ **የትምህርተ ሃይማኖት መጻሕፍት፡፡** እነኚህ መናፍቃንን የተቃወመባቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በሦስት መጽሐፍ ተከፍሎ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተጻፈው መጽሐፍ፤ የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ስለ መንፈስ ቅዱስ ላሳለፈው ውሳኔ መሠረት ነበር፡፡ **ስብከት እና መልእክታት፡-** ባስልዮስ እስከ ዛሬ አንደ አዲስ የሚሆኑ ሃያ አራት ስብከቶቹ በጽሑፍ ደርሰውናል፡፡ ለአባቶች (ለምሳሌ ለቅዱስ አትናቴዎስ)፤ ለምእመናን (ለምሳሌ ለኦሎምፒያ) ለአብያተ ክርስቲያናት እና ለነገሥታት የጻፋቸው የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርት፣ የሥነ ምግባር እና የጊዜውን ችግር ፈቺ ሆነው የተጻፉ (፫፻፷፮)366 መልእክታት አስተላልፎአል፡፡ እነዚህም ዘመናትን ተሻግረው ለዛሬ ደርሰዋል፡፡ ሌላው **ቅዳሴው ነው፡፡** ቅዱስ ባስልዮስ አንድ የቅዳሴ መጽሐፍ አዘጋጅቷል፡፡ **የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎችም** የስድስቱ ዕለታት ፍጥረታትን ያብራራበት የመዝሙርና የኢሳይያስ ትርጓሜዎችም ይጠቀሳሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ባስልዮስ የገዳማዊ ሕይወት መጻሕፍትን ማዘጋጀቱ በዘመኑ የተጀመረውን የምንኩስና ሥርዓት ያዳበረ ነበር፡፡ መጻሕፍቱ፡- **ገዳማውያን የሚጠበቁባቸውን ነገሮች፣ የግብረ ገብ ትምህርቶች እና የምንኩስና መመሪያ የሆኑ መጻሕፍትም** ይገኙባቸዋል፡፡ እነዚህም መነኮሳት በዕለታዊ ኑሮዋቸው የሚመሩባቸው በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት ያገኙ ትምህርቶችን የያዙ ናቸው፡፡

6. **ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ከ፫፻፮-፫፻፸፫**(306-373ዓ.ም):- ለቁጥር የሚያታክቱ መጻሕፍት፣ መልእክታትና ቅኔያዊ ዜማዎች የደረሰው ቅዱስ ኤፍሬም ***"የዓለም ዶክተር" "የመንፈስ ቅዱስ ዋሸንት" "ዓምደ ቤተ ክርስቲያን"*** የሚሉ ቅጽል ስሞችን ያገኘ ጸሐፊ ነው፡፡ የቅዱስ ኤፍሬምን መጻሕፍት እንደሚከተለው እንከፍላቸዋለን፡፡ **የትርጓሜ መጻሕፍት** (የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ያብራራበት ነው፡፡) **ለመሠረተ እምነት ክርክሮች** (Dogmatico polemica) **በመልስ መልክ የተጻፉ መጻሕፍት፡፡** (ቅዱስ ኤፍሬም በዘመኑ ለነበሩ የስሕተት ትምህርቶች:- ማሪያውያን፣ መርቅያን ለመሳሰሉት መልስ የሰጠባቸው ናቸው፡፡) **መዝሙራት፡፡** (ስለ እምነት፣ የድንግልና ሕይወት ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ስቅለትና ትንሣኤ ክርስቶስ፣ ውዳሴ ማርያምና የመሳሰሉት… ናቸው፡፡) **ስብከቶች፡፡** በተለያዩ ርእሶች የሰበካቸው ገናና ትምህርቶችም አሉት፡፡

7. **ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ፫፻፴፭-፫፻፺፭**(335-395) **ዓ.ም፡-** የባስልዮስ ዘቂሣርያ ታናሽ ወንድም ሲሆን፤ በዘመኑ የነበረውን ትምህርት የተማረ እና በጥልቅ ዕውቀቱ የሚደነቅም ተናጋሪ ነበር፡፡ አግብቶ ሚስቱ ወዲያው ስለ ሞተችበት ፣ በንጽሕና ኖሮ ክህነት ተቀብሎአል፡፡ በኋላም የኑሲስ ጳጳስ ሆኖ በ፫፻፸፩(371)ዓ.ም ተሾመ፡፡ አርቶዶክሳውያን በአርዩሳውያን ሲሣደዱ ከ፫፻፸፭-፫፻፸፱(375-379) ከመንበሩ በአርዩሳዊው ንጉሥ ቫሌንሲ ተሰዶ የመከራውን ዘመን በገዳም አሣለፈ፡፡ በቁስጥንጥንያው ጉባኤ ፫፻፹፩(381)ዓ.ም ከተገኙት አባቶች አንዱ ሲሆን በ፫፻፺፬(፭)394(5)ዓ.ም ከዚህ ዓለም ዐርፎዋል፡፡ እንደ ሊቅነቱና አባትነቱ በርካታ መጻሕፍት አስተላልፎልናል:- **ፍካሬ መጻሕፍት፡-** (የሙሴን ሕይወት መሠረት አድርጎ ስለ መንፈሳዊነት፤ ፩ኛ እና ፪ኛ ነገሥትን ፤ መዝሙረ ዳዊትን ፣ መክብብን እና መኃልየ መኃልይንም ተርጉሞልናል፡፡) **በመሠረተ እምነት መጻሕፍቱ፡፡** መንፈስ ቅዱስ ላይ የተነሣውን ኑፋቄ የተቃወመባቸው ዐሥራ ሁለት መጻሕፍት፣ ስለ ምስጢረ ሥላሴ፣ ሥጋዌ እና ሌሎችንም የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ሲያብራራ ከመናፍቃን፣ ከአይሁድ እና ከጣዖት አምልኮ ጋር አነፃፅሮ አብራርቶዋል፡፡ ከታላቅ እኅቱ ማክሪና ጋር በወንድማቸው በባስልዮስ ሞት ምክንያት የተነጋገሩትን ተመርኩዞ ስለ ሞት እና ትንሣኤ ያስተማረበት መጽሐፍም ከታዋቂ ሥራዎቹ መካከል ይጠቀስለታል፡፡ **ስለገዳማዊ ሕይወት** ሲጽፍ የድንግልና ሕይወትን ክብር አስተምሮበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም **የተለያዩ ጉዳዩች የተነሡበት** መጽሐፍ የግብረ ገብ፣ የመሠረተ እምነት እና የቅዱሳንንና የሰማዕታትን ክብር የያዘ ነው፡፡ በተለያዩ ክርክሮች ላይ ተመሥርቶ የጻፋቸው ሃያ ዘጠኝ መልእክታትም ደርሰውናል፡፡

www.zeorthodox.org

**ማጠቃለያ፡-** አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ብዙ ውጣ ውረዶችን መልካምና አሳዛኝ ክሥተቶችን የታዩበት ለቀጣዩ የቤተ ክርስቲያን ጉዞ ጠቃሚ ማንተም ትቶ ያለፈ ዘመን ነው፡፡ ሂደቶችን ጠቅልለን ስናስቀምጣቸውም:-

1. ቤተ ክርስቲያን የአምልኮት ነጻነትዋን በ፫፻፲፫(313) ዓ.ም የመንግሥት ሃይማኖትነትን በ፫፻፹፯(387) ዓ.ም በዐዋጅ አገኘች ፡፡
2. ከጵርስቅላውያን፣ ከዶናቲስቶችና ከአርዮሳውያን የተነሣው የሃይማኖት እና የሐሳብ ልዩነቶች የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች ነበሩ፡፡
3. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከሚታወቁት ሦስት ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ሁለቱ (የኒቅያ በ፫፻፳፭ (325) ዓ.ም እና የቁስጥንጥንያ በ፫፻፹፩(381) ዓ.ም) ተካሂደዋል፡፡
4. የምንኩስናና ብሕትውና ገዳማዊ ኑሮ በግብጽ ተጀምሮ የተስፋፋው በዚህ ክፍለ ዘመን ነበር፡፡
5. በቤተ ክርስቲያን አባቶች እና በቅዱሳን በሺሕ የሚቆጠሩ በርካታ መጻሕፍትም በዚህ ዘመን ተጽፈዋል፡፡

## ተግባር፡-

1. ከመጻሕፍት፣ ከድረ ገጽ እና መምህራንን በመጠየቅ ከላይ ካየናቸው አባቶች የአንዱን ትምህርት መርጣችሁ በጽሑፍ አብራሩ፡፡
2. የአባቶችን ሕይወት አርዓያ በማድረግ ክርስቶስን ለመምሰል ተለማመዱ፡፡

## *ጥያቄዎች፡-*

1. በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያን በገጠማት የውስጥ ፈተናዎች አስደናቂ በረከቶችን (መልካም ውጤቶችን) እንዳስገኙላት ተምራችኋል፡፡ እነዚህ መልካም ውጤቶች የተባሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች አራቱን በዝርዝር በመጥቀስ አብራሩ፡፡
2. መምህር ተማሪዎችን በሰባት ቡድን በመክፈል፤ ከዚህ በታች በዝርዝር የተጠቀሱትን ታላላቅ አባቶች (ለእየአንዳንድ ቡድን አንድ አባት) ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎቹ ስለተሰጣቸው አባት መምህራንን ጠይቀው፤ መጻሕፍትን አንብበው ታሪካቸውን፣ አገልግሎታቸውንና ጽሑፎቻቸውን ጽፈው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

   ሀ. አውሳብዮስ ዘቂሣርያ

   ለ. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ

   ሐ. ቅዱስ አትናቴዎስ

   መ. የኢየሩሳሌሙ ቁርሎስ

   ሠ. ባስልዮስ ዘቂሣርያ

   ረ. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ

   ሰ. ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ

www.zeorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከአምስተኛው እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (አራት)

## ዐሥራ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ቤተ ክርስቲያን መከፋፈል እና ውጤቱን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች አብራርተው ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠኑ ጥቅሶች፡-**

- *"እርስ በእርሳችሁ ብትነካከሱ እርስ በእርሳችሁ እንዳትጠፋፉ"* .
- *" ጌታ ሆይ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ አሉት፡፡ እርሱም ጠላት ይህን አደረገ አላቸው፡፡"* ማቴ.፲፫ ፥፳፯-፳፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ›› ፤ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (1978 ዓ.ም)

**መግቢያ፡-** ባለፉት ተከታታይ ክፍሎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተምረናል፡፡ ያለፉትን ሳምንታት ትምህርታችንን መሠረት በማድረግ ከአራተኛው እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደማጠቃለያ በዛሬው ትምህርታችን እናያለን፡፡

### ዋናው የትምህርቱ ይዘት፡-

እነኚህ ሁለት መቶ ዓመታት የአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቀጣይ ታሪኮች ይመስላሉ፡፡ በእነኚህ ሁለት ክፍለ ዘመናት ታላላቅ አባቶችና የሚከተሉት ዋና ዋና ታሪካዊ ክሥተቶች አልፈዋል፡፡

www.zeorthodox.org

**ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (፫፻፵፯-፬፻፯(347- 407) ዓ.ም)፡-** በእናቱ ጠንካራ እምነት ተኮትኩቶ ፣ በዕውቀት ታንፆ ያደገው አንደበተ ርቱዕ ቅዱስ ዮሐንስ ብዙዎችን የለወጡና ዘመናት ተሻግረው የሄዱ ትምህርቶችን፤ በቃል ሰብኮ፣ በጽሑፍ ከትቦ ያስተላላፈልን ታላቅ አባት ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች፣ በተለያዩ ርእሶች ያስተማራቸው ትምህርቶች፣ የምንኩስናን አስፈላጊነት አስመልክቶ የጻፋቸው መጻሕፍት፣ ለመናፍቃንና ለአጽራረ ቤተ ክርስቲያን መለስ የሰጠባቸው ከ238

በላይ መልእክታትን ጽፎአል፡፡ ዝርዝሩን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሚለው የትምህርት ርእስ ተመልከቱ፡፡

**አባ ጀሮም (ከ፫፻፵፯-፬፻፳(347-420) ዓ.ም)፡-** በድልማጥያ አካባቢ የተወለደውና በሮሜ የነበሩትን ትምህርቶች ያጠናው ጀሮም፤ በ፫፻፷፮(366) ዓ.ም ገደማ ተጠመቀ፡፡ ከአቂላ ክርስትናን ሲማር የብሕትውናን ኑሮ ያዘወትር ነበር፡፡ ወደ ሶርያዋ አንፆኪያ ሄዶ የእብራይስጥ እና ግሪክ ቋንቋን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንም በጥልቀት አጠና፡፡ በሶርያ በረሐዎች እና በቤተልሔም በብሕትውና ተጋድሎ በመኖር ገዳም ገድሞአል፡፡ በእውነተኛ ንስሓ ኖሮ ቤተ ክርስቲያንን ያገለገለ ሲሆን በርካታ መጻሕፍትን ጽፎ አስተላልፎአል፡፡ ከእነዚህም በስፋት የሚታወቅበት የትርጉም ሥራው ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ከዕብራይስጥና ከግሪክ ወደ ጥንቱ ላቲን ተርጉሞአል፡፡ የሌሎችን ትንታኔዎችንም ወደ ላቲን መልሶዋል፡፡ ራሱም የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችና ትንታኔዎችን አዘጋጅቶአል፡፡ የመሠረተ እምነት፣ ስለ ምንኩስናና ለሃይማኖታዊ ክርክሮች የተሰጡ መልሶችን የያዙ የምክር መጻሕፍትም አዘጋጅቶ አስተላልፎአል፡፡

**ቅዱስ ቄርሎስ (ከ፫፻፸፭-፬፻፵፬(375–444) ዓ.ም)፡-** አጐቱን ፓትርያርክ ቴዎፍሎስን ተከትሎ፤ የእስክንድርያ ፖትርያርክ የሆነው ቅዱስ ቄርሎስ በጥልቅ ዕውቀቱና በትምህርቶቹ የሚታወቅ አባት ነው፡፡ በኤፌሶን ጉባኤ የተወገዘውን የንስጥሮስ የክህደት ትምህርት ቀድሞ በመረዳት እና በመቃወም የኦርቶዶክሳዊት እምነት ጠበቃ በመሆን ብዙ ተጋድሎ አድርጎአል፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በወቅቱ ሁኔታ መነሻነትና በአባትነቱ ካዛጋጃቸው በርካታ መጻሕፍት፡- **ለቤተ ክርስቲያን ጥብቅና የቆመባቸው መጻሕፍት፡-** ለጁልያን ጸረ ቤተ ክርስቲያን ሦስት መጻሕፍት መልስ የሆኑ ሠላሳ መጻሕፍትን አዘጋጅቶልናል፡፡ **ትርጓሜ መጻሕፍት፡-** አብዛኛዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአሌክሳንድርያ ትምህርት ቤት የትርጉም መንገድ ተርጉሞአቸዋል፡፡ ሌላው **ለዶግማዊ ክርክሮች** ፡- በቅድስት ሥላሴ ፤ በክርስቶስ ባሕርይ (ሁለት አካል፣ሁለት ባሕርይ ለሚለው የንስጥሮስ ኑፋቄ) ፣ በእመቤታችን የአምላክ እናትነት ላይ ለሚነሡ ክርክሮች መልስ የሰጠባቸው መጻሕፍት አሉ፡፡ **መልእክታት** እና **ስብከቶቹም** በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የተጻፉ ናቸው፡፡

1. **ጉባኤ ኤፌሶን (፬፻፴፩(431)ዓ.ም)፡-** ንስጥሮስ የተባለ የአንፆኪያ ሊቀ ጳጳስ፤ ‹‹ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ሁለት አካል አለው፡፡ ድንግል ማርያም የወለደችው ሰው ነው፤ አምላክ አይደለም›› ብሎ በማስተማሩ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ እመቤታችን የወለደችው አምላክ የአምላክ ልጅ ነው፣ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኗል ብሎ መለሰ፤ በመጨረሻም በኤፌሶን ጉባኤ ተደርጐ ንስጥሮስ ተወገዘ፡፡

www.zoorthodox.org

2. **ጉባኤ ኬልቄዶን (፬፻፶፩(451)ዓ.ም)፡-** ፖፕ ልዩን ከሁሉም (በወቅቱ ከነበሩት የኢየሩሳሌም ፣ የእስክንድርያ ፣ የአንፆኪያ፣ የቁስጥንጥንያ እና የቂሣርያ መናብርት ) የሮም መንበር ይበልጣል፤ ብሎ ለማጸደቅ እና ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ አንድ አካል ነው፤ የሚል አዲስ የሃይማኖት ውሳኔ ሐሳብ

ይዞ አስነበበ። የእስክንድርያው ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ሁለት አካል ካልን ሁለት ባሕርይ እንላለን እንጂ አንድ ባሕርይ አንልም። ነገር ግን ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኖ በተዋሕዶ የከበረ ነው አለ። ይህንንም በመጽሐፍ እና በምክንያትያዊ አቀራረብ አስረዳ ። የሮም መንበርም የምትበልጥበት ምክንያት እንደሌለም አስረዳ። ነገር ግን በስብሰባው የነበሩት የሮም ወታደሮች ቅዱስ ዲዮስቆሮስንና በእምነት የሚመስሉትን እየደበደቡ ከስብሳበው አውጥተው አሰሩዋቸው - የራሳቸውን የሃይማኖት ውሳኔም አሳልፈው ትምህርታቸው በአግባበቡ ሳይሰማ የወጡትን አወገዙዋቸው። የሶርያ፣ ሕንድ፣ አርመንያ፣ ግብጽ እና የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችም በተዋሕዶ ሲጸኑ፤ ሮም እና ተከታዮችዋ ካቶሊክ (የሁሉም) የሚል ስያሜ ለራሳቸው በመስጠት ክርስቶስንም ሁለት ባሕርይ በማለታቸው ቤተ ክርስቲያንን ከፈልዋት።

ከዚያም ካቶሊካዉያኑ በተዋሕዶ እምነት የጸኑትን ኦርቶዶክሳውያን የሮምን ጦር በማዝመት አሳደዋቸዋል። ዲዮስቆሮስ ጢሙ ተነጭቶ ፣ ጥርሱ ተሰብሮ በእስር ዐረፈ። በሶሪያ እና በአካባቢዋ የነበሩ ኦርቶዶክሳውያንም ከከተማ ወደ ገዳም ቢሸሹም ከዚያም እያሳደዱዋቸው በመከራ ኖሩ። አባቶችም በኬልቄዶናውያኑ ከመንበራቸው ተባረዋል፣ ታስረዋል፣ ተገድለዋልም። ለምሳሌ ማክሲሞ ሁለተኛ ፬፻፵፱-፬፻፶፭(449-455) ዓ.ም የተባሉት የአንፆኪያ ፓትርያርክ በእስር ተጥለው ባሲል እና አቃክ የተባሉ ኬልቄዶናውያን ፬፻፶፮-፬፻፶፱(456-459)ዓ.ም ተተኩ። ለጥቅት ዓመታት ኦርቶዶክሳዉያን በመንበራቸው ከተተኩ በኋላ ፓትርያርክ ቅዱስ ሰቨረስን አስረው፣ ከ፭፻፲፰-፭፻፵፮(518-546) ዓ.ም ካቶሊካዊ ጳጳሳትን ሾመውባቸው ነበር። ይህ ግፍ በአጠቃላይ ክርስትናን ያዳከምና አረማዉያን ከጥንቱዋ ፐርሺያና ከደቡባዊ ዐረቢያ ተነሥተው ክርስትናን እንዲያጠፉ በር የከፈተ ነበር። በተለይም ለእስልምና ምቹ በር የከፈተ ስሕተት ነበርና ክርስትና በመካከለኛው ምሥራቅ ተዳከመ።

**ዘጠኙ ቅዱሳንም በዚህ ስደት ነው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት**። ከላይ ከገለጥነው በተቃራኒ ይህ ሂደት ያነሣው ስደት በእንግዳ ተቀባይዋ ኢትዮጵያ መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ሆነ። ይህም ዘጠኙ ቅዱሳን በተዋሕዶ እምነታቸው ምክንያት ከቢዛንታይን ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የቅዱስ ጳኩሚስን ሥርዓተ ምኩስና አስፋፉ። በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹን ገዳማት ደብረ ዳሞን፣ እንዳ አባ ገሪማ፣ ጳንጠሌዎን ገዳም ወ.ዘ.ተ… ገደሙ። በአባ ሰላማ የተጀመረውን ሓዋርያዊ ተልእኮና የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም አስፋፉ።

በዚህ ወቅት እግዚአብሔር ቅዱስ ያሬድን ፭፻፭-፭፻፸(505-570)ዓ.ም አስነሥቶ ሰማያዊውን ዜማ ገልጦለት፣ ቅዱሳት መጻሐፍትን እንዲደርስም አድርጎታል። ድጓ፣ ዝማሬ መዋሥዕት፣ ምዕራፍ እና አንቀጸ ብርሃን የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ናቸው። በሌሎች ለተዘጋጁት የቅዳሴ መጻሕፍት እና ለውዳሴ ማርያምም ዜማ አዘጋጅቶአል።

www.zeorthodox.org

ዐፄ ካሌብ በዛሬዋ የመን በጥንቷ ናግራን የነበሩ ክርስቲያኖች በግፍ በመገደላቸው ዘምቶ ነጻ አወጣቸው። ከዚያም በኋላ ወደ መንበረ መንግሥቱ አክሱም ሲመለስ ዘውዱን ወደ ኢየሩሳሌም የጌታ መቃብር ልኮ እርሱ በምናኔ ለመኖር ከቤተ መንግሥቱ ወደ አባ ጰንጠሌዎን ገዳም የገባው

በዚህ ዘመን ነበር። የዐፄ ካሌብ ተከታይ ዐፄ ገብረ መስቀል በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን አንፀዋል። ዘጠኙ ቅዱሳን ወንጌልን አስፋፉ። ቅዱስ ያሬድም ቤተ ክርስቲያንን በሰማያዊ ዜማ አስዋባት። ይህም ክርስትና በሕይወት የሚገለጥ እምነት እና ኑሮ እንዲሆን አስቻለ።

## ምን ተማርን?

1. የቤተ ክርስቲያንን መከፋፈል ምንጩ የሥልጣን የበላይነት እና የተሳሳተ መሠረተ እምነት (ኑፋቄ) ነበር።
2. ሃይማኖትን በማስተዋል ካልያዝነው ጠላታችን ክፉ ፈተና እና ውድቀትን ያመጣብናል። የመናፍቃኑ ችግር ይኸው ነበር።
3. መጽሐፍ ***" እንግዶችን መቀበልን አትርሱ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና።"*** ዕብ.፲፫፥፪ እንዳለ፤ አባቶቻችን እንግዳ ተቀባዮች ስለ ነበሩ የቅዱሳኑን በረከት መቀበል ችለዋል። እናንተም ቅዱሳንን ማክበር እና እንግዶችን መቀበልን አትርሱ ።

### *ጥያቄዎች:-*

1. መምህር ለተማሪዎችዎ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅዱሳን አባቶች፣ ማንነት እና ለቤተክርስቲያን የሠሩትን ታላቅ ሥራ፣ ትምህርትና ጽሑፎቻቸውን በአጠቃላይ ታሪካቸውን ጽፈው እንዲያቀርቡ ያድርጉአቸው።
   *ሀ. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ*
   *ለ. አባ ጀሮም*
   *ሐ. ቅዱስ ቄርሎስ*
2. ጉባኤ ኤፌሶን መቼ እና የት ተካሔደ? ጉባኤው የተካሔደበት ምክንያት ምን ነበር? በጉባኤው መጨረሻ ስለተወሰነው ውሳኔ እና ውግዘት አብራሩ።
3. የኬልቄዶን ጉባኤ ምክንያቱ ምን ነበር? ውጤቱስ? በዝርዝር ግለጹ።
4. ወደ ኢትዮጵያ በስደት የገቡት ቅዱሳን ስንት ናቸው? እነማን ይባላሉ? ከፈጸሙት ተግባራት ዋና ዋናዎቹን ግለጹ?
5. ቅዱስ ያሬድ የኖረበት ዘመን መቼ ነበር? ለቤተክርስቲያን ምን ሠርቶአል?
6. ዐፄ ካሌብ ማን ነበር? ምን አደረገ? መጨረሻው ምን ሆነ?

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከ፲፯ኛው-፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን(አንድ)

## ዐሥራ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡- ተማሪዎች ከ፲ኛው እስከ ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ በተለይ ደግሞ ከ፲፯ኛው እስከ ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ።

**የሚጠኑ ጥቅሶች**፡-*"ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።"* ሮሜ.፲፪÷፲፰ *" በብርቱ ይፈልጉአችኋል ለመልካም አይደለም ነገር ግን በብርቱ ትፈልጉአቸው ዘንድ በውጭ ሊአስቀሩአችሁ ይወዳሉ።"* ገላ.፮÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ 1974 ዓ.ም፤ ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም፤ገጽ.18-22

**መግቢያ፡-** ከ፲፯ኛው - ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በጎና ክፉ የሚባሉ ክሥተቶች አልፈዋል። በዛሬው ትምህርታችን ከእነዚህ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍሎች መሠረታዊዎቹን እንመለከታለን።

**የሳምንቱ ትምህርት**፡- አባቶቻችን ሐዋርያት ከእስራኤል ወደ አሕዛብ ባደረጉት ስብከተ ወንጌል የመጀመሪያው ተሰባኪና አማኝ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። የሐ.ሥ ፰÷፳፯ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስትና በኢትዮጵያ የተሰበከ ሲሆን በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአቡነ ሰላማ ክህነት እና ምስጢራትን መፈጸም ተጀመረ። ክርስትናም ከ፫፻፶(350) ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕጋዊ እና ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነ።

www.zeorthodox.org

ምንኩስናና ገዳማዊ ሕይወት በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተሰዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ተስፋፋ። በዚህም ገዳማቱ የትምህርት፣ የመንፈሳዊ ልምምድ እና የተልእኮ ማዕከላት እንዲሆኑ አስቻለ። ደብረ ዳሞ ፣ እንዳ አባ ገሪማ ፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

በስጦታው ባለጠጋ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ለቅዱስ ያሬድ ተገልጦ ለቤተ ክርስቲያን

የሰጣት ሰማያዊው ዜማ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርሰቶቹም በዚህ ዘመን የተገኙ የቤተ ክርስቲያን መብራቶች ናቸው፡፡

የእስልምና ከደቡብ ዐረቢያ ተነሥቶ መስፋፋት፣ የእርስ በርስ ጦርነት እና የዩዲት የጥፋት እጆች የቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች ነበሩ፡፡

ከ፲ኛው እስከ ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የዛግዌ መንግሥት አብያተ ክርስቲያናት በማነፅ ለክርስትና መጠንከር ጉልህ ሚና ተጫውቶአል፡፡ በሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት ከ፲፪፻፸ (1270) ጀምሮ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ሲሦ መንግሥት፣ በኢትዮጵያውያን አበው የተደረጉ ሐዋርያዊ ተልእኮዎች ፣ የመጻሕፍት መጻፍ እና መተርጐም ክርስትናን መልሶ አጠናከረ፡፡

በ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እነ አባ ጊዮርጊስን የመሰሉ ቅዱሳን ሊቃውንት በርካታ ድርሰቶችን በመድረስ መጻሕፍት እንዲጻፉ፣ እንዲተረጎሙ አድርገዋል፡፡ ይህ ዘመን ስብከተ ወንጌል በመላ ኢትዮጵያ የተደረሰበት፤ ገዳማዊ ሕይወት የተጠናከረበት፣ መንፈሳውያን መጻሕፍት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጎመበት፣ በሀገሪቱ ታላላቅ ሊቃውንት ብዙ የቤተክርስቲያን መጻሕፍት የተጻፉበት ዘመን ነበር፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ታንፀዋል፣ በውጭ በነበረው መልካም ግንኙነት ነገሥታቱ ዐፄ ዳዊት በኋላም ዘርዓ ያዕቆብ የጌታችንን መስቀል እና ንዋያተ ቅድሳት ወደ ሀገራችን አስገብተዋል፡፡

በሌላ በኩል ለቃለ ወንጌል መስፋፋት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲከበር የተጋደሉ አባቶች አባ ኤዎስጣቴዎስ፣ አባ አሮንና ተከታዮቻቸው፣ እነ አባ ፊልጶስ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መሪ የመንፈስ ቅዱስ በረከቶች ነበሩ፡፡ በዚህ ክፍለ ዘመን ማጠቃለያ ላይ የነበሩት ዐፄ ናዖድ ከስምንተኛው ሺሕ አታድርሰኝ እያሉ ኖረው ነሐሴ ፯ ቀን ፲፭፻ ዓ.ም ዐረፉ፡፡

በዚህ መንገድ ለስምንተኛው ሺሕ መባቻ የደረሰው የኢትዮጵያ ክርስትና ጉዞ እንዴት ነበረ፡፡ የሚለውን የቀጣይ አምስት መቶ ዓመታት ታሪክ በተከታታይ ሳምንታት እንመለከታለን፡፡ ይህን ዘመን ለማጥናት እንዲመቸንም እንደሚከተለው ከፍለን እናጠናዋለን፡-

1) *ከ፲፭፻-፲፮፻፳፫(1500 -1623) ዓ.ም ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት*
2) *ከ፲፮፻፳፫-፲፯፻፸፩(1623 -1771) ዓ.ም ኢትዮጵያ በብቸኝነት የኖረችበት ዘመን፡፡*
3) *ከ፲፯፻፸፩-፲፰፻፵፭(1771 -1845) ዓ.ም ዘመነ መሳፍንት ፡፡*
4) *ከ፲፰፻፵፭-፲፱፻፷፮(1845-1966) ዓ.ም በዘመናዊት ኢትዮጵያ የነበረው የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ፡፡*
5) *ከ፲፱፻፷፮(1966)-አሁን - ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የመንግሥት ሃይማኖት መሆኗ ቀረ፡፡*

www.zeorthodox.org

## 1) ከ፲፭፻-፲፮፻፳፫1500 -1623) ዓ.ም ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት

**ዐፄ ልብነ ድንግል፡፡**(ከ፲፭፻-፲፭፻፴(1500-1530 ዓ.ም) ብዙ ቋንቋዎችን ከሚያውቅ ሊቅ ዘንድ የተማሩ ናቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሙያም ነበራቸው፡፡ መንፈሳዊ መጻሕፍትንም የደረሱ፣ በአንድ

ሚስት የታመኑና በሥርዓት የኖሩ ንጉሥ ስለነበሩ ቤተ ክርስቲያን መስከረም ፳ ቀን ታስባቸዋለች፡፡ በዘመናቸው ቤተ ክርስቲያን በጎ እና ክፉ የሚባል አሳዛኝ ታሪካዊ ክሥተቶችን አሳልፋለች፡፡ እነዚህንም ከዚህ ቀጥሎ እናያቸዋለን፡፡

*1. የቅዱሳት መጻሕፍት ዝግጅት፡-* በዚህ ዘመን ከውጭ የተተረጎሙ እና በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተጻፉ በርካታ መጻሕፍት አሉ፡፡ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የዕብራውያን ትርጓሜ (ተግሣጽ ዘዮሐንስ አፈወርቅ) ፣ ገድለ ጊዮርጊስ፣ አረጋዊ መንፈንሳዊ፣ መጽሐፈ ሐዊ) የ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትርጉሞች ናቸው፡፡ በሰዓታት የሚባሉት ለኖኅ ሐመሩ ፣ ተፈስሒ ማርያም ፣ ስብሐተ ፍቁር ዘእግዝእትነ (በዐፄ ልብነ ድንግል) ሲደረሱ፤ ገድለ ተክለ ሃይማኖትም በዚህ ወቅት ተጽፎአል፡፡

*2. የአብያተ ክርስቲያናት ግንባታ፡-* በዚህ ዘመን በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ታንፀዋል፡፡

3. *ታላቁ የቤተ ክርስቲያን መከራ፡- (ከ፲፭፻፳፯-፲፭፻፵፪(1527-1542) ዓ.ም)* በቱርክ እና በሞንጉላውያን ሙስሊሞች እርዳታ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ የተነሣው ግራኝ አህመድ (ይማም አህመድ ቤን ኢብራሂም ኤልቃዜ) ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ጋር ጦርነት አድርጎ ድል ሲቀናው፡- በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ ንዋያተ ቅድሳትንና ትምህርት ቤቶችን አቃጠለ፡፡ አክሱም ጽዮን ማርያም፣ ደብረ ሊባኖስ፣ እግዚአብሔር አብ፣ አርባዕቱ አንሰሳ ወ.ዘ.ተ ሌሎችም በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በውስጣቸው ካሉት ቅዱሳት መጻሕፍትና ንዋያተ ቅድሳት ጋር ተቃጥለዋል፡፡ ከትምህርት ቤቶችም የሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርት ቤት ይገኝበታል፡፡ በዚህ የመከራ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ፡-

1. ተሰደዱ፡፡ የተወሰኑት በዋሻ እና በዱር ሲሰደዱ፤ ካህናቱም ንዋያተ ቅዱሳቱንና ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዘው ስለተሰደዱ ዛሬ በቦረዳ ዋሻ ፣ በየረር ሥላሴ እና በመሳሰሉት የተገኙት ነዋያተ ቅድሳት ምሥክሮች ናቸው፡፡
2. በሰማዕትነት ዐረፉ፡፡ በቀያቸው፣ በየአድባራቱና በየገዳማቱ የቀሩት ክርስቲያኖች ሃይማኖታችንን አንቀይርም በማለታቸው እና አብያተ አምልኮታቸው ሲቃጠሉ በመቃወማቸው ግራኝ መሐመድ እና በወታደሮቹ ሰይፍ እና እሳት ብዙዎቹ በሰማዕትነት ዐረፉ፡፡
3. ሃይማኖታቸውን በግድ ቀየሩ፡፡ ሁሉም አይጸናምና መሰደድ ያልቻሉና መጽናት ያቃታቸው ክርስቲያኖች ማተባቸውን በጥሰው ፣ ስማቸውን ቀይረው ካዱ፡፡

www.zeorthodox.org

*ለዐሥራ አምስት ዓመታት የቆየው ጦርነት ማብቃቱን ተከትሎ በክርስቲያኖች ዘንድ ፡-*

1. ኢ ክርስቲያናዊ ምግባራት ተበራከቱ ፡- ብዙ ማግባት፣ ቁባት ማስቀመጥ፣ ጥንቆላና አምልኮ ባዕድን እየቀላቀሉ መፈጸም ተጀመረ፡፡

2. **የቤተ ክህነት የሙያ ደረጃ ዝቅ አለ** ፡- በካህናት ስደት እና ሞት ምክንያት የቤተ መቅደሱን አገልግሎት ለመሸፈን ሲባል ብቻ በትምህርት እና በሕይወት ልምምድ ያልበሰሉ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛው መዐርገ ክህነት ተሾሙ፡፡
3. **የታሪክ ክፍተት ተፈጠረ**፡- በጦርነቱ ከወደሙት ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት እና መጻሕፍት ጋር በርካታ መረጃዎች ወደሙ፡፡ በዚህ ምክንያትም የነገረ ሃይማኖትና ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን ታሪኮች ተዛብተው ለዛሬ ስለደረሱ እውነታው ከአፈ ታሪኩ ሊለይ አልቻለም፡፡ ክርስቲያናዊ ስያሜ ያላቸው ቦታዎች ተቀይረው በሌላ መጠራት ጀመሩ፡፡
4. **ክርስቲያናዊ ግንኙነቶች ተቋረጡ**፡- በደረሰው ጥፋት ክርስቲያን የነበሩ አካባቢዎችና ሕዝቦች መገናኘት ስላልቻሉ፤ በካህናትና አገልጋይ እጥረት በአንዳንዱ አካባቢ ክርስትና ወደ ተረት እና ባህል ተቀይሮ ሲከስም፤ ሌሎቹም ሰለሙ፡፡ ኦርቶዶክሳዊ ሳይሆኑ መስቀልና ጥምቀት የሚያከብሩ ሕዝቦች በዙ፡፡

## የጦርነቱ ፍጻሜ

ዐፄ ልብነ ድንግል በተለያዩ ቦታዎች እየተዋጉና እየሸሹ ቆይተው በመጨረሻ በደብረ ዳሞ ገዳም ሠፈሩ፡፡ በዚያም በዘመኑ ኃያላን ከነበሩት የካቶሊክ ክርስቲያን መንግሥታት ከአንዱና ከዋናው ከፓርቱጋላውያን ጋር በመጻጻፍ እርዳታ ጠየቁ፡፡ የፓርቱጋል ጦር ሲደርስ ልብነ ድንግል በደብረ ዳሞ ሞተው፤ ልጃቸው ዐፄ ገላውድዮስ ተተክቶ ነበር፡፡ በፓርቱጋሎች እገዛ ጦርነቱ ቀጥሎ ግራኝ አህመድ በሽንብራ ኩሬ ሞተ፡፡ ሠራዊቱም በሂደት ተሸነፈ፡፡ የተረፈውም በምሥራቃዊ የሀገሪቱ ክፍል ተቀመጠ፡፡

በተገኘው ጥቂት እፎይታ አብያተ ክርስቲያናትን ማደስ ፣ ክርስቲያኖችን ማጽናናት ተጀመረ፡፡ አቡነ ዕንባቆም የተባሉት የደብረ ሊባኖስ እጨጌ መጽሐፈ ቀደር የተባለውን መጽሐፍ አዘጋጅተው ፈርቶ የሰለመውን የንስሓ ጥምቀት እያጠመቁ መለሱት፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ታነፁ፤ የተሰደዱት ተመለሱ፡፡

ፖርቱጋላዊ የካቶሊክ ቄስ ቤርሙዴዝ መሬት ተቆርሶ ለፖርቱጋል እንዲሰጥና ኦርቶዶክሳውያን ካቶሊካውያን እንዲሆኑ ጠየቀ፡፡ ወጣቱ ንጉሥ ገላውድዮስም ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋር ተማክሮ እምነቱን አሳወቀ፡፡ ይህም እስከ አሁን የገላውድዮስ የሃይማኖት መግለጫ (Gelawdeows Confession) የሚባለው የታሪክ ሰነድ ሲሆን ÷ የኦርቶዶክሳውያን ሙሉ መሠረተ እምነት መግለጫም ነው፡፡ ይህ እንዳልተሳካላቸው የተረዱት ካቶሊካውያን በቫቲካን የኢትዮጵያ ኮሌጅ ከፍተው የሕዝቡን ቋንቋና ባህል አጥንተው ወደ ኢትዮጵያ የሚሰማሩ ምሁራንን ማሠልጠን ጀመሩ፡፡

www.zeorthodox.org

ዐፄ ገላውድዮስም በግራኝ ሚስት ድል ወንበርዋ ትእዛዝ አፈግፍጎ ከነበረበት እንደገና የመጣውን የግራኝ ተከታዮች ጦር ለመግጠም በአርብ ስቅለት ባደረጉት የመጨረሻ ጦርነት ድል አድርገው በመጨረሻ ተገደሉ፡፡ ተከታዮቻቸው ዐፄ ሚናስ እና አፄ ሠርፀ ድንግል ሀገር በማረጋጋት ሥራና ግዛት በማስጠበቅ ተጠመዱ፡

ከዐፄ ገላውድዮስ በኋላ ካቶሊካውያን ***"ኢየሱሳውያን"*** በሚል የቡድን ስያሜ ወደ ሀገሪቱ ገቡ፡፡ ከእነዚህም በሁለተኛው ዙር መሪ የነበረው ጴጥሮስ ፖኤዝ አማካኝነት ከፍተኛ ሁከት ተከሥቷል፡፡

***የካቶሊካውያን ሁከት፡-*** በፖኤዝ የሚመራው የ ***"ኢየሱሳውያን"*** ቡድን ፥ ንጉሥ ዐፄ ሱስንዮስ ይመኙት የነበረውን ኢትዮጵያን የማሠልጠን ሐሳብ ተጠቅሞ፤ ካቶሊካውያን ቢሆኑ እንደሚሳካ አግባብቶ አሳመናቸው፡፡ እርሳቸውም ሥዕላት በቅርጾች፣ ረቡዕ እና ዐርብ ጾም በማክሰኞ እና ሐሙስ እንዲተኩ፤ ካህናቱ እንደገና እንዲካኑ፣ አብያተ ክርስቲያናቱም በድጋሚ እንደ ካቶሊካውያን እንዲባረኩ፣ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ በሮማ ካቶሊኩ እንዲቀየሩ፣ የተዋሕዶ እምነትም በካቶሊካዊነት እንዲተካ ዐወጁ፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ተቃወሙ፡፡ በሂደቱም ከ 8,000 በላይ ክርስቲያኖች ደም ፈስሶ፣ ንጉሡ ከሥልጣናቸው ለቀቁ፡፡ ፖኤዝም ሞተ፡፡ የሱስንዮስ ልጅ ፋሲል ተተኩ፡፡

**ማጠቃለያ፡-** በተለይ ከ12ኛው - 15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ዘመን አብያተ ክርስቲያናት የታነፁበት፣ በርካታ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉበት፣ ዓለም አቀፋዊ ትብብሮች የተደረጉበትም ዘመን በመሆኑ በበጎ ጎኑ እናስታውሰዋለን፡፡ ከዚያ በኋላ በግራኝ መሪነት በደረሰው የአብያተ ክርስቲያናት፣ የንዋያተ ቅዱሳት እና የቅዱሳት መጻሕፍት ውድመት የክርስቲያኖች እልቂት እና የኢትዮጵያውን ደም መፋሰስ አሳዛኝ ክሥተት የምንማርበት ነው፡፡

**ተግባር፡-** አለመቻቻል፣ አለመዘጋጀት እና ክፉ እና ጠቃሚ ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖን አለመለየት ሀገራችንን እና ቤተ ክርስቲያናችንን ዋጋ ያስከፈለ ነው፡፡ መጽሐፍ ***"ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፡፡"*** ሮሜ.፲፪፥፲፰ እንዳለ፡፡ ከወንድሞቻችን ጋር ልንኖርባት እግዚአብሔር በሰጠን ሀገር ለሌሎች ፍቅር በመስጠት እና በጎ በመመኘት ልንኖር ይገባናል፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች፡-***

1. መጀመሪያ ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው እንዴት? በማን አማካኝነት ነው?
2. ክህነት እና ምስጢራተ ቤተክርስቲያን መፈጸም የተጀመረበት፤ ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት የሆነበት መቼ ነው? እንዴት? በማን አማካኝነት?

3. ምንኩስና እና ገዳማዊ ሕይወት ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ የተስፋፋው እንዴት ነው? መቼ?
4. ከዮዲት ጉዲት ጥፋት በኋላ የአብያተ ክርስቲያናት መታነፅ እና ክርስትና የተጠናከረበት ጊዜ ከስንተኛው እስከ ስንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው? በማንኛው ሥርወ መንግሥት?
5. በተለይ ከ12ኛው እስከ 15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለው ጊዜ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ በምን ይታወቃል? ግለጹ፡፡
6. በቤተክርስቲያን ታሪክ ታላቁ የቤተ ክርብቲያን የመከራ ዘመን የሚባለው ከ፲፭፻፳፯-፲፭፻፵፪ (1527-1542) ዓ.ም ስለነበረው ዘመን መነሻው እና ውጤቱ በማብራራት ግለጹ፡፡
7. በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን በጴጥሮስ ፓኤዝ (ኢየሱሳውያን) አማካኝነት የነተነሣውና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በሊቃውንቷ እና ክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ፈተና ምን ነበር? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከ፲፮ኛው-፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (ሁለት)

## ዐሥራ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፡- ተማሪዎች በተለይም በዘመነ መሳፍንትን ወቅት ቤተ ክርስቲያን የደረሰባትን ችግሮችና ውጤቶቹን ያውቃሉ፤ በመምህሩ የማሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ**፡- *“ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ። ”* ኤፌ.፭፥፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፤ 1982

**መግቢያ፡-** ከ፲፮ኛው - ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በጎና ክፉ የሚባሉ ክሥተቶች አልፈዋል። በዛሬው ትምህርታችን ከእነዚህ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍሎች ከ፲፮፻፳፫-፲፯፻፸፩(1623-1771) ዓ.ም (ከዐፄ ፋሲል - ዘመነ መሳፍንት መጀመር።) እና ከ፲፯፻፸፩-፲፰፻፵፭ (1771 -1845) ዓ.ም (በዘመነ መሳፍንት) የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ሂደት እንመለከታለን።

## ትምህርቱ፡-

### 1. ከ፲፮፻፳፫-፲፯፻፸፩(1623 -1771) ዓ.ም ከዐፄ ፋሲል - ዘመነ መሳፍንት መጀመር።

በ፲፮፻፳፫(1623) ዓ.ም ዐፄ ፋሲል ሲነግሡ ‹‹ኦርቶዶክስ ትመለስ›› የሚል ዐዋጅ አስነገሩ። የጎንደርን ከተማ መናገሻ ከተማ በማድረግ አስደናቂውን ቤተ መንግሥታቸውን አሳንፀዋል። በከተማይቱ ውስጥ(አደባባይ ኢየሱስ ፣ጎንደር መድኃኒ ዓለም፣ እልፍኝ ጊዮርጊስ ፣ሌሎችም) እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች (በተለይም በግራኝ የፈረሰቻውን የአክሱም ጽዮን ማርያም እንደገና በማሳነፅ) አብያተ ክርስቲያናትን አስተክለዋል። በዘመናቸው መጻሕፍት እንዲጻፉ አበረታተዋል። በተጨማሪ እስከዚያ ዘመን ድረስ በሚጻፉ መጻሕፍት ላይ ዘመናት እየተጠቀሱ አይጻፍም ነበር። ይህንን ችግር በማረም ጸሐፍያን ዘመን ጠቅሰው እንዲጽፉ በማስገደዳቸው ታሪካዊ ውለታቸው የጎላ ነው። እንደ ሰው ድካምም ለአባታቸው የመጣችውን ሚስት እና እኅቷን በማስነወር በድለው እና የተቃወሙዋቸውን አባቶች በማስገደላቸው ከእግዚአብሔር በተላከ አባት ተግሣጽ ንስሐ ገብተው ለመካስ ጥረት አድርገዋል።

www.zeorthodox.org

በዘመናቸው ***"ኢየሱሳዉያን"*** ከሀገር እንዲወጡ ተደርገዋል። ሆኖም ***"አልፎንሱ ሜንዴዝ"*** የተባለ ካቶሊካዊ (ፖኤዝን የተካ ነው) በሐማሴን አሞኛል ብሎ ተኝቶ፤ ለጎጃሙ ኤዎስጣቴዎስ ዘሳንኪ ጊዮርጊስ ‹‹ቅብዐት›› የተባለ እምነትን፤ ለሸዋው ቁርንጭ ተክለ ሃይማኖት ‹‹የጸጋን›› እምነት አስተማረ። ያደረገው ክፉ ሥራ ተደርሶበት ከሀገር ሲባረርም ***"ሁለት እሾህ ተክያለሁ"*** ማለቱ በትውፊት ይነገራል።

ይህም ከ፲፯ኛው-፳ኛው መቶ ክፍላተ ዘመናት ቤተ ክርስቲያንን ያወዛገበ እና ያዳከመ ፈተና ነበር። ሊቃውንቱ ሕዝቡን ማስተማር እና ማጥመቅን ትተው ቅብዐት፣ ጸጋ፣ ካራ በሚሉና ተዋሕዶን ለማስጠበቅ በሚደረግ ጥረት ተያዙ። በዚህ ምክንያትም በሩቅ ያሉ አካባቢዎች በንግድ እና በድንበር ገጠም ሙስሊም መንግሥታት ተጽዕኖ ሰለሙ። (ስለ ቅባት እና ጸጋ እምነት አባሪ ትምህርቱን ተመልከቱ።)

በጸጋ እና ቅባቶች ምክንያት ወንድማማቾች እርስ በርስ ሲተላለቁ፤ ነገሥታቱም በዚህ ክፍፍል ገብተው እያከራከሩ አንዱን በመደገፍ እና ሌላውን በማሰር ተጠምደው ብዙ ጉባኤያትም ተደርገዋል ። ተዋሕዶዎቹ እያሸነፉ ጸጋ ፣ ቅባቶች እና ካራዎች ተወግዘዋል ። ተዋሕዶዎቹን በክርክር ማሸነፍ ሲያቅትም በግፍ ለማስገደል የተሞከረበት ዘመንም ነበር።

ከእነዚህ ቀዳሚው የአፈንጉ ጉባኤ (፲፮፻፵፮(1646) ዓ.ም) ሲሆን የተዋሕዶው አፈ ጉባኤ አዳም ዘእንፍራንዛ እና በቅባቱ ዘኢየሱስ ዕውሩ መካከል ክርክር ተደርጎ ዘኢየሱስ ተወግዞአል። በዐፄ ዮሐንስ አንደኛ ዘመን ቅባቶችና እና ጸጐች በአንድነት መጥተው ተዋሕዶዎች ላይ በንጉሡ አማካኝነት ጫና በማሳደራቸው ተዋሕዶዎቹ እያዘኑ ወደ አክሱም ተመልሰዋል።

በዐፄ ዮሐንስ ተከታይ በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመን ክርክሮ ቀዘቅዞ በዐፄ ተክለ ሃይማኖት ዘመን አገረሸ። ጳጳሱ እና ንጉሡ ባሉበት ጉባኤ ተካሂዶ ተዋሕዶዎቹ ሲያሸንፉ ከጎጃምና ከጎንደር የመጡት ቅብአትና ጸጎች በጳጳሱ ተወግዘው በንጉሡ ተጋዙ። ተተኪው ንጉሥ ዐፄ ተክለ ቴዎፍሎስ ሳያከራክሩ እና ጉባኤ ሳይጠሩ በዐዋጅ ቅባትን አስነገሩ። ለምን ሲባሉ የማይመስል መልስ ስለሰጡ ተዋሕዶዎቹ ወደ ፈጣሪያቸው በማሳሰብ በሐዘን ተቀመጡ ። ለየት ያለው ክርከር የአፄ ዳዊት ዘመን ነበር። ቅባቶች የንጉሡን ቢትወደድ ዘጊዮርጊስን ይዘው ጉባኤ አስጠሩ። ጳጳሱም ጉባኤውን እንዲመሩ ተደረገ። ነገር ግን ቢትወደዱን ለማስደሰት ከተሾሙበት ከእስክንድርያ ሃይማኖት በተቃራኒ ቆሙ። ይህም የዕውቀት ማነስ ጥቅመኛነት ነበር። በዚህ ሰበብ በተፈጠረው ግርግር ቢትወደዱ ተዋሕዶዎችን በአረማውያን ሲያስጨፈጭፍ፤ በተዋሕዶ ወገን ከነበሩት እጨጌ ተክለ ሃይማኖትም በሰማዕትነት ዐረፉ። ይህ ሁኔታ እስከ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ (፲፯፻፸፪-፲፯፻፸፯(1772-1777) ዓ.ም) ዘመን ቀጠለ። አባቶች ከግብጽ አለመምጣታቸው ተጨመረና ቤተ ክርስቲያን እጅጉን ተዳከመች።

www.zeorthodox.org

## 2. ከ፲፯፻፸፩-፲፰፻፵፭(1771 -1845) ዓ.ም ዘመነ መሳፍንት

ይህ ዘመን ነገሥታቱ እና የየአካባቢው ሹማምንት በጦር አበጋዞቻቸው ሥር ወድቀው በመሳፍንቱ የተመሩበት የየራሳቸውን የአካባቢ መንግሥትም ያቋቋሙበት ዘመን ስለነበረ፤ በታሪክ ‹‹ዘመነ መሳፍንት›› ተብሎ ይታወቃል፡፡ ካህናቱም በዚህ ተፅዕኖ ሥር ሲወድቁ፤ ባራኪ ጳጳስም አልነበረም፡፡ ሙስሊሞችም መምህራንን መድበው በቆላማና በድንበር አካባቢ ያሉትን ኢትዮጵያውያንን በትምህርት እና በጥቅም እየደለሉ ሲያሰልሙ፤ ምዕራባውያንም ፕሮቴስታንቲዝምንና ካቶሊካዊነትን ለማስፋፋት ጥረዋል፡፡ ብዙ ቅርሶች እየተዘረፉ ከሀገር ወጥተዋል፡፡

በሀገሪቱ መዳከም ምክንያት በቱርክ መንግሥት ለግብጽ የተሾመው አህመድ ኢብን እስከ መተማ (ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ) ወረራ አደረገ፡፡ በሺሕ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችን ገድሎ ከሁለት ሺሕ በላይ ክርስቲያኖችን በጉልበት ሥራ ለባርነት ወሰደ፡፡ ይህንንም በወቅቱ የነበሩት መሳፍንት እና መኳንንት ከካህናቱ ጋር ለፈረንሳዩ ንጉሥ ከጻፉት ደብዳቤ መረዳት ይቻላል፡፡ መከፋፈሉ ከአገሪቱ አልፎ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት አዳክሟል፡፡ በዘመነ መሳፍንት ማገባደጃ ብዙ ክርስቲያኖች አስታዋሽ በማጣት ሰለሙ፡፡ አብዛኛዎቹ የዛሬ የኢትዮጵያ ሙስሊም አካባቢዎች ከግራኝ ወረራ ይልቅ በዘመነ መሳፍንት በንግድ እና በስብከት በመጡት የሰለሙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በዚህ ዘመን በሰሜንና በምሥራቅ እስልምናን ያስፋፋው መሐመድ ኢትማን አልማርጋኒ ቤን ነው፡፡ ይህ ሰው ከግብጹ ንጉሥ ተልኮ በንግድና በስብከት ብዙዎችን አስልሟል፡፡

እንግሊዛዊው የታሪክ ጸሐፊ ባጅ እስፔንሰር እንደጻፈውም፤ አባቶችን እየጠበቁ በሰሜን እና ሰሜን ምሥራቅ ጫፍ በደቡብ፣ በምዕራብ እና በምሥራቅ የነበሩ ሕዝቦች በየሰንበቱ እየተሰባሰቡ ጸሎት ያደርጉ ነበር፡፡ እንዲሁም በፈራረሱ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው ቢሰባሰቡም ፤ ለአራት ትውልድ ጥምቀት፣ ትምህርት እና ምስጢራት ያልተፈጸሙለት ሕዝብ ተፅዕኖውን መቋቋም አቅቶት ሰለመ፤ሌላውም ተገልሎ ተቀመጠ፡፡

በሌላ በኩል አገር ለማሰስ የሚመጡት ፣ በአውሮፓ ደም የተፋሰሱት ካቶሊካውያንና ፕሮቴስታንቶቹ ምዕራባውያን ፡- አገሪቱን በመጎብኘት ሰበብ ጥናቶቻቸውን ለአገሮቻቸውና ለአብያተ ክርስቲያኖቻቸው በመላካቸው ከቀን ቀን ቁጥራቸው ጨመረ፡፡ የሀገር መሪዎችን በማማከር ፣ ወንጌል በመስበክ እና ጥበበ እድን በማስተማር ሰበብ ፤ ፕሮቴስታዊነት እና ካቶሊክነትን ያስፋፉ ጀመር፡፡ በተለይ በዘመነ መሳፍንት ከመጡት ቀዳሚው ጀምስ ብሩስ (በ፲፯፻፷፪(1762) ዓ.ም) በኢትዮጵያ ተቀምጦ ባደረገው ጥናት ባለ አምስት ቅጽ መጽሐፍ ጽፎአል፡፡ በዚህ ምክንያት በሌሎች ዘንድ ኢትዮጵያ ትኩረት እንድታገኝ እና ምዕራባውያኑ በብዛት እንዲመጡ በር ተከፍቶአል፡፡ እነ ሄንሪ ሳልት(Hanry Salt)፣ ናትናኤል ፒርስ (natnael Piers) እና ኮፊን (Coffin) በኋላም ሳሙኤል

www.zeorthodox.org

ጎባት (Samuel Gobbat)፣ ኢዘንበርገ ዎልፍ (Isenbureg wolf)፣ ብሉናር ክራፍ (Bluenard Craft) የሚባሉ ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ አንቶን ዲባዲ እና ወንድሙ አርኖ ዲባዲ የቤተ ክስቲያንን ትምህርት እና የሀገሪቱን ቋንቋ አጥንተው ወደ ፈረንሳይ የላኩዋቸው መጻሕፍት ብዙ ነበሩ፡፡ ዛሬም ድረስ በፈረንሳይ ቤተ መጻሕፍት ይገኛሉ፡፡ በርካታ ንዋያትም ይፋዊ ባልሆነ መንገድ ከአገር ወጥተዋል፡፡ ኢትዮጵያ በኢየሩሳሌም የነበራትን ይዞታዎችም ያጣችው በዚህ ወቅት ነበር፡፡

በተቃራኒው የእኛ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የውጪውን ዓለም ቋንቋ፣ ይትበሀል እና መንፈሳዊ ይዘት ከሚስዮናውያን አጥንተው፤ ወደ ውጭ ጉዞ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ሥራ የሠሩ አባቶችም ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የጎጃሙ ተወላጅ ኢትዮጵያዊው አባ አብርሃም በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ ከተከታተሉ በኋላ በጀምስ ብሩስ አማካይነት በምጽዋ ወደ ሕንድ ከዚያም ወደ ግብጽ እና ኢየሩሳሌም ሄደዋል፡፡ በግብጽም ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አማርኛ ተርጉሞዋል፡፡ (ከ፲፰፻፲፮-፲፰፴፻፪(1816-1832) ዓ.ም) በኋላም ወደ ኢትዮጵያ የገቡት እነ ማርቲን ፍላድ የሀገሪቱን ቋንቋ አጥንተው በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስን ለማሳተማቸው መሠረት ነበሩ፡፡

ሌላው ችግር ካህናቱ በመሳፍንቱ ተይዘው ፤ የክፍፍሉ አካላት ከመሆናቸው በተጨማሪ አንዱ መስፍን የቅባት ሌላው የጸጋ ወዘተ ደጋፊ በመሆን የተሳሳቱ ትምህርቶችን ማስፋፋታቸው እና ማዕካላዊ ጉባኤ አለመደረጉ የፈጠረው ክፍተት ትልቅ ነበር፡፡

**ማጠቃለያ፡-** በዛሬው ትምህርታችን ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር በተያያዘ በቤተ ክርስቲያን የተፈጠረውን አደጋ ተምረናል፡፡ ከእነዚህም፡-

1. የፈረሱት አብያተ ክርስቲያናት መታነፃቸው፣ አባቶች መጻሕፍትን መጻፋቸው እና መተርጎማቸው በጎ ተፅዕኖዎች ነበሩ፡፡
2. የካቶሊካውያን ኦርቶዶክሳውያንን መከፋፈላቸው፣ የቅባት ጸጋ ክርክር፣ የዘመነ መሳፍንት መከፋፈል፣ ለስብከተ ወንጌል ትኩረት እንዳይሰጥ ማድረጉ፤ ብዙ ምእመናንን ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው እንዲቀሩ ያደረገ አሳዛኝ ክስተት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

1. ክርስትና ከአካባቢያዊነት በላይ ማሰብን ሰማያዊ መሆንንም ይጠይቃል፡፡ ***"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው ደሀ ወይም ባለጠጋ የተማረ እና ጨዋ ወንድ ወይም ሴት የለም፤ ሁሉም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ነው"*** ገላ. ፫፡ በቅዳሴ እግዚእም ***"በሰማይ ይሐሉ ልብክሙ … ልባችሁ በሰማይ ይሁን"*** የተባልነውን መዘንጋት የለብንም፡፡ ሰዎችን በምድራዊው ኑሮ፣

በአካባቢ፣ በጎጥ እና በቋንቋቸው እየለየን ክፉ ብናደርግባቸው ክፉ ውጤቶች ይመጣሉ። እናም ከእንዲህ ዓይነት ስሕተቶች በመራቅ ሰውን ሁሉ በሰውነቱ በመውደድ ተጠበቁ።

2. ክፉም ሆነ በጎ አጋጣሚዎችን ለትምህርት አድርጉአቸው። አባቶቻችን በማይመች ዘመንና ሁኔታ ጠቃሚ የሆኑ ታላላቅ ሥራዎችን ሠርተው ማለፋቸውንም በማስታወስ ለተሻለ ዓላማ ተዘጋጁ።

## *ጥያቄዎች፡-*

1. በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን በጴጥሮስ ፓኤዝ (ኢየሱሳውያን) አማካኝነት ካቶሊካዊነትን በዓዋጅ ሕዝቡ እንዲቀበልና የመንግሥት ሃይማኖት እንዲሆን ተሞክሮ በተፈጠረው ሁከት ብዙ ክርስቲያኖች ሰማዕትነትን ተቀብለዋል። ከዚያ በኋላ ‹‹ኦርቶዶክስ ትመለስ›› የሚል ዐዋጅ ያስነገሩት ንጉሥ ማን ናቸው? መቼ?
2. ለጎጃሙ ኤዎስጣቴዎስ ዘሳንኪ ጊዮርጊስ የ‹‹ቅብዐት››፣ ለሸዋው ቁርንጭ ተክለሃይማኖት የ‹‹ጸጋ››› እምነት ኑፋቄ አስተምሮ የተባረረው ካቶሊክ ማን ይባላል?
3. ‹‹ዘመነ መሳፍንት›› በመባል የሚታወቀው ጊዜ ከመቼ እስከ መቼ ያለውን ዘመን ያካትታል? ስለዘመነ መሳፍንት መገለጫዎች፣ በወቅቱ የተከሠቱ ችግሮች፣ በቤተ ክርስቲያን እና ምእመናኗ ላይ የደረሰውን ችግር አብራሩ።

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከ16ኛው-20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (ሦስት)

# ዐሥራ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**:- ተማሪዎች የዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ይገነዘባሉ። መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ።

**የሚጠኑ ጥቅሶች**:- *"በለሱን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል፥ ጌታውንም የሚጠብቅ ይከብራል።"* ምሳ.፳፯፥፲፰. *"ወይናችን አብቦአልና የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮች ፥ ጥቃቅኑን ቀበሮች አጥምዳችሁ ያዙልን።"* መኃ. ፪፥፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት**:- ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ 1982፤‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› ሉሌ መልአኩ።

**መግቢያ**:- በተከታታይ ክፍሎች ከ፲፮ኛው - ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት የነበረውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተምረናል። በዛሬው ትምህርታችንም ከ፲፰፻፵፭-፲፱፻፷፮(1845-1966) ዓ.ም ያለውን ታሪካዊ ጉዞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንቃኛለን ።

## ትምህርቱ:-

### 1. የዐፄ ቴድሮስ መነሣት ፲፰፻፵፭-፲፰፻፷(1845-1860)

እንደ ዘመኑ የንግሥና ባህልና ሕግ ይህ ነው የማይባል ንጉሣዊ የዘር ግንድ የማይቆጠርላቸው እና በቆራ የተወለዱት ካሣ በጎንደር ቅድስት ሥላሴ ገዳም ተምረው ያደጉና፤ በመጨረሻው የዘመነ መሳፍንት ገዥ ራስ አሊ ጦር ውስጥ የነበሩ ዝነኛ የጦር ሰው ናቸው። በኋላም ኢትዮጵያን ከዘመነ መሳፍንት መከፋፈልና የእርስ በርስ ጦርነት የታደጉና አንድ ያደረጉ መሪ ናቸው። በአንድ ሚስት የተወሰኑትና ቆራቢው ዐፄ ቴዎድሮስ ለቤተ ክርስቲያን የሚበጁ ዐዋጆችን ያወጡ ነበሩ። ለምሳሌ:- የደብረ ታቦር ጉባኤ። የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ.ም በደብረ ታቦር ከተማ ማሜ ግራር በተባለው ሰበካ ፤ ሊቃውንቱ በአቡነ ሰላማ ሰብሳቢነት የሃይማኖት ጉባኤ ተጠሩ። በመጨረሻም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ እንዲታወጅ አደረጉ።

www.zeorthodox.org

ዐፄ ቴዎድሮስ ሕዝቡ ከዘመነ መሳፍንት ክፍፍል ወጥቶ አንድ እንዲሆን ጥረዋል ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ይዞታ በአግባቡ እንዲሆን አገልጋዩ ከበላተኛው እንዲለይም ጥረት አድርገዋል፡፡ በዘመናቸው የግብጹ ፓትርያርክ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሲሆን ይህም በታሪክ የመጀመሪያው ነበር፡፡ በመጨረሻም ከምዕራባውያን ጋር በተፈጠረው አለመግባባት በተነሣ ጦርነት እንግሊዞች ንጉሡ በመቅደላ ያሰባሰቡዋቸውን በርካታ መጻሕፍት እና ነዋያተ ቅድሳት ዘርፈው ወሰዱ፡፡ እርሳቸውም ሞቱ፡፡

## 2. የዐፄ ዮሐንስ ዘመን ፲፰፻፷፫-፲፰፻፹፩(1863-1881)ዓ.ም

ዐፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ ጦርነት ሞተው አፄ ዮሐንስ ሲነግሡ የካቶሊኮቹ ውጤቶች የሆኑት የቅባትና የጸጋ ተከታዮች ቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ከበፊቱ በበለጠ ተጠናክረው ተነሡ፤ በተለይ በቅብዓቶች የነበረውን ሙግት እየቀዘቀዘ ሲመጣ የጸጐች እንደ አዲስ አገረሸ፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ስለ አስቸገሯትም በ፲፰፻፸፰(1878) ዓ.ም በወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሜዳ ላይ ጉባኤ ተደረገ፡፡

በጉባኤው ላይ የተገኙት ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስ፤ ንጉሥ ምኒልክ እና ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከቤተ ክህነት እጨጌ ቴዎፍሎስ ነበሩ፡፡ የተዋሕዶዎች አፈ ጉባኤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ሲሆኑ ረዳታቸው የነበሩት አለቃ ተክለ ሥላሴ እና መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ናቸው፡፡ የጸጐች (የሦስት ልደት ባዮች) አፈ ጉባኤ ሥነ ጊዮርጊስ እና ረዳት አለቃ ሀብተ ወልድ፣ አለቃ ውቤና አለቃ ቤተ ሌዊ ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ ተዋሕዶዎች ከጸጐች ጋር ክርክር አደረጉ፡፡ ጸጐችም ተረቱ፡፡ ንጉሥ ምኒልክ ‹‹ነገሩ ይደርና እንመካከርበት›› ሲሉ፤ የተዋሕዶ አፈ ጉባኤ የሆኑት መልዐከ ብርሃን ‹‹ይህ ፍርድ አይደርብን›› በማለት ንጉሡን ስለተማጸኑዋቸው፤ ‹‹ይፍረድ አስፈርድ›› የሚል ትእዛዝ ዐፄ ዮሐንስ ሰጡ፡፡ እነ አለቃ ሥነ ጊዩርጊስም ተወግዘዋል፡፡ የቅብዓትና ጸጋ ትምህርትም ውሎ አድሮ ከምድረ ኢትዮጵያ እየጠፋ መጣ፡፡

የዐፄ ዮሐንስ ጥረት በግድ የሠለሙትንና ከላይ ባየነው ታሪካዊ ክፍተት የተዘነጉትን ክርስቲያን ለማድረግ ጥረዋል፡፡ የተረሱ እና ፈርሰው የቀሩ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትንም አሳንፀዋል፡፡ ለምሳሌ ደብረ ሊባኖስ ይጠቀሳል፡፡ በኢየሩሳሌም የነበረን ይዞታ እንዲጠናከር እና አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ አስደርገዋል፡፡ ባይሳካም ዞረው የሚያስተምሩ እና ክህነት የሚሰጡ አራት ጳጳሳት ከእስክንድርያ እንዲሾሙ ለማድረግ የተወጠነ ሂደት ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

በመጨረሻም ደርቡሾች ጎንደር ድረስ በመሄድ ለጥምቀት ቀን በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን አጥፍተው ክርስቲያኖችን ገደሉ፡፡ ይህ በውጭ ኃይሎች በምዕራብ ኢትዮጵያ በእስልምና ስም የተከፈተውን ጦርነት በመተማ ተዋግተው ድል ቢያደርጉም በመጨረሻ ሞቱ፡፡

### 3. ዘመነ ምኒልክ

ዐፄ ዮሐንስ በመተማ ሲሞቱ ንጉሥ ምኒልክ ዐፄ ተብለው በንጉሠ ነገሥትነት ተሾሙ፡፡ ሥልጣን መያዛቸውን ተከትሎም በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ ግዛት ሲያስፋፉ ፦ አብያተ ክርስቲያናት ተክለዋል፤ ዘመናዊ የመንግሥት አወቃቀር ሲደረግም ትምህርት ሚኒስቴርነት ለቤተ ክርስቲያን እንዲሰጥ አድርገዋል ፡፡ ዘመነ ምኒልክን በቤተ ክርስቲያን የሚጠቀሰው ሌላው ዓቢይ ጉዳይ የፍትሕ ፣ የእኩልነት እና የሰብዓዊነት ልዕልና ምልክት በሆነው በአድዋ ጦርነት ታቦተ ጊዮርጊስን ይዘው መዝመታቸው ነው፡፡ ጣልያናውያን በመሰከሩለት ባለ ነጭ ፈረሱ በቅዱስ ጊዮርጊስ እርዳታ ጥቁር ሕዝብ የጣሊያንን የሠለጠነ ጦር ድል አድርጎ በምዕራባውያን ላይ ያስመዘገበው ድል ነበር፡፡

### 4. ልጅ ኢያሱ፡፡ ፲፱፻፫-፲፱፻፱(1903-1909)ዓ.ም

ዐፄ ምኒልክ የተናዘዙላቸው እና በንጉሡ የጠና ደዌ መያዝ ሀገሪቱን በአልጋ ወራሽነት የመሩት ልጅ ኢያሱ ናቸው፡፡ ልጅ ኢያሱ ለእምነት ነጻነትና እኩልነት ያሳዩት ዝንባሌ በአንድ በኩል ኦርቶዶክሳዊውን የክርስቲያን መንግሥት መዳከም ለሚመኙት እንደ ቱርክ ላሉት ወርቃማ አጋጣሚ መሰላቸው፡፡ በሌላ በኩል የአዲስ አበባውን ቀጨኔ መድኃኔ ዓለምንና የመሳሰሉትን በማሠራታቸው በበጎ ቢነሡም፤ ‹‹እስላም አገቡ ሰለሙ›› በሚለው አወዛጋቢ ወሬ ለጥቃት በተመቻቸላቸው የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸው መዳፍ ወደቁ ይህም ሆኖ ሕዝቡ ለኢያሱ የነበረው መልካም ስሜት ነበር፡፡ በመጨረሻም ልጅ ኢያሱ በግዞት ሞቱ፡፡

### 5. አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፲፱፻፱-፲፱፻፳፪(1909-1922)ዓ.ም

የዐፄ ምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ አገሪቱን የመሩበት ዘመን በቤተ መንግሥት በነበረው የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት ያልተረጋጋ ቢሆንም እንደ በአታ ለማርያም ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት አሳንፀዋል፡፡ የበአታን የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ትምህርት ቤት በአባታቸው ስም ከፍተዋል፡፡ አልጋ ወራሹ ራስ ተፈሪ መኮንን የኅትመት መሣሪያ አስመጥተው (፲፱፻፲፪-፲፱፻፲፬(1912-0914) ዓ.ም) በርካታ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ታትመዋል፡፡ በዘመናቸው የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ተቋቁሞአል፡፡ ይህንንኑ ተከትሎ አምስት ኢትዮጵያውን ኤጲስ ቆጶሳት መሾማቸው ከንግሥቲቱ መንፈሳዊነት ጋር ተዳምሮ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቤተ መንግሥቱን ያስታውሱናል፡፡

www.zeorthodox.org

### 6. ዘመነ ተፈሪ መኮንን (ዐፄ ኃይለ ሥላሴ) ፲፱፻፳፫-፲፱፻፷፮(1923-1966) ዓ.ም

ይህን ዘመን (ዘመነ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ) ታሪካዊ ክሥተቶቹ ለቤተ ክርስቲያን ከነበራቸው ፋይዳ አንጻር እንደሚከተለው ከፍለን እንመለከተዋለን፡፡

*6.1. ከ፲፱፻፳፫-፲፱፻፳፰(1923-1928)ዓ.ም፣ መልካም ጅማሮዎች*

ይህ ዘመን አልጋ ወራሽ ተፈሪ - ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በሚል ስመ መንግሥት የተሾሙበት የመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዓመታት ናቸው፡፡ በዚህ መሠረትም በወቅቱ ምሁራንና የምዕራብ ቆንስላዎች ከፍተኛ ድጋፍና ምክር የነበራቸው ወጣቱ ንጉሥ ሕገ መንግሥት፣ ማዕከላዊነቱን የጠበቀ ብሔራዊ ሠራዊት ፣ ምክር ቤት በማቋቋም ሕጋዊ መሠረት ያለው ዘመናዊ መንግሥት መሠረቱ፡፡

ቤተ ክርስቲያኒቱም በሕገ መንግሥቱ ሕጋዊ እውቅና አገኘች፡፡ የበላይነቷንም አጸናላት፡፡ የዘውዱን ሃይማኖትም ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐወጀላት፡፡ ይህም በዘመኑ በመላው አውሮፓ አሜሪካንን፣ ጨምሮ በክርስትና ስም፣ በዐረቡ ምድርም እስልምናን መሠረት አድርጎ የሚሠራበት የመንግሥታት አስተዳደር ስልት ነበር፡፡ በኢትዮጵያም ኦርዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አብዛኛው ሕዝብ ስለሚከተላት፣ ከሕዝቡ ባህል እና አኗኗር ጋር የተዋሐደው ማራኪ ሥርዓትዋ እና አገራዊ ሚናዋ በማንም የማይተካ ነበር፡፡ እንደ ሀገር በቀል ሃይማኖት (Indigineous Religion) የሚያስቆጥራትም ስለነበረ የመንግሥት ሃይማኖትነትዋ በአማካሪዎች የምዕራብ ቆንስላዎች እንኳዋን ከጥያቄ የሚገባ ጉዳይ አልሆነም፡፡

ሌላው በዚህ ዘመን የተጀመረውና በፋሺስት ወረራ የተሰናከለው ወሳኝ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ***"የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ኮሚቴ"*** መቋቋሙ ነው፡፡ ይህ የሊቃውንት ስብስብ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራውን እያከናወነ በ፲፱፻፳፰(1928)ቱ የጣልያን ወረራ ተቋረጠ፡፡

## ማጠቃለያ

ከ፲፰፻፷-፲፱፻፳፰(1860-1928)ዓ.ም ኢትዮጵያ ከዘመነ መሳፍንት መከፋፈል ወጥታ ወደ አንድነት እና ዘመናዊነት የተጓዘችበት ወቅት ነው፡፡ ለዚህም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተምረው ያደጉት ነገሥታትና ሊቃውንቱ ታላቅ ሚና ነበራቸው፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

1. ከዘመናዊነት እና ከለውጥ ጋር የሚመጡትን ገንቢ እና ጎጂ ጎኖች ከክርስትና አንጻር ተወያዩባቸው፡፡
2. ለቤተ ክርስቲያን ከእኔ ምን ይጠበቃል? ለሀገርስ? በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ሐሳባችሁን በማስታወሻ ለራሳችሁ አስቀርታችሁ ለመምህር አሳዩ፡፡

*ይቆየን...*

***ጥያቄዎች፡-***

1. ዐፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩበት ዘመን መቼ ነው? በእርሳቸው ዘመን የተደረጉትን ዋና ዋና ተግባራት ግለጹ፡፡
2. ዐፄ ዮሐንስ በንጉሥነት ኢትዮጵያን የመሩበት ጊዜ መቼ ነው? በዐፄ ዮሐንስ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተደረጉት ዋና ዋና ሥራዎች ምንድን ናቸው?
3. በመንግሥት አወቃቀር ለቤተክርስቲያን ‹‹የትምህርተ ሚኒስቴርነት›› ተግባር እና ሓላፊነት የተሰጣት በማን ዘመነ መንግሥት ነበር? ኢትዮጵያውያን(ጥቁር ሕዝብ) በጣልያን የተደራጀ ጦር (ምዕራባውያን) ላይ በመላው ዓለም ታሪክ ከፍተኛ ድል የተቀዳጁበት ጦርነት ምን ይባላል? የት? አብራሩ፡፡
4. በአዲስ አበባ በአታ ለማርያም ቤተክርስቲያን ያሳነፁ እና በበአታ የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቱን የከፈቱ የኢትዮጵያ መሪ ማን ናቸው?
5. በዘመነ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የተደረጉ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚጠቀሱ ተግባራትን በአጭሩ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ ከ፲፮ኛው-፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (አራት)

# ዐሥራ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *ተማሪዎች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን የቅርብ ጊዜ ዘመናዊ ታሪክ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡*

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *" ሁሉም ያልፋል"*

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን እስከ ፲፱፻፳፰(1928)ዓ.ም ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የማጠቃለያውን ታሪክ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### *6.2. ቤተ ክርስቲያን በአምስቱ ዓመታት የፋሺስት ጣልያን ወረራ ዘመን ፲፱፻፳፰-፲፱፻፴፫(1928-1933) ዓ.ም*

ጣልያን በአድዋ ጦርነት ተሸንፎ ከአርባ ዓመታት ሰፊ ዝግጅት በኋላ ጣልያን ኢትዮጵያን ዳግመኛ ወረረ፡፡ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ፖፕ የጦር መሣርያውን በመባረክ፣ የሰውና የገንዘብ መዋጮ በማድረግ ፋሽስት ጣልያንን ረዳች፡፡ የኢትዮጵየ አርበኞች ለነጻነታቸው በዱር በገደል ሲዋደቁ ከተሜውም በከተማ አርበኛነት ተሰለፈ፡፡ ግፉን መቃወም ያለባት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንም በመሪዎችዋ (አቡነ ሚካኤል እና አቡነ ጴጥሮስ) አማካይነት ተቃወመች፡፡ በዚህ ተቃውሞ የተበሳጨው የጣልያን ጦር መሪ ግራዝያኒ ብዙ ሕዝብ ሲያስገድል ገዳማትና አድባራትን አስመዘበረ፡፡ (ለምሳሌ የአዲስ አበባው ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን አቃጠለ)፡፡ ብዙ ቅርስም ዘረፈ (የአክሱም ሐውልት ያኔ ተወስዶ ነው በስልሣኛ ዓመቱ በ፳፻(2000) ዓ.ም የተመለሰው፡፡) በአጠቃላይ በአምስቱ ዓመት የፋሽስት ጣልያን ወረራ ብዙ ሕዝብ ሲሞት ከሁለት ሺሕ በላይ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፡፡ የወደመውና የተዘረፈው ቅርስ ለቁጥር የሚታክት ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

የተሰደዱት የሀገሪቱ መሪም ከዲፕሎማሲያዊው ሀገራዊ ሓላፊነታቸው ጎን፡- ታቦት የያዙ ፣ ጸሎት የሚያደርጉ አበው ይዘው ስለሄዱ፤ ዛሬ በተለምዶ ስደተኛ የሚባለውን ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም (የኃዘንተኞች መጠጊያ) የሚባለውን ታቦት በመማጸን ኖሩ፡፡ ***"በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴ"*** የተዘጋጁትን ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ለንደን በመውሰድ በአማርኛ ቋንቋ አሳተሙ፡፡

**የጳጳሳት ሹመት፡-** ቀደም ብለን እንዳየነው ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ለመጀመሪያ ጊዜ (፲፱፻፳፩(1921) ዓ.ም) ተሾመው ነበር፡፡ ይህ ለሕዝቡ የሰጠውን ደስታ የተረዳው ጣልያንም ከግብጻውያን ጋር በመነጋገር ሌሎች አባቶች እንዲሾሙ አደርጎአል፡፡ የዚህንም ምክንያት ታሪክ ያጠኑ፤ በአባቶች እና በወገኖቹ መገደልና በአብያተ ክርስቲያናት መቃጠል ያዘነውን ኢትዮጵያዊ ልብ ለማባባል ነው፤ ይላሉ፡፡

### *6.3. ከ፲፱፻፴፫-፲፱፻፶፩(1933 - 1951) ዓ.ም፤ መልሶ ግንባታ*

በእግዚአብሔር ቸርነት ፣ በአርበኞች ተጋድሎ እና በሕዝቡ በጸሎት በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍም ፋሺስት ጣልያን ተሸንፎ ንጉሡ ለሀገራቸውና ለዙፋናቸው በቁ፡፡ ከዚያም ከፋሺስት በኂላ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ለመቻል ጥረት ተጀመረ፡፡ ጣሊያን ያፈረሳቸው አብያተ ክርስቲያናት ታነፁ (ለምሳሌ፡- ደብረ ሊባኖስ )፣ ሌሎቹም የተጎዱቱን አሳደሱ (ምሳሌ፡- ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ)፡፡ ተቋርጦ የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት ኮሚቴ ሥራ ቀጥሎ በ፲፱፻፵፰(1948) ዓ.ም መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ታተመ፡፡

## 7. ከ፲፱፻፶፩-፲፱፻፷፮(1951-1966) የቤተ ክርስቲያን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ፡፡

፲፱፻፶፩(1951) ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የተከፈተበት ዘመን ነው፡፡ ከሺሕ ዓመታት ጥረት በኂላ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ተሾሙ፡፡ ከእርሳቸውም ጋር ሌሎች ሊቃነ ጳጳሳት ተሾሙ፡፡ መንፈሳዊ ኮሌጅ በ፲፱፻፶፫ (1953) ዓ.ም ተከፈተ፡፡ ሰንበት ትምህርት ቤት እና የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤም ተቋቋመ፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ታነፁ፡፡ መንፈሳውያን መጻሕፍትም ታተሙ፡፡

በአንጻሩም ፕሮቴስታንታዊ የሚሲዮናውያን እንቅስቃሴ እንደ አዲስ ተጠናከረ፡፡ በመጨረሻም በ፲፱፻፷፮(1966)ቱ ዓ.ም ንጉሡ ከሥልጣናቸው ሲወርዱ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘውዳዊ ሥርዓት ወጣች፡፡

## 8. ከ፲፱፻፷፮-፲፱፻፹፫(1966 - 1983) ዓ.ም

ወታደራዊው ደርግ ሥልጣን ሲይዝ የተከተለው ርእዮተ ዓለም ሶሻሊዝምን ነበር ፡፡ ይህም ጸረ ቤተ ክርስቲያን አቋም እንዲያራምድ ምክንያት ሆኖት ከቤተ ክርስቲያኒቱ በተቃራኒ አሰለፈው፡፡ የለውጥና የራእይ አባት የነበሩትን ሁለተኛውን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ገደለ፡፡ ሌሎች ሊቃነ ጳጳሳት ታሰሩ፡፡ በግልጥ የሚደረጉ የወጣቶችን መንፈሳዊ ጉባኤያት ስም ከማስቀየር እስከ ማገድ ተደረሰ፤ የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የፊት መግቢያው በር ተዘጋ፡፡ በዚህ ዘመን ሁለት ፓትርያርኮች ሦስተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት እና አራተኛው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ተሾመዋል፡፡

www.zeorthodox.org

በዘመኑ ሌላው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚጠቀስ በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በዝዋይ የተጀመረው ሰፊ ሥራ ነው፡፡ ብፁዕነታቸው ወጣቶችን በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም እያሰባሰቡ በማስተማር ለሐዋርያዊ ተልእኮ አዘጋጁ፡፡ አሁን የሚታየው የሰንበት ትምህርት ቤቶች እና የማኅበራት ጠንካራ እንቅስቃሴ መሠረቱን ከዝዋዩ ገዳም ትምህርት ቤት ይጥላል፡፡

## 9. ከ፲፱፻፹፫(1983) ዓ.ም - እስከ አሁን

ደርግ ባነሣው ሰይፍ በ፲፱፻፹፫(1983) ዓ.ም ወደቀ፤ ሕዝበ ክርስቲያኑም ወደ ቤተ ክርስቲያን ጎረፈ፡፡ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንደ አዲስ ተጠናከሩ፡፡ በአዲስ አበባ የቅድስት ሥላሴ እና የመቀሌው ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጆች በድጋሚ ተከፈቱ፡፡ ከኮሌጆቹና ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ማሠልጠኛ ማእከላት በወጡ ሰባክያን ስብከተ ወንጌል ተስፋፋ፡፡ በአባቶች እና በሕዝቡ ጥረት በርካታ አብያተ ክርስቲያናት፣ ትምህርት ቤቶች እና የልማት ሕንፃዎች ተሠርተዋል፡፡ በደቡብ፣ በምዕራብና በምሥራቅ የሀገሪቱ ገጠራማና ጠረፋማ አካባቢዎች የሚኖሩ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ሕዝቦች ወደ እናት ቤተ ክርስቲያናቸው መጥተው ተጠምቀዋል፡፡

አምስተኛው ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት መሆናቸውና ዘመናዊው እውቀታቸው ቤተ ክርስቲያኒቱ በዓለም አቀፍ መድረኮች ያላትን ተቀባይነት ከፍ አድርጎታል፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ለሃያ ዓመታት ቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግለው በ፳፻፬(2004) ዓ.ም ሲያርፉ ቀጣዩ ጉዞ በሚጀመርበት የታሪክ ምዕራፍ ላይ እንገኛለን፡፡

መደራጀት በመቻሉ በርካታ መንፈሳውያን ማኅበራት ለተለያየ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን መሰባሰብ ችለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት አክብረው እያገለገሉ ነው፡፡ በርካታ መንፈሳዊ መጻሕፍት በትርጉም እና በወጥ ዝግጅትነት ሲታተሙ፣ ተጀምረው የተቋረጡና በሥርጭት ላይ ያሉ መንፈሳዊ መጽሔት እና ጋዜጦችም አሉ፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ባደረባቸው ሕመም ነሐሴ ፲ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም ዐረፉ፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ስድስተኛው ፓትርያርክ ሆነው፤ የካቲት ፳፬ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም ተሾሙ፡፡

## ማጠቃለያ

ያለፉት አምስት መቶ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ ይህን ይመስላል ፡፡ አስደሳች አሳዛኝና የሚያወያዩ ታሪካዊ ሒደቶችም አልፈዋል፡፡ የግራኝ አህመድ ሰይፍ ፣ የካቶሊካውያን ሴራ ፣ የዘመነ መሳፍንት አካባቢያዊነት፣ በነገሥታቱ አካባቢ የነበረው በቤተ ክርስቲያን ስም መጠቀም፣ በደርግ ሥርዓት የነበረው ተፅዕኖ፣ የዘመናችን ወገንተኛነት ቤተ ክርስቲያን ያጋጠሙዋት ፈተናዎች ናቸው፡፡

በፈተናዎቹ ያገኘቻው ድል፣ የጉባኤያቱ ክርክሮች ያስገኙዋቸው የሊቃውንት ጥልቅ ትምህርቶች፣ ነገሥታቱ ለቤተ ክርስቲያን የነበራቸው ወገንተኝነት ፣ የወጣቶች መነቃቃትና ወደ ቤተ ክርስቲያን

www.zeorthodox.org

መምጣት፣ የስብከተ ወንጌል መስፋፋት፣ የኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሹመት፣ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ያለን ውክልና ከፍ ማለት ከመልካም ጎኖች ይጠቀሳሉ ፡፡

## ተግባር

- ከዘመናዊነት እና ከለውጥ ጋር የሚመጡትን ገንቢ እና ጎጂ ጎኖች ከክርስትና አንጻር ተወያዩባቸው፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. በፋሽት ጣልያን የወረራ ዘመን (ከ፲፱፻፳፰-፲፱፻፴፫)ዓ.ም ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የደረሰባትን ግፍና መከራ ዋና ዋናዎቹን ግለጹ፡፡
2. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በፓትርያርክነት የተሾሙት አባቶች (እስከ አሁን ድረስ ያሉት)ስንት ናቸው? ዝርዝራቸውን ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ካቶሊክ እና ክፍፍሎቹ(አንድ)

## ዐሥራ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- ተማሪዎች ስለ ካቶሊካውያን ክፍፍል ያውቃሉ፤ ለሃይማኖት ከማይጠቅሙ አካሄዶች መጠበቅን ይገነዘባሉ፤ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፤ ያብራራሉ።

**የሚጠና ጥቅስ** ፡- *" ጠላት ይህን አደረገ "* ማቴ.፲፫፥፳፰

**ተጨማሪ ምንባብ**፡- ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ›› ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፤ ‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር›› ቀሲስ ዶ/ር ምክረ ሥላሴ፤ ‹‹General Church History››; Dn.Mebrahtu Kiros(unpublished)

**መግቢያ**፡- በዓለማችን በክርስትና ስም ከሚጠሩት ሃይማኖቶች ትልቁን የሕዝብ ቁጥር የምትይዘው ካቶሊክ ናት። ካቶሊካውያን በብዙ ታሪካዊ ስሕተቶች ከየማዕዘናተ ዓለሙ ይወቀሳሉ። የተወሰኑትን አምነው ይቅርታ ሲጠይቁባቸው ፣ በዝምታ ያለፉዋቸውም አሉ። ከእነኚህ ታሪካዊ ስሕተቶች መሠረታዊውና ምናልባትም ለሌሎቹ ስሕተቶች በር የከፈተው በክርስትናው ዓለም ለተፈጠረው መከፋፈል የነበራቸው አደገኛ ሚና እና ይህንኑ ጉዳይ የያዙበት መንገድ ያስተላለፈው ክፉ ልማድ ነው። ለምሳሌም ፡- የእስክንድርያውን ቅዱስ ዲዮስቆሮስን በጉባኤ ክርክር ሳይደረግ አስወግዘው በግዞት እንዲሞት አድርገዋል። ይህ ክፉ ተግባር ለሁዋለኞቹ ጭካኔዎችና ኢ ክርስቲያናዊ ግድያዎች ክፉ ትምህርት እና ልምድ ነበር። በዚህ መነሻነት፡- የተሳሳቱ መሠረተ እምነቶች፣ የተበላሸ አስተዳደርንና ቋንቋን መሠረት ባደረገ ጎሰኝነት ምክንያት ካቶሊክ መከፋፈልን አስተናግዳለች።

ከላይ በዓላማው እንደተገለጠው እነኚህ ክፉ ድርጊቶች በክርስትና ስም የተፈጸሙ በመሆናቸው ፣ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችንና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎታችን በጥንቃቄ የሚያግዙ ከክፉ ተግባራት የምንጠበቅበትን ትምህርቶች ይሰጡናል። የዛሬው ትምህርታችንም የመጀመሪያውን ክፍል ያስቃኘናል።

www.zeorthodox.org

**መምህር**፡- አባሪ ሆኖ የተያያዘውን ትምህርት ተማሪዎች በክፍልና በቤት ሥራ መልክ እንዲያነቡና የተረዱትን እንዲያብራሩ ያድርጉ።

# የሳምንቱ ትምህርት

**የሚተኮርባቸው ነጥቦች**

- የሮማ ቤተ ክርስቲያን ‹‹ካቶሊክ›› የሚለውን ስያሜ መጠሪያዋ ያደረገችው መቼ ነው?
- በዚህ ስያሜ ዙርያ የተሰባሰቡት የትኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ?
- የክፍፍሎቹ መልክ ምን ይመስል ነበር ?

# ዋናው ክፍለ ትምህርት

**ስያሜው**

**ካቶሊክ** ፡- ማለት ‹‹***የሁሉም***››፣ ‹‹***ዓለም አቀፋዊት***›› ***ማለት ነው፡፡*** ይህንን ቃል የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ደቀ መዝሙር እና የአንጾኪያ (ሶሪያ ) ሊቀ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ አግናጥዮስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲያብራራ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቅሞበታል፡፡ ካቶሊክ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ባሕርይ መገለጫና ስያሜዋም ነው፡፡ ነገር ግን ሮማውያን ይህን ስያሜ ለራሳቸው የሰጡት ከቃሉ መሠረታዊ ፍቺ በተቃራኒ፤ የሮምን የበላይነት ተቀበሉ በሚል አስተሳሰብ አጅበው ነበር፡፡

በ፬፻፶፩(451) ዓ.ም በኬልቄዶን በተደረገው ጉባኤ ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ነው፣ የሮሙ ፖፕ የበላይ ነው የሚሉ ውሳኔዎችን በሮም የበላይነት የተደረገው የኬልቄዶን ጉባኤ አሳለፈ፡፡ ይህ ስሕተት መሆኑን የተቃወሙትን የእስክንድርያና የአንጾኪያ አባቶችንም በውግዘት፣ በእስርና በግድያ አሳደዱ፡፡ ከዚያም ካቶሊክ የሚለውን ስያሜ ለራሳቸው ሰጡ ፡፡ ከላይ ሲታይ፤ ***የሁሉም የሆነች ቤተ ክርስቲያን፤*** የሚል ሲመስል ፤ ሒደቱ እና የውሳኔው ሐሳብ የሚነግረን ግን፤ ሮም **የሁሉም** የበላይ ነች፤ የሚል ነው፡፡

በግብጽ፣ በሶሪያ፣ በሕንድ፣ በአርመንና በኢትዮጵያ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናትም ከኒቂያ ጉባኤ (፫፻፳፭(325) ዓ.ም) ጀምሮ ዓለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን በምትጠራበት ‹‹***ኦርቶዶክስ***›› ስያሜ ቀጠሉ፡፡ (**መምህር** ፡- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከ፭ኛ-፮ኛ መ/ክ/ዘ፤ በሚለው ትምህርት ያለውን ድኅረ ኒቂያ ታሪክ እንዲያነቡና እንዲከልሱ በማድረግ ያወያዩዋቸው፡፡)

ከ፭ኛው - ፰ኛው ክፍላተ ዘመናት በሁለቱም ወገን የነበሩ ደጋግ አባቶች ልዩነቱን ለማጥበብ ፣ ስሕተቱንም በመቃወም እና መከፋፈሉን በማስወገድ ወደ አንድነት ለመመለስ ጥረዋል፡፡

www.zeorthodox.org

## በሮም ካቶሊክ የሚመሩት - ምዕራባውያንና ምሥራቃውያን

ከ፬፻፶፩-፲፻፶፬(451-1054) ዓ.ም በሰሜናዊ እስያ፣ በምዕራብና በምሥራቅ አውሮፓ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት፤ በሮም መንበር እና ፖፕ እየተመሩ ራሳቸውን ‹‹ካቶሊክ›› ሲሉ፤ በኦርቶዶክሳውያኑ ‹‹መለካውያን›› (ተገዢዎች ወይም የንጉሥ ፈቃድ ፈጻሚ) ይባሉ ነበር፡፡

***መከፋፈሉ፡-*** እነኚህ ከላይ ያየናቸው አብያተ እስከ 11ኛው መ/ክ/ዘ አብረው ቆይተው ተለያይተዋል፡፡ ለመከፋፈላቸው ከ8ኛ-11ኛው መ/ክ/ዘ የተከሠቱ ዓለማዊና መንፈሳዊ ምክንያቶች ነበሩት፡፡

**1. *ዓለማዊ ምክንያቶቹ፡-*** ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሮም እና በቁስጥንጥንያና ለሁለት በተከፈለችው የሮማ ግዛት የበላይ ለመሆን በሚደረገው ጥረት የሮም ፖፖች መግባታቸውና ማባባሳቸው በምሥራቅ ያሉትን ከአንድነት የሚያሸሽ ነበር፡፡

ይህን ተከትሎም በወቅቱ ብዙዎች ይጠቀሙበት የነበረውን የግሪክን ቋንቋ የበላይነት በላቲን ለመተካት ሮማውያን ያደረጉት ጥረት የባህልና የማንነት ጥያቄ አስነሥቶ ያለመግባባቱ እንዲሰፋ አድርጎታል፡፡

**2. *መንፈሳዊ ምክንያቶች፡-*** የሮሙ ፖፕ የበላይና ትክክል ነው የሚለው የልዮ ሐሳብ እየሰፋ ሄዶ በምድር ላይ ያለች ማንኛዋንም ቤተ ክርስቲያንን ይቆጣጠራል በሚል በቢዛንታይን አብያተ ክርስቲያናት የውስጥ ጉዳይ የሮም ፖፕ መግባትና ውሳኔ ማሳለፍ ጀመረ፡፡ የቁስጥንጥንያ ፖትርያርኮች ለስምምነት እና ስሕተቶችን ለማረም ቢጥሩም ሮማውያን ከበላይነት ስሜቱ ጋር የተሳሳቱ ትምህርቶችን ጨምረው ተቀበሉን በማለታቸው ልዩነቱ ሰፋ፡፡ ከእዚህም ዋናው መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ይሠርጻል ማለታቸው ነው፡፡

በካቶሊክ እና በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተቀባይነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ስለመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ የተወሰነው ‹‹***መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይሠርጻል***›› የሚል ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ጌታችን ያስተማረን ‹‹***ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ***›› ዮሐ.፲፭፥፳፮ ብሎ ነው፡፡ ነገር ግን የሮሙ ፖፕ ከዚህ በተቃራኒው ***መንፈስ ቅዱስ ከአብና እና ከወልድ ይሠርጻል*** የሚል ማሻሻያ በማድረግ አዲስ የሃይማኖት መግለጫ አዘጋጅተው በመላው ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች እንዲቀበሉት በማስገደድ ላኩ፡፡

ምሥራቃውያኑም ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከአባቶች ትምህርትና ጉባዔያት የወጣ ስለነበር ተቃወሙት ፡፡ በዚህ ባለመስማማታቸውም በ፲፻፶፬(1054) ዓ.ም ተወጋግዘው ተለያዩ፡፡ ካቶሊካውያን እዚህ ላይ የፈጸሙት ስሕተት በ፬፻፶፩(451) ዓ.ም ከፈጸሙት ጋር በዓላማና በአካሄድ ተመሳሳይ ነው፡፡ የሚለያየው በሰዎቹና በዘመኑ ነው፡፡ ዋናው ዓላማው የሮም የበላይነት ሲሆን አካሄዱ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ውይይት ተደርጎ ውሳኔ ሳይሰጥበት በማውገዝና በማስገደድ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው፡፡

እዚህ ላይ ካቶሊካውያኑ ለሚከሠቱ ችግሮች በመንፈሳዊው መንገድ (ጸሎት እና ትምህርት)፣ ውይይት፣ እርቅ እና በሰላም ከመፍታት ይልቅ፤ ኃይል እና የበላይነት በመምረጣቸው ወደ አደገኛ

www.zoorthodox.org

ስሕተት ሄደዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ምዕራባውያኑ ካቶሊክ ምሥራቃውያኑም የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተብለው ተለያዩ፡፡

ካቶሊክ በሚለው ስያሜ እና እምነት የቀጠሉት የምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች (ከሮም እስከ እንግሊዝ) ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ በኋላም ባደረጉት ስምምነትና መስፋፋት በምሥራቅ አውሮፓ በደቡብ አሜሪካ በእስያ እና በአፍሪካ ተስፋፍተዋል፡፡

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ በሚል መጠሪያ ዋና መንበራቸውን በቁስጥንጥንያ ያደረጉትም፣ ራሳቸውን የቻሉ እና በየፓትርያርኮቻቸው የሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ ሲሰባሰቡ ከእኩዮቹ ፓትርያርኮች የመጀመሪያው በሚል ማዕረግ የቁስጥንጥንያው አባት ስብሰባውን በማስተባበር ይመራል፡፡ ዋናው ውሳኔም በሲኖዶሱ ይሰጣል፡፡ ሁሉም ፓትርያርኮች እኩል አንድ አንድ ድምፅ አላቸው፡፡ ከካቶሊክ ጋር የሚቀበሉዋቸው ሰባት ዓለም አቀፍ እና በራሳቸው ያደረጉዋቸው ከዐሥር የሚበልጡ ጉባኤያትም አሉ፡፡

በምሥራቅ እና ደቡብ ምሥራቅ አውሮፓና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙት እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በሚገኙበት ሀገሮች ስም፡- ግሪክ፣ ሩስያ፣ ቤላሩስ፣ ዩክሬይን፣ ሚልዶቫ፣ ጆርጂያ፣ ሩማንያ፣ ሰርቢያ፣ ሞንቴኔግሮ፣ ቡልጋሪያ፣ ሜቂዶንያ፣ ቆጵሮስ፣ ሊባኖስ፣ ሶሪያ፣ ዮርዳኖስ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ይባላሉ፡፡ አሁን ያላቸው የተከታዮቻቸው ብዛትም ሦስት መቶ ሚልዮን ነው፡፡

ልዩነቱን ለማጥበብ እና ወደ አንድነት ለማምጣት ብዙ ጥረት ቢደረግም መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ምክንያቶች ላይ በተደራረቡት ክሥተቶች አልተሳካም፡፡ ከእነዚህም ፡- በሰባተኛው መ/ክ/ዘ የተነሣው እስልምና ከደቡብ ዐረቢያ ተነሥቶ እስከ ግብጽ፤ ከዚያም አልፎ ኢየሩሳሌምን ሲወር፤ በምዕራብ አውሮፓ ነገሥታት መሪነት እና በምሥራቃውያኑና በሮም ፖፖች ጥሪ የመስቀል ጦረኞች ከአውሮፓ ተነሥተው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ተከላክለዋል፡፡ በምሥራቃውያኑ ላይም ጉዳት አድርሰዋል፡፡ በተለይም በ፲፪፻፬(1204) ዓ.ም የቁስጥንጥንያ የሀግያ ሶፍያ ቤተ ክርስቲያን መበዝበዛቸው ልዩነቱን አስፍቶታል፡፡ (ለዚህ ፖፕ ጆን ፖል 2ኛ እ.አ.አ በ፳፻፬ (2004)ዓ.ም ይቅርታ ጠይቀውበታል)

የምሥራቁ የቁስጥንጥንያ መንግሥት በ1453 ዓ.ም በእስልምና ተሸነፈ፡፡ በታላቁ ቆስጠንጢኖስ
www.zeorthodox.org
የተሠራችው ውቧ የሀግያ ሶፊያ ቤተ ክርስቲያንም መስጊድ ሆነች ፡፡ የምዕራቡ ሮምም የረባ ድጋፍ ማድረግ አልፈለገም፡፡ የእርቁ ጉዳይም በዚያው ሲቀር በምሥራቅ ያሉ ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት በፍሎሬንስ ጉባኤ (፲፬፻፴፱(1439) ዓ.ም) ማስተካከያ እና ቀድሞ በነበራቸው ግንኙነት ከሮም ጋር ተቀላቀሉ፤ አብዛኛዎቹም በእምነታቸው ጸኑ፣ የቀሩትም ሰለሙ፡፡

## ማጠቃለያ

1. ካቶሊክ በ፬፻፶፩(451) ዓ.ም በሮም መንግሥት እና ርእዮት ላይ ተመሥርታ የበላይ ለመሆን ያመጣችው ሐሳብ ክርስትናን ከፋፍሎአል፡፡
2. ካቶሊካውያን በመንፈሳዊና ዓለማዊ ጉዳዮች ሲወዛገቡ ኖረው በ፲፻፶፬(1054) ዓ.ም ተለያይተዋል፡፡
3. የመለያየቶቹ ምክንያቶችም የበላይ የመሆን ፣ የዶግማ እና የፖለቲካ ልዩነቶች ነበሩ፡፡

## ተግባር

1. ክርስትና የትህትና ሃይማኖት ነው። ጌታችን፤ *‹‹ደግሞም ማናቸውም ታላቅ ሆኖ እንዲቈጠር በመካከላቸው ክርክር ሆነ። እንዲህም አላቸው ... እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፥ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን። በማዕድ የተቀመጠ ወይስ የሚያገለግል ማናቸው ታላቅ ነው? የተቀመጠው አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ፡፡››* ሉቃ.፳፪፥፳፬-፳፯ እንዳለ ከጌታችን ተምረን የምንኖረው የክርስትና ሕይወት በትሕትና ራስን ዝቅ ማድረግ እንጂ ትዕቢት አይደለም፡፡ ከዚሁም ጋር ሊዮን እና ተከታዮቹ እንዳሉት፤ ጴጥሮስ እና መንበሩ ይበልጣሉ ብሎ፤ ጌታችን አላስተማረም፡፡ እኛም በሕይወታችን ሌላውን ማክበር እንጂ በበላይነት ስሜት ፣ በንቀትም ሌላውን ማወክ መንጋውንም መረበሽ አይገባንም ፡፡
2. ሃይማኖት በጥንቃቄ የሚሠራ ነው፡፡ የሃይማኖትን ሥራ በግድ የለሽነት፣ በይሉኝታ ወይም በእልህ አይሠራም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ የተከፋፈሉትን ምእመናን እንዲህ ይመክራል፡፡ *የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንፃል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንፅ ይጠንቀቅ። ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንፅ፥ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፥ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል፡፡ ማንም በእርሱ ላይ ያነፀው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፡፡ የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፥ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል፡፡ ፩ኛ ቆሮ.፫፥፲-፲፭* እኛም ሃይማኖትን ከዓለማዊ ልምዶቻችንና አስተሳሰባችን ለይተን፣ በእግዚአብሔር ብቻ በመታመን ልንይዘው ይገባናል ፡፡

www.zeorthodox.org

**አባሪ ጽሑፍ** (ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መማሪያ የተወሰደ።)

ካቶሊካውያን ከ11ኛው መ/ክ/ዘ በኋላ በአንድነት መዝለቅ አልቻሉም ። ከ8ኛው-11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሂደት እና በቅጽበት በተከሠቱ አለመግባባቶችና በሃይማኖታዊ ልዩነቶች ለሁለት ተከፈሉ። እነዚህ አለመግባባቶች ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ሲሆኑ የሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ነበሩ። በምዕራባዊው የሮም ግዛት የተሞከረውን ፖለቲካዊ የበላይነት የሮም መንበር መደገፉ ፣ የባህልና ቋንቋ ልዩነትን ማስተናገድ አለመቻል፣ የቤተ ክርስቲያናቱ የመናብርት እኩለነት ላይ ውስጣዊ አለመግባባት መከሠቱና እና በመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ላይ የተነሣው ሃይማኖታዊ ልዩነት እንደ ምክንያት በዋናነት ይጠቀሳሉ ። እነዚህንም በመቀጠል እናያለን ፦

1. **ዓለማዊ ምክንያቶች፦** ለካቶሊካውያን ለሁለት መከፈል ፖለቲካውን መሠረት ያደረጉ መከፋፈሎች ይቀድማሉ። የዚህ መነሻውም የግዛቱ መከፋፈል ነበር። ከሦስተኛው መ/ክ/ዘ ጀምሮ ከሰሜናዊ አውሮፓ እየተነሡ ሮምን የሚያጠቁት የበርበራውያንን ወረራ ለመከላከል እና የተለጠጠውን ሰፊ ግዛት ለማስተዳደር እንዲመች የሮም ግዛት በምዕራብ እና በምሥራቅ ለሁለት ተከፈለ። ይህን የአስተዳደር ስልት ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ በሁለት ቄሳሮች እንደራሴነት እና በሁለት አውግስጦሶች ንጉሥነት በማደራጀት ጀምሮታል። ታላቁ ቆስጠንጠኖስም የቁስጥንጥንያን ከተማ በመመሥረት እና ሌላኛዋ የሮም መንግሥት ማዕከል በማዘጋጀት አጠናከረው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮም ቁስጥንጥንያ የሮም መንግሥት ሌላኛዋ ማዕከል ሆነች። ከዚያም ምዕራቡ በሮም ከተማ፤ ምሥራቁም በቁስጥንጥንያ ከተማ ማዕከልነት ይተዳደሩ ጀመር።

በዚህ መንገድ እስከ 8ኛው መ/ክ/ዘ የኖረው የሮም መንግሥት እያደር መዳከም ጀመረ። በተለይም የሮሜ ከተማ ማዕከላዊነት በበርበራውያን ተደጋጋሚ ወረራ ይበልጥ ተዳከመ። የሮምን መንግሥት ለማጠናከር እና የሮምን የበላይነት ለመመለስ የጣሩ በርካታ የጦር መሪዎችና ነገሥታትም ነበሩ። ከእነዚህም ከጀርመን የተነሣውና ***ቅዱስ የሮም ልዕለ መንግሥት*** ለመመሥረት የተነሣው ቻርልስ ምሥራቁን ለመጠቅለልና ለማስተባበር ያደረገው ጥረት በምሥራቃውያኑ አልተወደደለትም። ይህንን በመደገፍም የሮም ፖፕ በ፰፻(800) ዓ.ም በዓለ ልደት ቅብአ መንግሥት በመቀባት ያሳየው ፖለቲካዊ ወገንተኝነት ምሥራቃውያኑን አስከፋ። ይህና ሌሎች መሰል ዓለማዊ ምክንያቶች ካቶሊካውያን በሂደት እንዲከፋፈሉ ያደረገ ቀዳሚ ምክንያት ሆነ።

www.zeorthodox.org

2. **የባህል ተቃርኖ ፦** የተለያየ የማንነት መገለጫ ያላቸው ሕዝቦች በአንድነት ለመኖር የባህል እና የቋንቋ መወራረስ እና መከባበር አስፈላጊ ነው። በተለይም በሮም - ቁስጥንጥንያ መንግሥት፤ የላቲን ቋንቋ ተናጋሪው የሮም መንግሥት በስፋት የሚነገረውን ግሪክን መጠቀሙና የግሪክ መስፋፋት የአንድነቱ ጠንካራ መሠረት ነበር። እየቆየም ላቲን የሮም፣ ግሪክ የቁስጥንጥንያ ቋንቋ

ሆነው አደጉ፡፡ በምዕራብ ግሪክን፣ በምሥራቅም ላቲንን የማያውቁም እየበዙ መጡ፡፡ በቋንቋ አለመወራረስና አለመዋሐድን ተከትሎም ምሥራቃውያኑ በላቲን ምዕራባውያኑም በግሪክ የተጻፉትን መጻሕፍትና ሐሳቦችን ለመረዳት አስተርጓሚ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ ይህ አለመግባባት አድጎም አንዱ የሌላውን ወደ አለመፈለግ አደረሰው፡፡ በተለይም ቅዱስ የሮም ልዕለ መንግሥትን የመመሥረት ሓሳብና ጥረት መነሣቱን ተከትሎ የምሥራቁ የቢዛንታውያን ክፍል ማንኛውንም ምዕራባዊ ተፅዕኖ ፣ ባህልና ቋንቋ እንዳይቀበሉ ገፋቸው፡፡ ይህም በምሥራቅና በምዕራብ የነበረው የሮም ክፍል እንዲሰነጠቅ የገፋ ተጨማሪ ምክንያት ነበር ፡፡

3. **የአብያተ ክርስቲያናት እውቅና፡-** በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን የኢየሩሳሌም፣ የእስክንድርያ፣ የሮም፣ የቁስጥንጥንያ፣ የአንጾኪያ እና የቂሣርያ መናብርት ይታወቃሉ፡፡ እነዚህም በሐዋርያት ትምህርት የተመሠረቱ ሲሆኑ፤ በዘመነ ሐዋርያትም ሆነ እስከ ፬፻፶፩(451)ዱ ዓ.ም ጉባኤ በእኩልነት ይታዩ ነበር፡፡ በኬልቄዶን ጉባኤ ፖፕ ልዮ ሮም በቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ተመሠረተች የበላይ መንበር ናት፤ ብሎአል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ የሮሙን ፖፕ የበላይነት የተቃወሙት የጥንታውያን የኦርቶዶክስ አባቶች ( እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ )፤ ሁሉም መናብርት እና ፓትርያርኮች እኩል ናቸው፡፡ የበላይ እና የበታች መንበር የለም ሐዋርያት ‹‹***ማን ይበልጣል?***›› ብለው ሲጠይቁትም ጌታችን ያላቸው፤ ***ታላቅ ለመሆን የሚፈልግ ታናሽ ይሁን ነው እንጂ የበላይና የበታች መንበር አልሠጠንም፣*** ሌላው ቀርቶ ክርስቶስ ያስተማረባትና መንፈስ ቅዱስ የወረደባት የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እንኳዋን የበላይ አልተባለችም ብለው መከሩ፡፡

ነገር ግን ምዕራባውያኑና ምሥራቃውያኑ ምክሩን ሳይቀበሉ ለቤተ ክርስያን የማይገባ የግፍ ድርጊት ፈጽመው እና አውግዘው ተለዩ፡፡ የሐሰት ትብብር ቢዘገይም በእውነት ይበተናልና የፖለቲካና የባህል ተቃርኖው ማደጉን ተከትሎ ምሥራቃውያኑ የሮሙን ፖፕ የበላይነትና የሌሎችን መንበረ ፓትርያርኮች እኩልነት አነሡ፡፡

ምሥራቃውያኑ፤ ሐዋርያዊ መንበር እና አባቶች ያሉዋቸው ራሳቸውን የቻሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እኩል ናቸው ሲሉ፤ ሮማውያኑ፤ ሐዋርያዊ መሠረት ያላት የሮም መንበር ብቻ ናት አሉ፡፡ በቁስጥንጥንያውያን ዓለማዊው የሥጋ አስተዳደር በንጉሥ ሲመራ፤ በበርበራውያን ተደጋጋሚ ወረራ በተዳከመችው ሮማ በፖፑ የበላይነት የሚመራው አስተዳደር ከቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አመራር ጋር ጠቅሎ ማዘዝ ጀመሩ፡፡ ይህንን ተከትሎም የሮሙ ፖፕ ፍጹም የበላይት ገነነ፡፡ የቁስጥንጥንያ አባቶችም ጣልቃ ሳይገቡ ዝም አሉ፡፡ ነገር ግን ፖፑ የበላይነቱን በምሥራቅ ለማስፋት በመጣሩና የአብያተ ክርስቲያናቱን ነጻነትና እኩልነት ባለመቀበሉ የፖፑ የበላይነትና ውሳኔዎችን የተቃወሙት ምሥራቃውያን የሮሙ ፖፕ የክብር ቅድምና እንጂ የሁሉም የበላይነት

www.zeorthodox.org

አልተቀበሉም። የመጨረሻው ሃይማኖታዊ ውሳኔም በዓለም አቀፍ ጳጳሳት በሚካሄደው ጉባኤ መወሰን አለበት እንጂ በሮሙ ፖፕ አይደለም አሉ። በሂደትም ፖፑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች በምዕራቡ ብቻ ተወስነው በምሥራቅ ቀባይነት አጡ። ይህም ልዩነቱን የእኩልነት (በእኩልነት እውቅና የማግኘት) አደረገው፤ ይህንኑ የአብያተ ክርስቲያናትን ነጻነት ሮም አለመቀበልዋን ተከትሎም የመከፈል መሰንጥቅ ሁኔታ በገሀድ ታየ።

4. ***የመሠረተ እምነት ልዩነት - ሥርጸተ መንፈስ ቅዱስ፡-*** በካቶሊካውያኑም ሆነ በጥንታውያን ኦርቶዶሳውያን እስከ 8ኛው መ/ክ/ዘ ማብቂያ በጸሎተ ሃይማኖት ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ የነበረው እምነት፣ ትምህርትና ውሳኔ ዛሬ እኛ እንደምንጸልየው፤ ***ከአብ በሠረጸ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፤*** የሚል ነበር። ***መንፈስ ቅዱስ ከአብ እና ከወልድ ይሠርጻል፤*** የሚል አዲስ ትምህርት በስፔን ተጀምሮ በፈረንሳይና በጀርመን ተስፋፋ። በኋላም በቻርሊማኝ በሥዕላት በተደረገው ጉባኤ ከአብ በሚለው ላይ ከአብና ከወልድ የሚሠርጽ የሚል ተጨመረበት በ፰፻፰(808) ዓ.ም የነበሩት የሮም ፖፕ ሊዮ 3ኛ በዋናው የሃይማኖት ውሳኔ ላይ መጨመር ስሕተት ነው ሲሉ ተቃወሙ። ይህ በምሥራቅና በምዕራብ ካቶሊካውያን ስሕተትነቱ ተረጋግጦ ውድቅ ከተደረገ ከሥልሳ ዓመታት በኋላ የሮሙ ፖፕ ኒኮላስ ይህን ለሚያቀነቅኑት ለጀርመናውያን ሙሉ ድጋፍ እና እውቅና ሰጠ። ይህን አዲስ ትምህርት ምሥራቃውያኑ፡- በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ፣ በካቶሊክና በሌሎቹም ተቀባይነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ያልተወሰነና በአባቶች ትምህርት የሌለ ፍጹም ስሕተት በመሆኑ ተቃውመው አወገዙ ።

ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ - በ፲፻፶፬(1054) ዓ.ም ካቶሊክ በጸሎተ ሃይማኖት አካተተችው። የሮሙ ፖፕ ሊዮ 9ኛ በምሥራቅ ለነበሩት ይህንኑ አዲስ ውሳኔ አስተላለፈ። የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ሰርግዮስም የአባቶች ዝርዝር ካለበት መዝገብ ሊዮ 9ኛን ሰረዘው። ይህን ተከትሎም ቢዛንታይንና ሮም የቅዱስ ቁርባን አንድነታቸው ተቋረጠ። በዚህ ያላቆሙትና የሮምን የበላይነት ብቻ የፈለጉት ሮማውያን በቢዛንታይን ግዛት ያሉት የግሪክ ተናጋሪዎች ላቲንን እንዲጠቀሙ ማስገደድ ጀመሩ። የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ሚካኤልም ላቲኖችም ግሪክ እንዲጠቀሙ ጠየቀ። በስምምነት ለመፈጸም የፖፑን ስም በአባቶች ዝርዝር መልሶ አካተተና ለውይይት ተዘጋጀ። ሊዮም ወዲያው ለውይይቱ መልእክተኞችን ላከ። ውይይቱም ካለ ውጤት ተበተነ። ሁለቱም ተወጋግዘው ተለያዩ ። በተጨማሪም የቀሳውስት ጋብቻ በምሥራቅ ተፈቅዶ በምዕራብ መከልከሉና በምስጢረ ቁርባን ዝግጅት መለያየታቸውም ይጠቀሳል። በመስቀል ጦርነት ከምዕራባውያኑ የተነሡት የመስቀል ጦረኞች ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት፣ የምሥራቅ ክርስቲያኖች ላይ የፈጸሙት ማግለልና ግፍ ዘላቂውንና እስከ አሁን የቀጠለውን ልዩነት አመጣ።

www.zeorthodox.org

ይህም የመጨረሻውና ዋናው የመለያየት ምክንያት ሆነና በቤዛንታይን (በምሥራቅ) ያሉት ዋና መንበራቸው ቁስጥንጥንያ ሆኖ ‹‹የምሥራቅ ኦርቶዶክስ›› ተባሉ። ምዕራባውያኑም በሮም ማዕከላዊነት ‹‹ካቶሊክ›› የሚለውን መጠሪያ ይዘው በ፲፻፶፬(1054) ዓ.ም ተለያዩ።

**ጥያቄዎች፡-**

1. ካቶሊክ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ካቶሊካውያን የተከፋፈሉበትን ምክንያቶች
   *ሀ. ዓለማዊ ምክንያቶች*
   *ለ. ባህላዊ ምክንያቶች*
   *ሐ. የአብያተ ክርስቲያናትን እውቅና በተመለከተ*
   *መ. የመሠረተ እምነት ልዩነት፤ አራቱን ርእሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ አጭርና ዋና ዋና ጉዳዮችን በማብራራት ግለጹ።*

www.zeorthodox.org

# ካቶሊክ እና ክፍፍሎቹ(ሁለት)

## ሃያኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለካቶሊክ እና ፕሮቴስታንት መከፋፈል ታሪክ ያውቃሉ፤ አንድ ስሕተት በሌላ የባሰ ስሕተት እንደማይታረም ተገንዝበው መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄ በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ ፡-** *"ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ያለ እድፍና ያለ ነቀፋ ሆነህ ትእዛዙን ጠብቅ "* ፩ኛ ጢሞ.፮፥፲፬

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ››፣ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፤ ‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር›› ቀሲስ ዶ/ር ምክረ ሥላሴ፤ ‹‹General Church History;›› Dn. Mebrahtu Kiros(unpublished)

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን የካቶሊካውያንን መከፋፈል የመጀመሪያውን በምዕራብ እና በምሥራቅ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት የተከሰተውን መከፋፈል አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የፕሮቴስታንትንና የካቶሊክን መከፋፈል እንማራለን፡፡

ዐሥራ ስድስተኛው መ/ክ/ዘ በአውሮፓ ሀገሮች በሁሉም ዘርፎች መነቃቃት የታየበትና ብዙ ግኝቶችና ለውጦች የተካሄዱበት ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ዘመነ ህዳሴ (renaissance age) ይባላል፡፡ በዚህ ዘመን በታሪክ ከታዩት ክሥተቶች አንዱ ከካቶሊካውያን የወጣው የፕሮቴስታንቲዝም ንቅናቄ ነው፡፡ ይህን ተከትሎም የአንግሊካን እና ሌሎች በርካታ የፕሮቴስታንት ክፍልፋዮች ወጥተዋል፡፡

በዚህ ክፍል ሁለቱ ጽንፎች (ካቶሊክና ፕሮቴስታንት) የሠሩትን ሌላ ስሕተት እናያለን፡፡ በዘመናት ያልታረመውና የባሰበት የካቶሊካውያን አስተዳደር፣ የመሰረተ እምነት እና የአካሄድ ስህተት በአንዱ አቅጣጫ፤ የፕሮቴስታንቶች የተሳሳተ ስሌት በሌላው ማዕዘን ተሰልፈው የዘመኑን መልካም ዕድሎች አባከኑ፡፡ ከታሪካዊው ዳራ ለመነሣት እንዲያመችን የአውሮፓውያንን ዘመነ ሕዳሴ እናስቀድማለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

**ዘመነ ህዳሴ በአውሮፖ፡-** ከዐሥራ አምስተኛው መ/ክ/ዘ ጀምሮ አውሮፓ በኪነ ጥበብ፣ በፖለቲካ እና በሳይንሳዊ ግኝቶች ለውጦችን ያስተናገደችበት ዘመን ነው፡፡ በ፲፬፻፶፮(1456) ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የኅትመት ማሽን በጉተንበርግ በመሠራቱ ዓለማዊና መንፈሳዊ መጻሐፍት በብዛት ተሰራጩ፡፡

ውጤቱም አብዛኛው ሕዝብ እንዲነቃና በዕውቀት እንዲመራ ምክንያት ሆነ። ይህም ንቅናቄዎችን አስነሣ። ሕዝቡም በንጉሡና በፖፑ ላይ ጥያቄና ተቃውሞ እንዲያነሣ አደረገው። ይህም ካቶሊክን ከውስጥ ለሚቃወሙ የሃይማኖታዊ ለውጥ አራማጆች ወርቃማ አጋጠሚ የፈጠረላቸው ሆነ።

በወቅቱ የነበረው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ አስተዳደር በሥነ ምግባር ጉድለት፣ በዘረኝነት የተሞላ መሆኑ ፣ ብዙዎችን የሚያሳዝን ነበር። የካቶሊክ ምሁራን በአስተዳደር ችግሮች ሳይገደቡ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ፣ ሥርዓት እና ትውፊት ላይ ጥያቄ ሲያነሡ እና ለውጥ ሲሞክሩ በአካልና በሞት ተቀጡ ። ዊልያም ቴንዳየል ከእነዚህ አንዱ ነው።

እነ ሉተርም ምንኩስናን፣ የቅዱሳንን ምልጃ፣ ትውፊትን፣ ክህነትን ይቃወሙ ነበር። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ለእነዚህ መልስ ከመስጠት ይልቅ በኃይል ለማሸነፍ ሞከረች። አብዛኛው ሕዝብ በዚህ ሂደት በተሰላቸበትና ግራ በተጋባበት ወቅት ፖፕ ሊዮ ከዓለማችን ድንቅ ቅርሶች አንዱ የሆነውን የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ ክርስቲያን ግንባታ ለመፈጸም አቅም ስላጠራቸው « ***የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ሰርትፊኬት*** » ብለው መሸጥ ጀመሩ ። ይህም ውስጥ ውስጡን ሲታመስ ለነበረው የለውጥ እንቅስቃሴ መልካም አጋጣሚ ሆኖ ተገኘና ፕሮቴስታንቶች የተሓድሶ ለውጥን በማቀንቀን ተነሡ።

## ፕሮቴስታንቲዝም - ተቃውሞ

ፖፕ ሊዮ ዐሥረኛ የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ የተባለችዋን ሰርተፍኬት እንዲሸጥ ወደ ጀርመንዋ ዊተንበርግ ጆን ቴዝልን ላኩት። ቴዝል በዊተንበርግ ተገኝቶ ሰርተፊኬቱን የያዘ ኃጢአቱ እንደሚሰረይና መንግስተ ሰማያት እንደሚገባ እየገለጸ፤ በሲዖልና በመካነ ንሥሐ ላሉት ወገኖቻቸው ሰርተፊኬቱን ለመግዛት ገንዘባቸው ባወጡበት ቅጽበት ወደ ገነት እንደሚገቡ አስተማረ። ሉተር ይህንን ድርጊት ተቃውሞ፤ ‹‹የሚያድን እምነት ነው እንጂ ትኬት መግዛት አይደለም›› አለ ። በአንድ እሑድም ሉተር ባለ ዘጠና አምስት አንቀጾች የእምነት አቋሙን በከተማይቱ በተነ፤ በየአብያተ ክርስቲያናቱም ለጠፈ። ይህን ተከትሎ ብዙ ውዝግብና ግጭቶች ተስተናገዱ። ሉተር በካቶሊኩ ፖፕ ሲወገዝ፤ እርሱም የውግዘቱን ደብዳቤ በአደባባይ አቃጠለ። በሂደትም ሰሜናዊ ጀርመን የሉተር ደብባዊው የካቶሊክ ሆነ።

www.zeorthodox.org

በ፲፭፻፳፱(1529) ዓ.ም በስፒረስ(ቆጵሮስ) በካቶሊካውያን ተጽዕኖ ጉባኤ ተካሄደ። የሉተራውያንን አስተምህሮ ኮንነው፤ የሉተር ተከታዮች በማይበዙበት ብቻ የተሐድሶ አራማጆቹ እንዲያስተምሩ እግድ ተጣለ። በዚህ ወቅት ተሐድሶውያኑ የሉተር ተከታዮች ተቃወሙ። በዚህ መነሻነትም ‹‹***ፕሮቴስታንት - ተቃዋሚዎች***›› ተባሉ።

በስዊዘርላንድ በዊልያም ፋሬል እና በጆን ካልቪን፣ በስካንድኒቪያን ሀገሮች (ዴንማርክ፣ ኖርዌይ እና ስዊድን) የሉተር ተከታዮች በንጉሥ ክርስቲያን ሁለተኛ ትብብር፣ በፈረንሳይና በኔዘርላንድ በጆን ካልቪን፤ በኋላም በእንግሊዝ በዊልያም ቴንዳየል መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መነሻነት፤ በካልቪንስቱ በቶማስ ክራንመር መሪነት ፕሮቴስታንቲዝም በተሐድሶ ንቅናቄ አራማጆች ተስፋፋ።

ካቶሊክ በመጀመሪያ በማውገዝ፣ ከዚያም ኢንኩዚሽን (inquisition) በተባለ የቅጣት ተቋም አማካይነት ከተጠየቅ አካሄድ እስከ ፍርድ ከዚያም እስከ አካል ቅጣትና ግድያ የሚደርስ እርምጃ በመውሰድ፣ የተሐድሶ ንቅናቄ አራማጆችን (ፕሮቴስታንቶችን) ለመግታት ሰፊ ዘመቻ አካሄደች።

በኋላም ሕልውናዋን ለማስጠበቅ ለተሐድሶዎቹ አጸፋ ( counter reformation ) የሚሰጡ ተቋማትን አደራጅታ በዓለም በማዝመትና ሰፊ ክርክር የተደረጉባቸው ረጃጅም ጉባኤያት አደረገች። ለምሳሌም፡- የኢየሱሳውያን ተልእኮና ለዐሥራ ስምንት ዓመታት የተካሄደው የትሬንቱ ጉባኤ ፲፭፻፵፭-፲፭፻፷፫(1545-1563)ዓ.ም ይጠቀሳሉ።

በዚህ የካቶሊክ እርምጃ እና በትሬንትና ከዚያ በኋላ ባካሄደቻቸው ጉባኤያት ውሳኔ ላቲናዊ ሥርዓተ ቅዳሴ እና የምሥራቅ ሥርዓተ ቅዳሴ፤ (ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ካካቶሊክ ጋር ስምምነት የፈጸሙ ያልናቸው የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትን አስታውሱ) የሚከተሉ ሁለት ክንፎችን በሃያ ሦስት ሥርዓታት አሰባስባ የዓለማችን ከፍተኛ ቁጥር ያላት ሃይማኖት ለመሆን አስችሎታል። በተጨማሪም በአንዳንድ የካቶሊክ ዋና ዋና ቦታዎች ለምሳሌ በሰሜን ጀርመን፣ በደቡብ አሜሪካ ፕሮቴስታንቶችን ማገድ ችላለች።

ሆኖም በካቶሊካውያን ውስጥ የተፈጠረውን ክፍተት እና ክፍፍል ማስቆም አልተቻለም ነበር። ስለዚህ ራሳቸውን ካቶሊክ ብለው የሚጠሩ ከካቶሊክ የወጡ ዐሥራ ስምንት አብያተ ክርስቲያናት በዓለም አሉ ። እነዚህ በቀጥታ በፖፑ የማይታዘዙ ናቸው። ከዚህም ጋር ሮም ዓለም አቀፋዊውን የተሐድሶአውያንን ንቅናቄ ማስቆም አልቻለም። ይልቁንም በአውሮፓ ዘግይቶም በአሜሪካንና ሌሎች የዓለም ክፍሎች በዝተዋል።

የተሐድሶ (Reformation) አራማጆቹ በዋናነት በሉተር ፣ በጆን ካልቪንና በመሰሎቻቸው የካቶሊካውያንን ስሕተት ሲቃወሙ መሠረታዊ ትምህርቶችንም አዛብተዋል። ለምሳሌም፡- ክህነትን ፣ ክብረ ቅዱሳንን፣ ምንኩስናንና የመልካም ሥራን አስፈላጊነት መቃወማቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስን ማንም በራሱ መረዳት ይችላል... ማለታቸው ከፋፍሎአቸዋል። ፕሮቴስታንት፡- ሉተራውያን፣ ካልቭኒስቶች፣ ፐሪስቢተራውያን፣ ኮንግሪጌሽናል፣ አናባፕቲስት፣ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ጴንጠቆስጤያውያን ... ወዘተ የሚባሉ ከሃያ ሁለት ሺሕ በላይ ክፍልፋዮችን ፈጥሯል። የካቶሊክን የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ካህናት አስወጥተው የተኩዋቸው አስጠኝዎች የትችት (Bible Criticism)

www.zeorthodox.org

ስልት አመጡ ይህም አድጎ ወደ አፍራሽ ትችት (Distructive Bible Criticism) ተሸጋገረና መጽሐፍ ቅዱስን በእምነት ከመቀበል ወጥተው ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ ***በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚቸግር ነገር አለ ። ... ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው የሚያጣምሙ*** ›› ፪ኛ.ጴጥ.፫፥፲፮ እንዳለው ሆኑ። የሚገርመው ይህ ፈጣን መከፋፈልና ማፈንገጥ ብዙ ክፍላተ ዘመናትን ሳይፈጅ በአንድ እና በሁለት ክፍለ ዘመን ታላቅ ደረጃ መድረሱ ነው።

የዚህ ችግር መነሻና ማሳያ ከሚሆኑን እና ሉተር በዘጠና አምስቱ አንቀጽ ያነሣቸው ካልቪንና ተከታዮቹም ካስተማሩዋቸው የተወሰኑትን እንይ፦

1. ከቁርባንና ከጥምቀት ውጪ ያሉ ምስጢራትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም በሚል አልተቀበሉዋቸውም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው። ለምሳሌም የሚከተሉትን ጥቅሶች አነጻጽሩ፦ ሜሮን (፩ኛ ዮሐ.፪፥፳)፣ ንስሓ (ዮሐ.፳፥፳፫)፣ ተክሊል (ኤፌ.፭፥፳፪-፴፪) ፣ ቀንዲል (ያዕ.፭፥፲፬-፲፭) ፣ ክህነት (ማቴ.፲፮፥፲፮-፲፰)
2. መጽሐፍ ቅዱስን ተርጓሚ አያስፈልገውም ማንም በራሱ መረዳት መተርጎም ይችላል። ብለዋል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ‹‹ ***ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደለትም*** ›› ፩ኛ ጴጥ.፩፥፲፱ ይላል። ትንቢተ ኢሳይያስን እያነበበ ‹‹ ***የምታነበውን ታስተውለዋለህ..*** ›› ሲባል፤ ***የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል፤*** በማለቱ ከተተረጎመለት፤ የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ጋርም አይስማማም።

   ይህ ስልት መከፋፈልን የሚፈጥር አደገኛ ትምህርት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አስጠኚዎቻቸውና አጥኚዎቹ በመሰላቸው እየተረጎሙ በግለሰቦች መረዳት ላይ የተመሠረቱ ብዙ ክፍልፋዮች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል። በተጨማሪም ይህ መርሕ ጸረ ክርስትና አቋም ያላቸው እና በቅድስት ሥላሴ የማያምኑ ቡድኖችን ፈጥሯል። ለምሳሌ ጆሆቫ ዊትነሶች ፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እና ሞርሞኖችም መጽሐፍ ቅዱስን በግል መረዳት በመተርጎም ሂደት ከፕሮቴስታንት የተገኙ ናቸው።

3. ምንኩስና የሰው ሥርዓት ነው፤ አያስፈልግም፤ ብለዋል። ነገር ግን ምንኩስና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው አኗኗር ነው። ኤልያስ ፣ ዮሐንስ መጥምቅ ፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ ፣ ቅዱስ ጳውሎስ በብቸኝነት እና በድንግልና ኖረዋል ። ጌታችንም ሐዋርያት ሳያገቡ መኖር ይሻላል? ሲሉት፤ ***ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉም አይደለም፤*** ብሎአል። ለእግዚአብሔር መንግሥት ሲሉ ጃንደረባነትን መምረጥንም፤ ***ሊቀበለው የሚወድ ይቀበለው፤*** አለ እንጂ አልተቃወመውም። ማቴ.፲፱፥፲፩-፲፪ የቅዱስ ጳውሎስ ምርጫ ይኸው ኑሮ ነበር። ፩ኛ ቆሮ.፯፥፯ ከዚህም የመረጡት የሚገቡበት ሕይወት መሆኑን እንረዳለን።

www.zeorthodox.org

ከእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች ፕሮቴስታንቶች ትክክለኛ ጉድለቶችንና ስሕተቶች በመቃወም ያገኙትን ድጋፍና ኃይል መልካሙን ነገር ለማጥፋት አዋሉት።

**ወደ ተነሣንበት ታሪክ ስንመለስ፤** ካቶሊካውያኑ በአምባገነንነት፣በፖለቲካ በተቃኘና ሃይማኖታዊነት በጎደለው መንገድ፣ በስለላ በማጥቃትና በስሕተት ላይ ስሕተት በደራረበው አካሄዳቸው በአንድ ጽንፍ ገፉ። የፕሮቴስታንት አራማጆችም በሌላ በኩል ሉተራውያን፣ ካልቪኒስት ወዘተ… በሚሉ የተለያዩ ቡድኖች ካቶሊክን በሌላው ጽንፍ ተቃወሙ። ከሁለቱም ጽንፍ መካከል(via media) ነን፤ ብለው አንግሊካውያን ተነሡ።

**አንግሊካን ፦** ሄነሪ ሦስተኛ ሚስቱን ፈትቶ ለማግባት በመፈለጉ የካቶሊኩ ፖፕ ሲቃወሙት፣ ካልቪኒዝምን በሚደግፈው ሊቀ ጳጳስ ቶማስ ክራንመር ድጋፍ አግኝቶ ሁለተኛ ሚስቱን አገባ። በአጋጣሚው ቀና ያሉት እና ድጋፍ ያገኙት ካልቪኒስቶች በእንግሊዝ ተስፋፉ። በካቶሊካውያኑና በፕሮቴስታንቶች መካከል ያለው ሽኩቻ አድጎ በእንግሊዝ ምድር ብዙ ደም አፋሰሰ። በ፲፭፻፶፱(1559) ዓ.ም የሄነሪ ሦስተኛ ልጅ ንግሥት ኤልሳቤጥ ከሁለቱም ያልሆነና መሐከለኛ (via media) የተባለውን መንገድ መርጣ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያንን መሠረተች። አንግሊካውያን ሁለቱንም ማለትም ካቶሊካውያንና ተሐድሶኣውያን (ካልቪኒስቶች) እንደሆኑ ያምናሉ። ምስጢራትን ይቀበላሉ፣ በኤጲስ ቆጶስም ይመራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባላቸው የትርጉም መንገድም ከፕሮቴስታንቶች በተለይም ከካልቪኒስቶች ጋር ይመሳሰላሉ። በዚህ ዘመን የሴቶችን ክህነት የሰዶማውያንን ጋብቻ በመፍቀድዋም ከካቶሊክ ትለያለች። በአንግሊካን ኅብረት የሚቆጠሩ እና አብዛኛዎቹ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የተመሠረቱ ከአርባ ሁለት በላይ አንግሊካን አብያተ ክርስቲያናት በዓለማችን አሉ ።

በዚህ መንገድ የቀጠለው የካቶሊካውያንና የክፍልፋዮቹ ታሪክ የዛሬውን የምሥራቅና እና ምዕራብ ካቶሊክ የምሥራቅ ኦርቶዶክሶች፣ አንግሊካንና ከሃያ ሁለት ሺሕ የሚበልጡ የፕሮቴስታንት ክፍልፋዮችን በክርስትና ስም ይዞ እስከ አሁን አለ። በዘመናችን ካቶሊክ ዓለም አቀፍ ጉባኤያትን በማካሄድ፤በላቲን አሜሪካ፣በሰሜን አሜሪካ፣በእስያና በአፍሪካ ራስዋን በማስፋፋት፤ በተሐድሶአውያን የተወሰደባትን ለመመለስ በመጣርና ለማኅበራዊ አገልግሎቶች ትኩረት በመስጠት ቀጥላለች።

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

1. የአውሮፓው ዘመነ ሕዳሴ ሃይማኖታዊ የለውጥ ጥያቄዎችንም አስነሥቷል፤ ነገር ግን ካቶሊካውያኑና የለውጥ አራማጆቹ የያዙበት መንገድ በክርስትናው ስም የተከሠቱ ደም መፋሰሶችን አስከሥቷል።
2. በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከካቶሊክ በወጣው ሉተር የተጀመረው የተሐድሶ ንቅናቄ በርካታ ተከታዮችን ያፈራና ከሃያ ሁለት ሺሕ በላይ ክፍልፋዮች በክርስተና ስም የፈጠረ ነው።

3. አንግሊካን የመሐሉን መንገድ ስትመርጥ ፖለቲካዊ ሁነቶች ስለዘወሩት ትክክለኛ መፍትሔ አልሆነም፡፡

## ተግባር

1. ለውጥ አይቀርም፤ ሁሌም አለ፤ የነበረና የሚኖርም ነው፡፡ እኛ እንደ ክርስቲያን ለውጥን ማየት እና ማስተናገድ ያለብን መሠረታዊውንና የቤተ ክርስቲያንንና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትምህርት ጠብቀን ነው፡፡ ይህን ከሳትን ሁሉንም አዲስ ከሚያደርገው ከክርስቶስ መሰረት ልንወጣ እንችላለን፡፡ ***"እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ፡፡ ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ "*** ፩ኛ ቆሮ.፫፥፲-፲፩
2. እውነተኛው ለውጥ የልብ ለውጥ ነው፡፡ ***" የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ "*** ሮሜ.፲፪፥፪ ይህ ለውጥ በንስሐ ይገኛልና፡፡ ንስሓ በመግባት ለመለወጥ ተዘጋጁ ፡፡
3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፡-***" እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ..."*** ኤፌ.፭፥፳፯ በገዛ ደሙም የዋጃትን ቤተ ክርስቲያንን ከስሕተት መጠበቅም ለጳጳሳት የተሰጠ ሓላፊነት ነው፡፡ የሐዋ.፳፥፳፰ ይህን የሚያደርገው የጳጳሳት ጉባኤም ሲኖዶስ ይባላል፡፡ እኛም እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጆነታችን ለቤተ ክርስቲያን የማይገቡ ነገሮችን ስናይ ደረጃውን ጠብቀን ለካህናት፣ ይጠብቅዋት ዘንድ አደራ ለተሰጣቸው ለጳጳሳትና ለጉባኤው (ቅዱስ ሲኖዶስ) እናቅርብ፡፡ *ሥጋና ደም* በሚያመለክተን ወይም ዓለምን በሚመስለው የአመጽ መንገድ አንገኝ፡፡

**ጥያቄ፡-**

www.zoorthodox.org

1. *መምህር ተማሪዎችዎ፤ የካቶሊክ መከፋፈል እና የፕሮቴስታንት መፈጠር* ምክንያት *ታሪክ* እና *ያስከተለው* ውጤት፤ በሚለው ርእሰ ጉዳይ *መጽሐፍ* ቅዱስን፣ የቤተ ክርስቲያን *ታሪክን* *መሠረት* በማድረግ፤ *መጻሕፍትን መርምረው መምህራንን* ጠይቀው ጽሑፍ እንዲያቀርቡ *ያድርጉ*፡፡ ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ በክፍል ውስጥ ይወያዩበት፡፡

# ጥንታዊ ኦርቶዶክሳውያን(አንድ)

## ሃያ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የጥንታውያን ኦርቶዶክሳውያንን ታሪክ ማንነታቸውን እና መሠረተ እምነታቸውን ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች አብራርተው ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠኑ ጥቅሶች፡-** *"በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው፡፡"* ማቴ.፯፥፲፬ *"ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥ አድርገውም በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል፡፡"* ኢያ.፩፥፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ይሁ.፩፥፫ ፤ ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ››፣ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ ‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር›› ቀሲስ ዶ/ር ምክረ ሥላሴ፤ General Church History; Dn. Mebrahtu Kiros (unpublished) ‹‹Syrian Sunday school curriculum.››

**መግቢያ፡-** በዓለማችን ጥንታውያን የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚባሉ ስድስት አብያተ ክርስቲያናት አሉ፡፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ከሮማ ካቶሊክ እና ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በእምነት ይለያሉ፡፡

1. የሮም ካቶሊክና የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቶስን ሁለት ባሕርይ ሲሉት ጥንታውያን ኦርቶዶክሳውያን ‹‹አንድ ባሕርይ›› እንላለን፡፡
2. ካቶሊካውያን ‹‹መንፈስ ቅዱስ ከአብ እና ከወልድ ይሠርጻል›› ሲሉ እኛ ‹‹ከአብ ብቻ ይሠርጻል›› ብለን እናምናለን፡፡
3. ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ምክንያቶች ጥንታዉያን አብያተ ክርስቲያናት ከካቶሊክና የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን በቅዱስ ቁርባንና በአምልኮት አንድነት አይተባበሩም፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ዋና ትምህርት

ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ነጻነትዋን በታላቁ ቆስጠንጢኖስ አማካይነት አገኘች፡፡ ይህን ተከተሎም ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡት በንስሓ ያልተለወጡ ዓለማዉያን በማስመሰል ፤ ሌሎችም ለሥልጣን እና ለክብር ሲሉ የክርስቲያን ያልሆኑ እምነቶች እና ድርጊቶችን ለማስገባት ሞክረዋል፡፡ የአርዮስ ትምህርት ከግሪካውያኑ የሁለት አምላክ ፍልስፍና የተቀዳና በመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት የታጀበ ነበር፡፡

ሌላው ችግርም ዋና የመሆን ትግል ነው፡፡ የሮም መንበር ራስዋን እንደ ክርስትና የበላይ ትቆጥር ነበር፡፡ በቁስጥንጥንያ እና በኤፌሶን ጉባኤያት የቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነት ለመጠበቅ ትግል ሲደረግ ቀጥታ አልተሳተፈችም፡፡ በመልእክተኛ የውሳኔው አካል ትሆን ነበር፤ ይሕም ራስዋን እንደ መጨረሻ ውሳኔ ሰጭ በማስቀመጥ አስማሚ ሆና በሮም መንግሥት ፊት ለመታየት ከመፈለግ ነው፡፡

በእስክንድርያና በአንጾኪያ በኩልም የቁስጥስጥንያን መንበር ለመያዝ ከፍተኛ ትግል ነበር፡፡ ይህን የሚያስረዳን ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ የቁስጥንጥንያን መንበር በእስክንድርያ ሥር ለማድረግ ሞክሮ መንበረ ቁስጥንጥንያ ላልፈለጋት ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሆነች፡፡ በኋላም ቴዎፍሎስ አጋጣሚ ሲፈልግ ኖሮ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ስደት አስነሥቷል፡፡

ለበላይነት በተደረገው ጥረት ከሁሉም ጎልቶ የወጣው በሮሙ ፓፕ ልዮ አደገኛ ፍላጎትና ድርጊት የተደረገው ጥረት ነው፡፡ ለዚህም አዲሶቹን ነገሥታት በሮም የበላይነት ሐሳብ በማናወዝ በፓፕ ሊዮ አስተባባሪነት በ፬፻፶፩(451) ዓ.ም በኬልቄዶን ጉባዔ ተጠራ፤ የእስክንድርያ እና የአንጾኪያን ፓትርያርኮች ጨምሮ ስድስት መቶ ሠላሳ ስድስት ጳጳሳት ሲገኙ የሮሙ ፓፕ አልተገኘም፡፡ ስብሰባው በቅድስት አፎሚያ ቤተ ክርስቲያን ሲጀመር በሮሙ ፓፕ ሊዮ የተዘጋጀው ሰነድ ተነበበ፡፡ በይዘቱም ክርስቶስን ሁለት ባሕርይ፣ የሮሙን ፓፕ የሁሉም የበላይ ነው፤ ሌሎች ፓትርያርኮች በእርሱ ይታዘዛሉ፡፡ ወዘተ የሚል፤ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ የማይታወቅ የሃይማኖት መግለጫ ተነበበ፡፡

www.zeorthodox.org

የጉባኤውን አካሄድና የይዘቱን ስሕተትነት የተቃወሙት አባቶች በፈርጣማዎቹ የሮም ወታደሮች እየተደበደቡ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ወኅኒ ተጣሉ፡፡ በመቀጠልም በሌሉበትና ሐሳባቸው ሳይሰማ ተወገዙ፡፡ እነዚህ አባቶች የትምህርተ ሃይማኖቱን ኑፋቄ ፣ የድርጊቱን ሥጋዊነት በእስርም ሆነው በአፍ እና በመጽሐፍ አስረድተው፤ አወገዙ፡፡ እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በግዞት ሞቱ፤ ሌሎችም ከመጀመሪያው እስር ተርፈው በስደትና በግዞት ኖሩ፡፡

አባቶቻቸው በሮማ የተጋዙባቸውና የተገደሉባቸው የእስክንድርያ፣ የአንጾኪያ (ሶርያ) እና የአርመንያ አብያተ ክርስቲያናት ከሕንድ እና ከኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን መጠሪያ - ኦርቶዶክስ ፤ ክርስቶስን አንድ ባሕርይ በሚለው በተዋሕዶ እምነታቸው ጸኑ!!! በዚህ ትምህርታችን እነኚህ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትን ከሌሎቹ ለመለየት ጥንታዊ ኦርቶዶክስ ይባላሉ፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን ጥንታዊ ኦርቶዶክስ (Oriental Orthodox) የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
2. የግብጽ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
3. የያዕቆባዊት የሶሪያ (ሲርያክ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
4. የኤርትራ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
5. የሕንድ-ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
6. የአርመንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

## ማጠቃለያ፡-

በዓለማዊ ምክንያት እውነተኛውን መሠረተ እምነት ለመለወጥ እና ኑፋቄአቸውን ለመትከል በኃይል ቢንቀሳቀሱም በእውነተኛ መንፈሳዊነትና በቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት ተመሥርቶ በተጋድሎ የጸናው እውነተኛው እምነት ነው፡፡ እኛም ኢያሱ ***“ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥ አድርገውም በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል፡፡”*** ኢያ.፩፥፯ ተብሎ እንደተመከረ በእውነተኛ ሕይወትና በመንፈሳዊው የትምህርተ ሃይማኖት ዕውቀት አባቶቻችንን ልንመስል ይገባል፡፡

ከላይ ያየናቸው አብያተ ክርስቲያናት አኃት አብያተ ክርስቲያናት ይባላሉ፡፡ በክርስቶስ ላይ ባላቸው የቀና የተዋሕዶ እምነት እና ኦርቶዶክስ በሚለው መጠሪያቸው ይታወቃሉ፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- የትምህርተ ሃይማኖት በተለይም የነገረ ሥጋዌ መጻሕፍት አንብባችሁ ስለ ተዋህዶ ተረዱ፡፡
- ያናበባችሁት በቡድን በመወያየት በሁለት ተወካዮቻችሁ ለ10 ደቂቃዎች አቅርቡ፡፡

***ጥያቄዎች:-***

1. ጥንታውያን አኀት (እኅትማማቾች) ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት የሚባሉት ስንት ናቸው? ማን ማን ይባላሉ? (ዝርዝራቸውን ጥቀሱ)
2. ጥንታውያን አኀት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ከካቶሊካውያን እና ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በእምነት የሚለያዩበትን አስረዱ፡፡
3. በጥንታውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነት ‹‹ተዋሕዶ›› የሚለውን መጠሪያ ያደረጉበት ምክንያት ምንድነው? ‹‹ተዋሕዶ›› ማለት ምን ማለት ነው?
4. ካቶሊካውያን ከጥንታዊ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የተለዩት መቼ ነው? ለምን?

www.zeorthodox.org

# ጥንታዊ ኦርቶዶክሳውያን (ሁለት)

## ሃያ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የጥንታውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አጭር የመግቢያ ታሪክ ያውቃሉ፡፡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ፡፡ ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፥ እያሳቱና እየሳቱ፥ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ፡፡ አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤"* ፪ኛ ጢሞ.፫፥፲፪-፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ይሁ.፩፥፫ ፤ ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ›› ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ ‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር›› ቀሲስ ዶ/ር ምክረ ሥላሴ፤ ‹‹General Church History››; Dn. Mebrahtu Kiros (unpublished)፤ ‹‹Syrian Sunday school curriculum›› ፤ ‹‹Introduction to Coptic orthodox Church›› ; Father Tadros Y Malaty

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ስለ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ስምና ታሪክ መግቢያውን አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የኢትዮጵያን ፣ የግብጽንና የሶርያን አብያተ ክርስቲያናት አጭር ታሪክ እናያለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

#### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ኢትዮጵያውያውን ኦሪትን አስቀድመው የተቀበሉ ናቸው፡፡ ፩ኛ.ነገሥ.፲፥፩-፲፩ ሥርዓተ አምልኮታችን፣ የሕዝቡ ልማድና ቅርሶቻችን ይህንኑ ያረጋግጡልናል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብቸኛ የታቦት ሥርዓት፣ ከኦሪቱ የሚመሳሰል ልብሰ ተክህኖ ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳትና አፈጻጸም ሥርዓት አላት፡፡ ክርስቲያኑ ሕዝብ በክርስትና ክልክል ያልሆኑትን አይበላም፣ ሥርዓተ ግርዘት ይፈጽማል፡፡ በአክሱም፣ በጣና ቂርቆስ፣ በተድባበ ማርያም፣ በደብረ ብርብር ማርያም ያሉት ኦሪታዊ ምልክቶችና መሠዊያዎችም የዚህ ምስክር ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ኢትዮጵያውያን ወደ ኢየሩሳሌም ለኦሪት በዓል የሚሄዱና የሚያከብሩ መሆናቸው ተጽፏል፡፡ የሐዋ.፰፥፳፯፡፡ ነቢያቱ የእስራኤልን እምነት ከኢትዮጵያ እምነት ጋር አስተሳስረው ገልጠዋል፡፡ *"የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር "*

www.zeorthodox.org

አሞ.፱፥፯ ዳዊትም *" ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"* መዝ. ፷፯፥፴፩ የሚል ጽኑዕ ትንቢት ተናግሯል፡፡

ኢትዮጵያውያን በበዓለ ጰራቅሊጦስ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ከተሰባሰቡት እና ወደ ይሁዲነት ***የተመለሱ*** ከተባሉት መሐል ነበሩ፡፡(የሐዋ.፰፥፳-፲፪) የሐዋርያትን ሥራ የጻፈው ሉቃስ ያልጠቀሳቸው ቁጥራቸው ትንሽ ስለነበር ነው፡፡ (ቅዱስ ዮሐስን አፈወርቅ) እነኚህ ሰዎች ክርስትናን የሰሙና ወደ ኢትዮጵያችን ይዘው የመጡ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ናቸው፡፡

በ፴፬(34) ዓ.ም ያመነውና የተጠመቀው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ለሕዝቡ ሐዋርያ ሆኗል፡፡ (አውሳብዮስ) በ፫፻፴(330) ዓ.ም ክህነትና ሥርዓትን ወደ ኢትዮጵያ ያመጣው አቡነ ሰላማ(ከሳቴ ብርሃን) ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከግብጽ በሚሾሙ ጳጳሳት እስከ ፲፱፻፶፩(1951)ዓ.ም ቆይታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራስዋን ፓትርያርክ እና አባቶች መሾም ጀምራለች፡፡ (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክን በቦታው እንመለስበታለን)

## የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

ወደ ጥንትዋ የግብጽ መዲና እስክንድርያ በመዝለቅ ወንጌልን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰበከው ቅዱስ ማርቆስ ነው፡፡ አንያኖስ በተባለ ጫማ ሰፊ ቤት የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተጀመረች፡፡ ማርቆስ ብዙዎችን አሳምኖ በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡ አንያኖስም እርሱን ተካው፡፡ ጥንታዊው የእስክንድርያ ትምህርት ቤትም በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ተቋቋመ፡፡ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶችንና ሊቃውንትን አፍርቷል፡፡ እስክንድርያ ሦስቱም ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ሲካሄዱ በአባቶችዋ መሪነት የቀናውን ትምህርት አስጠብቃለች፡፡ ምንኩስና የተጀመረው በግብጽ በረሐዎችና አባቶች ነው፡፡ በ፬፻፶፩ (451) ዓ.ም በተደረገው ጉባኤ የታሰረውና በግፍ የሞተው ታላቁ ቅዱስ ጎርጎርዮስ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ነበር፡፡ በብዙ ተጽዕኖ የሁለት ባሕርይን ትምህርት እንዲቀበሉ ቢገደዱም ሕዝቡ ከአባቶች ጋር ባደረገው መንፈሳዊ ተጋድሎ ተዋሕዶ ሃይማኖቱን አጽንቷል፡፡ ዲዮስቆሮስን የተካው የተዋሕዶ አባት ጢሞቴዎስን ወደ እስክንድርያ ላለማስገባት በሩን ሲዘጉ ሕዝቡ ከሮም ወታደሮች ጋር ታግሎ እውነተኛውን አባቱን አስገብቷል፡፡

ዜኖን የመሳሰሉ ጥቂት ነገሥታት ለማግባባት ካደረጉት ጥረት በስተቀር፤ በተከታታይ የተነሡት ነገሥታት በኃይል ‹‹ኬልቄዶንን ተቀበሉ›› አሉ፡፡ ይህ ድርጊት ከ፮፻፪-፮፻፲፩(602-611) እስከ ነገሠው ፎካስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ቀጠለ፡፡ ሕዝቡ እንዲያምጽ ከማድረጉ በስተቀር የአቋም ለውጥ አልመጣም፡፡ ክርስትና በውስጥ እንዲህ ተዳክሞ የፋርስ ጦር የሮምን ጦር አሸንፎ እስክንድርያ ገባ፡፡ የፋርስ ሰዎች ፀሐይ አምላኪዎች ነበሩ፡፡ በእነርሱ ግዛት የተቀመጠውን፤ የንስጥሮሳውያንን ትምህርት ተቀበሉ፤ በማለት በአንድ ቀን ብቻ ስምንት መቶ ሺሕ ክርስቲያኖችን በእስክንድርያ አስገደሉ፡፡ በኋላም እስልምና ከሰባተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ባደረገው መስፋፋት

www.zeorthodox.org

አብዛኛው የግብጽ ሕዝብ ሰለመ፡፡ በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ በገዳማቱ ቅዱሳን እየተነሡ ነበር፡፡ የግብጽ ቤተ ክርስቲያንም በቁጥር መንምና በጥንካሬ ቀጠለች፡፡ አሁን በ118ኛ ፓትርያርክዋ የምትመራው የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፤ ዐሥራ አንድ ሚሊዮን ክርስቲያኖች ያሉዋትና በታላቅ መንፈሳዊ እድገት ላይ የምትገኝ እኅት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡

## የሲርያክ (ሶርያ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

የሶሪያ ቤተ ክርስቲያን በአንጾኪያ መንበር ተመሠረተች፡፡ በአንጾኪያ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን ተባሉ፡፡ የሐዋ.፲፩፥፳፮፤ በሮም መንግሥት ሦስተኛ የአስተዳደር ማዕከልነት፣ የአካባቢው የጦር መምሪያ በመሆንና በነበራት ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ ቁስጥንጥንያ ዝነኛና ታላቅ ከተማ ነበረች፡፡ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ውብ ቤተ ክርስቲያን በመሥራቱ ተከታዮቹ ነገሥታትም በአንጾኪያ በርካታ አብያ ክርስቲያናትን ሠሩ፡፡ ታዋቂው የአንጾኪያ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት በጥንታዊነቱ የሚታወቅና ታላላቅ አባቶችን ያፈራ ነበር፡፡ እነቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የዚህ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ነበሩ፡፡ በመሆኑም አንጾኪያ ከዋናዎቹ የክርስትና ማዕከላት አንድዋ ሆነች፡፡

ከአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአንጾኪያ ክርስትና ተዳከመ፡፡ ለዚህም የሚከተሉት ምክንያች ነበሩት፡- ካቶሊካውያን ከኬልቄዶን ጉባኤ በኂላ ያስነሡት መከራ፣ በከተማይቱ የደረሰው ከፍተኛ የመሬት መናወጥ፣ ፋርሳውያን በ፭፻፴፰(538) ዓም ያደረሱት ጥቃት፣ የዐረብ ሙስሊሞችም በ፮፻፴፰(638)ዓ.ም አንጾኪያን ወርረው ሕዝቡን ማስለማቸውና ክርስትና ላይ የፈጠሩት ጫና በዋናነት የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያንን ያዳከሙ ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት እውነተኛ ትጋትና የቀና ሃይማኖት ያላቸው አባቶች ተመናመኑ፡፡ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያንም ከሌላው ዓለም ተለይታ ተዳከመች፡፡ በዚህ ዘመን ያዕቆብ ዘአልበረዲ ተነሣ፡፡ ቤተ ክርስቲያንንም ታደገ፡፡ በእርሱ አማካይነትም ክርስትናና ክህነት በሶሪያ መቀጠል ቻለ፡፡

ሲርያክ ጥንታዊ የአካባቢው ቋንቋ ነው፡፡ የሶሪያ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ቋንቋ የምትጠቀምና ዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ወደ ሕንድና አካባቢው አባቶችን በመላክ፣ በውስጥ በክርስቲያናዊ ጽናት በገዳማዊ ሕይወትም ተጠናክራ የቆየችው የሲርያክ(ሶርያ) ቤተ ክርስቲያን በ20ኛው መ/ክ/ዘ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ በብራዚልና በአውስትራሊያ ጳጳሳትንና ኤፒስ ቆጶሳትን በመሾም በዓለምአቀፋዊ አገልግሎት ተጠናክራለች፡፡ ቅዱስነታቸው ሞራን ሞር (ብፁዕ ወቅዱስ) አግናጥስ ዛካ አንደኛ ኢዋሲ የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በፓትርያርክነት ይመራሉ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- ጥንታውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የአባቶች ሐዋርያትና የዓለም አቀፍ ጉባኤያትን መሠረተ እምነት የያዙ ናቸው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የኢትዮጵያን የግብጽንና የሶርያን

አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ ታሪክ አይተናል፡፡ መከራ ከቤተ ክርስቲያን ተለይቶ አያውቅም፡፡ ሆኖም ቤተ ክርስቲያን እውነት ይዛ ቀጥላለች፡፡

## ተግባር

- በተጨማሪ እንድታነቡዋቸው የተጠቆሙትን ስለ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚያስረዱ ጽሑፎችን አጥኑ፡፡

***ጥያቄዎች፦***

1. ኢትዮጵያውያን ኦሪትን አስቀድመው ለመቀበላቸው ማረጋገጫዎች የሆኑትን በዝርዝር ግለጹ፡፡
2. መጀመሪያ የተጠመቀው ኢትዮጵያዊ ማነው? መቼ? በማን ተጠመቀ?
3. ክህነትን፣ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በኢትዮጵያ የጀመረው የመጀመሪያው አባት ማን ይባላል?
4. በግብጽ እስክንድርያ ወንጌልን መጀመሪያ የሰበከው አባት ማነው?
5. የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው የት(በማን) መንበር ነው? ታዋቂው የአንጾኪያ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት ካፈራቸው ታላላቅ መምህራን አባቶች ታዋቂውን ጥቀሱ፤

www.zeorthodox.org

# ጥንታዊ ኦርቶዶክሳውያን(ሦስት)

## ሃያ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የጥንታውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን ታሪክ መግቢያ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *“ በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ። ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፥ እያሳቱና እየሳቱ፥ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ። አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤ ”* ፪ኛ ጢሞ.፫፥፲፪-፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ይሁ. ፩፥፫ ፤ ‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ›› ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፤ ‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር›› ቀሲስ ዶ/ር ምክረ ሥላሴ፤ ‹‹General Church History›› Dn. Mebrahtu Kiros (unpublished)፤ ‹‹Syrian Sunday school curriculum››፤ Christian in Asia before 1500›› pp 90-107; Ian Gillman, Hans-Joachim Klimkeit ፤

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ስለ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ማጥናት ጀምረናል። በዛሬው ትምህርታችንም ይህንኑ በመቀጠል የአርመንያን እና የሕንድን አብያተ ክርስቲያናት አጭር ታሪክ እናያለን።

### የአርመንያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *“ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።”* ማቴ.፳፰፥፲፱ ባለው መሠረት ሐዋርያት በዓለም ዞረው አስተምረዋል። ከእነዚህም ቅዱስ ታዴዎስ ከ፵፫-፷፮(43-66) ዓ.ም፤ በርተሎሜዎስም ከ፷፮-፷፰(66-68) ዓ.ም በአርመኒያ ሰበኩ።

www.zoorthodox.org

አርመኒያ በምሥራቅ አውሮፓ የምትገኝ የሙት ባሕርና የካስፒያን ባሕር የሚያዋስኗት ሀገር ናት። ከጆርጂያ፣ ኢራን፣ ቱርክ እና አዘርባጃን ጋርም ትዋሰናለች። በርተሎሜዎስና ታዴዎስ ወደዚህች አገር ገብተው ወንጌልን አስተማሩ። በሐዋርያቱ ስብከት ብዙ ሰዎች አምነው ተጠመቁ። በክርስቲያኖች ሕይወትና በሚደረገው ተአምራትም ብዙ ሰው ክርስቲያን ሆነ። ይህ ያስቆጣቸው

አረማውያን ታዴዎስን በ፷፮(66) ዓ.ም፤ በርተሎሜዎስንም በ፷፰(68) ዓ.ም ገደሉ፡፡ ብዙ ክርስቲያኖችም በሰማዕትነት ዐረፉ፡፡ ሆኖም ክርስትና ከላይ እየተመታም ውስጥ ውስጡን እንደ ሰደድ እሳት መስፋፋቱን ቀጠለ፡፡ መከራውም እንዲሁ ይከፋ ነበር፡፡

በሦስተኛው መ/ክ/ዘ (በ፪፻፹(280) ዓ.ም ገደማ) በሮሙ ንጉሥ ዲዮቅልጢያኖስ ስለ ፊት ስለ ሃይማኖታቸው በጽናት የመሰከሩት ቅዱሳት አንስት በቅድስት አርሴማ መሪነት ከሮም ወደ አርመኒያ ተሰደዱ፡፡ በወቅቱ በአርመኒያ የነበረው ንጉሥ ድርጣድስ ሦስተኛ ነው፡፡ ዲዮቅልጥያኖስ ከሮም ስለመጡት ደናግላን ደብዳቤ ላከለት፡፡ ድርጣድስም አስጠርቶ አናገራቸው፤ ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡና ቅድስት አርሴማንም ንግሥት አድርጎ እንደሚያገባት በመናገር ሊያግባባቸው ሞከረ፡፡ ሆኖም እርስዋም ሆነች ሌሎቹ በሃማኖታቸው ጸንተው መሰከሩለት፡፡ በመጨረሻም ቅዱሳቱንና ሌሎቹን ክርስቲያኖችን ጣዖት ይሠዋበት በነበረበት ተራራ በሰይፍ አስገደላቸው፡፡ እነርሱም በክርስቶስ እምነት ጸንተው፤ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው እየመሰከሩ ዐረፉ፡፡

ንጉሡ ብዙ ሳይቆይ ታመመ፡፡ ክርስቲያን የሆነቸው እኅቱ ክርስትናን እንዲቀበል መከረችው፡፡ ክርስቲያን በመሆኑ የታሰረው ጎርጎርዮስም በተአምራት ፈወሰው፡፡ በመጨረሻም ንጉሡ ክርስቲያን ሆኖ ተጠመቀ፡፡ ጎርጎርዮስም በስብከት ቤተ መንግሥቱንና ሕዝቡን አስተምሮ እስከ ዛሬዋ ጆርጂያ ግዛት ድረስ ሕዝቡን አሳመነ፡፡ የቂሳርያው ሊዮረንስ ጎርጎርዮስን ጵጵስና ሾመው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዶሻ ይዞ በዚህ ሥፍራ (ኢችሚያዚን) እያለ ቦታውን ሲመታ ለጎርጎርዮስ ተገለጠለት፡፡ ያች ስፍራ ቅድስት አርሴማና ሠላሳ ሰባቱ ቅዱሳት የሞቱባት ቦታ ናት፡፡ እርሱም በዚያች ስፍራ ቤተ ክርስቲያን ሠራ፡፡ ስምዋንም ጌታ በተናገረው ቃል ‹‹ኢችሚያዝን›› ብሎ ሰየማት፡፡ ይህች ቦታ እስከ አሁን የአርመናውያን መንበረ ፓትርያርክ ናት፡፡

በ፫፻፩(301) ዓ.ም ድርጣድስ ክርስትናን የግዛቱና የመንግሥቱ ሃይማኖት አድርጎ ዐወጀ፡፡ ይህም በዓለማችን የመጀመሪያዋ ክርስቲያን ሀገር ያደርጋታል፡፡ ጎርጎርዮስ ፓርቶቭ(ብርሃን ገላጭ) ተብሎ ተሰየመ፡፡ ጎርጎርዮስ የአርመንያን ቤተ ክርስቲያን በአህጉረ ስብከት፣ በጳጳሳትና በካህናት እንዲሁም በወንጌል ትምህርት አስፋፍቶ ጎርጎርዮስ በ፫፻፳፭(325) ዓ.ም ዐረፈ፡፡ ከዚያም ተከታዮቹ ክርስትናን አስፋፉ፡፡

www.zeorthodox.org

በ፫፻፷፭(365) ዓ.ም በተደረገው የአርመኒያ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲኖዶስ አረማዊነትንና የዘመድ ጋብቻን ከለከለ፡፡ ሁሉም ሰው በአግባቡ ግብር እንዲከፍልና የተሰበሰበው ገንዘብም የህሙማንና የደካሞች መርጃ ማዕከላት የሆኑ ገዳማት እንዲቋቋሙበት ወሰነ፡፡ መንግሥትም ይህንን ፈጸመ፡፡ በአጭር ጊዜ ሁለት ሺሕ ማዕከላት ተቋቁመው ክርስትና በሀገሪቱ ሁሉ ተስፋፋ፡፡

ከ፫፻፹፯-፬፻፴፱(387-439) ዓ.ም በተሾመው አባት አቡነ ይስሐቅ ዘመነ ፕትርክናም መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎችም ቅዱሳት መጻሕፍት በቅዱስ መስሮኘ በተመሩ አንድ መቶ ሊቃውን ተተረጎመ። ይህም አርመኒያ መጽሐፍ ቅዱስን ቀድመው ካገኙ ጥንታዊ ቋንቋዎች አንዱ እንዲሆን አስቻለ። ቋንቋውም የጽሑፍ ቋንቋ ሆኖ አደገ።

በ፬፻፶፩(451) ዓ.ም የተደረገውን የኒቅያ ጉባኤ የአርመኒያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ በ፭፻፮(506) ዓ.ም እና በ፭፻፷፬(564)ዓ.ም ድዊን በተባለ ቦታ በተደረጉ ጉባኤያት አልተቀበለውም፤ አወገዘው። ጆርጂያ ካቶሊክ፣ አርመኒያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሆነው ተለያዩ። ካቶሊካውያንና መለካውያን በተደጋጋሚ አርመኒያን በሁለት ባሕርይ እምነት ለማሳመን ጥረት አድርገዋል። ሆኖም በአርመናውያን ጽናት አልተሳካም። አርመኒያን በርካታ ኃያላን ገዝተዋታል። ከፋርስ ፣ ከኦቶማን ቱርክና ከአውሮጳ የተነሡ በተለይም የፈረንሳይ ካቶሊኮች ሃይማኖታቸውን ለማስቀየር ጥረት አድርገዋል። ከላይ በተጠቀሱትና በሩሲያው ኮሚኒስታዊ ኢአማኒ መንግሥት የክርስቲያኖች ደም እንደ ውኃ ፈሷል። ሆኖም ሕዝቡ ሃይማኖቱን በማወቁና በእምነቱ በመጽናቱ ኦርቶዶክሳዊነትን በደሙና በሕይወቱ መሥዋዕትነት ጠብቆ አቆየ። ቤተ ክርስቲያኒቱም የሕዝቡ የማሕበራዊ ሃይማኖታዊ እሴት ምልክት እና ማዕከል ሆና ኖረች።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና መንበር በአርመኒያ ኢችሚያዚን ነው። በሲሊቅያ(ሊባኖስ)፣ በቁስጥንጥንያና በኢየሩሳሌምም መናብርት አሉ። የመናብርቱ መብዛት ዋናው ምክንያት የሕዝቡ መሰደድ ነው። ሆኖም ዋናዋንና እናት መንበር የሆነችውን የኢችሚያዝንን መንበር የበላይነት አክብረው ሦስቱም በኢችሚያዝን መንበር ይመራሉ፤ ለእናት መንበሯም ቅድምናም ይሰጣሉ።

እኛ ፓትርያርክ የምንለውን እነሱ ‹‹ካቶሊኮስ›› ብለው ይጠራሉ። በውጭ ያሉት አርመናውያን በቁጥር ይበልጣሉ። ዐሥር ሚሊዮን ከሚሆኑት አርመናውያን 85 በመቶው ሕዝብ ኦርቶዶክሳዊ ነው።

## የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን (የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን)

በሐዋርያው ቶማስ በ፶፪(52) ዓ.ም በማላበር ተመሠረተች። ዋናው መንበር በካራላ ግዛት (ማላበር) ይገኛል። በመጀመሪያዎች ክፍለተ ዘመናት ከሶርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር በአንድነት ትጠራ ነበር። ከሶሪያ ቤተ ክርስቲያን ከአንጾኪያ መንበር አባቶች ይላኩ ነበር። በ፰፻፳፪(822) ዓ.ም ሳፖር ኢሶ በተባለ ነጋዴ የተመሩ፤ አባ ሳቦር(ማር ሳፕሮ) እና አባ አፍራት(ማር ፕሮድ) የተባሉ ጳጳሳት ያሉበት ቡድን በስደት ኮላም(Quilon) በተባለ ቦታ ደረሱ። ይህች ቦታ የካራላ ግዛት ክፍል ናት። በኮላም ቤተ ክርስቲያን ሠርተው በንግድና በሌሎችም ሥራዎች ተስፋፍተው ተቀመጡ። ክርስቲያን የአካባቢ መንግሥት ተቋቋመ። ኦርቶዶክሳዊውን የቀና ሃይማኖትም አስፋፉ። ነገር ግን ከዘመናት

www.zeorthodox.org

በኋላ ከሶሪያ የሚላኩት አባቶች ቀሩ ፤ ክፍተት ተፈጠረ፡፡ በ16ኛው መ/ክ/ዘ ንስጥሮሳውያን ሰርገው መግባት ቻሉ፡፡ ሆኖም ትምህርታቸው ብዙም ሥር ሰዶ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ካቶሊካውያን በቫስኮ ደጋማ አሳሽነት ወደ ሕንድ ገቡ፡፡ በተለይም ከ፲፭፻፴፱(1539) ዓ.ም ጀምሮ የጎአ ጳጳስ አልቡርኩርኩ በአካባቢው ነገሥታት ትብብር የሮማን ካቶሊክ ያልተቀበሉትን ስደት አስነሣባቸው፡፡ በትምህርትና በገንዘብ ድጎማም ብዙ ሕዝብ ካቶሊክ አደረጉ፡፡ ከዚህ ውጭም በአረማውያን በሚደርስባቸው መከራ ቁጥራቸው ተመናመነ፡፡

በሜይ 22 ቀን 1653 ዓ.ም ሊቀ ዲያቆናት ማር ቶማ(ቶማስ) አንደኛ ሊቀጳጳስ ተብሎ በዐሥራ ሁለት አባቶች ንቡረ እድነት ተሾመ፡፡ በካቶሊካውያን ሴራ ብዙዎች ሹመቱን አልተቀበሉትም፤ የተወሰኑትም ካቶሊክ ሆኑ፡፡ ወደ እስክንድርያና አንጾኪያ አባት ሹመቱን እንዲያጸኑ ደብዳቤ ተላከ፡፡ ከዐሥራ ሁለት ዓመታት በኋላ የሶርያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ማር ቶማ ጎርጎርዮስ አብዱል ጃሊል ከኢየሩሳሌም መጥተው የማር ቶማ አንደኛን ሊቀ ጵጵስና አጸኑ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሕንድ ኦርቶዶክስ (ማላንካራ) ቤተ ክርስቲያን በማር ቶማ ተከታይ አባቶች ትመራ ጀመር፡፡

በ፲፱፻፸፭(1975) ዓ.ም ታላቋ ብሪታንያ የማላባር ግዛትን ቅኝ ግዛት ያዘች፡፡ ከአንግሊካን ቤተ ክርስቲያንም ጋር ግንኙነት ተጀመረ፡፡ በአንግሊካን ቀሳውስት አነሣሽነትም በ፲፰፻፲፫(1813)ዓ.ም የማላንካራ ቤተ ክርስቲያን በኮታያም የአንግሊካኖችን ፕሮቴስታንታዊ ተልእኮ የሚያስፈጽም ሴሚናል መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከፈተች፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንግሊካኖች ቤተ ክርስቲያኒቱን በፕሮቴስታንት የተሐድሶ ትምህርት ለመቀየር ስለጣሩ ግንኙነቱ ተቋረጠ፡፡ ሆኖም ውስጥ ውስጡን የተፋፋመው እሳት በ19ኛው መ/ክ/ዘ ማብቂያ ቤተ ክርስቲያኒቱን በተሐድሶአውያንና በጥንትዊት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ጠባቂዎች ከፈላት፡፡

- ❖ አብዛኛው ሕዝብ ተሐድሶዎችን ትቶ ፤ በማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ቀጠለ፡፡
- ❖ ጥቂቶች በአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ክፍልነት የደቡብ ሕንድ ቤተ ክርስቲያን ተባሉ፡፡
- ❖ በፕሮቴስታንት የኑፋቄ ትምህርት የተሐድሶ እንቅስቃሴን ይዘው የቀሩትም ራሳቸውን የማር ቶማ ቤተ ክርስቲያን ብለው ጠሩ፡፡ በተሐድሶ ኑፋቄያቸው በቅዳሴው እና ሌሎች ሥርዓቶችም ለውጥ አድርገው ከውጭ ጣልቃ ገብነት ነጻ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ብለው ለብቻቸው ቀጠሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ዋነኛዋ የሕንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ከሶሪያ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የሚላክላትን አባት በራስዋ ለመሾም ጠይቃ መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፪ ዓ.ም ባስልዮስ ጳውሎስ አንደኛ በሚል ማዕረግ ሚሪታማዢ ጳውሎስ ማር ኢቫኖስ ተሾሙ፡፡ ፓትርያርክ የሆኑት አባቶች እንደ አርመኒያ ካቶሊኮስ ብለው ይጠሩዋቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት አሁን ያሉት አባት ዘጠነኛው ናቸው፡፡ የማላንካራ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ሚሊየን የሚሆኑ ኦርቶዶክሳውያን የያዘች ናት፡፡

## ማጠቃለያ

- የአርመኒያና የሕንድ አብያተ ክርስቲያናት ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ ጸንቶ የቆየውን ክርስትናና የቀና ሃይማኖት ይዘው የኖሩ ጥንታዊ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያ ክርስቲያናት ናቸው፡፡
- በተለያዩ ዘመናት በፖለቲካኞች በአረማውያንና በተሸነፉ ሰዎች በደረሰባቸው መከራ ቁጥራቸው ቢያንስም ክርስትናን ከሐዋርያዊ አኗኗር ጋር ማስቀጠል ችለዋል፡፡
- ክርስትና መጀመሪያ ነጻነት ካገኘባቸውና የመንግሥት ሃይማኖት መሆን ከቻለባቸው ሀገሮች የመጀመሪያዋ አርመንያ ናት፡፡
- መጽሐፍቀ ቅዱስ መጀመሪያ ከተረጎሙ ስድስት ቋንቋዎች አራት (ሶርያ ፣ ኮፕቲክ ፣ አርመንና የኢትዮጵያ ግእዝ) በጥንታውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የተተረጎሙ ናቸው፡፡
- በጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሠረትነት የጸናው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ሃይማኖት እንዲሁ አልተላለፈም፡፡ በብዙ መከራ ያለፉት አባቶች ድካም እና ተጋድሎ ብዙ መሥዋዕትነት ከፍለውበት በእምነት ጽናታቸው ተጠብቆ ለትውልድ የተላለፈ ነው፡፡

## ተግባር

- በአባሪነት የተሰጡትን መጻሕፍት እና ሌሎች ጽሑፎች አንብቡ፡፡
- ሃይማትን ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍና ማስፋፋት እንዴት እንደሚጫል ተወያዩ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. አርመንያ የት የምትገኝ ሀገር ናት? የሚያዋስኗት እነማን ናቸው? በመጀመሪያ በዚች ሀገር ወንጌልን ያስተማሩት ሐዋርያት እነማን ናቸው?
2. በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሮሙ ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ፊት ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው በጽናት መስክረው ከሮም ወደ አርመንያ የተሰደዱት ቅዱሳት አንስት በማን ይመሩ ነበር? የእነዚህን ቅዱሳት አንስት ፍጻሜና ምክንያት ግለጹ፡፡
3. የአርመንያ መንበረ ፓትርያርክ (እናት መንበር) የት ትገኛለች? ማን ትባላለች? የመሠረታት እና ይህን ስያሜ የሰጣት አባት ማን ነበር?
4. የሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መቼ ተመሠረተች? ማን መሠረታት? የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያኒቷ ሊቀጳጳስ ማን ይባላሉ?

www.zeorthodox.org

# ቅንዓት /Zeal and Jealousy/

## ሃያ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- ተማሪዎች ስለ ቅንዓት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠኑ ጥቅሶች**፡- ‹‹***ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ፥ በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቍር አደረገ የበቀልንም ልብስ ለበሰ፥ በቅንዓትም መጐናጸፊያ ተጐናጸፈ***›› ኢሳይ.፶፱፥፲፯ ***"የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና፥ የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ወድቆአልና፡፡"*** መዝ. ፷፰፥፱ ‹‹***ቅንዓትም እንደ ሲኦል የጨከነች ናትና፡፡ ፍንጣሪዋ እንደ እሳት ፍንጣሪ፥ እንደ እግዚአብሔር ነበልባል ነው***፡፡›› መኃ.መኃ.፰፥፮

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ‹‹ቅንዓት›› በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ፤ በትምህርቱ የተሰጡትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡

**መግቢያ፡-** ስለ ቅንዓት ሰዎች የተለያየ አመለካከት አላቸው፡፡ ክፉ ቅናቶችን እንደ ጥንቃቄና መከላከያ ዘዴ የሚቆጥሩም አሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ስለ ቅንዓት ያስተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ ቅንዓት እንማራለን፡፡

- **ቀንዓ ፣ ይቀንዕ** ፡- መቅናት፣ መመቅኘት፤ ማዘን መቆጣት መበሳጨት በሌላው ዕድልና ሀብት፡፡ ወይም እንደርሱ ለመሆን መንቃት መትጋት፣ አብነት ማድረግ (መዝ.፴፮፣ ምሳ.፯፥፯፣ ራእ.፫፥፲፱) ቀናዒ እውነተኛ ማለትም ነው፡፡ ኪ.ወ.ክ መዝገበ ቃላት፡፡
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት "ቅንዓት"ን ለሌላ ሰው የሆነውን ለራስ መፈለግ፣ ክብር ወይም ፍቅር ወደ ሌላ ሲያልፍ መቆጣት፣ የእግዚአብሔር ቅንዓት ማለት ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ፍቅር ለሌላ እንዳይሰጥ መፈለጉ ሲል ይፈታዋል /ይተረጉመዋል/፡፡
- በመሆኑም በግእዝ ቅንዓት መመቅኘት ማለት ሲሆን ፤ ቅንዓት ቅን ፍርድ መፍረድ ማለት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

### መለኮታዊ /አምላካዊ/ ቅንዓት

እግዚአብሔር በአምላክነቱ ቀናዒ አምላክ ነው፡፡ እግአብሔር በአምላክነቱ፣ ንጉሥ በመንግሥቱ፣ ጎልማሳ በሚስቱ እንደሚባለው፡፡ መለኮታዊው ቅንዓት ከእግዚአብሔር ፍጹምነት የተነሣ ነው፡፡

ከፍጹም ፍቅሩ የተነሣ አባት በቅንዓት ተነሣሥቶ ልጁን እንደሚቀጣ እየቀጣ ያስተካክለናል። እስራኤልን የቀጣበት ቅንዓት እንዲታረሙ ነበር። ***"እነሆ፥ አንተን ከሩቅ ዘርህንም ከምርኮ አገር አድናለሁና ባሪያዬ ያዕቆብ ሆይ፥ አትፍራ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ አንተም እስራኤል ሆይ፥ አትደንግጥ ያዕቆብም ይመለሳል ያርፍማል ተዘልሎም ይቀመጣል ማንም አያስፈራውም። አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና፥ ይላል እግዚአብሔር፤ አንተንም የበተንሁባቸውን አሕዛብን ሁሉ ፈጽሜ አጠፋለሁ፥ አንተን ግን ፈጽሜ አላጠፋህም በመጠን እቀጣሃለሁ፥ ያለ ቅጣትም ከቶ አልተውህም"*** ኤር.፴፥፲-፲፩

ሐዋርያውም እግዚአብሔር እንድንታረም ለእኛ ጥቅም ብሎ እንደሚቀጣን ነግሮናል። ***"እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር። ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል። ለመቀጣት ታገሡ፤ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም። ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸውም ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን?እነርሱ መልካም ሆኖ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፥ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል። ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።"*** ዕብ.፲፪፥፳-፲፩

እግዚአብሔር ከፍጹምና ቅን ፈራጅነቱ የተነሣ ቀናተኛ ነው። ***"ስሙ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር ቅንዓት ያለው አምላክ ነውና ለሌላ አምላክ አትስገድ"*** ዘጸ.፴፬፥፲፬ የሚለውን ትእዛዙን የሚተላለፉትንና ፈጽመው የማይመለሱትን ለአምላክነቱ ቀንቶ ይቀጣቸዋል። የእስራኤል መንግሥት መከፈል እና ምርኮአቸው ለአምላክነቱ ቀንቶ ያመጣባቸው ቅጣቶች ነበሩ። ናቡከደነፆርን እንደ እንስሳት ሣር እስኪበላ ድረስ ከሰው ያሳነሰውም ለአምላክነቱ ቀንቶ ነው። ***"በዚያም ሰዓት ነገሩ በናቡከደነፆር ላይ ደረሰ ጠጕሩም እንደ ንስር፥ ጥፍሩም እንደ ወፎች እስኪረዝም ድረስ ከሰዎች ተለይቶ ተሰደደ፥ እንደ በሬም ሣር በላ፥ አካሉም በሰማይ ጠል ረሰረሰ"*** ዳን. ፬፥፴፫

የእግዚአብሔር ቅናት ለማዳን ነው። ኢሳይያስ እግዚአብሔር ወልድ ዓለሙን ስለማዳኑ ሲናገር፤ ‹‹***ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ፥ በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቍር አደረገ የበቀልንም ልብስ ለበሰ፥ በቅንዓትም መጐናጸፊያ ተጐናጸፈ***›› ኢሳይ.፶፱፥፲፯ ያለው ይህንን ያስረዳል። ቅዱሳንም በእርሱ መንፈስ ስለሚመሩ ለእግዚአብሔር እና ለሰው መዳን ይቀኑ ነበር።

**የሰው ቅናት**

❖ የሰው ቅናት ሁለት ዓይነት ነው።

www.zeorthodox.org

**አንደኛው - ክፉ (ሰይጣናዊ) ቅናት፡-** ክፉ ሁሉ ከዲያብሎስ ነው፤ ***"ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና"*** ፩ኛ ዮሐ.፫፥፰ ይህ ቅንዓት የሌላውን ከመመኘት ከምቀኝነትና ከጨካኝ ልብ የሚነሣ ነው። ‹‹***ቅንዓትም እንደ ሲኦል የጨከነች ናትና። ፍንጣሪዋ እንደ እሳት ፍንጣሪ፥ እንደ እግዚአብሔር ነበልባል ነው***።›› *መኃ.መኃ.፰፥፮* ዳዊት ‹‹***በክፉዎች አትቅና***›› እንዳለም የማይገባ ቅንዓት አለ። ከሥር የተገለጡትን ታሪኮች አጥኑ፡-

- **የዲያብሎስ ቅንዓት**፡- ዲያብሎስ በትዕቢቱ ከክብሩ ከተዋረደ በኋላ በተፈጠረው አዳም ክፉ ቅንዓት ስላደረበት እሱ በወደቀበት አምላክ የመሆን ክፉ ምኞት እንዲሳብና እንዲወድቅ ምክንያት ሆኗል። ዘፍ.፫፥፩
- **የቃየን ቅንዓት**፡- ቃየን በቸልቸኝነት ያቀረበውን ንጹሕ ያልሆነውን መሥዋዕት እግዚአብሔር አልተቀበለም። ወንድሙ አቤል ከበጎ ሕሊና የተነሣ በንጹሕ መንፈስ ያቀረበውን ንጹሕ መሥዋዕት እግዚአብሔር ስለተቀበለለት በቅናት ተነሣሥቶ ወንድሙን ገድሎታል። ቃየላዊ ቅንዓት ሌሎች ጸጋን ሲያገኙና ሲደሰቱ መከፋት፤ ጥላቻን እያሰቡ የራስን ልቦና ማቊሰል ነው፤ ***"ትሑት ልብ የሥጋ ሕይወት ነው፤ ቅንዓት ግን አጥንትን ያነቅዛል"*** (ምሳ.፲፬፥፴)
- **የዮሴፍ ወንድሞች**፡- የዮሴፍ ወንድሞች በአባቱ ዘንድ ይወደድ በነበረው በወንድማቸው በዮሴፍ ላይ በቅንዓት ይንገበገቡ ነበር። የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍ በሕልሙ፤ የእነሱ ነዶዎች ለእርሱ ነዶ እየሰገዱ፤ ማየቱን ሲነግራቸው ደግሞ ቅናታቸው አይሎ ወንድማቸውን ለባርነት ሸጠውታል። ዘፍ.፴፯፥፩-፳፰
- **የሄሮድስ ቅንዓት**፡- የገሊላ ገዥ የሆነው ሄሮድስ በዘመኑ ***"የአይሁድ ንጉሥ"*** መወለዱን በመስማቱ በቅንዓት ተገፋፍቶ ያንን በቅናት ያንገበገበውን ንጉሥ ለማግኘት ሲል ሕፃናትን አስፈጅቷል።
- ሌላውን ሆን ብሎ ማስቀናትም ክፉ ነውና አይገባም። ለምሳሌ አንዳንዶች አጋራቸውን ያስቀናሉ። ይህም ግን አይገባም። ***"ክፉ ትምህርትን እንዳትማርብህ ባጠገብህ የምትተኛ ሚስትህን አታስቀናት"*** ሲራ.፱፥፩ ይህ ዓይነቱ ማስቀናት በጓደኝነት እና በጾታዊ ትንኮሳዎችም ይገለጣል። ለዚህ ነው ሲራክ ***"በምተስቀናት ገንዘብ ከሴት ጋር አትናገር።"*** ፴፯፥፲፩

ከላይ ያየናቸውን ቅንዓቶች በቅዳሴ እግዚእ ‹‹***ቅንዓት ጥቅም አያግኝ***›› ተብለዋል።

**ሁለተኛው የሰው ቅንዓት በጎ (መንፈሳዊ) ቅንዓት ነው።**

በጎ ቅንዓት የሚባለው በአንድ በኩል ሕገ እግዚአብሔር በሰው ሁሉ እንዲከበርና መንግሥተ እግዚአብሔር በምድር እንዲሰፍን ከመፈለግ የተነሣ የሚኖር የመፍቀርያነ እግዚአብሔር /የቅዱሳን/

www.zeorthodox.org

ቅንዓት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች መልካም የሠሩትን በማየትና በመስማት ለመልካም ሥራ ሲነሣሡ በጎ ቅናት ይባላል፡፡

**የዳዊት ቅናት**:- ንጉሡ ዳዊት ለአምልኮተ እግዚአብሔርና ለቤተ እግዚአብሔር በእጅጉ የሚቀና ነበር፡፡ ራሱ በዝግባ በተሠራ ቤት በመኖሩ ከመደሰት ይልቅ ታቦተ ጽዮን በድንኳን በመኖሯ ልቡ በቅንዓት ይቃጠልበት ነበር፡፡***"እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጬአለሁ፥ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በመጋረጆች ውስጥ እንደ ተቀመጠ እይ"*** ፪ኛ.ሳሙ.፯፥፪ በማለት በነቢዩ ናታን ፊት ተናግሯል፡፡ በመዝሙሩም ***"በእውነት ወደ ቤቴ ድንኳን አልገባም፥ ወደ ምንጣፌም አልጋ አልወጣም፥ለዓይኖቼም መኝታ ለሽፋሽፍቶቼም እንቅልፍ፥ ለጕንጭቼም ዕረፍትን አልሰጥም፥ለእግዚአብሔር ስፍራ፥ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያ እስካገኝ ድረስ"*** መዝ.፻፴፩፥፫-፭ ሲል እንሰማዋለን፡፡ ቅዱስ ዳዊት በእግዚአብሔር ስም በሚነሣሡት ላይም ***"የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና፥ የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ወድቆአልና፡፡"*** መዝ.፷፰፥፱ ሲል እንሰማዋለን፡፡

**የኤልያስ ቅንዓት**:- ነቢዩ ኤልያስ አምልኮተ እግዚአብሔር ሲጠፋ፣እስራኤል ቃል ኪዳኑን ትተው መሠዊያዎችን ሲያፈርሱ፣ ብቻውን የቀረ እስኪመስለው ድረስ ነቢያት ሲገደሉ እጅግ በቅንዓት ይቃጠል ስለነበረ እንዲህ ይል ነበር፡፡ ***"ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፥ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፥ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ ነፍሴንም ሊወስዱአት ይሻሉ"*** ፩ነገ.፲፱፥፲

**የዮሐንስ ቅናት**:- *መጥምቁ ዮሐንስ አይሁድን* ***"እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጣው ቍጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? ...መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል"*** ማቴ.፫፥፩-፲ እያለ ይገሥጻቸውና መንገድ የተባለውን ልቦናቸውን ለወንጌል ያቀና የነበረው፤ ለሕገ እግዚአብሔር፣ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ከነበረው ጥልቅ ቅንዓት የተነሣ ነው፡፡ ለሰማዕትነት ያበቃው በሰይፍ የመቀላት ቅጣት የተወሰነበትም በቅናት ሄሮድስን ሳይፈራ በመገሠጹ ነው፡፡ ማቴ.፲፬፥፩-፲፪

**የጳውሎስ ቅንዓት**:- አስቀድሞ በቅንዓት ቤተ ክርስቲያንን ያሳድድ የነበረው ቅዱስ ጳውሎስ በኋላ ደግሞ ወንጌልን ለማስፋፋት ጥልቅ የሆነ ቅንዓት በልቡ ተቀጣጠለበት፡፡ ***"ስለ ቅንዓት ብትጠይቁ፥ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ ነበርሁ፤ በሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ፥ ያለ ነቀፋ ነበርሁ፡፡ ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቈጥሬዋለሁ"*** ፊልጵ.፫፥፮-፯ ለዚህም ነው መከራውን ሁሉ ሳይሰቀቅ ስለ ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በቅንዓት ያስብ የነበረው፤ ***"የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው"*** ፪ኛ.ቆሮ.፲፩፥፳፰

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

❖ መለኮታዊው ቅናት ሰዎችን ለመጥቀም አምላክ የሚቀጣበትና የሚያድንበት መንገድ ነው፡

## ተግባር

❖ መንፈሳዊውን ቅናት ለማዳበር ክፉውን ለማስወገድ ጣሩ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ቅንዓት ማለት ምን ማለት ነው?

   ሀ. በግእዝ (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ) መዝገበ ቃላት

   ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት መሠረት ግለጹ፡፡

2. መለኮታዊ ቅንዓት ምንድ ነው? አብራሩ፡፡
3. የሰው ቅንዓት በስንት ይከፈላል? ምን እና ምን?
4. በክፉ ቅንዓት የሚጠቀሱትን ምሳሌዎች በማቅረብ አብራሩ፡፡
5. መልካም (መንፈሳዊ) የሆነው ቅንዓት ምሳሌዎች ምን ምን ናቸው? ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

## ሃያ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ሕይወት ታሪክ፣ አገልግሎት እና መንፈሳዊ ተጋድሎ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *" መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ " ፪ኛ ጢሞ.፬÷፯*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ‹‹መጽሐፈ ስንክሳር››፣ ‹‹ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ›› (ያረጋል አበጋዝ)

**መግቢያ፡-** በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻና በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ የነበረው፤ ከአንፆኪያ የተገኘውና በቁስጥንጥንያ ፓትርክና የተሾመው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ በሕይወቱ፣ በትምህርቱ እና በመንፈሳዊ ቅንዓቱ ብርሃን ሆኖ ያለፈ አባት ነበር፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ከሕይወቱ እና ከትምህርቱ በአጭሩ ለእኛ ሕይወት የሚሆነንን ያህል እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**1. ውልደቱ እና እድገቱ**

ከዝነኛ ወታደር አባቱ ሴኮንዶስ እና በቅድስና ሕይወቷ ለሌሎች አርዓያ ከሆነች ክርስቲያን እናቱ አንቱዛ በ፫፻፵፯(347) ዓ.ም በአንፆኪያ የተወለደው ዮሐንስ አንዲት እኅት ያለችው ሁለተኛ እና የመጨረሻ ልጅ ነበር፡፡

አባቱ በልጅነቱ ስለሞተ እናቱ በጠንካራ እምነት ፣ በወቅቱ (የፍልስፍናና የንግግር ጥበብ ትምህርቶችን) እንዲማር በማድረግ አሳደገችው፡፡ በወጣትነቷ ባልዋ ሞቶባታል፡፡ ሆኖም ሌላ ጋብቻ ሳያምራት ለልጆቿ አርዓያ ሆና አሳደገቻቸው፡፡ ዮሐንስ መምህራኑ እንዲተካቸው እስኪመኙ በጥሩ አቀባበል ትምህርቱን ፈጸመ፡፡ በአንፆኪያ በጥብቅና ሥራ በተሰማራበት ወቅት ከትምህርቱ ቀጥሎ ለእውነት ለመቆም የተዘጋጀበት የተግባር ትምህርት ቤቱ ነበር፡፡ በዮሐንስ ንግግር ክህሎት የሚደነቁ ብዙዎች በፍርድ ቤቶች የርሱን የጥብቅና ክርክር ሊሰሙ ይሰበሰቡ ነበር፡፡ በታላቋ ሮም ሥርዓተ መንግሥት ከወታደርነት ቀጥሎ ለመንግሥት ከፍተኛ ሥልጣን የሚያበቃው የጥብቅና ሞያ ነበር፡፡ ነገር ግን እውነት እና እግዚአብሔርን መፍራት ከእናቱ ለተማረው ለዮሐንስ ለሐሰት ቆሞ መከራከር በሠለጠነበት ዘመን በንጹሐን ላይ የሚፈጸመውን ግፍ እያየ በዝምታ ማለፍ (መኖር) የሚመች

www.zeorthodox.org

አልነበረም፡፡ እናም ጥብቅናውን ትቶ በገዳም ለመኖር ቢመኝም እንዳይለያት በምትፈልገው እናቱ ልመና አብሮዋት ቆየ፡፡

ዮሐንስ በሃያ ሦስት ዓመቱ ተጠመቀ፡፡ እናቱ አንቱዛ በልጅነቱ ዮሐንስን ያላጠመቀችበት ምክንያት በብዙ ታሪክ ጸሐፊያን ሐሳብ የተሰጠበት ሲሆን፤ ዋናው ምክንያት ግን በወቅቱ አርዮሳውያን ከኦርቶዶክሳውያን አለመለየታቸው ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ በፍጹም ልቡ አምላኩን ተከተለ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ***"እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን፡፡"*** ሮሜ.፮÷፬ እንዳለው፤ ዮሐንስም ዓለማዊውን ኑሮ ንቆ በመተው በአዲሱ እውነተኛ የክርስትና ሕይወት ኖረ፡፡ ስለ ቅዱስ ዮሐንስ የጻፈልን ጳላድየስ ዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ የነበረውን ሕይወት ሲገልጥ፤ ***"ፈጽሞ አልማለም፣ አልረገመም፣ በሐሰትም አልተናገረም፣ ረብ ጥቅም የሌለው ነገር ታግሦ አልሰማም፣ ጥምቀቱ ይህንን ዓለም ፈጽሞ የካደበትና ክርስቶስን ለማገልገል ራሱን የሰጠበት፣ ከዓለም ለክርስቶስ የተለየበት፣ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያደረገበት ነበር፡፡ ለውጡም ፍጹምና ዘላቂ ነበር፡፡"*** ብሏል፡፡

## 2. ገዳማዊ ሕይወቱና አገልግሎቱ

### ሀ. ጥሪና ገዳማዊ ሕይወት

የአንፆኪያው ጳጳስ መላጥዩስ ዮሐንስን በአናጉንስጢስነት ሾመው፡፡ ዮሐንስ ግን የእናቱን ቤት ገዳም አድርጐ ገዳማዊ ሕይወትን ጀመረ፡፡ ራሱን ከሌላው ዓለም ለይቶ ብሕትውናን ተለማመደበት፡፡ በጾም፣ በጸሎት፣ መሬት በመተኛት ኖረ፡፡ በሕፃንነቱ አባቱን፣ በወጣትነቱ ተወዳጅ እናቱን ቢያጣም ወደ ገዳማዊ ሕይወቱ ሄዶ በአንፆኪያ አቅራቢያ ባለ ተራራ በሚገኝ ገዳም ለአራት ዓመታት ከአባቶች ጋር፣ ለሁለት ዓመታት በዋሻ ለብቻው ኖረ፡፡ ***"እውነተኛ ፍልስፍና"*** በሚለው ገዳማዊ ሕይወት ሰባት ዓመት ሲኖር በተጋድሎው ብዛት ሰውነቱ ስለተጐዳ ወደ አንፆኪያ ተመለሰ፡፡ ይህም ሰፊውን የስብከተ ወንጌል አገልግሎቱን የሚሰጥበት አጋጣሚ ሆነ፡፡

### ለ. በስብከት እና ቅስና የነበረው አገልግሎት

www.zeorthodox.org

ሊቀ ጳጳስ መላጥዩስ ዲቁና ሾመው፡፡ በዚሁ መዓርግም በታማኝነት አገለገለ፡፡ በ፫፻፹፮(386) ዓ.ም ከጳጳሱ ከፍላቪያን ቅስና ተቀበለ፡፡ እስከ ፫፻፺፯(397)ዓ.ም በቅስና መዓርገ ክህነት በሰባኪነት አገለገለ፡፡ ይህንንም ዋናው ሥራው አድርጎ ዓለምን የለወጡ ትምህርቶችን አስተላለፈበት፡፡ በዐቢይ ጾም ተከታታይ ሰንበታትም ያስተምር ነበር፡፡

### ሐ.አስታራቂው ቅዱስ ዮሐንስ

በአንፆኪያ በተቀሰቀሰው ዓመጽ የምዕራቡን ሮም በአንፆኪያ ሆኖ የሚመራው ንጉሥ ከተማዋን ለማጥፋት ሲወስን፤ ሕዝቡም በግብር ተማሮ የንጉሡንና የቤተሰቡን ሐውልት አፈረሰ፡፡ አረጋዊው ጳጳስ ፍላቪያኖስ ንጉሡን ለመማለድ በታሪክ ጸሐፊያን በዮሐንስ እንደተረቀቀ የሚታመን ደብዳቤ ይዞ ቁስጥንጥንያ ሄደ፡፡ ዮሐንስም የአንፆኪያን ሕዝብ የሚያጽናና፣ ተስፋ የሚሰጥና የተግሣጽ ትምህርት አስተማረ፡፡ ይህ አጋጣሚ የቅድሱን እውቀት፣ ጥልቅ መንፈሳዊነትና አርቆ አሳቢነት ያሳየበት፤ በሕዝቡም መወደድን ያተረፈለት ነበር፡፡ ደብዳቤው ንጉሡን ሲያስለቅስ ስብከቱ ሕዝቡን ወደ አምላኩ የመለሰና ከተለመዱ ክፉ ድርጊቶች ያረመበት ነበር፡፡

አርዮሳውያን የሮምን ነገሥታት በመያዝ የፈጠሩት ክፍፍል የአንፆኪያ ቤተ ክርስቲያንን አውኮአታል፡፡ ኤዎስጣቴዎስ የተባለው ጳጳስ ታስሮ ጳጳስ መላጥዩስ ተተካ፡፡ ይህም የኤዎስጣቴዎስ ደጋፊዎችን ***ኤዎስጣቴዎሳውያን*** በሚል እንዲደራጁ በር ከፈተ፡፡ መላጥዮስንም ተቃወሙት፤ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ መላጥዮስ በግዞት ወርዶ ጳውሊኖስ ተሾመ፡፡ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ አዎስጣቴዎስ ዐርፈ፡፡ መላጥዮስም ወደ አንፆኪያ ተመለሰ፡፡ ነገር ግን ከጳውሊኖስ ጋር አልተስማሙምና፤ መንበሩን ለማን ይሁን? የሚለው ሲያወዛግብ እስክንድርያና ሮም ለጳውሊኖስ እውቅና ሰጡ፡፡ ይህም ልዩነቱን አባባሰው፡፡ መላጥዮስ ሲያርፍ ፍላቪያንን ተካ፡፡ በአንድ መንበር ማገልገል ያለባቸውን አባቶች ጸብ አስቀርቶ ሰላም ለማምጣት ብዙ አባቶች ጥረት አድርገዋል፡፡ በኋላም ቅዱስ ዩሐንስ በመላጥዩስ የተተካውን ፍላቪያንን ከሮም እና እስክንድርያ ጋር አስታረቀው፤ በፍላቪያን በ፬፻፲፭(415) ዓ.ም የተተካው አሌክሳንደር ኤዎስጣቴዎሳውያንን ወደ ቤተ ክርስቲያን መለሰ፡፡ በዚህም ጸቡ እንዲቆም በማድረግ ዋና የነበረው እና በማስተማር፣ በምክር፣ በማስታረቅም የደከመው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ነበር፡፡

### 3. በጽሑፍ የደረሱን የቅዱስ ዮሐንስ ሥራዎች

ቅዱስ ዮሐንስ ዛሬ ድረስ ተወዳጅ የሆኑትን ስብከቶች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎችና በተለያዩ አርእስት ከተጻፉት መጻሕፍት አብዛኛዎቹን አዘጋጅቶአል፡፡ የተወሰኑትም ሲያስተምር በነበሩት በሰማዕያን የተጻፉ ናቸው፡፡ እነዚህንም ጸሐፍያን እንደሚከተለው ይከፍሉዋቸዋል ፡-

www.zoorthodox.org

***3.1. በመጽሐፍ መልክ ያዘጋጃቸው ሥራዎቹ*** ፡፡ እነዚህ ገዳማዊ ሕይወትን በተመለከተ ፣ ስለ ክህነት፣ ስለ ድንግልናዊ ሕይወት፣ ስለ ንጽሕናና ራስን ስለመግዛት ፣ ስለ ሃይማኖትና ስለ እግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ የተጻፉ ናቸው፡፡ ለጳጳሳት እና ለሌሎች ወዳጆቹ የተላኩ የማጽናኛ መልእክታት እና የቅዳሴ መጻሕፍትም ይገኙባቸዋል፡፡

***3.2. በተለያዩ ርእሰ ጉዳዩች ላይ የሰበካቸው ስብከቶቹ እንደሚከተለው ይከፈላሉ፡፡***

**በታሪካዊ ክሥተቶች የተጻፉ** ለምሳሌ ‹‹በእንተ ሐውልት›› ሕዝቡ የንጉሡንና የቤተሰቦቹን ሐውልት ማፍረሱን ምክንያት አድርጎ የመከረበት፤ ንግሥት አውዶክስያ በቤተ ክርስቲያኑ ፊት ሐውልት አቁማ እንዲዘፈንበት በማድረግዋ ለቤተ ክርስቲያን ክብር ቆሞ ያስተማረው ትምህርቶች ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

**በአጽራረ ቤተ ክርስቲያንና በአጽራረ ሃይማኖት ላይ ያስተማራቸው ትምህርቶች** ፤ በዘመኑ ለተነሡ መናፍቃን የተሰጡ መልሶች ናቸው፡፡

**ስለ ግብረ ገብነት፤ ስለ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን፤ ስለ ቅዱሳንና ሰማዕታት የሰበካቸው** ስብከቶቹ እስከ ዘመናችን የሚነበቡ እና የሚሰበኩ ናቸው፡፡

**በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ክፍሎችና ርእስ ጉዳዩች ላይ ያስተማራቸው** አሉ፡፡ እነዚህ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን (ለምሳሌ ፡- የሳምራዊቷን ታሪክ ፣ ዘመዶቹ በጣራ ያስገቡትን በሽተኛ ፣ በማቴዎስ ወንጌል ፷፮ ጌታችን የጸለየውን ጸሎት ተንትኖ ያስተማረባቸው፡፡) እና መጽሐፍ ቅዱስን (ወንጌላትን ፣ መልእክታትን) ያብራራባቸው ትርጓሜዎች ናቸው፡፡

## 1. ዘመነ ፓትርክና

የሮም ግዛት ምሥራቅ እና ምዕራብ ተብሎ ለሁለት ሲከፈል ፤ የምዕራቡ ሮም የምሥራቁ ዋና ከተማም ቁስጥንጥንያ ሆኑ፡፡ በተለይ አዲስ ከተማ የነበረችው ቁስጥንጠንያ ውብ፣ ባለፀጋና ተወዳጅ ከተማ ሆነች፡፡ ለሁለቱም ሊቀ ጳጳሳት ተሾመ፡፡ በዚህ አዲስ መንበር የራሳቸውን ሰው ለማስቀመጥ እስክንድርያና ሮም ይፎካከሩ ነበር፡፡ በዚህ መሓል የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳት ኔክታርዩስ ዐረፈ፡፡ በዚህ የተነሣ በመንበሩ ላይ አባት ለመተካት ክፍተት ተፈጠረ፡፡ አንዳንዶቹም የራሳቸውን ሰው ለመሾም ሲጥሩ ንጉሡ አርቃዲዎስ ግን ቅዱስ ዮሐንስን በድብቅ ከአንፆኪያ ወደ ቁስጥንጥንያ የካቲት ፷፮ ቀን ፫፻፺፰ ዓ.ም አስመጥቶ እንዲሾም አደረገ፡፡ ዮሐንስ ከአንጾኪያ ሲወጣ የሚያውቀው ቤተ ክርስቲያን እንደሚመርቅ ብቻ ነበር ፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ በቁስጥንጥንያ ያጋጠመው የተለየ ነገር ነበር፡፡ ሀብት፣ ሥልጣንና ምቾት የፈጠሩዋቸው የቅምጥልነት ኑሮዎች ከባለ ሥልጣናትና ባለ ጠጎች አልፎ ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ሕይወትም ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ ሕዝቡም ኢክርስቲያናዊ አኗኗር ይጉላበት ነበር፡፡ የአርዮሳውያን እንቅስቃሴም በስድብ የተሞላና በሁከት የሚገለጥ ሆኖ አገኘው፡፡ ይህ ሁሉ ለውጥ ይፈልግ ነበርና፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም ይህንኑ አስፈላጊ ለውጥ ከመንበረ ፖትርያርኩ እና ከካህናቱ ጀመረ፡፡

ለቤተ ክርስቲያን የማያስፈልጉ ጌጣጌጦች ፣ ድግሶችና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን ለነዳያንና ለሕሙማን እንዲውሉ በማድረግ እንዲስተካከለ አደረገ፡፡ ራሱም በገዳም የነበረውን ሕይወት

www.zeorthodox.org

በመቀጠል አርዓያ ሆነ፡፡ በምግባር የሚታሙ ካህናትን በተግሣጽ ፣ በተጨባጭ የተመሰከረባቸውንም ክህነታቸውን በመሻር አረመ፡፡ መነኮሳት በገዳም ካህናት መንጋውን በማገልገል እንዲጠመዱ አደረገ፡፡

ምእመናንንም በሃይማኖት እንዲጸኑ የአርዮሳውያንን ክህደት በትምህርት አስረዳ ፤ በከተማ እየዞሩ የሚያውኩትን አርዮሳውንንም አስቆመ፡፡

የማይገባ ምግባር ፣ አለባበስና ኑሮ የነበራቸውን በግልጽ ገሠጸ፡፡ ድሆችን የሚረዳ ሆስፒታል አቋቋመ፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ድሆች ቀድመው እንዲረዱ እና ሐብታሞች ለድሆች ያለባቸውን ኃላፊነት አስረዳ፡፡

ይህ በጎ ለውጥ ያላስደሰታቸው ግን አልጠፉም፡፡ ሥልጣነ ክህነታቸው በጥፋታቸው የተያዘባቸው፣ ጥቅማቸው የተነካባቸው ካህናት እና ተግሣጹን እንደ ስድብ የቆጠሩት ወይዛዝርት ከቤተ መንግሥቱ ጋር ሊያጋጩት ነገር ይሠሩበት ጀመር፡፡ በተለይም ንግሥቲቷ አውዶክስያ በተቀማጠለ አኗኗርና አለባበሷ እንዲሁም በኃይለኛነቷ ትታወቅ ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ በቅምጥልነት ኑሮ እና ድሆችን ባለማሰብ ላይ አዘውትሮ ያስተምራል፡፡ እነዚህን ትምህርቶቹን ንግሥት አውዶክስያ ቀድሞም አትወዳቸውም ነበር፡፡ ንግሥቲቷ ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ያላትን ጥላቻ የሚያውቁ ጠላቶቹ ሁሉ የሚያስተምረውን ትምህርት ንግሥቲቷን ለመንካት ለማሳጣት እንደሚያስተምር ይነግሯት ጀመር፡፡ እሷም የበለጠ ጥላቻዋ እየከፋ በጠላትነት ታየው ጀመር፡፡ በኋላም መሬትዋን በግፍ የተነጠቀች ደሃ ከቤተ መንግሥቱ ፍትሕ ስላጣች ቅዱስ ዮሐንስን በሽምግልና ላከችው፡፡ ዮሐንስም በሽምግልና ወደ ንግሥቲቱ ሄዶ የደሀዋን መሬት እንድትመልስ ሊያግባባት ሞከረ፡፡ ንግሥት አውዶክስያ ግን ፈጽሞ ፈቃደኛ አልነበረችም፡፡ ከብዙ ጥረት በኋላ በድሀዋ ላይ ግፍ የፈጸመችዋን ንግሥት ከቤተ ክርስቲያን ተሳትፎ ለያት፡፡ ይህም ከታላቅ ድፍረት ተቆጠረና በቅዱሱ ላይ ከቤተ መንግሥቱ ቁጣ ቀሰቀሰ፡፡

በዚህ መሐል የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ባልሠሩት ሥራ አጥፍታችኋል ብሎ ያባረራቸው መነኮሳት እንዲያስታርቃቸው ወደ ዮሐንስ መጡ፡፡ ዮሐንስም አባቴ ነው ከሚለው ከቴዎፍሎስ ጋር መነኮሳቱን ለማስታረቅ ጥረት አደረገ፡፡ ሆኖም ቴዎፍሎስ እንቢታውን በዝምታ ስላሳየ መነኮሳቱ ለንጉሡ አመለከቱ፡፡ ንጉሡም በዮሐንስ ሰብሳቢነት ቴዎፍሎስ ወደ አንጾኪያ መጥቶ መፍትሔ እንዲሰጡ አዘዘ፡፡ ይህም ለክብሩ ልዩ ትኩረት የሚሰጠውን ቴዎፍሎስን በዮሐንስ ላይ እንዲነሣ አደረገ፡፡ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ወደ ቁስጥጥንያው መንበረ ፓትርያርክ አልሄደም፡፡ ከቅዱስ ዮሐንስ ጋርም አልተገናኘም፡፡ በቁስጥንጥንያ ከተማ የሰነበተው ቴዎፍሎስ ንግሥቲቱን እና አኩራፊዎቹን ካህናት አሰባስቦ ሲመክሩበት ቆየ፡፡ በኋላም ቅዱስ ዮሐንስ ከመንበሩ ተነሥቶ እንዲሰደድ የሐሰት ምስክሮችን ተጠቅሞ አስወሰነበት፡፡

www.zeorthodox.org

ሕዝቡ በዚህ ውሳኔ እጅግ ተቆጣ፡፡ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ በተላለፈው የግፍ ውሳኔና ቅጣት የእግዚአብሔር ቁጣ በልዩ ልዩ ተአምራት ተገለጸ፡፡ በዚህ ምክንያት ቅዱስ ዮሐንስ ወደ መንበሩ እንዲመለስ ተደረገ፡፡ ንግሥቲቱም በድንጋጤ የተመለሰች መሰለች፡፡ ቆይታም ወደ ቀደመ ግብርዋ ስለተመለሰች ሐውልቷን በቤተ ክርስቲያኑ ፊት አቁማ ይጨፈርበት ነበር፡፡ ይህም ቤተ ክርስቲያንን መድፈር ስለሆነ ዮሐንስ ድርጊቱን በስብከቱ ተቃወመ፡፡ ጸቡ እንደገና አገረሸና ቅዱሱ ወደ በረሓ ተጋዘ ፤ በመንገድም ላይ በ፬፻፯(407) ዓ.ም ዐረፈ፡፡

## ማጠቃለያ

- ❖ ቅዱስ ዮሐንስ ከቤተሰቡ የተማረውን መልካም አኗኗር በተግባር የተከተለ አባት ነው፡፡ እኛም መልካም አርዓያዎቻችንን ማወቅ እና መከተልን እንማራለን፡፡
- ❖ ቅዱስ ዮሐንስ በጾም እና በጸሎት መልካሙን ገድል የተጋደለ፤ ለማስታረቅ የተጋ አባት ነው፡፡ እኛም ይህን የእግዚአብሔር ኃይል ብንታጠቅ በመንፈሳዊው ተጋድሎ የክብር ዘውድ እንቀዳጅበታለን፡፡
- ❖ ቅዱስ ዮሐንስ ለእውነት የቆመ እና የተጋደለ አባት ነው፡፡የእውነትን እና የቅድስናን ኑሮም አሳይቶአል፤ ለእኛም አርዓያ ነው፡፡

## ተግባር

*1. ለነገ ዛሬ ተዘጋጁ፡፡* ቅዱስ ዮሐንስ በልጅነቱ ከትምህርት ቤት እና ከቤተሰቡ በአግባቡ መማሩ ጠቅሞታል፡፡ ሰውን የሚጠቅም እና እግዚአብሔርን የሚያስደስት ታላቅ ሰብዕና ላይ የምንደርሰው ዛሬን በአግባቡ ስንዘጋጅ ነው፡፡ መማር፣ እግዚአብሔርን በመውደድና በመፍራት ማደግ ዛሬ የምንተጋባቸው፤ ነገ በዚህ ዓለምና በእግዚአብሔር መንግሥት ታላቅ የሚያደርጉን ናቸው፡፡ ***" አንተ ጐበዝ፥ በጐብዝናህ ደስ ይበልህ፥ በጐብዝናህም ወራት ልብህን ደስ ይበለው፥ በልብህም መንገድ ዓይኖችህም በሚያዩት ሂድ፤ ዳሩ ግን ስለዚህ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንዲያመጣህ እወቅ፡፡ ሐዘንንትና ጐብዝና ከንቱዎች ናቸውና ከልብህ ኀዘንን አርቅ፥ ከሰውነትህም ክፉን ነገር አስወግድ፡፡"*** መክ.፲፩፥፱-፲

www.zeorthodox.org

*2. ጾምና ጸሎትን ቅዱሳት መጻሕፍት ከማንበብ ጋር ተለማመዱ፡፡* ***"ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡"*** ፪ኛ ጢሞ.፫፥፲፮ ቅዱስ ዮሐንስ ከጾምና ጸሎት ጋር ማንበቡ ቅዱሳት መጻሕፍትን እና ይህን ዓለም ተረድቶ ታላቁ አባት እና መምህር ለመሆን አብቅቶታል፡፡

***3. ለመልካም ነገር ተፈላጊ ሁኑ።*** ከታሪኩ እንደተማርነው ቅዱስ ዮሐንስ የተጣሉ ለእርቅ ፣ የተበደሉ አቤት እንዲልላቸው ፣ ለወሳኝ የአገልግሎት መስክ ተመራጭ እና ተፈላጊ ነበር። እኛም ‹‹***የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና***›› ማቴ.፭፥፱ እንደተባለ ለማስታረቅ፣ ለመፍትሔ፣ ለመልካም ምክር፣ ለጸሎት የምንፈለግ እንድንሆን፤ ሰላማዊ እና መንፈሳዊነትንም በእውነት የያዝን መሆን አለብን።

***4. ለእውነትና ለተሻለ ሥራ ተሰለፉ።*** መልካምነት እና እውነት ዋጋ ያስከፍላሉ፤ እንደ ውጤታቸው ግን አይሆንም። እናም ለእግዚአብሔር እና ለእውነት ኑሩ። ይህንንም ማድረግ የዘላለምን አክሊል ለመቀዳጀት ያበቃል።

***ጥያቄዎች***

1. የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እናትና አባት ማን ይባላሉ? የት ተወለደ? ማን አሳደገው?
2. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ገዳማዊ ሕይወትን የጀመረው እና የተለማመደው የት ነበር? እንዴት?
3. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ዲቁና የተቀበለው ከማን ነበር? የቅስና ሥልጣነ ክህነት የተቀበለውስ ከማን ነው? መቼ?
4. ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የማስታረቅ መልካም ሥራ ዋና ዋናዎቹን ግለጹ።
5. የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን የጽሑፍ ሥራዎች በልዩ ልዩ ርእሰ ጉዳዮች ይከፍሏቸዋል። በምን በምን ርእሰ ጉዳዮች እንደሆኑ በተማራችሁት መሠረት ግለጹ።
6. ስለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የፓትርያርክነት ሹመት ግለጹ። በማን? እንዴት ተሾመ?
7. በፓትርያርክነት አገልግሎቱ ያጋጠመው ፈተና ምን ነበር?

www.zeorthodox.org

# አባ ባሕርይ እና ሥራዎቹ

## ሃያ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ከአባ ባሕርይ ሕይወት፣ ታሪክና ሥራዎች ስለ ቤተ ክርስቲያንና መንፈሳዊ ሰብእና ይገነዘባሉ፡፡ መምህሩ የሚያቀርቡ ላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-***"እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ"* ፩ኛ ቆሮ.፲፩፥፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የአባ ባሕርይ ድርሰቶች (በጌታቸው ኃይሌ 1997 ዓ.ም)፤ ‹‹የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች›› ዳንኤል ክብረት (1998ዓ.ም)

**መግቢያ፡-** 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ የተነሣው ግራኝ አህመድ ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተነሣው የኦሮሞ መስፋፋትና የሰሜኑን የክርስቲያን መንግሥት እንደ አዲስ ያዋቀረው የዐፄ ሠርፀ ድንግል ታሪክ የተከሠተበት ዘመን ነው፡፡ አባ ባሕርይም በዚህ ዘመን የነበረ መንፈሳዊ ደራሲ እና የታሪክ ጸሐፊ ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለአባ ባሕርይ እና ድርሰቶቻቸው እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ዋና ትምህርት፡-

አባ ባሕርይ፡- በ፲፭፻፳፰(1528) ዓ.ም በጋሞ ጐፋ ተወለዱ፡፡ ከዚያም ወደ ብርብር ማርያም ሄደው ተማሩ (ብርብር ማርያም በደቡብ ኢትዮጵያ ከጨንቻ ከተማ 30 ኪ.ሜ ርቃ የምትገኝ በብሉይ ኪዳን የኦሪት ሥርዓት ይሠጥባት የነበረች ጥንታዊት ገዳም ናት፡፡) በዚያም አባ ባሕርየ በመነኮሳቱ ሕይወት ተማርከው መነኮሱ፤ በትውልድ ቦታቸው በተከሠተ ችግር ምክንያትም ወደ ምድረ አምሐራ ሄደው ኖሩ፡፡ በነበራቸው የሥነ ጽሑፍ ተሰጥዖ እና የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በአፄ ሠርፀ ድንግል ቤተ መንግሥት አገልግለዋል፡፡ ካሉን መረጃዎች ስለ አባ ባሕርይ የሚከተሉትን እንረዳለን፡፡

www.zeorthodox.org

1. **የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፡-** እግዚአብሔር በሰጣቸው የድርሰት ፀጋና በቤተ ክርስቲያን በሚገባ ባጠኑት ትምህርት ዕውቀትን እና መንፈሳዊነትን አስተባብረው የያዙት አባ ባሕርይ፤ ከጻፏዋቸው መጻሕፍት አራቱ በግጥም መልክ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ እነርሱም፡- መዝሙረ ክርስቶስ፣ አጭሩ መዝሙረ ክርስቶስ፣ መልክዐ ገብርኤል፣ ሰላመ ቅዱሳን ናቸው ፡፡ (እዚህ ላይ አባ ባሕርይ መዝሙረ ክርስቶስ ብለው የሰየሙዋቸው ሁለት ድርሰቶች አሉዋቸው፡፡ አንዳንድ ምሁራን ‹‹መዝሙረ

ክርስቶስ›› እና ‹‹አጭሩ መዝሙረ ክርስቶስ›› በማለት ይለዩዋቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርታችን ይህንኑ ስያሜ ተከትለን በተጻፉበት ዘመን ቅደም ተከተል እናያቸዋለን፡፡)

***1.1 አጭሩ መዝሙረ ክርስቶስ*** በ፲፭፻፶፫(1553) ዓ.ም አባ ባሕርይ የ፳፫ ዓመት ወጣት ሆኖ የደረሰው ነው፡፡ እንደ መዝሙረ ዳዊት ፻፶፩(151) መዝሙራት ሲሆኑ፤ እያንዳንዳቸው ባለ አምስት መስመር ግጥሞችን የያዙ ናቸው፡፡ ይህም አይሁድ በአምስት እየከፈሉ ከሚያደርሱት የመዝሙር ጸሎት እና ከቤተ ክርስቲያናችን የጸሎተ ቅዳሴ ምስባክ አምስት ጊዜ መባል ጋር ይመሳሰላል፡፡

ለድርሰታቸው የቅዱስ አትናቴዎስን የመዝሙረ ዳዊት ትርጓሜ ተጠቅመዋል፡፡ ይህ መዝሙር በአምስቱ ሕዋሳት ምሳሌ ለአምስት ተክፍሎ ለክርስቶስ የቀረበ ምሥጋና ነው፡፡ የክርስቶስን አምላክነት፣ መድኃኒትነት እና ፍቅር የሚሰብክ፣ ኦርቶዶካሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ጌታችን ያላትን ትምህርት የሚገልጥና ወደ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚማጸንም መጽሐፍ ነው፡፡ እኛም ተስፋችንን ክርስቶስን ከአባ ባሕርይ ጋር ፡-

***ፍዳ አስተሐመምኩ በእንቲአከ ተርጉሞ መዝሙር ቅዱስ***

***ሀበኒ አስበ ዘሥጋ ወነፍስ ፡፡***

***<u>ትርጉም</u>***

***ስለአንተ የተቀደሰውን መዝሙር በመተርጎም ስለደከምኩ***

***የሥጋና የነፍስ ዋጋ ስጠኝ*** እንላለን፡፡

***1.2 መዝሙረ ክርስቶስ*** በ፲፭፻፸፬(1574) ዓ.ም የተጻፈ ሲሆን ፡- በተጻፈበት ዘመን ፣ በይዘቱ እና በመጠኑም ከመጀመሪያው ይለያል፡፡ ፻፶፩(151) መሆኑ መዝሙረ ክርስቶስ በሚለው ስያሜውና ስለክርስቶስ የተደረሰ መሆኑም ያመሳስለዋል፡፡ በዚህኛው መዝሙሩ አባ ባሕርይ ስለ ሚያደንቃቸው ንጉሥ ስለ ዐፄ ሠርፀ ድንግል ለክርስቶስ ያቀረበው ጸሎት አለበት፡፡

እንደ መዝሙረ ዳዊት ፻፶፩(151) መዝሙራትን የያዘ በመዝሙረ ዳዊት መስመር እና የፊደል ቁጥር ልክ የተዘጋጀ ነው፡፡ ዓላማውም ከግራኝ በኋላ የጠፉ መጻሕፍትን እንደ አዲስ የመገልበጥ ሥራ በሊቃውንቱ ይሠራ ስለ ነበር የግእዙን መዝሙረ ዳዊት ልክ ማሳወቅ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

አባ ባሕርይ የዚህን መዝሙረ ክርስቶስ ሆሄያት ለዐሥራ ሁለቱ ወራት፣ ለዐሥራ ሁለቱ ከዋክብት ፣ ለሰባቱ ዕለታት እና ለዓመቱ ቀናት እኩል አካፍለው ሁለት ቀሩባቸው፡፡ ይህን ሲገልጡም ***"እነሱን ለራሴ አደረግኋቸው፡፡ እንዳልረሳቸውም ከፊቴ ጻፍኳቸው፡፡ የነዚያ ሆሄያት ስምም ሞት ነው፡፡ ከእነሱ ሩቅ የሆነው እግዚአብሔር እስከ አስደሰተው ድረስ ከኔ ያርቃቸው፡፡"*** ብለዋል፡፡

***1.3 ሰላመ ቅዱሳን፡-*** በመጽሐፈ ስንክሳር ለተጻፉት ቅዱሳን ከእሱ በፊት የነበሩትን አርከ ሥላሴን አብነት አድርጎ ባለ አምስት መስመር ሰላምታ በ፲፭፻፸፮(1576) ዓ.ም ጽፎአል። አባ ባሕርይ ቅዱሳንን ***"ለባስያነ መስቀል ዘዓርብ-የዓርብ መስቀል ለባሾች"*** ይላቸዋል። ስለ እራሱ ሲማጸንም ***"ወዳጃችን... ባሕርይ ሆይ "*** በሉኝ ይላል።

***1.4 መልክዐ ገብርኤል፡- "የብስራት ወራት ቀረበ፣የወንጌል ዘመን ደረሰ ብለህ የሐዲስ ኪዳን መጋብያን መጀመሪያ ሆንክ"*** ብሎ የሚጀምረው መልክዐ ለቅዱስ ገብርኤል ወዳጅነት የቀረበ ፣ የሚገባ ምሥጋና ነው። ይህም በሉቃ ፩÷፳፮ እና ዕብ ፩÷፲፬ ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ያስታውሰናል።

2. **የአባ ባሕርይ *ታሪካዊ* ሰነዶች። ስለ ኦሮሞ፡-** የተጻፈው በኀብረተሰብእ ጥናት (Anthropology) *መልክ* የቀረበ የቤተ ክርስቲያንን ብሔራዊ ሚና የምናስተውልበት ሲሆን ፤ የኦሮሞን ሕዝብ *ታሪክ*ና ባህል ይዞአል። ስለ ዐፄ ሠርፀ ድንግል *ታሪክ*ም በተለይ በዜና *መዋዕ*ላቸው የተጻፈው አስገራሚ *ታሪክ* ጸሐፊ አባ ባሕርይ ነው።

3. **የአባ ባሕርይ ሰብእና *መገለጫዎች*።** ከላይ ካየናቸው *መጻሕፍት* ስለ አባ ባሕርይ የሚከተለውን እንገነዘባለን፡-

***3.1 መጻሕፍት አንባቢ ነበሩ፡-*** አባ ባሕርይ ብዙ *መጻሕፍት*ን *ያ*ነበቡ ሲሆኑ ፤ ይህንንም በድርሰቶቻቸው በሚያነሡአቸው (በሚጠቅሷቸው) ኃይለ *ቃ*ላት እናስተውላለን። ከዚህም በተጨማሪ ራሳቸው ***"የጻፍኩት በራሴ ቃል ሳይሆን ከመጻሕፍት እያመጣሁ ነው።"*** ብለዋል። ‹‹*መዝሙረ* ክርስቶስ›› ለተባለው ድርሰታቸው ብቻም ዘጠና *መጻሕፍት*ን በዋቢነት ጠቅሰዋል። ይህም *መጻሕፍት*ን አንባቢ ብቻ ሳይሆኑ አስተዋይ እና በአግባቡ *መ*ጠቀም የሚችሉ እንደነበሩም *ያመ*ለክተናል።

***3.2 ትሑት ነበሩ፡-*** የዚህ ሁሉ እውቀት ባለቤትና ደራሲ የነበሩት አባ ባሕርይ፤ ሌሎችን አክብረው ራሳቸውን በትኅትና ዝቅ የሚያደርጉ ነበሩ። ጌታችን ***"በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን?"*** ተብሎ ሲጠየቅ ***"እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው።"*** *ማቴ* ፲፰÷፩-፬ እንዳለን። አባ ባሕርይም በምናኔ በብርብር ማርያም እያሉ ስለ ነበረው ሕይወት ሲጽፍልን ***"እኔ የደብረ ማርያም መናኝ ከካህናት የማንስ የመነኮሳት አገልጋይ ነኝ።"*** ይላሉ። የዚህንም ምክንያት ***"እኔስ ችሎታ ከእሱ ለሆነ ለእግዚብሔር ምስጋና ይሁን እላለሁ።"*** በማለት የቅዱሳኑን የትኅትና ሕይወት እግዚአብሔርን ማወቅ *መ*ሆኑን አስተምረውናል።

***3.3 የሥነ መለኮት ሊቅም ናቸው፡-*** ምስጢረ ሥላሴን ፣ ምስጢረ ሥጋዌን ፣ ስለ ሞትና ትንሣኤ የቅዱሳንንም ክብር በድርሰቶቻቸው በብዛት *ያ*ስተምራሉ። ለምሳሌ የሚከተለውን ስንኝ ተመልከቱ፡-

www.zeorthodox.org

| | |
|---|---|
| ***ብፁዕ ብእሲ ዘኢሐረ ኅበ ፍኖተ ካሕድ*** | ***ወደ ክህደት መንገድ ያልሄደ ሰው ምስጉን ነው*** |
| ***ወዘቆመ በእምነተ አብ ወወልድ*** | ***በአብ እና በወልድ እምነት የቆመ*** |
| ***ወበ ሃይማኖተ መንፈስ ቅዱስ ሥላሴ ዋሕድ*** | ***በሃይማኖተ መንፈስ ቅድስም አንድ የሆነ ሥላሴ*** |

❖ የቅድስና ሕይወት ከጥልቅ ዕውቀት ጋር ሲሆን ፍሬው ብዙ ነው፡፡

3.4 ***ታሪክ ጸሐፊው መነኩሴ*** ፡- አባ ባሕርይ በድርሰት ሥራዎቻቸው ብቻ ሳይሆን የታሪክ እና የማኅበረሰብ ጥናቶችም በማዘጋጀታቸው ይታወቃሉ፡፡ እነዚህም በኢትዮጵያ ታሪክ የተለየ ክሥተት ባስተናገደው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩትን ታሪካዊ ሁነቶች የጻፉባቸው ናቸው፡፡ በሰሜኑ ዘውዳዊ ሥርዓት በድጋሚ ያንሰራራውን እና ግራኝን ያሸነፈውን የዐፄ ሠርፀ ድንግልን ታሪክ፤ በሌላም በኩል በዚያው ዘመን ከደቡባዊ ምዕራብ እስከ ሰሜን የተንቀሳቀሰውን የኦሮሞ ሕዝብ ባህል ፣ ታሪክ እና ኅብረተሰብአዊ መዋቅር በስፋት ዘግቦልናል፡፡ ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባቶች የነበራቸውን ገንቢ እና ሀገራዊ ሚና የሚወክል ነው፡፡

4. **የአባ ባሕርይ ትንቢት**፡- አካባቢያችንን በመረዳት በሃይማኖት መኖር እና ለመጪው ትውልድ ጠቃሚ ነገር ማስተላለፍን አስተምረውናል፡፡ ***"ለእመ ምትኩ ካልአን ይጽሐፉ ዜናየ - ስሞት ታሪኬን ሌሎች ይጽፋሉ፡፡"*** እንዳሉን ይኼንኑ ታሪክን ፈጸምን፡፡

***"ለይትፈሥሑ ወይትሐሠዩ ዘይዜክሩ ስምየ በሠናይ - ስሜን በመልካም ለሚያነሡ ደስ ይበላቸው"*** ብለው ወደ ክርስቶስ በጸለዩት ጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ደስታ ያድልን፡፡ አሜን!!

## ማጠቃለያ፡-

አባ ባሕርይ በ16ኛው መቶ ክፍል ዘመን የነበሩ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በሚገባ የተማሩና እስከ አሁን የታወቁ አምስት ድርሰቶች እና የታሪክ መዛግብትን ያስተላለፉልን አባት ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

ስለ አባ ባሕርይ ተጨማሪ መረጃዎች በተጨማሪ ምንባባት ከተሰጡዋችሁ አንብቡ፡፡ ከመምህራንም ጠይቁ፡፡ በሥራችሁ ትጉታን እና ሁሉን የሚያስችል እግዚአብሔርን የምታመሰግኑ ሁኑ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. አባ ባሕርይ የተወለዱት የት ነው? መቼ ተወለዱ? የት ተማሩ ? አባ ባሕርይ የተማሩባት ገዳም የት ትገኛለች? በምን ትታወቃለች?
2. አባ ባሕርይ በግጥም መልክ ያዘጋጁአቸው መጻሕፍት ስንት ናቸው? ዝርዝራቸውን ግለጹ፡፡
3. አባ ባሕርይ በኅብረተሰብእ ጥናት መልክ እና በታሪክ ረገድ ስለ ጻፏቸው የጽሑፍ ሥራዎቻቸው ምንነት አብራሩ፡፡
4. የአባ ባሕርይን መገለጫዎች በተማራችሁት መሠረት ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# አዋልድ መጻሕፍት

## ሃያ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ አዋልድ መጻሕፍት ምንነት ያውቃሉ፤ በመምህሩ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-**«የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡» ፪ኛ ጢሞ ፫፥፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹አዋልድ መጻሕፍት›› ዲ/ን ዳንኤል ክብረት ፤

**መግቢያ፡-** ልጆች ስለ አዋልድ መጻሕፍት ምን ታውቃላችሁ? ለምን አስፈለጉ?

## የሳምንቱ ትምህርት

1. **የቃሉ ትርጉም፡-** ‹‹አዋልድ መጻሕፍት››፡- በሴት አንቀጽ፣ በብዙ ቁጥር፣ በሦስተኛ መደብ ያለ የግእዝ ቃል ሲሆን፤ ትርጉሙም ‹‹ልጆች›› ማለት ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ለማለት ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

2. አስፈላጊነታቸው (በቤተ ክርስቲያን ያላቸው አገልግሎት እና ቦታ)

   ሀ. **ለትምህርት፡-** የሃይማኖት ትምህርትን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜን ለማወቅ፤ ከዋነኞቻችን ሕይወት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖርን ለመማር፣ አዋልድ መጻሕፍት ያስፈልጉናል፡፡ *«ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጽ ዚአነ ተጽሕፈ-የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጻፈ»* ሮሜ ፲፭፥፬

   ለ. **ለምሥጋና እና ለጸሎት፡-** በማኅበር እና በግል እግዚአብሔርን ለማመሥገን፣ በጸሎት ለመለመን፣ በሥርዓትና በአገባብ አምልኮአችንን ለመፈጸም አዋልድ መጻሕፍት ያስፈልጋሉ፡፡

   ሐ. **ለተዘክሮ፡-** በዘመናት የተፈጸሙ የእግዚአብሔርን ሥራ እና የቅዱሳንን ተጋድሎ ለማሰብ፡፡

www.zeorthodox.org

4. **መመዘኛቸው**

   ሀ. ከዐሥራው መጻሕፍት (ከመጽሐፍ ቅዱስ) ትምህርት ያልወጡ መሆን አለባቸው፡፡

   ለ. በቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርት፣ ሥርዓት እና ትውፊት የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፡፡

   ሐ. ሰማያዊ ዓላማ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 5. ዓይነታቸው

### ሀ. የጉባኤ ቤት መጻሕፍት ፦

በቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት(መጻሕፍት ቤት) ከመጽሐፍ ቅዱስ(ብሉያት እና ሐዲሳት)ቀጥሎ የሚተረጎሙ ናቸው፡፡ ከዐሥራው መጻሕፍት ጋር ለአስረጅነት ይጠቀሳሉ፡፡ **ለምሳሌ፡-** የቦሩ ሜዳ ጉባኤ የተዋሕዶ ሊቃውንት በምንጭነት ይጠቅሱዋቸው መናፍቃኑንም ይጠይቁባቸው ነበር፡፡

አብዛኞቹ የተጻፉት በመጀመሪያዎቹ አምስት ክፍለ ዘመናት ሲሆን ምንጫቸውም የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች እና ጉባኤያት ነበሩ፡፡

እነዚህም ሁለት ዓይነት ሲሆኑ ሊቃውንት እና መነኮሳት ይባላሉ፡፡

1. **ሊቃውንት**፦ሃይማኖተ አበው፣ 14ቱ መጻሕፍተ ቅዳሴያት፣ቄርሎስ፣ፍትሐ ነገሥት የመሳሰሉት ናቸው፡፡
2. **መነኮሳት፡-** ማር ይስሐቅ፣ ፊልክስዮስ፣ አረጋዊ መንፈሳዊ የሚባሉት ናቸው፡፡

### ለ. የመታሰቢያ መጻሕፍት፡-

‹‹… ***እግዚአብሔርንም ለሚፈሩ ስሙንም ለሚያስቡ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተጻፈ*** …›› ሚልክ. ፫፥፲፮ ተብሎ እንደተተነበየ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ቅዱሳን መላእክት እና ጻድቃን ሰማእታት መታሰቢያ የተጻፉ መጻሕፍት ገድላት፣ ድርሳናት፣ ተአምራት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### ሐ.የጸሎት መጻሕፍት፡-

በቤተ ክርስቲያን በግል እና በማኅበር ለመጸለይ የሚሆኑ ናቸው፡፡ ከይዘታቸው እና አገልግሎታቸው አንጻርም የግል እና የማኅበር ጸሎት ናቸው፡፡

- በግል የሚጸለይባቸው፡- መልካ መልክ፣ውዳሴ ማርያም፣ውዳሴ አምላክ
- በማኅበር የሚጸለይባቸው፡-እነዚህም ለልዩ አገልግሎት እና ለዕለታዊ አገልግሎት የሚውሉ ናቸው፡፡ ለዕለታዊ አገልግሎት የምንገለገልባቸው፡- መጻሕፍተ ቅዳሴ፤ጸሎተ ኪዳን፤ ለልዩ አገልግሎት የምንገለገልባቸው፡-መጽሐፈ ተክሊል፣ግብረ ሕማማት ናቸው፡፡

### መ. የታሪክ መጻሕፍት

www.zeorthodox.org

የቤተ ክርስቲያንን ሂደት የሚያትቱ መጻሕፍት ሲሆኑ፤ በአባቶች ሕይወት፣ በገዳማት እና አድባራት ታሪክ እና በሁነቶች (ጉባኤያት፣ ስደት፣ የነገሥታት ዓዋጆች…) ተመሥርተው የቤተ ክርስቲያንን ድል እና መከራ የሚያስቃኙን በይዘታቸው ታሪካዊ አቀራረብ ያላቸው ናቸው፡፡ የዋልድባ ገዳም ታሪክ፣ የበረሓው ኮከብ፣ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔያት ውሳኔዎች፣ ወዘተ… ናቸው፡፡

**ሠ.የትርጓሜ መጻሕፍት**

የመጽሐፍ ቅዱስን፣የሊቃውንትን፣የመነኮሳትን፣የሌሎች መጻሕፍትን ምስጢራዊ ትርጓሜ የያዙ ናቸው፡፡ ወንጌል ትርጓሜ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ሠለስቱ ሐዲሳት፣ ቅዳሴ ትርጓሜ ይጠቀሳሉ፡፡

## 6. አዋልድ መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ቦታ እና ቁጥራቸው፡-

አዋልድ መጻሕፍት እንደ ስያሜያቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ናቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ቦታም የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች የሚለው ነው፡፡ ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል እና በላይ አይደለም፡፡

ቁጥራቸውም በየዘመናቱ የሚጻፉ ስለሆኑ ይህን ያህል ተብለው አይወሰኑም፡፡ የአዋልድ መጻሕፍትን የሃይማኖት መጻሕፍትነት የሚያረጋግጠው ቤተ ክርስቲያን ስትቀበላቸው ነው፡፡

**አዋልድ መጻሕፍትን ለመቀበላችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች**

ይሁ ፩፥፱ ቅዱስ ሚካኤል እና ዲያቢሎስ ስለ ሙሴ ሥጋ ያደረጉት ክርክር የሚገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ አይደለም፡፡ በገድለ ሙሴ /Assumption of Mosses/ ነው፡፡ ‹‹አንተ ጎልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፡፡ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ ሌላውም ያስታጥቅሃል፡፡ ወደ ማትወደውም ይወስድሃል አለው፡፡ በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ፡፡›› ዮሐ.፳፩፥፲፰፣ የቅዱስ ጴጥሮስ አሟሟት እንዴት ነበር? በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የለም፡፡ ከአዋልድ በገድለ ሐዋርያት እና በመጽሐፈ ስንክሳር ላይ እናገኘዋለን፡፡

# ማጠቃለያ

- ❖ አዋልድ መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ማለት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ሲሆን ለትምህርት፣ ለጸሎትና ለአገልግሎት ያስፈልጋሉ፡፡

# ተግባር

- ❖ አዋልድ መጻሕፍት የማንበብ ልምድ ይኑራችሁ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

www.zeorthodox.org

1. ‹‹አዋልድ መጻሕፍት›› ማለት ምን ማለት ነው? ስያሜው የተሰጠበት ምክንያት ምንድነው?
2. ‹‹አዋልድ መጻሕፍት›› ለምን ያገለግላሉ? በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ቦታ እና አገልግሎት ምንድነው? አብራሩ፡፡
3. ‹‹አዋልድ መጻሕፍት›› ለመባል መመዘኛው ምን ምን ናቸው?
4. የአዋልድ መጻሕፍት ዓይነቶች ስንት ናቸው? በዝርዝር ግለጹ፡፡
5. ‹‹አዋልድ መጻሕፍትን›› ለመቀበላችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን በመጥቀስ አብራሩ፡፡

# ትውፊት

## ወግ፤ ባህል፤ ትውፊት - በመጽሐፍ ቅዱስ (አንድ)

## ሃያ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ትውፊት ምንነት ያውቃሉ፤ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ፡፡›› ፩ኛ ተሰ. ፪፥፲፭*

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ›› አቡነ ጎርጎርዮስ /BIBLE DICTIONARY; ZONDERVAN'S; 1987; p.1031/Patrology Holy Trinity College lesson/

## መግቢያ

የማንነት ጉዳይ የሰው ልጆች ጥያቄ ሆኖ የኖረና የሚኖርም ነው፡፡ በግለሰብም ሆነ በማኅበረ ሰብእ ሰዎች ካሏቸው የማንነት መገለጫዎች አንዱ የእኔ፣ የወገኔ የምንለው ወግ እና ባህል÷ እንዲሁም በሃይማኖት የምንቀበለው ትውፊት ነው፡፡

አንዳንዶች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማንነታቸውን እንደሚያጠፋ ሲቆጥሩት ÷ ሌሎቹ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ሆነው ለወግ፣ ባህልና ትውፊት ጀርባቸውን የሰጡና መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚሉም አሉ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የቃሉን ፍቺና አስፈላጊነቱን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

**ትውፊት፡-**ቅብብል ማለት ሲሆን ÷ ከአባቶች ወደ ልጆች በቃል፣ በጽሑፍ እና በተግባር የሚተላለፍ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ትርጉሞች ***"ወግ" "ባህል" "የተቀበላችሁት" "የተቀበልኩት"*** (በግእዝ ትውፊት ማለት ነው፡፡) ተብሎ ተገልጾአል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት /እንግሊዘኛ/ የሚከተለውን ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ Tradition/Greece Paradosis, a giving over, by word of mouth or in writing./ **ትርጉም፡-** በግሪክ ባራዶሲስ ሲባል በቃልና በጽሑፍ የሚተላለፍ ነው፡፡ የነገረ መለኮት/ ቲዎሎጂ/ ዘርፍ የሆነው ፓትሮሎጂ (Patrology) ምሁራንም የሚከተለውን ትርጉም ይሰጡታል፡-

www.zeorthodox.org

**Tradition** the Dictionary of the word tradition is a custom or belief idea handed down from ancestors to postery. (and this is written in small letter tradition but… TRADITION (is the source of the orthodox churches) is a belief (faith) which our lord Jesus Christ has taught (imported) to the Apostles and which since the Apostles time handed down from generation to generation in the church. **ትርጉም፡-** የtradition (ባህል) *መዝገበ ቃላታዊ ትርጉሙ ልማድ ወይም እምነት ሆኖ ከአባቶች ወደ ልጆች (ተከታዮች) የሚተላለፍ ነው፡፡* TRADITION (*በካፒታል ሲገለጽ ግን) ከጌታችን ለሐዋርያት ከዚያም በአባቶች ለቤተ ክርስቲያን የተላለፈ መሠረታዊ ትምህርት ነው፡፡*

*መጽሐፍ ቅዱስ ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፉ ልዩ ልዩ ቅብብሎሾች እንዳሉ ያስተምረናል፡፡*

## ትውፊታዊ መረጃ በብሉይ ኪዳን

*ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት ነበር፡፡ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ትምህርት ለአዳም ያስተማረውን ተስፋ የሰጠው በቃል ነው፡፡ ዘፍ.፩፥፳፰ ፣፪፥፳-፲፯ የአዳም ልጆችም ተስፋውን በቃል ሲቀባበሉ ኖረው ነው በመጽሐፍ የተሰጣቸው፡፡ አቤልና ቃየል መሥዋዕት ያቀረቡት (ዘፍ ፬፥፫-፳) ዮሴፍ ዝሙትን ኃጢአት ያለው (ዘፍ. ፴፱፥፮) ከጹሑፍ በሚቀድመው የሕሊና ሕግና በትውፊት በተቀበሉት ትምህርት ስለተማሩ ነው፡፡ ነብዩ ሙሴ ከአዳም እስከ ዮሴፍ የነበረውንና (ከ400-4000) ዓመታት ከሙሴ ቀድሞ የተፈጸመውን ታሪክ የጻፈው ከአባቶቹ በትውፊት ተቀብሎና በአለብዎተ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡*

### ትውፊታዊ መረጃ በሐዲስ ኪዳን

*ሐዋርያት ወንጌልን ሲሰብኩ በጽሑፍ ያልሰፈሩ ግን በቃል ይተረኩ የነበሩ ትውፊታዊ መረጃዎችን ይጠቅሱ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጠው ሐቅ ነው፡፡ ከሐዋርያት የተቀበልናቸው ትውፊቶች ሐዋርያዊ ትውፊቶች ሲባሉ ምንጫቸው ጌታችን ነው፡፡* ***‹‹የተቀበልሁትን … አሳልፌ ሰጠኋችሁ››*** *፩ኛ ቆሮ ፲፭፥፫-፲፩*

*ጌታችን ያስተማረው በቃል ሲሆን በጽሑፍ ያሰፈሩልን ሐዋርያት ናቸው፡፡ እነርሱም በመጽሐፍ ካሰፈሩልን ያልተጻፈው እንደሚበልጥ በዮሐ. ፳፩፥፳፭ ላይ ተገልጾአል፡፡ ሉቃስ በቃል የተቀበለውን በጥንቃቄ ጽፎአል፡፡ ሉቃስ ፩፥፩-፬ ሐዋርያት በትውፊት የተቀበሉትን ትንቢት ጠቅሰዋል፡፡ ማቴ ፪፥፳፫ በነብያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ትንቢት በጽሑፍ አልተገኘም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ከቀደሙ አባቶች ያገኘውን ይዞ* ***‹‹እያኔስና እያንበሬስም ሙሴን እንደተቃወሙት እንዲሁ እነዚህ ደግሞ አእምሮአቸው የጠፋባቸው ስለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው እውነትን ይቃወማሉ፡፡››*** *፪ኛ ጢሞ ፫፥፯ ብሎዋል፡፡ በጳውሎስና በሙሴ ዘንድ ያለው የዘመን ርቀት እጅግ በጣም ብዙ ሆኖ ሳለ ቅዱስ ጳውሎስ ሙሴን*

www.zeorthodox.org

በፈርዖን ፊት ተአምር ሲያደርግ የተቃወሙትን ጠንቋዮችና አስማተኞች(ዘጸ ፯፥፲፩-፲፫) ሙሴ ስማቸውን ሳይገልጸው እርሱ ግን ስማቸውን ጠቅሶ መናገሩ በትውፊት ያገኘው መሆኑን የሚያሳይ ነው።

***ትውፊታዊ መረጃን መቀበል ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው።***

ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች *‹‹በቃላችንም በመልክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ››* ሲል ትውፊትን ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው። ሐዋርያው ***"ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም እነዚህን አድርጉ የሰላም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።"*** ፊልጵ ፬፥፱ ዛሬም እኛ በትውፊት የደረሰንን ሁሉ ልንቀበል እና ልንጠብቅ ሃይማኖታዊ ግዴታ አለብን ። በሃይማኖት ጸንቶ ለመቆም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ትውፊትን መቀበል ያስፈልጋል። ***‹‹ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ።››*** ፩ኛ ተሰ. ፪፥፲፯

እውነተኛውን ትውፊት (ወግ) ከተረት፣ ከምድራዊ አፈ ታሪክ እና ሰውኛ ወግ መለየት እንዳቃታቸው ሉተርና ተከታዮቹ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ /Sola scriptura-the bible alone/ ሳንል እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ተረቱን ተረት ትውፊቱን ትውፊት ለማለት መጽሐፍ ቅዱስ እና ቤተ ክርስቲያን ማረጋገጫዎቻችን ናቸው።

## ማጠቃለያ

1. ትውፊት ቅብብል ማለት ሲሆን ከእግዚአብሔር የተገኙ መንፈሳዊ ትውፊቶች እና በማኅበረሰብ ሒደት ያገኘናቸው ባህሎችን ያካትታል።
2. ቤተ ክርስቲያንም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያዘንን መንፈሳዊ ትውፊት አጥብቃ ታስተምራለች።

## ተግባር

1. በመንፈሳዊ ትውፊት እና በማኅበረሰብ ወግ መካከል ያለውን ልዩነት ተንትናችሁ በቡድን ሥሩ እና ሳምንት አቅርቡ።
2. ከክርስቶስ ተገኝቶ በሐዋርያት የተላለፈልንን የመልካም ኑሮ በተግባር መግለጥን ተለማማዱ። **ለምሳሌ** የጽዋ ማኅበር ሲጠጣ ድሆች ተጠርተው መሆን አለበት። ማኅበርተኞችም መንፈሳዊ ፍቅር እና መግባባት ያስልጋቸዋል።

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች፦***

1. ‹‹ትውፊት›› ማለት ምን ማለት ነው?
2. ስለ ትውፊት ያሉትን ማስረጃዎች ከብሉይ ኪዳን እና ሐዲስ ኪዳን በመጥቀስ አብራሩ።
3. ‹‹ትውፊታዊ መረጃን መቀበል ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው›› ሲባል ምን ማለት ነው? ሐሳባችሁን በማስረጃ በማቅረብ አብራሩ።

# ወግ ፤ ባህል ፤ ትውፊት በመጽሐፍ ቅዱስ (ሁለት)

## ሃያ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- ተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ከአባቶቻችን ስለ ምንወርሳቸው መልካም ባህልና ትውፊት ግንዛቤ ያገኛሉ፤ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይገልጻሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**፡-*" ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ "* ፩ኛ ቆሮ.፲፩፥፳፫-፳፮

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- በትምህርቱ የተዘረዘሩትን ጥቅሶች በሚገባ አጥኑ፡፡

**መግቢያ፡-** የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ዓላማ ሰዎች እግዚአብሔርን አምነውና ተስፋ አድርገው በመኖር የዘላለም ሕይወት እንዲወርሱ ነው፡፡ ይህንንም አስመልክቶ በቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ተጽፏል፡፡***"አምናችሁ በስሙ የዘላለም ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል፡፡"*** ዮሐ. ፳፥፴፩ ቅዱስ ጳውሎስም ***"በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏልና፡፡"*** ሮሜ ፲፭፥፬

በዚህም መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ዓላማ የዘላለም ተስፋችንን ማሳወቅ ፥ እንዴት መኖር? ማንን ማመን? እንዳለብንም ማስተማርና ማሳየት ነው፡፡ ከዚህ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ አንጻርም ስለተነሣንበት ርእሰ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ከዘላለማዊው ሕይወት፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማወቅና ከመፈጸም አንጻር የሚቃወመው፣ የማይቃወማቸውና እንድንጠብቅ የሚያስገድደን ወጎች፣ ባህሎች እና ትውፊቶች አሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### መጽሐፍ ቅዱስ እኛ በሃይማኖትም ሆነ በኅብረተሰባዊ ሂደት ከቀደሙት ስለምንወርሰው ምን ይለናል ?

www.zeorthodox.org

1. **መጽሐፍ ቅዱስ የሚቃወማቸው ወግና ባህሎች**፡-እነዚህ ከእግዚአብሔር ፍቃድ ውጪ የሆኑ ፤ በቀጥታም ይሁን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚሽሩ ከአምልኮተ እግዚአብሔር የሚያስወጡ ናቸው፡፡ ይሄንንም አስመልክቶ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ የተሰጠው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲህ ይለናል፡፡***"የአሕዛብን ፍቃድ ያደረጋችሁበት ዘመን ይብቃችሁ፡፡***

***በዝሙትና መዳራት፣ በዘፈንም ጣዖትም በማምለክ የኖራችሁበት ዘመን ይበቃልና፡፡ በዚህም ነገር ወደዚያ ከእነርሱ ጋር ስለማትሮጡ እየተሳደቡ ይደነቃሉ..."*** ፩ኛ ጴጥ ፬÷፫-፬ በሌላ ቦታ ***"ስለዚህ የልቦናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ፡፡ እንደሚታዘዙ ሰዎች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ... ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን÷ ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ፡፡ ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ÷..."*** ፩ኛ ጴጥ. ፩÷፲፰-፲፱

ከአባቶች የተወረሰ ከንቱ ኑሮ፣ ቀድሞ በትውልዶች ሁሉ ሲወደስ የኖረ ክፉ ምኞት፣ የአሕዛብንም ፍቃድ እያደረጉ መኖርንም አቁሙ ተው ነው የሚለው ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ፡፡ ምርጡ ዕቃ ቅዱስ ጳውሎስም እንደ አምላክ ሊያመልኩትና ሊሠዉለት የተዘጋጁትን ልማዳቸው ነው ብሎ አልተወውም፤ ተቃወማቸው እንጂ፡፡ የሐዋ.ሥ ፲፬÷፰-፲፰ እነኚህ ከቀደሙት ትውልዶች የተወረሱ ወጎች፡- ጣዖት አምልኮ፣ ዛር፣ ጨሌ፤ ሞራ በመግለጥ፣ ኮከብ በመቁጠር መጠንቆልና የመሳሰሉትም ናቸው፡፡ ብዙዎች የቤተሰቦቼ ልማድ ነው፤ ይህን ብተው እንዲህ ወይም እንዲያ እሆናለሁ፤ ብለው ከፈቃደ እግዚአብሔር ወጥተው ይጠመዱባቸዋል እና መጽሐፍ ቅዱስ ይቃወማቸዋል፡፡

በተጨማሪም በእግዚኣብሔር ስም የሰው ወግና ሥርዓት የሚያስተምሩ፣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ትተው የራሳቸውን ወግ የሚያቆሙም አሉ፡፡ እነዚህንም የእግዚአብሔር ቃል ይወቅሳቸዋል እነኚህ የእግዚአብሔርን ቃል በተሳሳተ አመለካከት የቀየሩ ናቸው፡፡ አባትህን ስደብ እያሉ የእግዚአ ብሔርን ቃል ስለ ወጋቸው የሚያስሽሩም ነበሩ፡፡ ማቴ.፲፭÷፩ እስከ ፍጻሜ ምዕራፍ ማር. ፯÷፩-፲፫ ቤተ ክርስቲያን በራስዋ በክርስቶስ ተመሥርታ ከእነኚህ የስሕተት ትምህርቶች ትጠበቃለች፡፡ ልጆችዋንም ታስተምራለች፡፡

ይሄንኑ አስመልክቶም ቅዱስ ጳውሎስ፡-***"እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ፡፡"*** ቆላ. ፪÷፰ ይለናል፡፡ ከቅዱስ ቃሉ እንደምንረዳው የእነኚህ ሰዎች ትምህርት፡- እንደ ክርስቶስ ትምህርት አይደለም፡፡ የሰው ወግ ነው፡፡ ዓለማዊ ትምህርት ፍልስፍናም ናቸው፡፡ ሰዎችንም በከንቱ (በልማዶቻቸው) የሚያታልሉም ናቸው፡፡ ማድረግ ያለብንን ሲያሳስበንም ***"ተጠበቁ!"*** ብሏል ፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስም የዚህ ዓይነት መምህራን እንደሚነሡ ገልጿል፡፡***"ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል÷ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል፡፡"*** ኢሳ ፳፱÷፲፫ ጌታችንም ***"ኢሳይያስ ስለእናንተ... በእውነት ትንቢት ተናገረ፡፡"*** ማቴ. ፲፭÷፯-፱ ሲል ይህንኑ ትምህርት አጽንቶታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ይህን የቀደመ ፀረ ቤተ ክርስቲያን ወጉን ራሱን በመውቀስ ሲቃወም እናነባለን፡፡ ገላ ፩÷፲፬

www.zeorthodox.org

አይሁድን ለዚህ ስሕተት ያበቃቸው ደግሞ በፊደል የተመረኮዘ የመጽሐፍ ንባብና ሐተታ ፣ ከእግዚአብሔር ፍቃድ ይልቅ የራሳቸውን ክብር ማስቀደማቸውም ነበር። ለዚህም ነው በደማስቆ የተጠራው ሐዋርያ ***"የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ÷ ለእግዚአብሔር ጽደቅ አልተገዙም።"*** ሮሜ ፲÷፫ ያለው። በዚህ *መሠረትም* ***"ስለ ወጋቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይተላለፉ ነበር።"*** ማቴ ፲፭÷፫-፱

በዘመናችም እነርሱ ቡና መጠጣት ስላልፈለጉ ከመሠረታዊውና ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው የሥነ ፍጥረት ታሪክና ትምህርት ጋር በሚጋጭ ሁኔታ ቡና የበቀለው በአርዮስ ከርስ ነው። ሲሉ እንደሰማን ሁሉ፦ በጭምትነት መኖርን ኋላ ቀርነት፤ ዘመናዊ ወግን ጽድቅ ብለው ሊጽፉ የሚሞክሩና የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ የሚፈልጉም አሉ። በተለይም እነዚህ ሴት ትካን፣ የጽድቅ መገለጫው ሀብት ነው፣ ድህነት ቅጣት ነው ወ.ዘ.ተ.... የሚሉና የዘመኑን ወግ -"motivation speaking" ከስብከተ ወንጌል የማይለዩ ናቸው።

ቤተ ክርስቲያን ያላስተማረችውን ትምህርት የሚያስተምሩ÷ እንደነሱ የማያስብ እና የማይኖረውን የእግዚአብሔር አይደለም ብለው የሚያሳድሙም ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ለቤተ ልሔም የሚሆን ትምህርትን ከሞዓብ የሚቃርሙ፤ ማለትም በሰው ፊት ለመደመጥ ብቻ የኑፋቄውን ዓለም መሠረተ ትምህርትና አነጋገር የእግዚአብሔር ነው ብለው ዳዊት የጎልያድን ሠይፍ ካልታጠቀ ጽድቅ የለውም ባዮች ናቸው። እውነቱ ግን ለዳዊት ኃይል በእግዚአብሔር ስም የተወረወረዉ ወንጭፍ ነው ለዚህም ነው መምህረ አሕዛብ ቅዱስ ጳውሎስ፤ ***‹‹መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያዳመጡ÷ ሃይማኖትን ይክዳሉ...*** ›› ብሎ ትምህርታቸውን ከገለጠ በኋላ ***‹‹ ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ። እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ።››*** ሲል ይመክራል። ፩ኛጢሞ.፬÷፩-፯

በዚህ *መሠረትም* ከመሠረታዊው የክርስትና ትምህርትና ቃለ እግዚአብሔር ጋር የሚጋጩ ሰውኛ፣ ሰይጣናዊና ዓለማዊ ትውፊት፣ ባህሎችና ትምህርቶችን ቤተ ክርስቲያን ትቃወማለች። አትቀበልምም። ለምሳሌ፦ የዝግመታዊ ለውጥ አስተሳሰብ (ኢቮሉሽን ቲዎሪ)፣ "ቡና ልዩ ፍጥረት" መሆኑን የሚተርኩ ሐሳቦች፤ መንፈሳዊና አካላዊ ጉዳት ያላቸው ባህሎች ወ.ዘ.ተ... ማንነት፣ ዕውቀትና ውርስ ናቸው ሳትል የተሳሳቱ ናቸው ብላ ቤተ ክርስቲያን ታወግዛለች።

www.zeorthodox.org

2. የኅብረተሰብ ባህሎች፦ እነኚህ በአንድ ኅብረተሰብ እንደ ማንነት መግለጫ ፣ የኅብረተሰቡ የጥንቃቄና ሕግ ውጤቶች፣ወ.ዘ.ተ..... ሆነው ሲተላለፉ የሚኖሩ በተለያዩ ታሪካዊ ክሥተቶች የሚጀመሩና የሚሻሻሉ ናቸው። ለምሳሌም በመጽሐፍ ቅዱስ እጅን የመታጠብ ባህልን ፈሪሳዊያን

ሲያነሡ እናነባለን። ማቴ.፲፩፥፩-፪። ጌታም ይህንኑ አልተቃወመም፤ ችግራቸው የጤናውን ጉዳይ ጽድቅ ማለታቸው ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ባህል ከመሠረታዊው የእግዚአብሔር ትምህርት ጋር ካልተጋጨ አይቃወመውም። ለምሳሌ- በለቅሶ ቤት ተገኝቶ ሐዘንተኛን ማጽናናትና ሐዘንን መካፈል የአይሁድ ባህል ነበር። ክርስቶስም ተባብሮአል። ዮሐ ፲፩፥ ፩ ትንሣኤ እንደሌላቸው ማዘንን ግን" ***ወንድሞች ሆይ ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።"*** ፪ኛ ተሰ. ፬፥፲፫ ሲል ይቃወማል። በአንድ ኅብረተሰብ ያለውን በጎ ልማድም ያከብራል እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ አይቃወምም። በጥንት ዘመን የነበረ የልውውጥ መገለጫ የሆነን ልማድ አልተቃወመም። ሩት ፬፥፯-፰

## ማጠቃለያ

1. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍቃድ የሚቃወሙ፡-ሰውኛ ሰይጣናዊና ኋላቀር ልማዶችን ይቃወማል።
2. መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጆችን ጠቃሚ ባህሎች ያከብራል።
3. በዘመናችን ከሚሰጡ የስሕተት ትምህርቶች ለመጠበቅም ሆነ በትክክለኛው እምነትና መንፈሳዊ ሕይወት ለመጽናት ቤተ ክርስቲያናችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምታስተምረን፤ ተረቱን ተረት መንፈሳዊውን ትውፊት የጽድቅ ትምህርት ብለን እንለያለን፤ እንጂ እንደ ሉተር አንዱን ጥለን አንዱን አንጠልጥለን (sola scriptura) ጽሑፍ ብቻ አንልም። ወይም ሰውኛ ወግ ሁሉ በሚጥመን መንገድ ስለመጣልንና የአባቶች ወግ ስለሆነ ብቻ እንቀበለውም።

### ጥያቄ፡-

1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚቃወማቸውን ወጎች እና ባህሎች ከኅብረተሰብ ባህሎች ጋር በማነጻጸር በመጽሐፍ ቅዱስ የሚኖራቸውን ተቀባይነት እና ተቃውሞ በማስረጃ እያቀረባችሁ አብራሩ። መምህር ተማሪዎችዎ በጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

www.zeorthodox.org

# መንፈሳዊው ትውፊት - በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ (ሦስት)

## ሠላሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈሳዊው ትውፊት የሚያስተምረውን ይረዳሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄ በማብራራት ይገልጻሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***" ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ፤"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፩÷፳፫-፳፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** በትምህርቱ የተዘረዘሩትን ጥቅሶች በሚገባ አጥኑ።

**መግቢያ፡-** የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ዓላማ ሰዎች እግዚአብሔርን አምነውና ተስፋ አድርገው በመኖር የዘላለም ሕይወት እንዲወርሱ ነው። ይህንንም አስመልክቶ በቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ተጽፏል። ***"አምናችሁ በስሙ የዘላለም ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል።"*** ዮሐ. ፳÷፴፩ ቅዱስ ጳውሎስም ***"በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏልና።"*** ሮሜ ፲፭÷፬

በዚህም መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ዓላማ የዘላለም ተስፋችንን ማሳወቅ ÷ በእምነት እንዴት መኖር እንዳለብንም ማስተማርና ማሳየት ነው። ከዚህ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ አንጻርም መጽሐፍ ቅዱስ እንድንጠብቅ የሚያስተምረንን መንፈሳዊ ትውፊት በዛሬው ትምህርታችን እናያለን።

### 3. መንፈሳዊ ትውፊት፡-

ይህ ትውፊት ሐዋርያዊ ትውፊት ይባላል። ከላይ እንደተገለጠው ከእግዚአብሔር የተገኘና ቤተ ክርስቲያን በቃል፣ በተግባርና በጽሑፍ ያሸጋገረችው ነው። ለምሳሌ፡- መጽሐፍ ቅዱስ፣ ያሬዳዊ ዜማ ፣ ገዳማዊው ሥርዓት... እነዚህ ከእግዚአብሔር የተገኙ ናቸው። የጽሑፎቹም ሆኑ በቃልና በተግባር የሚገለጡት በቤተ ክርስቲያን እኩል ክብርና ተቀባይነት አላቸው። በቤተ ክርስቲያን ማረጋገጫና መጠበቂያችንም የቃሉን በጽሑፍና ተግባር፤ የጽሑፍና ተግባሩን በቃል ፤ ጽሑፉንም በተግባርና በቃል በተላለፈልን ትውፊት ነው። ቤተ ክርስቲያን አንዱን ትታ ሌላውን አንጠልጥላ አታውቅም። ይህን ሐሳብም መጽሐፍ ቅዱስ ይደግፈዋል። እነዚህን በምሳሌዎች እንይ ፡-

www.zeorthodox.org

❄ ***"ወንድሞች ሆይ በሁሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደሰጠኋችሁ ወግን ፈጽማችሁ ስለያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ።"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፩÷፪ ከዚህ ኃይለ ቃል የምንረዳውም፡-

1. ይህ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የመጀመሪያው ነውና፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ ከጌታ ተቀብሎ ያሳለፈላቸው በጽሑፍ ሳይሆን በቃልና ተግባር ነበር፡፡
2. *"አሳልፌ እንደሰጠኋችሁ"* ነውና የሚለው ቅዱስ ጳውሎስ ከጌታው የተቀበለውን ለደቀ መዛሙርቱ አስተላልፏል፡፡ ይሄንኑ ነው ቤተ ክርስቲያን ትውፊት የምትለው፡፡
3. የተረከቡትን ወግ ፈጽመው ይዘው ተገኝተዋል፡፡ "***አሳልፌ እንደሰጠኋችሁ ወግን ፈጽማችሁ ስለያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ፡፡***" ከዚህም የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ለሐዋርያዊ ትውፊት የነበራትን ትኩረት እናስተውላለን፡፡

❅ ***"እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ÷በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ፡፡"*** ፪ኛ ተሰ. ፪÷፲፭ ክርስቲያኖች መጠበቅ ያለብን ከሐዋርያት በጽሑፍና በቃል የተላለፈልንን ወግ፤ትውፊት ሁሉ እንጂ አንዱን ነጥለን ብቻውን አይደለም፡፡

❅ ***"ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን፡፡"*** ፪ኛ ተሰ. ፫÷፮

1. ከሐዋርያት የተቀበልነው("በከመ አወፈየኒ" እንዲል ሥርዓተ ቅዳሴ) ወግ፣ትውፊት አለ፡፡
2. በፊትም ከዚህ ወግ የሚወጡ ስለነበሩ ነው ቅዱስ ጳውሎስ የተቃወመው፡፡
3. የእነዚህ ሰዎች መገለጫም ያለ ሥርዓት መሄድ ናቸው፡፡
4. ይህን ሐዋርያዊ ወግ፣ ትውፊት ከሚያፈርሱ እንድንለይም በጌታችን ስም ታዘናል፡፡ ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊውን ትውፊት ከዓለማዊ ወግ ፣ ከሰውኛ ፍልስፍና፣ ከሰይጣን አስተሳሰብም ለይታ የምታስተምረው፡፡

❅ ***" በሩቅ ሳለን በመልእክታችን በኩል በቃል እንዳለን በሥራ እንዲሁ ነን፡፡"*** ፪ኛ ቆሮ. ፲÷፲፩

በዚህ መንፈሳዊ ትውፊትም የመጻሕፍት ትርጓሜ ይቃናል ፣ ሥርዓት ይጠበቃል፣ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ይሸጋገራል፤ ቤተ ክርስቲያንም ሐዋርያዊ ትውፊቶችን፣ ክርስቶሳዊ ትምህርቶችን ጠብቃ እንድትቀይ አስችሏታል፡፡

❅ ***"ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን በመንፈስ ወይም በቃል "***

www.zeorthodox.org

የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያንና ሕግ በጽሑፍ ከመሰጠቱ በፊት የነበሩት አበው ይመሩ የነበረው በእግዚአብሔር መንፈስ መገለጥ፣ በቃል ትውፊትና በኅሊና ሕግ ነበር፡፡ በእግዚአብሔር የተወደደው የኖኅ መሥዋዕት፤ ዘፍ.፱÷፳-፳፪ የዮሴፍ በእግዚአብሔር ስም ከኃጢአት መጠንቀቅ ዘፍ.፴፱÷፯-፲፤ ሐዋርያት ተሰባስበው በይሁዳ ምትክ ማትያስን በጸሎትና በዕጣ መተካታቸው ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ሲያስተምር ***" ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት...***" ፩ኛ ቆሮ.፲፩÷፳፫-፳፮ ጌታ

በተያዘበት ቀን ጸሎተ ሐሙስ ቅዱስ ጳውሎስ በሳዉላዊው ስሙ በፈሪሳዊው ግብሩ ነበር፡፡ታዲያ ከየት አምጥቶ ***ለጌታ ተቀብያለሁ*** አለ ስንል ዛሬም በቤተ ክርስቲያን እንዳለው የቀደመችዋ ቤተ ክርስትያን በቃልና በተግባር የምታስተላልፈው የክርስቶስ ትምህርት እንደነበራት እናስተውላለን፡፡ በቅዳሴያችንም በከመ አወፈየኒ አወፈይኩከ - እንዳቀበለኝ አቀብልሃለሁ የሚል ክፍል አለ፡፡

❄ በእግዚአብሔር ትምህርትና ፈቃድ የሚያኖሩን መልካም ትምህርቶችን ለማጽናት ዋኖቻችንን ሐዋርያትንና ያስተላለፉትን መንፋሳዊ ትምህርት እንድንጠብቅ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ ***‹‹እናንተስ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ጸንቶ ይኑር፡፡ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ጸንቶ ቢኖር ÷ እናንተ ደግሞ በወልድና በአብ ትኖራላችሁ፤....››*** ፩ኛ ዮሐ.፪÷፳፬ በሌላም ቦታ እንዲህ ተብሎዋል፡፡ ***‹‹የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩኣችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፤ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡፡ ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፤››*** ዕብ.፲፫÷፯ ይህንን ነው ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ትውፊት ብላ የምትጠብቀው፡፡

## ማጠቃለያ

1. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍቃድ የሚቃወሙ፡- ሰውኛ ሰይጣናዊና ኋላቀር ልማዶችን ይቃወማል፡፡
2. መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጆችን ጠቃሚ ባህሎች ያከብራል፡፡
3. በጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት እንደሚታመነውና እንደሚታየው ከክርስቶስ በቃል የተላለፈ፤ በተግባር ሐዋርያት ያዩት፤ ከዚያም በየጊዜው ለነበሩት አበው፤ ***እስከ ዓለም መጨረሻ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፤*** ባለው መሠረት የገለጻቸው በርካታ መንፈሳዊ ትውፊቶች አሉ፡፡ እነዚህንም መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ትምህርት ጸንተን ለመቆም እንድንችል ያዙ ይለናል፡፡
4. በዘመናችን ከሚሰጡ የስሕተት ትምህርቶች ለመጠበቅም ሆነ ለመጽናት ቤተ ክርስቲያናችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምታስተምረን ተረቱን ተረት መንፈሳዊውን ትውፊት የጽድቅ ትምህርት ብለን እንለያለን፡፡ እንጂ እንደ ሉተር አንዱን ጥለን አንዱን አንጠልጥለን (sola scriptura) ጽሑፍ ብቻ አንልም፡፡ ወይም ሰውኛ ውግ ሁሉ በሚጥመን መንገድ ስለመጣልንና የአባቶች ወግ ስለሆነ ብቻ እንቀበለውም፡፡

www.zeorthodox.org

### ጥያቄ፡-

1. መምህር ተማሪዎችዎ ስለ መንፈሳዊ ትውፊት በተማሩት መሠረት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን እያቀረቡ በማብራራት ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

## ሠላሳ አንደኛ ሳምንት

**የትምርቱ ዓላማ**፡- ተማሪዎች የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከልደት እስከ ዕርገት ያለውን ታሪክ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡ ማስጠናት እና ከታሪኩም መማር የትምህርቱ መሠረታዊ ዓላማ ነው፡፡

**የሚጠና ጥቅስ** ፡-*"መሠረቶቹ (ቿዋ) በተቀደሱ ተራሮች ነው"* መዝ.፹፮(፹፯)፥፩

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ‹‹ነገረ ማርያም››፣ መጽሐፈ ስንክሳር የግንቦት ፩፣ የጥር ፳፩ እና የነሐሴ ፲፮፣ ‹‹The Holy virgin saint Mary››; by Pope Shenoda; pp 4-8;1999 Cairo.

**መግቢያ**፡- ይህ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሦስት ተከታታይ ክፍሎች ከቀረበው ትምህርት የመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት በመሆኗ የአምላክ እናት፣ እመቤታችን፤ ብለን እንጠራታለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ፡- ንግሥት ፣ ድንግል ፣ ቅድስት ፣ የተለየሽ ፣ የተባረክሽ እና ጸጋ የሞላብሽ በሚሉ ለማንም ሰው ባልተሰጡ ቃላት ያከብራታል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም በቃል እና በመጽሐፍ በተረዳችው ታሪኳን በወር እና በዓመት በዓላት ታስባለች፤ ታከብራለች፡፡ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ታሪክ በዛሬው ትምህርታችን እንመለከታለን፤ ምልጃዋ እና በረከቷ ከሁላችንም ጋር ይሁን አሜን፡፡

### ትንቢት ይቀድሞ ለነገር

አባቶቻችን ***ትንቢት ይቀድሞ ለነገር - ድርጊትን ትንቢት ይቀድመዋል*** ይላሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ቀድሞ ትንቢት ከተነገረላቸው ሰዎች በብዛትም ሆነ በክብር የላቀ ምሳሌ የተመሰለላት፣ ትንቢትም የተነገረላት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡

www.zeorthodox.org

1. **ለአዳም በተሰጠው ተስፋ ስለ እመቤታችን ተነግሮ ነበር**፡፡ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ያሳተውን እባብን ሲረግመው ፤ ለአዳም የሰጠው ተስፋ " ***ሴቲቱ*** " ነበረች፡፡" ***ከሴቲቱ የሚወለደው እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል ..." ዘፍ.፫፥፳፩*** ሴት ከተባለቸው ከድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘንዶውን ራስ ቀጥቅጦ ድል እና ነፃነት ሰጥቶናል፡፡ ለዚህም ነው በቅዳሴ ማርያም ፡- " ***የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ*** " የተባለው፡፡

2. **የተቀደሱ ተራሮች፡፡** ዳዊት ጌታችን የተገኘባቸውን የእመቤታችንን ቤተሰቦች " ***የተቀደሱ ተራሮች*** " መዝ.፹፮(፹፯)፥፩ ብሎአቸዋል፡፡ እመቤታችንም ከእነዚህ ቅዱሳን የተገኘችና በቅድስናም የኖረች ናት፡፡ ኢያቄም እና ሐና በቅድስና እግዚአብሔርን ያገለገሉና ደስ ያሰኙት ነበሩ፡፡
3. **በንጉሡ ቀኝ የምትቆመው የተከበረች ንግሥት፡፡** መዝሙረኛው ዳዊተ ለንጉሡ በዘመረው ትንቢታዊ መዝሙር ከንጉሡ ቀኝ በወርቅ ልብስ ተሸልማ በቀኙ ስለምትቆመው ንግሥት ሲተነብይ **"ንግሥቲቱ በወርቅ ልብስ ተሸፋፍናና ተጎናጽፋ በቀኝህ ትቆማለች"** መዝ.፵፬(፵፭)፥፱-፲፩ ብሎ ነበር፡፡
4. **ንግሥቲቷ የምትመጣው (የምትወለደው) በሊባኖስ ነው፡፡** ጠቢቡ ሰሎሞን በመኃልዬ መኃልይ ***"ከሊባኖስ ነይ"*** መኃ.መኃ. ፬፥፱ ብሏት ነበር፡፡ ይህም በኋላ በታሪኩ እንደምን መለከተው እመቤታችን የተወለደችበትን ሊባኖስን ያመለክተናል፡፡
5. **መሲሑን የምትወልደው በድንግልና ነው፡፡** እመቤታችን ጌታችንን የምትወልደው በድንግልና እንደሆነ **"እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች"** ኢሳ.፯፥፬ ሲል ነብዩ ኢሳይያስም ተናግሮ ነበር፡፡
6. **ለእመቤታችን በቀጥታ የተነገሩ ትንቢቶች፡፡** ለእመቤታችን በዚህ ምድር የሚያጋጠማትን ሐዘን እና ዘለዓለማዊ ክብርዋን ከሦስት ቅዱሳን ሰምታ ነበር፡፡ ቅዱስ ገብርኤል ጌታችንን እንደምትወልድ ፣ በጸጋ እና በክብር የተሞላች እና ከሴቶች ተለይታ የተባረከች እንደሆነች ትንቢት እና ምስክርነት ሰጥቶአል፡፡ ኤልሳቤጥም ይህንኑ አጽንታ ብፅዕት ብላታለች፡፡ አረጋዊው ስምዖንም በልብዋ ሰይፍ (ሐዘን) እንደሚያልፍ ለዐሥራ አምስት ዓመቷ ብላቴና ቀድሞ ነግሯት ነበር፡፡ ሉቃ.፩፥፳፮፡-፪፥፳፰

ከላይ ለአብነት ያየናቸው ትንቢቶች ከብዙ እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ከሰው ዘር እንደ እመቤታችን ያለ ክብር የተሰጠው እና ብቸኛ ምርጫ (የአምላክ) እናትነት ያገኘ የለም፡፡ ለመሆኑም እመቤታችን መቼ ? እና እንዴት? ተወለደች፡፡ ኑሮዋስ ምን ይመስል ነበር? እንዴትስ ከዚህ ምድር ወደ ሰማያዊው ሀገር አለፈች? የሚሉትን በታሪኳ እናያለን፡፡

www.zeorthodox.org

## ልደት እና እድገት

የእመቤታችንን ልደት ለማወቅ የቤተ ክርስቲያንን አዋልድ መጻሕፍት ፣ የታሪክ ሰነዶች እና ትውፊት ላይ ማተኮር ጠቃሚ ነው፡፡ በተለይም ነገረ ማርያም የተባለውና በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተጻፈ የሚታመነው መጽሐፍ ብዙ እና ጠቃሚ መረጃዎችን እናገኝበታለን፡፡

በዚህ መሠረት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደችው፤ በ5485 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ሲሆን ፤ አባትዋ ኢያቄም እና እናትዋ ሃና በቅድስና የሚኖሩ የተባረኩ ቤተሰቦች ነበሩ። ልጅ ስላልነበራቸውም እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው ተሳሉ። ሁሉን ቻይ ጌታም እመቤታችንን ሰጣቸው። በተሳሉት መሠረትም እመቤታችንን በሦስት ዓመቷ ወደ ቤተ መቅደስ ሰጥዋት።

ከሦስት እስከ ዐሥራ አምስት ዓመትዋ ያሉትን ዐሥራ ሁለት ዓመታት ውኃ በመቅዳት እና መጋረጃ በመስፋት እያገለገለች ፣ በጾምና በጸሎት ጸንታ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እየተማረች እና እያነበበች ኖረች። ለአቅመ ሔዋን ስትደርስም ካህናቱ ከቤተ መቅደስ ሊያስወጡዋት አሰቡ።

## ብስራት ፣ ልደት እና ስደት

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹***የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ***›› ገላ.፬፥፬ በማለት የገለጸው ጌታ ዓለምን የሚያድንበት ጊዜ ሲደርስ መልአኩን ቅዱስ ገብርኤልን ወደ ድንግል ላከው። እርሱም በክብር ‹‹ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ›› አላት። እርስዋም ‹‹እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?›› ብላ በልብዋ ስታስብ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፤ ‹‹ማርያም ሆይ አትፍሪ እነሆ ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፤ እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል።›› አላት። እርስዋም ‹‹ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?›› አለች። መልአኩም ከእርስዋ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደምትወልድ ነገራት። አክስቷ ኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ወራት ካለፈ በኋላ መውለዷን ጠቅሶ፤ የእርስዋም ያለ ወንድ ዘር መፅነስ ሁሉም በማይሳነው በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አስረድቶ፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም አላት። እርስዋም እንደቃልህ ይሁንልኝ ስትል። የእግዚአብሔር ልጅ ተፀነሰ። ሉቃ.፩፥፳፮-፵፩ ይህ የተደረገው መጋቢት 29 ቀን 5500 ዓመት (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ነበር።

በዘጠነኛው ወር ድንግል ማርያም ፣ ከጠባቂዋ ከዮሴፍ ጋር በገሊላ እያለች ሕዝቡ እንዲቆጠር ከሮሙ ቄሳር ዓዋጅ ወጣ። በዚህ መሠረት ለመቆጠር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከዮሴፍ ጋር ሆና ወደ ቤተልሔም ሄዱ። በዚያም የማደርያ ስፍራ አልተገኘምና በከብቶች በረት ተጠጉ። ጌታችንንም በዚያ በከብቶች በረት ውስጥ ሆና ወለደችው። በጨርቅ ጠቅልላም በግርግም አስተኛችው። መላእክት እና እረኞች መጥተው አመሰገኑ። እንደ ሥርዓቱም በስምንተኛው ቀን ሊሰየም ወደ ቤተ ግዝረት፣ ሄዶ በመልአክ እንደተነገረው ስሙ ኢየሱስ ተባለ። በዐርባኛው ቀንም የመንጻት ሥርዓት ለመፈጸም ልጅዋን ይዛ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደች። ስለእርስዋና ስለ ልጅዋ ከነብይት ሐና ሰማች። እርስዋም ሁሉንም በልብዋ ትጠብቀው ነበር።

በሁለተኛው ዓመት ኮከብ የመራቸውና ከምሥራቅ የተነሡ የጥበብ ሰዎች ፣ ለተወለደው ለአይሁድ ንጉሥ ሊሰግዱ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። በዚህ የታወከው ንጉሥ ሄሮድስ ሥልጣኑን

www.zeorthodox.org

የሚቀማው ንጉሥ የተወለደ መስሎት፣ ሕፃኑን ንጉሥ ለመግደል በርካታ ሕፃናትን አስፈጀ። ድንግል ማርያምም በመልአኩ መገለጥ ልጅዋን ታቅፋ በ፲፯ ዓመቷ የሲናን በረሐ አቋርጣ ወደ ግብጽ ሸሸች። ከሦስት ዓመት ከመንፈቅ በኋላ ወደ ናዝሬት ገብታ ኖረች። ማቴ. ምዕ.፪፥፩ እስከ ፍጻሜ ምዕራፍ በዚህ ወቅት ድንግል ማርያም የሃያ ዓመት ወጣች ነበረች።

## አስተርእዮ - የጌታ ለዓለም መገለጥ

ልጅዋን ተንከባክባ ማሳደግ እና ለዓለም ማቅረብን በንጽሕናና በትጋት ፈጽማ፣ ጌታችን በሠላሳ ዓመቱ ራሱን ለዓለም ሲግልጽ፣ የጌታችን እናቱ አርባ አምስት ዓመቷ ነበር። በቃና ዘገሊላ ሰርግ የተደረገው ጌታችን ከተጠመቀ ከአርባ ሦስት ቀናት በኋላ ነበር። ዮሐ.፪፥፩-፲፩ በሰርጉ ቤት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብራ ነበረች። የወይን ጠጅ አልቆበት ለተቸገረው ደጋሽ፣ ችግሩን ለጌታ አሳወቀችለት። ተመልሳም የሚላችሁን አድርጉ በማለት ሁሉን ቻይነቱን ቀድማ ለዓለም የገለጠችው እርስዋ እመቤታችን ናት። በመዋዕለ ትምህርቱም (ጌታችን በሚያስተምርበት ሁሉ እመቤታችንም) ትገኝ ነበር። ማቴ. ፲፪፥፵፯

ጌታችን በተሰቀለበት ቀን ከእናትነት ሐዘንዋ ጋር ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት በቀራንዮ አደባባይ ነበረች። ጌታችንም በመስቀል ላይ ሆኖ ‹‹ተፈጸመ›› ከማለቱ በፊት ከተናገራቸው የመጨረሻ ቃላት፣ ይወደው ለነበረው ደቀ መዝሙር ለዮሐንስ ‹‹እነኋት እናትህ›› ብሎ ለእርስዋም ‹‹እነሆ ልጅሽ›› ብሎ የሰጠበት ቃል ነው። ዮሐ.፲፱፥፳፮-፳፯ ደቀ መዝሙሩም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ወደ ቤቱ ይዟት ሄደ። በዚህ ጊዜም አርባ ዘጠኝ ዓመትዋ ነበር።

ቀጣዩ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ታሪክ የጸሎት ነው። በሐዋርያት ሥራ ምዕ.፩፥፲፬ እና ፪፥፩ እንደተገለጠው፣ በአንድ ልብ ሆነው ሐዋርያት በተጉበት ጸሎት ምዕራገ ጸሎት ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ ድንግል ማርያም ነበረች። በሌሎች መጻሕፍት እንምናነበውም በልጅዋ የመቃብር ሥፍራ በጎልጎታ እየጸለየች ዐሥራ አምስት ዓመታት ኖረች።

## ቃል ኪዳንና ዕረፍት

እንዳስለመደች ለጸሎት ስትሄድ ልጅዋ ተገልጦላት፣ ከዚህ ምድር የምትወሰድበት ቀን እንደደረሰም ነገራት። ቃል ኪዳን ገብቶላትም ጥር ሃያ አንድ ቀን በስልሣ አራት ዓመቷ ዐረፈች። ከሐዋርያት ይህንን የሚያውቀው አደራ ዮሐንስ ብቻ ነበር። ሌሎቹ ሐዋርያት ሲሰሙ ፣ በነሐሴ ተሰባስበው ሱባዔ ያዙ፣ በሁለተኛ ሱባዔ ሥጋዋ ተሰጥቷቸው በክብር ቀበርዋት። ቀብርዋን በተቃወሙና እንደ ልጅዋ ተነሣች እንዳትባል ባሉት አይሁድ ግፊት እጁ የተቆረጠውን ቴዎፍሎስን ጸሎቷ ፈውሶታል። ነሐሴ ዐሥራ አምስት ተቀብራ፣ ነሐሴ ዐሥራ ስድስት ቀን ተነሥታ አርጋለች። በረከትዋ ይደርብን። አሜን።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

1. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኢያቄም እና ሀና ከተባሉ ቅዱሳን በ5486 ዓመተ ዓለም(ከክርስቶስ ልደት በፊት) በዐሥራ አምስት ዓመት ቅድመ ልደት ክርስቶስ ተወለደች፡፡ በዚህ ምድር የኖረችው ለስልሣ አራት ዓመታት ነው፡፡
2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትወልድ በዐሥራ አምስት ዓመቷ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አበሰራት፤ በዘጠነኛው ወር በይሁዳ ቤተ ልሔም ወለደችው፤ በሁለተኛው ዓመት ወደ ግብጽ ተሰደዱ ፤ በዚያም ለሦስት ዓመት ከመንፈቅ ኖራለች፡፡
3. ጌታችን በሠላሳ ዓመቱ ሲገለጥ ‹‹*ስሙት*›› ብላ ስለ እርሱ ለሕዝቡ ነግራለች ፣ በምልጃዋም ውኃውን ወይን እንዲሆን አስደርጋለች፡፡ በመዋዕለ ትምህርቱም አልተለየችም፡፡ በመስቀል ሥር ነበረች፡፡ የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን በሆነው በበዓለ ጰራቅሊጦስ ሐዋርያት በጸሎት ሲተጉ ምልክት እና ምዕራገ ጸሎት ነበረች፡፡
4. ከእርገት በኋላ ለዐሥራ አምስት ዓመታት በጸሎት ኖራ፤ ጥር ሃያ አንድ ቀን ዐርፋለች ፤ ነሐሴ ዐሥራ አራት ቀን ተቀበረች ነሐሴ ዐሥራ ስድስት ቀን ዐረገች፡፡

**ተግባር:-** ስለ እመቤታችን የተጻፉ መጻሕፍትን አንብቡ፡፡

***ጥያቄዎች:-***

1. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከመወለዷ አስቀድሞ ትንቢት ተነግሮላታል፡፡ ለአዳም የተሰጠው ተስፋ ምን ነበር? በቅዳሴ ማርያም ‹‹የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ›› የተባለው ስለምንድን ነው? አብራርታችሁ ግለጹ፡፡
2. በመዝሙረ ዳዊት ስለ እመቤታችን የተነገሩት ትንቢቶች ምን ምን ናቸው?
3. እመቤታችን ጌታችንን የምትወልደው በድንግልና ስለመሆኑ የተናገረው ነቢይ ማን ነው? ትንቢቱንም ግለጹ፡፡
4. የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እናትና አባት እነማን ናቸው? እመቤታችን ያደገችው የት ነው? እስከ ስንት ዓመቷ ድረስ?
5. እመቤታችን ጌታችንን እንደምትወልድ ያበሠራት ማነው? በአበሠራት ጊዜ መልአኩ ያላትን እና እመቤታችን የመለሰችለትን ግለጹ፡፡
6. እመቤታችን ጌታችንን የወለደችው የት ነው? እንዴት እና ለምን በዚያ ቦታ ወለደችው?
7. የእመቤታችን ጠባቂ ማን ይባላል?

www.zeorthodox.org

8. እመቤታችን ልጇን ይዛ የተሰደደችው ወዴት ነበር? ልጇ ስንት ዓመቱ ነበር? የተሰደደችበት ምክንያት ምንድነው?
9. እመቤታችን ከልጇ ከጌታችን ጋር ተጠርተው የተገኙበት ቦታ የተ ነው? በዚየ ምን ነበር? እመቤታችን ያደረገችውስ ምንድን ነው? ግለጹ፡፡
10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው የት ነው? በተሰቀለበት ጊዜ ‹‹ተፈጸመ›› ከማለቱ በፊት የተናገራቸው የመጨረሻ ቃላት ምንድን ናቸው? ለማን?
11. እመቤታችን በምድር ስንት ዓመት ኖረች? ያረፈችበት? የተቀበረችበት? እና ከሞት ተነሥታ ያረገችበት? ዕለታት መቼ መቼ ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ክብረ ቅዱሳን

## ሠላሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ስለ ቅዱሳን ማንነት እና ያላቸውን ክብር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት መማር፡፡

**የሚጠኑ ጥቅሶች፡-** ***" ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፫፥፲፪ ***"ቅዱሳን በክብር ይመካሉ በምንጣፋቸውም ላይ ሐሴትን ያደርጋሉ፡፡"*** መዝ.፻፵፱፥፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የተሰጡትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡ ‹‹ክብረ ቅዱሳን›› በዲያቆን ያረጋል አበጋዝ፡፡

**መግቢያ፡-** ***"ቅዱስ"*** የሚለው ቃል "ቀደሰ" ከሚል የግእዝ ግሥ የወጣ ሲሆን አመሰገነ፣ ለየ፣ መረጠ፣ አከበረ የሚል ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ቅድስና የባሕርይ እና የጸጋ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

የባሕርይ ቅድስና፡- በባሕርዩ ቅዱስ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ቅድስናው ከእርሱ የማይለይ ፣ ከማንም ያልተቀበለው ፣ ማንም ሊወስድበት የማይችል የራሱ የሆነ ነው፡፡ ቅድስና ከእግዚአብሔር፤ እግዚአብሔር ከቅድስና ተለይተው የማይታሰቡ ናቸው፡፡ **"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች፡፡"** ኢሳ. ፮፥፫፣ ራእ.፬፥፰ **"እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና እንደ አምላካችንም ጻድቅ የለምና ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም፡፡"** ፩ኛ ሳሙ.፪፥፪ **"ሁሉን የምትገዛ ጌታ ሆይ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና"** ራእ.፲፭፥፬

የጸጋ ቅድስና፡- በባሕርዩ ቅዱስ ከሆነ እግዚአብሔር በጸጋ /በስጦታ/ የተገኘ ወይም የተሰጠ ማለት ነው፡፡ የቅድስና ምንጭ እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ የእጆቹ ሥራዎች የሆንን ሰዎች የእርሱን ቅድስና አርአያ እንድናደርግ **"እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ"** በማለት አባታዊ ጥሪን አቅርቧል፡፡ ዘሌ.፲፱፥፪ ቅዱስ ጴጥሮስም **"ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ፡፡ እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ሕይወት አትከተሉ፡፡ ዳሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፡፡"** በማለት ተመሳሳይ መለኮታዊ ጥሪን ጽፏል፡፡ ፩ኛ ጴጥ.፩፥፲፫-፲፭

www.zeorthodox.org

❖ የዛሬው ትምህርታችን ለዚህ መለኮታዊ ጥሪ አዎንታዊ መልስ ሰጥተው ለክብር የበቁ ቅዱሳንን ክብር እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**ቅዱሳን ምን የፈጸሙ ናቸው?**

*ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ናቸው፡-*

ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ሲሉ ያላቸውን ነገር ሁሉ ትተው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ፤ ምድራዊ ተስፋቸውን በሰማያዊ ተስፋ፣ የጊዜያዊውን ዓለም ደስታ በዘላለማዊ ሕይወት ለውጠው ኢየሱስ ክርስቶስን የተከተሉ አባቶችና እናቶች ናቸው፡፡ **"እውነት እላችኋለሁ ይህች ድሀ ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ሰጠች፤ እነዚህ ሁሉ ከትርፋቸው ወደ እግዚአብሔር መዝገብ ጥለዋልና፡፡ ይህች ግን ከጉድለቷ የነበራትን ትዳርዋን ሁሉ ጣለች፡፡"** ሉቃ.፳፩፥፬ ነቢዩ ኤልሳዕ ሁለት ጥማድ በሬ፤ ፩ኛ ነገ.፲፱፥፲፱ ፣ ሩት ሀገሯን እና ወገኗን፤ ሩት.፩፥፲፯ ትተው በመሄዳቸው የተመሰገኑ ሆነዋል፡፡

*ሕይወታቸውን በተጋድሎ ያሳለፉ ናቸው፡-*

መንፈሳዉያን ጠላት ስላለባቸው ሁሌም ለዚህ ተዘጋጅተው ይኖራሉ፡፡ ቅዱሳንም ይህንን ጦርነት አውቀው ራሳቸውን ለመንፈሳዊ ተጋድሎ አዘጋጅተው በእግዚአብሔር ኃይል ዲያብሎስን ያሳፈሩና በፈተና የጸኑ፣ ኃጢአትን እስከ መጨረሻው የተቃወሙ ናቸው፡፡ ተጋድሎአቸውም ከራስ ፍላጎት እና ከውጭ ፈተና ጋር ነው፡፡ ሮሜ.፰፥፲፪፣ ፩ኛ ቆሮ.፱፥፳፯

*ሩጫውን በድል የተወጡ ናቸው፡-*

መንፈሳዊ ተጋድሎ በሩጫ ይመሰላል፤ መንፈሳዊ ሰው ደግሞ በመንፈሳዊ ሯጭ ይመሰላል፡፡ መንፈሳዊ ሕይወት ከአጋንንት ጋር የሚደረግ የማያቋርጥ ሰልፍ ነው **"መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ዓለም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊው ሥፍራ ካሉ ከክፉ መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ፡፡"**ኤፌ.፮፥፲፪ በዚህ ሰልፍ ያሸነፈ አክሊልና ክብርን ይቀዳጃል፡፡ **"በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው... የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና፡፡"** ያዕ.፩፥፲፪ **"መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫውንም ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፡፡"** ፪ኛ. ጢሞ.፬፥፯-፰

www.zeorthodox.org

## 2. ክብረ ቅዱሳን፡-

ይህ በተለያዩ ነገሮች የተገለጸ ሲሆን ለአብነትም የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

በፍጥረታት የተሰጣቸው ሥልጣን

***"ኤልያስ እንደኛ የሆነ ሰው ነበረ፤ ዝናም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፡፡ ሁለተኛ ጸለየ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ"*** ያዕ.፭፥፲፯ ***"በገባዖን ላይ***

***ፀሐይ ትቁም በኤሎንም ሸለቆ ጨረቃ፣ ሕዝቡም ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይ ቆመ ጨረቃም ዘገየ። አንድ ቀንም ያል ለመግባት አልቸኮለም።*** ኢያ.፲፥፲፪ ***"አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲያወጧቸው በርኵሳን መናፍስት ላይ ሥልጣን ሰጣቸው።"*** ማቴ.፲፥፩

*በጸጋ አምላክ በመሆን፦*

**"ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮቱ ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።"** ፪ኛ ጴጥ.፩፥፬ እግዚአብሔር በባሕርዮ የሚሠራውን *ሥራ* ቅዱሳን ደግሞ ከአምላካቸው በተሰጣቸው ጸጋ የተነሣ የአምካቸውን ስም ጠርው *መሥራት መቻላቸውን* የሚገልጽ ነው። ዮሐ.፲፬፥፲፪ ‹‹***እግዚአብሔርም ሙሴን ... እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ።***›› ዘጸ.፯፥፩ እንዳለው ቅዱሳን የጸጋ አማልክት እስኪባሉ አክብሮአቸዋል። ***እኔ ግን፡ አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ*** *መዝ*.፹፩(፹፪)፥፮ ተብሎ እንደተጻፈ ነብዩ ሙሴ ብቻ ሳይሆን ቅዱሳን ሁሉ በዚህ ክብር ተከብረዋል። ለዚህ ነው ልዑል እግዚአብሔር ‹‹***የአማልክት አምላክ***›› *መዝ*.፵፱(፶)፥፩ የተባለው። *መዝ*.፹፩(፹፪)፥፩

3. ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን እንዴት ታከብራለች?

*ቤተ ክርስቲያን በስማቸው በማነፅ፦*

***"እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና፦ በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ። ...በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ።"*** ኢሳ.፶፮፥፬-፯ በዚህ ቤተ መቅደስ የሚፈጸመው *ሥርዓት* ሁሉ አንድ ነው፤ የሚመሰገነው እግዚአብሔር፣ የሚሰዋው የክርስቶስ ቅዱስ *ሥጋ* ክቡር ደም ሲሆን *መታሰቢያው* ለወዳጆቹ እንዲሆን ያዘዘውም ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው።

*በሚገባቸው ታከብራቸዋለች፦*

አክብሮት በብዙ *መልኩ* ሊገለጽ ይችላል፤ እግዚአብሔር ያከበራውቸን ቅዱሳንን ቤተ ክርስቲያን የአክብሮት ስግደት በመስገድ አክብሮቷን ትገልጻለች። **"የወኅኒ ጠባቂውም እየተንቀጠቀጠ ከጳውሎስና ከሲላስ ፊት ተደፋ ወደ ውጭም ወጥቶ ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?››** አላቸው ሐዋ.፲፯፥፳፰-፴፩ ቆርነሌዎስም ለቅዱስ ጴጥሮስ ሰግዷል። ሐዋ.፲፥፳፰-፳፯ ቅዱስ ጴጥሮስ ***"ተነሣ እኔ ደግሞ ራሴ ሰው ነኝ"*** ማለቱ የትሕትና አነጋገር ነው። ቅዱሳንን ***"ቅዱስ"*** ያሰኛቸው አንዱ ራሳቸውን በመናቅ ፍጹም ትሑት በመሆናቸው ነው **"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።"** ፩ኛ ጴጥ.፭፥፭

*በቃል ኪዳናቸው የማማለድ ክብር እንደተሰጣቸው ታምናለች፦*

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ለቅዱሳን ከሰጣቸው ቃልኪዳኖች መካከል አንዱ ‹‹ምልጃ›› ነው፡፡ ምልጃ አንዱ ስለሌላው የሚያቀርበው ልመናና ጸሎት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ምልጃ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ‹‹*ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ*›› ፩ኛ ጢሞቴ.፪÷፪ ኤቤሜሌክ እንዲድን አብርሃም እንዲጸልይለት እግዚአብሔር አዟል፡፡ ዘፍ.፳÷፩-፯ ኢዮብ ስለ ወዳጆቹ ያቀረበውን ጸሎት እግዚአብሔር ተቀብሏል *"እግዚአብሔርም የኢዮብን ፊት ተቀበለ"* ኢዮ.፵፪÷፯-፱ አብርሃም ስለ ሰዶምና ገሞራ ያቀረበው ልመና፣ ዘፍ.፲፰÷፳፪ ሙሴ ለእስራኤላውያን *"እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ፡፡"* መዝ. ፻፭÷፳፫ ፣ ዘጸ.፴፪÷፲

በሥጋ መሞትም ክብራቸውን ከፍ ያደርገዋል እንጂ አያስቀረውም ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ሲያስተምር *" ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ"* ፩ኛ ቆሮ.፲፫÷፲፪ ብሏል፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችንም ሞት ሁሉንም እንደሚያስቀር ለሚያምኑትና ትንሣኤ የለም ብለው ለሚያስተምሩት*" ስለ ሙታን ግን እንዲነሡ እግዚአብሔር፦ እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ እንዳለው በሙሴ መጽሐፍ በቍጥቋጦው ዘንድ የተጻፈውን አላነበባችሁምን ? የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም፡፡ እንግዲህ እጅግ ትስታላችሁ፡፡"* ማር.፲፪÷፳፯ በጌታችን አምኖ የሞተ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯል፡፡*"ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም"* ዮሐ.፭÷፳፬

ቤተ ክርስቲያንም በክርስቶስ ባላት እምነት በአካለ ነፍስ ካሉ ነገር ግን በሥጋ በዚህ ምድር ከሌሉ ቅዱሳን ጋር አንድ ናት፡፡*"ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል፡፡"* ዕብ.፲፪÷፳፪-፳፬ www.zeorthodox.org እናም ቅዱስ ጳውሎስ ያለው ጸሎት ፣ ምሥጋናና ምልጃ (፩ኛ ጢሞ.፪÷፩-፪) በሰማይና በምድር ምሉዕ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ስላለ እነርሱ ስለ እኛ ይጸልያሉ ፣ ምልጃም ያቀርባሉ፡፡ እኛም በክርስቶስ ባለን እምነት ከእነርሱ ጋር ሕብረት አለን፡፡ ይህን ጸጋ እና ክብር ለቅዱሳን ያደለው፣ ሁለቱን (ሰማያውያንንና ምድራውያንን) አንድ ያደረገው ክርስቶስ ነው፡፡ ኤፌ.፪÷፲-፳

ሆኖም ይህንን ባለመረዳት በቅዱሳን የሚደረግ ጸሎት በመስኮት መግባት፣ ወይም የአምላክ ብቻ የሆነውን ሁሉን አዋቂነት ለፍጡራን መስጠት የሚመስላቸው አሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ‹‹*ሕያዋን*

***እንዲሞቱ ያውቃሉና ሙታን ግን አንዳች አያውቁም መታሰቢያቸውም ተረስቶአልና ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም፡፡››*** መክ.፱፥፭ የሚለውን በመጥቀስ እንዴት ሊሰሙ ይችላሉ ፍጡራን አይደሉም ወይ ሲሉም ይጠይቃሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ምድር በጨካኝ ልብና በምቾት ኖሮ ሲያል የገባው ባለጠጋ ስለወንድሞቹ አውቆ ሲናገር ፤ ታላቁ የእምነት አባት አብርሃምም በሥጋ ከሞተ ከዓመታት በኋላ የተደረጉትን ታሪኮች፡- የሙሴና የነቢያትን መነሣት አውቆ የተናገረው ለፍጥረቱ ድንቅ ጸጋ በሰጠው በእግዚአብሔር ቸርነት ነው፡፡ ሉቃ.፲፮፥፲፱-፴፩ በምልጃ ያለው የቅዱሳን ዕውቀትም ቅዱሳኑን ያከበረው የጌታችን ጸጋ ነው፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- የቅዱሳን ክብር በባሕርይው ቅዱስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቸርነት የተገኘ ነው፡፡ እነርሱም ከሥጋ ምኞት ፣ ከኃጢአትና ከዲያብሎስ ከሚመጣው፤ ፈተና ጋር ታግለው ድል ያደረጉ ናቸው፡፡
- በጸጋ እግዚአብሔር ተገኝቶ፣ በተጋድሎ የጸናው ቅድስና፤ በዚህ ምድር እና በሰማይ ታላቅ ክብር አስገኝቶአል፡፡ ሥነ ፍጥረትን በማዘዝ፣ በጸጋና በመንፈሳዊ ኃይል በመመላለስ፣ በምልጃም የቅዱሳን ክብር ተገልጾአል፡፡ የላቀው የክብራቸው መጠን የጸጋ አማልክት መባላቸው ነው፡፡ ዘጸ.፯፥፩፣ ፪ኛ ጴጥ.፩፥፬

## ተግባር፡-

- የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ***"እግዚአብሔር ጻድቅ ነውና፥ ጽድቅንም ይወድዳል ቅንነት ግን ፊቱን ታየዋለች፡፡"*** መዝ.፲(፲፩)፥፯ እናንተም ቅድስናን በማግኘት እግዚአብሔርን ለመምሰል ቅዱሳንን አርአያ በማድረግ እደጉ፡፡
- ***"ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ"*** ሮሜ.፲፫፥፯ እንደተባለ ቅዱሳንን ማክበር ይገባል፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. ‹‹ቅዱስ›› ማለት ምን ማለት ነው? ‹‹ቅድስና›› በስንት ይከፈላል? ምን እና ምን?
2. የባሕርይ ቅድስና ማለት ምንድን ነው? በባሕርዩ ቅዱስ የሆነው ማን ነው? እንዴት? አብራሩ፡፡
3. የጸጋ ቅድስና ማለት ምንድን ነው? ከየት ይገኛል? እንዴት? አብራሩ፡፡
4. ቅዱሳን የሚባሉ እነ ማን ናቸው? በማስረጃ ግለጹ፡፡
5. ቤተክርስቲያን ቅዱሳንን የምታከብረው እንዴት ነው? በማስረጃ አብራሩ፡፡
6. ለቅዱሳን ከእግዚአብሔር ከተሰጣቸው ቃልኪዳኖች መካከል አንዱ ‹‹ምልጃ›› ነው፡፡ ‹‹ምልጃ›› ማለት ምንድነው? የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በተማራችሁት መሠረት በማቅረብ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ደብረ ዘይት - የዳግም ምጽአቱ መታሰቢያ

## ሠላሳ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም መምጣት ምልክቶች እና ምን ማድረግ እንደሚገባን ይገነዘባሉ፤ ስለ በዓሉና መታሰቢያው ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፡- ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው ? አሉት፡፡ "*** ማቴ.፳፬፥፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ.፳፬ እና ፳፭፣ ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ››፤ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ

**መግቢያ፡-** መምህር ተማሪዎችዎን ክፍል የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. ፳፬ እና ፳፭ በየተራ እንዲያነቡ ያድርጉአቸው፡፡ ከምንባቡ የተረዱትን ሐሳብ እንዲገልጹና እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡

ጌታችንና መድኃኒችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዳግም ምጽአቱ ያስተማረበት ነው፡፡ ጌታችን ዳግመኛ ሲመጣም በዚህ ተራራ አንጻር ዓለም ሁሉ እያየው እንደሚመጣ በቤተ ክርስቲያን ስለሚታመን የዳግም ምጽአቱ መታሰቢያ በዓል ደብረ ዘይት ይባላል፡፡

የዛሬው ትምህርታችንም በቤተ ክርስቲያናችን ዐቢይ ጾም በመባል የሚታወቀው ጊዜ የእኩለ ጾሙን መጠሪያ እና መታሰቢያ በሆነው ‹‹ደብረ ዘይት›› ላይ ያተኩራል፡፡ የቅዱሳን አምላክ ይግለጽልን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ደብረ ዘይት - ‹‹የዘይት ተራራ›› የሚል ቀጥተኛ ትርጉም አለው፡፡ ይህ ተራራ ዘይት የሚወጣበት የወይራ ዛፍ በብዛት ስለሚገኝበት ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ከኢየሩሳሌም በምሥራቅ አቅጣጫ፣ በቅርብ ርቀት (የሐዋ.ሥ.፩፥፲፪) በሚገኘው በዚህ ተራራ ጌታችን ብዙ ጊዜ እየወጣ ሲጸልይ ያድር እንደነበር ከወንጌል እናነባለን፡፡ ሉቃ. ፳፩፥፴፯፣ ፳፪፥፴፱ ፣ ዮሐ.፰፥፩፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታችን በዚህ ምድር በተመላለሰበት የመጨረሻ ሳምንት እንደ ልማዱ በደብረ ዘይት አድሮ ጠዋት ሲወርድ፤ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፡፡ ‹‹***ንገረን ፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው?*** ›› አሉት፡፡ ማቴ.፳፬፥፫ እርሱም የዓለም

መጨረሻ ምልክቶችን፣ ያን ጊዜ ማድረግ የሚገባንን፣ የዳግም ምጽአቱን ሁኔታ ፣ የቀኒቱና የሰዓቲቱ አለመታወቅ እና ተዘጋጅቶ መጠበቅ እንደሚገባም በተለያዩ ምሳሌዎች አስተማራቸው፡፡ ማቴ.፳፬ እና ፳፭፡፡ እነዚህንም ቀጥለን እናያለን ፡-

## 1. የዳግም ምጽአቱ መድረስ ምልክቶች፡፡

***የምጥ ጣር መጀመሪያዎቹ*** ፡- እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚሉ ***ሐሰተኛ ክርስቶሶች ፣ ሐሰተኛ ነቢያትም*** ይነሣሉ፣ ብዙ ***ምልክቶችንም ያደርጋሉ***፣ ብዙዎችም ***ይስታሉ***፡ ጦርነት፣ ሕዝብ በሕዝበ ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ መነሣቱ ፣ ራብ እና ቸነፈር የምድርም መናወጥ የመጀመሪያዎቹ የምጥ ጣሮች ናቸው ፡፡ ማቴ. ፳፬፥፭-፯ ፣ ፪ኛ.ተሰሎ.፪፥፫-፲ ፣ ራእ.፲፫፥፪-፲፰

የእነዚህ ሁሉ ውጤት የሆነውና የከፋው መከራ የፍቅር መቀዝቀዝ ነው፡፡ ለዚህም ጌታችን "***ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች*** " ማቴ.፳፬፥፲፪ ያለን፡፡ ሌላው ምልክት ***የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ሥፍራ*** ማየት ነው፡፡

የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው ፣ የማይሆነውን አይነግረንምና ይህን ሁሉ እያየን ነው፡፡ እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚሉ ሐሰተኛ መሲሆችና በቅዱሳን ስም የተነሡ ሐሰተኛ ነቢያት በተለያዩ ዘመናት ተነሥተዋል፡፡ በተለይ በዚህ ክፍለ ዘመን ከአሜሪካ እስከ ጃፓን ከአውሮጳ እስከ አፍሪካ የተነሡት ሐሰተኛ ነቢያት እጅግ ብዙዎች ናቸው፡፡

በዓለማችን በርካታ ጦርነቶች፣ ራብና ቸነፈር ተከሥተው በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች አልቀዋል፡፡ አሁንም የታላላቅ ብዙኃን መገናኛ (ሚዲያዎች) ዋና ዜና ይኸው አሰቃቂ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋ ነው፡፡ ወንድማማቾች፣ ቤተሰብ፣ በፍቅራቸው የሚያስደንቁ ወዳጆች ዓይንህን ላፈር ሲባባሉ ማየት የተለመደ ሆኖአል፡፡ በቤተ መቅደሱ የምናየው የማይገባ ድርጊትም የጥፋቱ ርኩሰት ዋዜማና ልምምድ ይመስላል፡፡ ታዲያ ማድረግ ያለብን ምንድነው? ማዘን፣ መደንገጥ፣ ችግሩን ማወቅ ብቻ አይጠቅምም፡፡ ማድረግ የሚገባንን ጌታችን በወንጌል አስተምሮናል፤ ቅዱሳንም አብራርተውታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የምናየውም ይህንኑ ነው፡፡

## 2. ማድረግ የሚገባን

www.zeorthodox.org

ብዙ ሰዎች የዳግም ምጽአቱን ምልክቶች ሲያዩ ይጨነቃሉ፣ አንዳንዶቹም በማያተርፍ ጥላ ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስና ቅዱሳን ሐዋርያቱ የመከሩን ***ተጠንቀቁ፣ ተጠበቁ፣ ጽኑ እና አስተውሉ፤*** ብለው ነው፡፡

**ተጠንቀቁ ፡-** ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ነቢያት እንደሚነሡ ቀድሞ የተነገረን እንድንጠነቀቅ ነው ፡፡ በሐሰተኛ ትምህርትና ተአምራቸው የሚስቱት ብዙዎች ናቸውና፡፡ እኛም እንዳንስት ነው፤ ***ማንም***

***እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤*** የተባልነው፡፡ ጠንቃቃ ለሚሰማው፣ ለሚያየውና፣ ለሚያምነው ነገር ሁሉ ይጠነቀቃል፡፡ ዘመናችን የመረጃ ዘመን ስለሆነ ብቻ ጥንቃቄ በጎደለው የመረጃ አወሳሰድ ከሚጎዱ ሰዎች ጋር መሰለፍም የለብንም፡፡ በሐሰተኞቹ ትምህርት እና በዲያብሎስ ሐሳብ ዘላለማዊ ተስፋችንን እንዳናጣ፡- በመንፈሳዊ ዕውቀት፣ በጸሎትና እግዚአብሔር በሰጠን አእምሮ ተጠቅመን ጠንቃቃ መሆን ይገባል፡፡ እዚህ ላይ ***ያልጠረጠረ ተመነጠረ*** የሚለውን አገርኛ ብሂል ማስተዋል ጠቃሚ ነው፡፡

**ተጠበቁ ፡-** ጠንቃቃ ከጥፋት ደቀ መዝሙርነት፣ ከሐሰተኛ ትምህርት፣ ከመንፈሳዊ ዝለት፣ መጨረሻው ሞት ከሆነው ሁሉ ይጠበቃል፡፡ መጠበቅ ማለት በመንፈሳዊ ሕይወታችን በምናደርገው ጉዞ በድርጊትና በንግግርም በሌላም በምናደርገው ድርጊት ሁሉ ተጠንቅቀን ከኃጢአት እንድንጠበቅ ልናደርገው የሚገባንን ጥንቃቄ የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የምናየው፣ የምንሰማው እና የሚያጋጠመን ሁሉ እንዳያስደነግጠንና ከመልካም አቋማችን እንዳያናውጠን፡፡ መጠበቅም ነው፡፡ ***ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፤ አትደንግጡ*** ፤ ማቴ.፳፬÷፬

**ጽኑ፡-** በመከራው ሁሉ ውስጥ፤ ‹‹***እስከ መጨረሻው የሚጸና እርሱ ይድናል፡፡››*** ማቴ.፳፬÷፲፫ ፈተናውን በመሻገር በድል ለመቆም የምንችለው በሃይማኖት፣ በምግባር እና በፍቅር መጽናት ስንችል ነው፡፡ ጽኑዕ ለመሆንም እምትና ትዕግሥት ያስፈልገናል፡፡ ሐሰተኛው ክርስቶስ ሲነሣ ድል ማድረግ የሚችሉ ቅዱሳንን ጽናት የነገረን ዮሐንስ፤ ‹‹***የቅዱሳን ትዕግሥት እና እምነት በዚህ ነው፡፡››*** ራእ.፲፫÷፲ እንዳለው እኛም መጽናትን መለማመድ ይገባናል፡፡

**አስተውሉ፡-** ከማንጠብቃቸው አቅጣጫዎች የሚመጡና እውነት የሚመስሉ ትምህርቶች፣ ድንቆችና ክስተቶች ያጋጥሙናል፡፡ በቅድስናው ቦታ የማይገባ ድርጊት ወዘተ ይኖራል፡፡ በዚህ ዘመን በቅዱሳት መጻሕፍት ያለውን ትምህርት ማስተዋል ከስሕተት ይጠብቀናል፡፡ ለዚህም ነው ጌታችን፤ ‹‹***በነብዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ሥፍራ ሲያይ አንባቢው ያስተውል*** ፡፡ ማቴ ፳፬÷፲፭ ያለን በመሆኑም፤ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረንን በማስተዋል ሚዛናችንንም በእርሱ ላይ በማድረግ ዘመኑን ማስተዋል ያለብን ፡፡

**ወደ ተራሮች መሸሽ ወደ ኋላ አለመመለስ፡-** "***በዚያን ጊዜም በይሁዳ ያሉት ወደ ተራሮች ይሽሹ ፣ በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፣ በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ቤቱ አይመለስ፤ በዚያን ጊዜ ለሚያጠቡና ለእርጉዞች ወዮላቸው*** " ማቴ.፳፬÷፲፮-፲፱ ተራራ ከፍ ያለ ቦታ ነው፡- ክርስቲያንም በመንፈስ ልዕልና ከፍ ብሎ (በቅድስና) ይኖራል፤ ወደ መንፈስ ውርደት (በኃጢአት አዘቅት) አይግባ፤ ከሰማይ ካለው አባቱ ጋር ይኑር ማለት ነው፡፡ ተራራ ቤተ ክርስቲያንም ናት፡፡ ከኃጢአት እና ከክህደት ያመለጡ ወደ ኋላ፤ ማለትም ወደ ክህደት፣ ኃጢአት እና ዓለማዊነት መመለስ የለባቸውም፡፡ በእግዚአብሔር ቤት በቅድስና ኖሮ መጽናት እንጂ፡፡

www.zeorthodox.org

***እርጉዞችና የሚያጠቡ፡-*** በስደት እና በመከራ መፅነስም ሆነ ወልዶ ማጥባት ለመሸሽ አይመችም፡፡ በመንገድ ላይ እያሉ መውለድና የተወለዱትን መከባከብ ወተት ምግብ ሲሉ ለልጅ እንዲስማማ አድርጎ ማቅረብ አይቻልም፡፡ በዚህ ምሳሌያዊ ትምህርትም ***እርጉዞችና የሚያጠቡ*** ማለት ኃጢአትን በማሰብ (በኃልዮ) ፀንሶ፤ በመናገር (በነቢብ) ወልዶ፤ በተግባር (በገቢር) መፈጸም ነው፡፡ እናም ኃጢአትን ቆርጠው መተው ያስፈልጋል፡፡ በመንፈሳዊነት መለወጥ ያልቻሉ፤ ንስሐ ለመግባት ስለሚሰንፉ - በኃጢአት ይሞታሉ እነዚህን ወዮላቸው አለን፡፡

***ጸሎት***፡-ሁሉንም በጽናት ለማለፍና ላለመታለል ወይም በስሕተት ውስጥ አለመወድቅ፤ በሰው አቅም አንችልም፡፡ መውጫውን የሚያሳየን ጽናትንም የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመቆምም ድካማችንን አውቀን በጸሎት መትጋት እና መጽናት አለብን፡፡ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን፤ ***ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤*** አላቸው፡፡ በአቡነ ዘበሰማያት ጸሎታችንም፤ ***አቤቱ ወደ ፈተናም አታግባን፤*** ብለን እንጸልያለን ፡፡ ይህም መከራውን አሳልፈን ወደ መንፈሳዊ ፈተናዎች (ክህደት ፣ ጥርጥር ፣ ኃጢአት…) አታግባን ማለት ነው፡፡

ጌታችን የመከራውን ጊዜ በክረምትና በሰንበት መስሎ፤ ***ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ትጉና ጸልዩ*** ፤ አለ፡፡ ክረምት ለስደት አይመችም፣ በሰንበት የሚጓዝም አስቸጋሪ ነው፡፡ በእስራኤል ልማድ ሰው የማይንቀሳቀስበት ወቅት ነውና፤ ረዳት የሌለው ሽሽት ነው፡፡ መከራውን ማለፍ እና አለመሰናከል፣ ክረምቱን በሚያስጠልል እና ከብቸኞች ጋር በሚሆን በእግዚአብሔር ጥበቃና ዕርዳታ ካልሆነ አንችለውም፡፡ ይልቁንም በጸሎት መትጋትና የእግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ ከከፋ መከራ ያድነናል ፡፡

***ስለ ቅዱሳን*** ፡- ጥንቃቄ፣ መጠበቅ፣ ማስተዋል፣ እምነት፣ ትዕግሥትና ጸሎት መከራውን ማስቀረት ባይችሉም፤ ሁሉን የሚያይ እና የሚያውቀው ጌታ ስለተመረጡት ቅዱሳን ሲል የመከራዎቹን ቀናት ያሳጥራቸዋል፡፡ ማቴ.፳፬፥፳፪

### 3. የጌታችን ዳግም መምጣት እንዴት ነው ?

ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች የመምጣቱ ዋዜማዎች ናቸው፡፡ ጌታችን ዳግም ሲመጣም የሚከተሉት እንደሚደረጉ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡

www.zeorthodox.org

***በግልጥ ዓለም በሙሉ እያየው ይመጣል*** ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ‹‹ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢሉአችሁ አትመኑ፤›› ካለን በኋላ፣ ‹‹***መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ የሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል፡፡›› ***ማቴ.፳፬፥፳፫-፳፯ ብሎ ክርስቶስ በዚህ ቦታ፣ በዚያ አገር ታየ፣ መጣ የሚሉትን እንዳናምን ነግሮናል፡፡ አዎን ጌታችን ሲመጣ የወጉት ሁሉ፤ ዓለምም በሞላው እያየው ነው፡፡ መዝ.፵፱፥፩-፬ ፣ ማቴ. ፳፭፥፴፩-፴፪

**መላእክቱን በመለከት ድምፅ ይልካቸዋል፡፡ መለከት ይነፋሉ፤ ሙታን በአራቱ ንፋሳት** ይሰበሰባሉ፡፡ ማቴ.፳፬፥፴፩ ፣ ፩ኛ.ተሰሎ.፬፥፲፮

**የፍጥረት መናወጥ እና ማለፍ ይሆናል፡፡** ፀሐይ ጨረቃ ይጨልማሉ ፣ ከዋክብት ይረግፋሉ በታላቅ ትኩሳትም ይፈታሉ፣ የሰማይ ኃይላትም ይናወጣሉ፡፡ ማቴ.፳፬፥፳፱-፴፡፡ ምድርም በታላቅ ትኩሳት ይቃጠላል፡፡ ፪ኛ ጴጥ.፫፥፱-፲ ፣ ራእ.፳፥፲፩

**ጌታችን በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ይፈርዳል** ፡፡ ጻድቃንን በቀኝ ኃጥአንንም በግራ ያቆማቸዋል፡፡ ለጻድቃን የዘላለም ሕይወትና ርስትን ለኃጥአንም ለሰይጣንና ለሠራዊቱ በተዘጋጀውን በገሀነም እንዲኖሩ ይፈርድባቸዋል፡፡ ማቴ. ፳፭፥፴- እስከ ፍጻሜ ምዕራፍ፣ ራእ. ፳፩፥፩ እስከ ፍጻሜ ምዕራፍ ፣፳፪፥፱ እስከ ፍጻሜ ምዕራፍ፡፡

### 4. መቼ ይመጣል ? ዘመኑ ፣ ቀኑ ወይም ሰዓቲቱ ትታወቃለች ?

የመጨረሻው ዘመን ስምንተኛው ሺሕ መሆኑን የመዝሙረ ዳዊት ርእስ ይነግረናል፡፡ ዳዊት የዘመኑን ክፋት በትንቢት መነጽር አይቶ *አድነኝ* ሲል፤ በመዝ.፲፩(፲፪)፥፯-፰ እናነባለን፡፡ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትም ስምንተኛው ሺሕ የፍጻሜ ዘመን መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ስምንተኛው ሺሕ ከተጀመረም አምስት መቶ ዓመታትን አስቆጥሮአል፡፡ ሆኖም ከስምንተኛው ሺሕ ከሚገኙት አንድ ሺሕ ዓመታት የትኛው ዓመት እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ጌታችንም በምን ሰዓት እንደሚመጣ እንደማይታወቅ፡- ጌታቸው በምን ሰዓት እንደሚመጣ ስለማያውቁ ታምነው የተሰማሩትን አገልጋዮች ምሳሌን ደጋግሞ አስተምሮአል፡፡ ማቴ. ፳፬፥፴፱-፶፩ ፣፳፭፥፩-፴ ፡፡ **ለዚህም ነው ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና ንቁ!** ያለው፡፡ በዚህ መሠረትም የጌታችን ዳግም መምጫ እንደማይታወቅ፤ ‹‹**ስለዚያች ሰዓትና ስለዚያች ቀን ግን ከአባት ብቻ በቀር የሚያውቅ የለም መላእክትም ቢሆኑ የሰው ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም**፡፡›› ማቴ. ፳፬፥፴፮ ብሎ በግልጥ ነግሮናል ፡፡

### 5. ተዘጋጅቶ መጠበቅ

**በንስሐ መዘጋጀት** ፡- ጌታችን ስለዳግም መምጣቱ አስተምሮ ሲፈጽም፤ ተዘጋጅተን እንድንኖር በቀጥታ ትምህርትና በምሳሌ አስተምሮናል፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው በንስሐ መዘጋጀትና የምንችለውን መልካም ነገር መሥራት ነው፡፡ ማቴ.፳፬፥፴፯ እስከ ፍጻሜ ምዕራፍ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም በዚህ የወንጌል ቃል ተመሥርታ ዳግም ምጽአቱን በዓመት ሁለት ጊዜ በዐቢይ ጾም መሐል (በእኩለ ጾም) እና በጳጉሜን ሦስት ቀን ታስበዋለች፡፡ ሌሎቹ በዓላት ከዚህ ቀደም በተደረጉ ተፈጽመው ባለፉት ሁኔታዎች ተመሥርቶ የሚከበሩ ሲሆን ይህ በዓል ከሌሎቹ ተለይቶ ወደፊት ለሚሆነው በተስፋ የሚከበር በዓል ነው ፡፡ **በመሆኑም በዕለቱ** ፡-

**የምጽአቱ መታሰቢያ ይነበባል፣ ይዘመራልም** ፡፡ ከላይ ያየናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እና ስለዳግም ምጽአቱ የሚያስተምሩ ምንባባት ሲነበቡ፤ መዝሙራቱም ይህንኑ ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ፩ኛ.ተሰሎ.፬÷፲፫፣ ፪ኛ. ጴጥ.፫÷፯፣ የዕለቱ መዝሙር፤ እንዘ ይነብር እግዚእነ በደብረዘይት - ጌታችን በደብረ ዘይት ተቀምጦ፤›› ይባላል፡፡

**ስለ በጎ አድራጎት ትምህርት ይሰጣል፤ በተግባርም ይፈጸማል፡፡** ነዳያንን መመገብ፣ ህሙማንንና የታሠሩትን መጠየቅ፣ ያዘኑትን ማጽናናትም ጌታ ሲመጣ የሚጠይቀው ነውና፡፡ ማቴ. ፳፭÷፴፩-፵፮ ይኽንኑ በማሰብም ይፈጸማል ፣ ትምህርትም ይሰጥበታል ፡፡

## ማጠቃለያ

በዓሉን ስናከብር ጌታችን የሰጠንን ተስፋ በእምነት መጠበቅ ፣ መልካም በማድረግ ለጌታችን ቃል መታዘዝን፣ ዘመኑን ማስተዋልና ጌታ ተጠንቀቁ ባለን መሠረት ከኃጢአት ተጠንቅቀን ለዘላለማዊው ሕይወት ተዘጋጅተን መኖርን እንማራለን፡፡

## ተግባር

1. ከዘመኑ ክፉት እና ጥፉት ለመጠበቅ ፍርሀት መፍትሔ አይደለም፡፡ ይልቁንም መዝሙረኛው ዳዊት ‹‹***አቤቱ አድነኝ***›› እንዳለ፤ በጸሎት መበርታት፣ በፍቅር መኖር፣ ከስሕተት ትምህርት ለመጠበቅም መንፈሳዊ ትምህርትን አጥብቆ መማር ይጠቅማል፡፡
2. ቅዱስ ጳውሎስ “ ***የወንድማማች መዋደድ ይኑር፡፡ እንግዶችን መቀበል አትርሱ፤በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና*** ” ዕብ.፲፫÷፩-፪ እንዳለን ለሌሎች መልካም የማድረግ ቃላችንንና ተግባራችንን የምናጸናበት ዕለት ነው፡፡

### ጥያቄዎች፡-

1. ‹‹ደብረ ዘይት›› ማለት ምን ማለት ነው? ስያሜው የተሰጠበት ምክንያት ምንድነው? ‹‹ደብረ ዘይት›› ተራራ በምን ይታወቃል? ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ አስረዱ፡፡
2. የጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የመድረሱ ምልክቶች ምን ምን ናቸው? ማድረግ የሚገባንስ ምንድነው? በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ አብራሩ፡፡
3. በቤተ ክርስቲያናችን ‹‹ደብረ ዘይት›› በዓል መቼ ይከበራል የሚከበርበት ምክንያትና መታሰቢያነቱ ለምንድ ነው?

www.zeorthodox.org

# እኔ የማን ነኝ?

## ሠላሳ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች መንፈሳዊ ይዘታችንን ለመፈተሽ፣ ለማወቅ እና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን አንድነት ለማሳደግ ምን ማድረግ እንደሚገባን የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነጥቦችን ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-***"አንተ የማን ነህ? ወዴትስ ትሄዳለህ? በፊት ያለው ይህስ የማን ነው?"* ዘፍ. ፴፪÷፲፯

**መግቢያ፡-** በቃለ እግዚአብሔር በመመርኮዝ ራሳችንን መጠየቅ፤ በእግዚአብሔር ፊትና ለኅሊናችን እውነተኛ መልስ  በመስጠት የትምህርቱን መሠረታዊ ዓላማ ማሳካትም ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል፡፡ መንፈሳዊ ደረጃዎቻችንና፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት እንዴት ነው? እያተረፍን ነው? ወይስ እየቀበርን?.... ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የምንሰጥበት ነው፡፡

ራስን መፈለግ በጣም ጠቃሚና ውጤታማ የሆነ መንፈሳዊ ጥረት ነው፡፡ የጠፋው ልጅ ምሳሌን አስታውሱ፡፡ ወደ አባቱ ለመመለስ ያበቃው የመጀመሪያ ደረጃ ***"ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ...."*** ሉቃ. ፲፭÷፲፯ የሚለው ነው፡፡ ይህም ራሱን እንዲያውቅና ወደ እውነተኛው የሕይወት መንገድ እንዲመለስ አስቻለው፡፡ ያዕቆብ ከወንድሙ ጋር ለመገናኘት ሲጓዝ የተጠቀመበትን ጉዞ በጥልቀት ከልሱ፡፡ ያዕቆብ ወንድሙን በጣም ፈርቶታል፡፡ እግዚአብሔርን ጠይቆና ተገልጦለትም ጥሩ  ዝግጅት አድርጎ ተጓዘ፡፡ ዘፍ.፴፩÷፫፣ ፴፪÷፩-፲፪

የዕቅዱ አንድ ክፍል መልእክተኞችን ወደ ሌላው መላክ ነበር፡፡ ዘፍ. ፴፪÷፲፫-፳፩፡፡ ለኤሳው ስጦታ አስይዞ አዘጋጃቸው፡፡***"አንተ የማን ነህ? ወዴት ትሄዳለህ?በፊትህ ያለው ይህስ የማን ነው?"***የሚሉ ሦስት ቁልፍ ጥያቄዎችንም ከትክክለኛ መልሶቻቸው ጋር አዘጋጀ፡፡ በዘፍ. ፴፪ ና ፴፫ እንደተገለጠውም የሁለቱ ወንድማማቾች ግንኙነት የተሳካ ሆነ፡፡

www.zeorthodox.org

እነዚህን ሦስት መሠረታዊ ጥያቄዎች በትክክል ጠይቀን በእውነትና በድርጊት ከመለስናቸው ከአምላካችንና ከጌታችን ጋር ያለንን ግንኙነትና መንፈሳዊ ሕይወታችንን እናሻሽላለን፡፡ በጌታ ፊት የምንመልሰው ፣ የምናቀርበው በጎ ነገር ፣ ትርፍም ይኖረናል፡፡

# የትምህርቱ ዋና ይዘት

***የመጀመሪያው ጥያቄ፡ አንተ የማን ነህ?***

የዚህ ጥያቄ ሐሳብ በነፍስህ፣ በልብህና በፍላጎቶችህ ሥልጣን ያለው ማነው? ሕይወትህንና ጠባይህን እንዲመራው የፈቀድክለትስ ለማን ነው? የሚል ነው፡፡

***ገንዘብ በእናንተ ላይ ሥልጣን አለው?***

በመጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብን የሚያመልኩና ሙሉ ሥልጣን በላያቸው ስለነበረው ሰዎች በብዙ በምሳሌ ተጽፎአል፡፡ የአስቆሮቱ ይሁዳ ጌታውን የሸጠው ለገንዘብ ነበር፡፡ በኋላም ተጸጽቶ ራሱን አጥፍቶአል፡፡ የዘላለም ሕይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ? ብሎ የጠየቀው ባለጠጋም ጌታችን ለድሆች እንዲመጸውት ሲነግረው ገንዘቡን መርጦ ***"እያዘነ ተመለሰ"*** ማር. ፲፥፲፯-፳፪

ስለዚህ ገንዘብ ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚያወጣን ሌላ ጌታ ሳይሆን፤ ጽድቅ የምንሠራበት፣ ለመልካም ፍላጎቶቻችን መሟላት የምንጠቀምበት መሣሪያ ሊሆን ይገባል ስለዚህ በገንዘብ ተጠቅመን መልካም ሥራ ልንሠራበት እንጂ ለገንዘብ ተገዝተን ክፉ ልናደርግበት አይገባም፡፡

**ውጤት** ገንዘብ ኃይለኛ ጌታ ነው፡፡ በድካም ይሰበሰባል፣ በፍርሃት ይጠበቃል፣ በሐዘን ትቶ ይሄደል፡፡

***ኃጢአት በእናንተ ላይ ሥልጣን አለው?***

***"ለኃጢአት የተገዛ የኃጢአት ባርያ ነው፡፡ "***ይህም ማለት "ዲያብሎስ በኃጢአተኛ ነፍስ ላይ ሥልጣን አለው ማለት ነው፡፡ ያ ሰውም የኃጢአትና ዲያብሎስ ባርያ ነው፡፡"

***ምሣሌዎች***፡የሶምሶንን ታሪክ ተመልከቱ፡፡ /መሳፍንት ፲፮/ ሶምሶን የእግዚአብሔር መንፈስ በርሱ ላይ ነበርና እጅግ ጠንካራ ነበር፡፡ በአንድ ወቅትም አንድ ሺሕ ፍልስጥኤማውያንን ድል አድርጎአል፡፡ ከገሊላ ጋር በኃጢአት ሲወድቅና ምስጢሩን ሲያወጣ ግን ደካማ ሆነ፤ ፀጉሩን ቆረጠችው ዐይኑን አሳወሩትና በእስር አስቀመጡት፡፡

**ውጤት**፡ ኃጢአትና ዲያብሎስ ጨካኝ ጌቶች ናቸው፤ በባርነት ይዘው ከእግዚአብሔር ይለያሉ፡፡

***እኔ የፈጣሪዬና የመድኃኒቴ ነኝ፡-*** እግዚአብሔር ፈጣሪዬ ነውና ለርሱ ብቻ እገዛለሁ፡፡ እግዚአብሔር እስከ መስቀል ወዶኛል፣ በሙሉ ልቤ የምወደውና የማመልከው እርሱን ብቻ ነው፡፡ በዚህም የሕይወቴ ጌታና ንጉሥ የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር ነው፡፡

**ውጤቱ፡-** የሰላም ሕይወት እኖራለሁ ምክንያቱም የሠላም ንጉሥ እግዚአብሔር ለሕይወቴ ንጉሥዋ ነውና፡፡ በሰማይም ከእግዚአብሔር ጋር ሥፍራ አለኝ ምክንያቱም በቃል ኪዳኑ አምናለሁና፡፡

***ሁለተኛው ጥያቄ ወዴት ትሄዳለህ?*** ሁላችንም ከምድር የምንሄድበት ቀን አለና ይህን ጥያቄ መመለስ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ይሄን ጥያቄ ሲጠየቁ ብዙ ሰዎች የሚከተሉትን መልሶች ይሰጣሉ፡፡

www.zeorthodox.org

**የት እንደምሄድ አላውቅም - አደገኛ መልስ ነው፡፡**

- ❖ ዓላማ ሳይኖረው፤ መድረሻውን ሳያውቅ የሚጓዝ ሰው የትም አይደርስም፡፡ ጊዜውን በከንቱ ያባክናል፡፡
- ❖ መኪና የሚነዳ የሚደርስበትን ካላወቀ፤አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ነው፡፡

**እግዚአብሔር ያውቃል እኔ አላውቅም፡፡**

- ❖ ይሄም ጥሩ መልስ አይደለም፡፡ በርግጥ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው፡፡ ነገር ግን ሁለት መንገዶች እንዳሉም ነገሮናል፡፡ ወደ ሲኦል የሚያደርሰው ቀላል፤ ወደ ገነት የሚያደርሰው ከባዱ መንገድ ናቸው፡፡ ማቴ. ፯÷፲፫-፲፬፡፡እግዚአብሔር እንደፈቃደ ሁላችንም እንድንድን ይፈልጋል፡፡ ***"ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ"*** ብሏልና፡፡

**እንደ ሥራዬ እሄዳለሁ፡፡**

- ❖ የእኛ ሥራ ብቻውን እንደማያድነንም ቅዱስ ጳውሎስ ***"ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለምና"*** ኤፌ. ፪፤፱

**ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደምገባ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡**

- ❖ ተስፋ ብቻውን ግን በቂ አይደለም፡፡

**የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ሲኦል አይተወኝም፡፡**

- ꙮ በዚህ ምድር ምሕረት የለመኑ ይቅርታ እንዳገኙ ተጽፎአል፡፡ ከሞት በኋላ ምሕረት የለመነው ካለ በጣም ዘግይቶ ነበርና ይቅርታ አላገኘም፡፡ ሉቃ ፲፮÷፲፱-፴፩ ከኃጢአት ጋር መሞት፤ የዘለዓለም ሞት ነውና፡፡ ራዕ. ፳÷፲፬

**ገነት እንደምገባ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ይሄንን በተስፋ እየጠበቅሁ የታዘዝኩትንም እፈጽማለሁ፡፡**

- ꙮ አይገባኝም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው ቃል ግን እኖራለሁ፡፡ የጌታዬ ደም ከኃጢአቴ ያነጻኛልና እቀርባለሁ፡፡
- ꙮ አይገባኝም ግን በእግዚአብሔር ፍቅር አምናለሁ፡፡ ባይገባኝም እስከ መጨረሻይቱ ሕቅታ ሕይወቴን ሙሉ እታገላለሁ፡፡
- ꙮ አይገባኝም ነገር ግን ሰማያዊ ሕይወትና ተስፋ ለማግኘት በምድራዊ ሕይወቴ እጥራለሁ፡፡ በጸሎት፣ በሰማያዊ ፍቅርና ቅዱሳንንም በመማጸን እኖራለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

**ሦስተኛው ጥያቄ ይህስ የማን ነው?**

- ꙮ ያለን በሙሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው፡፡ ጥያቄው እንዴት እንጠቀምበታለን ነው? አንዳንድ የእግዚአብሔር ስጦታዎችን አንሥተን እንይ፡፡

**ጤና** ***"ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ***

***መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?"*** ፩ኛ.ቆሮ.፮÷፲፱ ጤናው የተጠበቀለትን ሥጋዊ አካላችንንና አቅማችንን ለመንፈሳዊ እድገታችን (ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ትጋት...) ለቤተ ክርስቲያን እድገት በመድከም እና ለኅብረተሰባችን እድገትና ለውጥ ጠቃሚ ነገሮችን ለመፈጸም እናውለው። ***"የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይረደርሱ፤"*** መክ. ፲፪÷፩ ተብሎ እንደተጻፈ። ጤናችንን፤ የወጣትነት ኃይላችንን እና ዘመናችንን በአደንዛዥ ዕፆች፣ በስካር፣ በዝሙትም ልናባክነው አይገባም። በመልካም ምግባርና በክርስቲያናዊ ሕይወት ተጠብቆ የባለቤቱ መጠቀሚያ ቤተ መቅደስ ይሁን እንጂ።

*ገንዘብ፡-* *ዐሥራት* በማውጣት፣ በአግባቡ ለሚያስፈልገን መልካም ነገር በማዋል የምንጠቀምበት ነው። ይሄን ስናደርግም ***"በቤቱ ውስጥ መብል እንዲሆን ዐሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ ...በረከቴንም አትረፍርፌ ባላፈስባችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል÷ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።"*** ሚልክ. ፫÷፲

**ጊዜ** መጽሐፍ ስለ ጊዜ ***"ለሁሉ ዘመን አለው÷ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው።"*** መክ. ፫÷፩ በማለት ያስተምረናል። እኛስ ጊዜያችንን እናባክናለን ? ወይስ በአግባቡ እንጠቀማለን ? ጊዜ አጠቃቀም በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። በአንድ ከተማ የቆመ ሰዓት ሥር ***"በፍጹም ወደኋላ አይሄድም"*** ተብሎ ተጽፎአል። የተሰጠንን መክሊት ልናተርፍበት የተሰጠን ነውና፤ ጊዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም ውጤታማ ማድረግ አለብን።

## ማጠቃለያ

1. ራሳችንን በግልጽ እንወቅ። የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን በጥንካሬ እንከተለው። የልባችን መሪም እናድርገው። በየትኛውም የሕይወታችን አቅጣጫም እግዚአብሔርን በመሪነት እንዲቀድመን እንጥራው።
2. የእግዚአብሔር መሪነት ለሕይወታችን ወሳኝና አለኝታችን፣ ጥቅማችን፤ አስፈላጊያችንም መሆኑን ካመን። ሌሎቹን ከልባችን እናውጣ።***"መንገዱን ጥረጉ ጥርጊያውንም አቅኑ።"*** ተብሎልና። ማቴ. ፫÷፫
3. ለዘላለማዊ ሕይወታችን እንሥራ። ሰማያዊ ሕይወታችንን የሚያቃናልን ሥራ በየዕለቱ እናከናውን። ዛሬስ ለዘላለማዊ ሕይወታችን ምን ሠራን?
4. ያለንን ሁሉ የሰጠን እግዚአብሔር ነው። በመጨረሻው ቀንም ‹‹ምን ሠራችሁበት?›› ብሎ ሊጠይቀን ይመጣል። የተሰጠንን እንደ **ገብር ኄር** በጥንቃቄ ተጠቅመንበታል? ወይስ ቀብረነዋል? በአፋጣኝ ለራሳችን መልስ ሰጥተን ዛሬ መልካሙን ሁሉ ለማድረግ እንነሳ። ነገ የኛ አይደለም። ***"ለነገ አትጨነቁ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል።"*** ማቴ ፮÷፴፬

www.zeorthodox.org

5. *"ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን እናንተም ጌታቸው መጥቶ ደጁን ሲያንኳኳ ወዲያው እንዲከፍቱለት፤ ከሰርግ እስኪመለስ ድረስ የሚጠብቁ ሰዎችን ምሰሉ፤ ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው፤ እውነት እላችኋለሁ÷ ታጥቆ በማዕድ ያስቀምጣቸዋል ቀርቦም ያገለግላቸዋል።"* ሉቃ. ፲፪÷፴፭-፴፯ እንደተባልን ሁሌም የተዘጋጀን፣ጌታችንን በፍቅርና በመታመን የምንጠብቅም መሆን አለብን።

***መዝሙር***

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል

በዕረፍት ውኃ በለምለም መስክ እኔን ይመራኛል።

***ጥያቄዎች፡-***

መምህር ተማሪዎችዎ ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ምላሽ የሚሆኑ ሐሳባቸውን ጽፈው እንዲያቀርቡና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩበት ያድርጉ።

1. ከፈጣሪያችን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ምንድን ነው?
2. ራሳችንን መመርመር እና ስለማንነታችን ስለራሳችን ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው? ማወቅ ያለብንስ ምንድን ነው?
3. ከእግዚአብሔር ጋር በመኖር ለዘላለማዊው ሕይወት ለመብቃት ምን ማድረግ አለብን?

www.zeorthodox.org

# ሰው ምንድን ነው ?

## ሠላሳ አምስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** *ተማሪዎች፤ ሰዎች የከበርን ፍጡራን መሆናችንን ተረድተን ከፈጣሪያችን ጋር ያለንን መንፈሳዊ ግንኙነት እንዴት ማጠናከር እንዳለብን ይገነዘባሉ፤ የሚቀርብላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡*

**ጥቅስ፡-** ***"ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፡፡"*** መዝ.፻፴፰(፻፴፱)፥፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** **‹‹ሰው ምንድነው›› በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ፤ ‹‹ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ››**

***መግቢያ፡-*** *የሳይንሱ ዓለም የከበረውን የሰውን ልጅ በዝግመተ ለውጥ* /Evolution/ *አሁን ያለበት ደረጃ የደረሰ ፍጡር እንጂ በእግዚአብሔር የተፈጠረ አለመሆኑን በድፍረት ይናገራል፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ግን የሰው ልጅ ምድራዊውን እና ሰማያዊውን ዓለም*/Physical and Spiritual world/ *የሚወክል ክቡር ፍጡር፤ የፍጥረታት ሁሉ ራስ መሆኑን በግልጽ ያስተምረናል፡፡*

***"የሰው ልጅ ተገልጦ የማያልቅ መጽሐፍ ነው"*** *ቢባልም ስለራስ ማወቅ ከፈጣሪያችን ጋር ለሚኖረን ግንኙነት መሠረት ስለሆነ ስለ ኦርቶዶክሳዊ ስነ-ሰብእ* /Orthodox Anthropology/ *እንማራለን፡፡*

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

1. የሰው አፈጣጠር

ሰው የሁሉ አስገኚ በሆነ በእግዚአብሔር በስድስተኛው የሥነ ፍጥረት ቀን የተፈጠረ ክቡር ፍጡር ነው፡፡ አፈጣጠሩም እንደ ሌሎች ፍጥረታት በቃል ወይም በአርምሞ /በዝምታ/ ሳይሆን በፈጣሪው እጅ ከምድር አፈር የተፈጠረ በመሆኑ ከሌሎቹ የከበረና የተለየ ያደርገዋል፡፡ **"እግዚአብሔርም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው"** ዘፍ.፪፥፯ እግዚአብሔርም ሰውን መፍጠሩ **"እጅግ መልካም"** እንደነበር መግለጹ፤ የሰውን ክቡርነት የሚያሳይ ነው፡፡ ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ነው፡፡ **"እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር… እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡" ዘፍ.፩፥፳፮-፳፰** ይህ አርአያና ምሳሌ የሚገለጠውም፡-

www.zeorthodox.org

ሀ. በገዢነቱ፡-*“ ምድርንም ...ግዙአት ፤ የባህር ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።”* ዘፍ.፩፥፳፰

ለ. በአዋቂነቱ፡-አብዛኛውን ጊዜ ዕውቀቱን በአግባቡ አይጠቀምም እንጂ ከፍጥረታት ያለፈውን የሚያስታውስ የሚመጣውን የሚገነዘበው ሰው ብቻ ነው። *“አእምሮ እንደ ሌለው ክቡር ሰው እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ።”* መዝ. ፵፰(፵፱)፥፳

ሐ. በቅድስናው፡-*“እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ”* ፩ኛጴጥ.፩፥፲፳

መ. በሕያውነቱ፡- *“ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻ ቀን አስነሣዋለሁ።”* ዮሐ.፮፥፶፫

ሰው የሚለው የወል መጠሪያ ስም ወንድንም ሴትንም የሚያመለክት ነው። **“በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።”** ዘፍ.፩፥፳፮-፳፰ ምንም እንኳን ወንድና ሴት በአንድ ቀን የተፈጠሩ ባይሆንም፣ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሴት ህልውና በአዳም ውስጥ እንደ ነበረና ወደ ፊት እንደምትፈጠር በትንቢት መልክ የሚያስረዳ ነው። በጾታ ለይቶ ግን *“... እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት።”* ሲል የሔዋን አፈጣጠር ከአዳም አካል እንደሆነ ይገልጻል። ዘፍ.፪፥፳፪ ስለዚህ መጽሐፍ *“ሰው”* ሲል የሚያመለክተው ወንድንም ሴትንም መሆኑን ልብ ልንል ይገባል።

2. የሰው ባሕርያት

ከምድር አፈር የተበጀው የሰው ልጅ ሰባት ባሕርያት እንዳሉት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ያስረዳሉ። እነዚህም ሰባት የሚባሉት ባሕርያት አራቱ የሥጋ ባሕርያት /ነፋስ፣ እሳት፣ ውኃ፣ አፈር/ ሲሆኑ ሦስቱ ደግሞ የነፍስ ባሕርያት /ሕያውነት፣ ተናጋሪነት፣ አሳቢነት/ ናቸው። እነዚህን ሰባቱን አጠቃለው የያዙት ሥጋ እና ነፍስ ስለሆነ በመቀጠል እነርሱን እንመለከታለን።

*ሀ. የሥጋ ባሕርያት፡-* ሰው አካል ያለው ፍጡር መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው። አካሉም የዳበረው ከላይ በጠቀስናቸው በአራቱ ባሕርያት (elements) ነው። እነዚህም በሰው ልጅ የዕድገት ሂደት /developmental process/ የራሳቸው የሆነ አሻራቸውን እንደሚተዉ የቤተ ክርስቲያችን የሥነ ፍጥረት መጽሐፍ የሆነው መጽሐፈ አክሲማሮስ ያትታል።

www.zeorthodox.org

ይህ ከምድር የተገኘው የሰው አካል /ሥጋ/ ደካማ እና ለኃጢአት በቀላሉ የሚያዘነብል ሲሆን፤ ነፍሳችን ከሥጋችን በተለየ ጊዜ በመቃብር ይበሰብሳል። በትንሣኤ ዘጉባኤ ደግሞ አዲስ መንፈሳዊ አካልን በመላበስ ለዘላለም የሚኖር ነው።

**ለ. ባሕርያተ ነፍስ፡-** እግዚአብሔር ሰውን ከአፈር ብቻ አበጅቶት ዝም አላለም፤ ሕያው ሆኖ እንዲኖር ነፍስንም ፈጠረለት እንጂ፡፡ ***"... በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ፡፡"*** ዘፍ.፪፥፯ ነፍስ በተፈጥሮዋ የማትታይ ፣ ረቂቅ ግን ደግሞ የራሷ የሆነ አካል ያላት ስትሆን፤ አፈጣጠሯም እም ኀበ አልቦ ነው፡፡ ነፍስ ሦስት መገለጫዎች አላት፡፡ እነዚህም፡-

**ሕያውነት፡-** ሰውን ዘላለማዊ ነው የሚያሰኘው ይህ የነፍስ ሕያውነት ባሕርይ ነው፤ ነፍስ አትሞትም፡፡ ***"ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፣ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፉ የሚቻለውን ፍሩ፡፡"*** ማቴ.፲፥፳፰

**ለባዊነት፡-**የሰው ልጅ አዋቂ የሚያደርገው ይህ የነፍስ ባሕርይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከላይ እንደተመለከትነው፡፡ ይህ የነፍስ የአዋቂነት ባሕርይ ሰውን የፈጣሪው አምሳል ያደርገዋል ፡፡

**ነባቢት፡-** ሕያው ሆኖ እንዲኖር የተፈጠረው ሰው በለባዊነቱ ያሰበውን ፣ ዕውቀት የሚናገርበት ባሕርዩን ከነፍስ ያገኘው ነው፡፡ ከላይ እንደ ተመለክትነው ምንም እንኳን የሰው ልጅ የነፍስ እና የሥጋ ጥንቅር ቢሆንም አንድ ሰው ይባላል እንጂ ሁለት አይባልም፡፡ ከሁለት አንዱ የተለየው ሰው ***"ሰው"*** ተብሎ አይጠራም፡፡ ***"ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው፡፡"*** ያዕ.፪፥፳፮

3. ሰው ለምን ተፈጠረ?

እግዚአብሔር የማንንም ድጋፍ የማይሻ በራሱ ቀዋሚ የሆነ አምላክ ነው፡፡ መላእክትን እና እኛን እንዲሁም ሌሎች ፍጥረታትን የሚያመሰግነው አጥቶ እናመሰግነው ዘንድ የፈጠረን አይደለም፤ በባሕርዩ ምስጉን ነውና፡፡ ዮሐ.፲፯፥፭ ፣ ፳፬ እግዚአብሔር እኛን የፈጠረን ፡-

- **ለሰው ካለው ፍጹም ፍቅሩ የመነጨ ነው፡-** ከዓለም አስቀድሞ እግዚአብሔር ባሕርዩ ባሕርዩን እያመሰገነው ይኖር ነበር፡፡ ከፍጹም ፍቅሩ የተነሣ በእርሱ ያለውን ቅድስና ንጽሕና ይወርስ ዘንድ ሰውን ፈጠረ፡፡ ይህም ለሰው ያለውን ፍቅር ይገልጻል፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ አክብሮ ቢቆይ ዘላለማዊ ደስታንም አዘጋጅቶለት ነበር፡፡
- **ስሙን ለመቀደስ መንግሥቱን ለመውረስ፡-** የተፈጠርንበት ዋና ዓላማ እና ግብ የፈጠረንን እግዚአብሔር እያመሰገንን እንድንኖር ነው፡፡ የእኛ ምስጋና ፈጣሪያችን ባለው ክብር ላይ የሚጨምር ሳይሆን፤ ማመስገናችን ከእርሱ ቅድስና ተካፋዮች ስለሚያደርገን ነው፡፡ በኋላም ከትንሣኤ ዘጉባኤ በኋላ የክብር ትንሣኤ የሚነሡ ኑሮአቸው ለዘለዓለም ከመላእክት ጋር እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ነው፡፡ ይህም የመፈጠራችን ምክንያት እርሱን በማመስገን የሚገኘውን ቅድስና መካፈል መሆኑን ያስረግጣል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር፡-

- ❖ በክብር የተፈጠርን መሆናችንን ተገንዝባችሁ ለራሳችሁ እንዲሁም ለሰው ሁሉ አክብሮት ስጡ፡፡
- ❖ እግዚአብሔርን መምሰላችን በቅድስና መኖራችን ስለሆነ የቅድስናን ሕይወት ተለማመዱ፡፡

## *ጥያቄዎች፡-*

1. ሰውን የፈጠረው ማን ነው? ሰው እንዴት ተፈጠረ?
2. ‹‹ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ነው›› ሲባል ምን ማለት ነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ በተማራችሁት መሠረት አብራሩ፡፡
3. የሰው ባሕርያት ስንት ናቸው? በስንት ይከፈላሉ ምን ምን ናቸው? በማብራራት ግለጽ፡፡
4. ሰው የተፈጠረው ለምንድ ነው?

www.zeorthodox.org

# መንፈሳዊው ሰው

## ሠላሳ ስድስተኛ ሳምንት

**ዓላማ:-** ተማሪዎች ስለመንፈሳዊነትና የመንፈሳዊውን ሰው መገለጫዎች ግንዛቤ ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይገልጻሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** ***"ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡"*** ፊልጵ.፬፥፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት:-** ‹‹መንፈሳዊው ሰው›› (ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ)

**መግቢያ:-** ብዙዎቻችን መንፈሳዊ ሰው ማለት አንገቱን የደፋ፤ መንፈሳዊ አለባበስ የምንለውን ያልነውን የለበሰ ይመስለናል፡፡ ለአንዳንዶችም በቦታውም አለቦታውም የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ይመስላቸዋል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ መንፈሳዊ ሰው ማንነት እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት - የመንፈሳዊ ሰው መገለጫዎች

### 1. በነገሮች ሁሉ እግዚአብሔርን ያስቀድማል

በሁሉ ነገር የመጀመሪያው እግዚአብሔር ነው፡፡ **"አልፋና ያሜጋ ÷ ፊተኛውና ኋለኛው÷ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ፡፡"** ራዕ.፩፥፲፰፣፳፪፥፲፫፣ ኢሳ.፵፬፥፮ ስለዚህ ከሁሉ ነገር የመጀመሪያውን ለእርሱ እንዲሆን አዟል፡፡ ዘጸ.፲፫፥፪፣ ዘሌ.፳፫፥፲ መንፈሳዊው ሰውም በሕይወቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ያስቀድማል፡፡ ለፈጣሪው ያለውን ፍቅር እና ተገዢነት እንዳያሰናክልበት ከእግዚአብሔር ይልቅ ሌላ የሚያስቀድመው ነገር አይኖርም፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***"ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፡፡ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት፡፡"*** ሉቃ.፲፥፵፩ በማለት እንደ ተናገረ፤ ሰዎች ቅድሚያ የሚሰጡት ነገር ይለያያል፡፡

www.zeorthodox.org

***በሕይወታችን እግዚአብሔርን እናስቀድማለን?*** መንፈሳዊው ሰው ከሁሉ በፊት እግዚአብሔርን ከፊቱ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ አብርሃም ልጅህን ሠዋልኝ በተባለ ጊዜ ልጁን ለመሥዋዕትነት ለማቅረብ ዳግመኛ ማሰብ አላስፈለገውም፡፡ ዘፍ.፳፪፥፪ እንዲሁም ሐና እመ ሳሙኤል መካን ሆና ያገኘችውን የመጀመሪያ ልጇን ለእግዚአብሔር ለመስጠት አላንገራገረችም፡፡

*በሕይወታችን መጀመሪያ ለእግዚአብሔር ቅድሚያ ልንሰጥ ተገቢ እንደ ሆነ ቅዱሳን ሐዋርያት አስተምረውናል። “**ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል።**” ሐዋ. ፭÷፳፱ የራስን ፍላጎት ከእግዚአብሔር ጋር አለማወዳደር የመንፈሳዊ ሰው መለያ ነው። ስለዚህም “**እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል**” ይላል። ዮሐ.፫÷፴*

## 2. ልቡ ከእግዚአብሔር ጋር ነው

*መንፈሳዊው ሰው ሕይወቱ አፍአዊ እና ለይምሰል (እንደ ፈሪሳውያን) ሕግጋትን በመፈጸም ላይ ብቻ ያተኮረ አይደለም።ይልቁንም ጌታ “**ልጄ ሆይ÷ ልብህን ስጠኝ÷ ዓይኖችንህም መንገዴን ይውደዱ**” እንደሚል ልቡን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ነው። ምሳ.፳፫÷፳፮ የሰው መንፈሳዊነት የሚመነጨው ከልቡ ነው፤ ስለዚህ የልቡን ንጽሕና (ንጽሐ ልቡና) ይጠብቃል። ልብ ንጹሕ ከሆነ መንገድን አጥርቶ ለማየት እና ለመለየት ያስችላል። ከዚያም አልፎ እግዚአብሔርን ማየት የምንችለው ልባችን ንጹሕ ሲሆን ነው “**ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና።**” ማቴ.፭÷፰*

*መንፈሳዊው ሰው ልቡ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሆነ የሚፈጽማቸው ድርጊቶች በሙሉ በቀናነት ከእውነት ነው። ሰውን ሲያመሰግን፣ ይቅርታ ሲጠይቅ፣ ሲጸልይም እንዲሁ ከልቡ ነው። ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት እንዳለ ስለሚያስብ ሥራው ሁሉ ከማስመሰል የራቀ ነው። “**ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ። ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና።**” ያዕ.፩÷፳፪-፳፫*

## 3. ጠንካራ እና በኃይል የተመላ ነው

*መንፈሳዊው ሰው ጠንካራ ነው ሲባል አካላዊ ጥንካሬ ሳይሆን የመንፈሳዊ ሕይወቱን ጠንካራነት የሚያመለክት ነው። ብርቱ የሆነውም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለሆነና ከመንፈስ ቅዱስ ካገኘው ኃይል የተነሣ ነው። ፩ኛ ቆሮ.፫÷፲፮ የጥንካሬው መሠረትና ምንጭ እግዚአብሔር ነው። **“ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።”** ፊልጵ.፬÷፲፫ **“ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው÷ እርሱም መድኃኒት ሆነልኝ።”** መዝ. ፻፲፯(፻፲፰)÷፲፬ ጥንካሬውም በአቅም የደከሙትን በመጨቆንና በማሰቃየት ሳይሆን በጽናት፣ ለይቅርታ ባለው ልብ፣ ሌሎችን በመርዳት…ወዘተ የሚገለጥ ነው። “**እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል።**” ሮሜ.፲፭÷፩*

www.zeorthodox.org

## 4. ራሱን የሚገዛ ነው

*መጽሐፍ “**በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል።**” ምሳ.፲፮÷፴፪ እንደሚል ራሱን ከልዩ ልዩ ሥጋዊ ፍላጎቶች ራሱን የገዛ ነው። ወደ ኃጢአት እንዳያመራም ራሱን*

ይጠብቃል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መመራት መንፈሳዊ ሰው ከሚገለጥባቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡ ራስን መግዛት በልዩ ልዩ መልክ ይገለጻል፡፡ ለአብነትም፡-

**ሀ. አንደበትን በመግዛት፡-** መንፈሳዊ ሰው በኅሊናው ያሰበውን ሁሉ በአንደበቱ አያወጣውም፡ እያንዳንዱን ቃል ከመናገሩ በፊት በሚገባ ይመዝናል፡፡*"...አነጋገርህ ይገልጥሃል"* እንደተባለ የሚናገራቸው ቃላት ማንነቱን ስለሚያሳዩ፤ በሰሚዎች ዘንድ በጎም ሆነ ክፉ ተፅዕኖ እንደሚኖራቸው በመረዳት ጥንቃቄ ይወስዳል፡፡ ሁሌም*"እንዲሁም ደግሞ አንደበት ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል፡፡ እነሆ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ጫካ ያቃጥላል፡፡ አንደበትም እሳት ነው፡፡"* የሚለውን ቃል ያስባል፡፡ ያዕ.፫፥፭-፮

**ለ. ሕሊናን በመግዛት፡-** መንፈሳዊ ሰው ሕሊናው ስለ ምድራዊ ነገሮች በማሰብ እንዳይባክን፣ የሐሳብ ኃጢአቶች እንዳያሸንፉት ይጠነቀቃል፡፡ ሀሳቦች በእውንም ሆነ በእቅልፍ ሊመጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሐሳቦች ልቡ እንዳይቀበላቸው ያደርጋል፡፡ ብፁዕ አቡነ ሽኖዳ በ‹‹መንፈሳዊ ውጊያዎች›› መጽሐፋቸው፤ **"ዲያብሎስ ያለ ሰው ፈቃድ በሕሊና ውስጥ አንድ አሳብ ሊያስተዋውቅህ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አሳብ ወደ ሕሊናህ እንዲገባ ሓላፊነቱን ባትወስድም ልትቀበለው ሓላፊነቱን የምትወስደው ግን አንተ ነህ፡፡"** ይላሉ፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው አሳቦቹን ለመምራት ራሱን ያለማምዳል እንጂ በአሳቦቹ አይመራም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው **"በሰይጣን ሐሳብ እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና፡፡"** ፪ኛ ቆ.፪፥፲፩

**ሐ. ሕዋሳትን በመግዛት፡-** ሕዋሳት የክፉ ሐሳቦች መግቢያ በር ናቸው፡፡ ስለዚህም መንፈሳዊ ሰው የኃጢአት አስተሳሰቦች ወደ እርሱ እንዳይመጡ ሕዋሳቱን ከክፉ ነገሮች ያርቃል፡፡"... **ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ፡፡"** ሮሜ.፮፥፲፫

**መ. ስሜቱን በመግዛት፡-"ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቁጣም የዘገየ ይሁን፤ የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና"** መንፈሳዊ ሰው ስሜቱን ከቁጣ ለማራቅ ይተጋል፡፡ ያዕ.፩፥፳

## 5. በሁሉ አሸናፊ ነው

www.zeorthodox.org

መንፈሳዊ ሰው በሁኔታዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ከፊት ስለሚያደርግ፣የሥጋ ፈቃዱን ለፈቃደ ነፍሱ በማስገዛት በአጋንንት ላይ ድል ይቀዳጃል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተመላ ጠንካራ ስለሆነም የአሸናፊነት ኃይል ከእርሱ ጋር ነው፡፡

ዘወትር ራሱን ለማሸነፍ ይተጋል፡፡ ራሱን ከውስጥ የሚያሸንፍ ሰው ዓለሙንና ዲያብሎስን ማሸነፍ ይችላል፡፡ በራሱ የሚሸነፍና በራሱ ፊት በድካም የሚቆም ከሆነ ግን በማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ይወድቃል፡፡ ጻድቅ ዮሴፍ እጅግ ከባድ የሆነ ውጭያዊ ውጊያ ቢገጥመውም አስቀድሞ

ራሱን ያሸነፈ ስለነበር በቀረበለት የኃጢአት ግብዣ አልወደቀም **"በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?"** በማለት ዲያብሎስን አሳፈረ እንጂ፡፡ ዘፍ.፴፱፥፱

ክፋትን እንጂ ክፉ ሰዎችን ለማሸነፍ አይጥርም፤ ለደካሞች መትጋት ዓይነተኛ መገለጫው ነው፡፡ **"እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል፡፡"** ሮሜ.፲፭፥፩

***ማጠቃለያ፡-*** በዛሬው ትምህርታችን መንፈሳዊው ሰው ፡- እግዚአብሔርን የሚያስቀድም ፣ ልቡ ከእግዚአብሔር ጋር የሆነ፣ በጠንካራ ኃይል የተሞላ፣ ራሱን የሚገዛ እና በሁሉ አሸናፊ መሆኑን ተምረናል፡፡

## ተግባር፡-

- የተማራችሁትን ለብቻችሁ ሆናችሁ ከጸሎት ጋር ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሰላስሉት ፣
- ራሳችሁን መርምራችሁና አይታችሁ ለተግባር ተዘጋጁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

መምህር ተማሪዎችዎ በሚከተሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩበት አድርጉ፡፡

1. መንፈሳዊነት ምንድነው?
2. የመንፈሳዊነት መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# መንፈሳዊ ዕድገት (ክፍል አንድ)

## ሠላሳ ሰባተኛ ሳምንት

**ዓላማ፦** ተማሪዎች ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ምንነት እና በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ ሂደቶችን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይገልጻሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፦** ***"...በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ።" ዕብ.፲፪፥፪***

**ተጨማሪ ምንባባት፦** ‹‹Ascending the Hights ; A Lay Man Guide to the Ladder of Divine ascent (Father John Mark)

**መግቢያ፦** መንፈስ ከእግዚአብሔር ከባሕርዩ የሚገኝ (የአምላክነቱ ባሕርይ) ነው። ረቂቅ፣ የማይዳሰስ፣ የማይታይ፣ በመንፈስ የምንረዳው እና ህልውናው በሥራው የሚታወቅ አካላዊ ነው። **"ነፋስ ወደ ወደደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።"** ዮሐ.፫፥፰ ሰው በተፈጥሮው መንፈሳዊ ነው፤ ይህም ባሕርዩ የማይጠፋ እና ዘላለማዊ ነው።

መንፈሳዊነት ዓለምን በእግዚአብሔር ዓይን መመልከት ነው። በተጨማሪም መንፈሳዊነት ከስሜታዊነት የራቀ ውሳጣዊ ሕይወት ነው። ይህ የመንፈሳዊነት ሕይወትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደግን፣ ፈተናዎችን እያለፍን እና በስተመጨረሻም ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆን የምንሄድበት የጉዞ መስመር ነው።

## የሳምንቱ ትምህርት፦

### 1. ሰው እንዴት መንፈሳዊ መሆን ይችላል?

**ሰው መንፈሳዊ ከመሆኑ በፊት ክርስቲያን መሆን ይገባዋል፦** ክርስቲያን የሚኾነው ከመንፈስ ቅዱስና እና በዕለተ ዓርብ ከጌታ ጎን በፈሰሰው ውኃ ስንጠመቅ ነው። በዚያ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንሆናለን፤ መንፈሳዊ ሕይወትንም እንጀምራለን።

www.zeorthodox.org

**መንፈሳዊ ሀብትን እና ጸጋን ሁል ጊዜ በመሻት፦** ያለ እግዚአብሔር ረዳትነት ምንም ማድረግ እንደማይችል መረዳት አለበት። **"...ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፤ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።"** ፩ኛ ጴጥ.፭፥፭

**በትምህርት፦** ቃለ እግዚአብሔርን ዘወትር በመስማት ፣ በሁሉ ነገር እና በማንኛውም ነገር ***ለመማር የተዘጋጀ*** መሆን አለበት።

## 2. የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃዎች

ክርስቲያናዊ ሕይወት በሂደት ላይ ያለ በመንፈሳዊ ተጋድሎ ተስፋችን ወደ አለበት ቦታ የሚገሰግስ ሰማያዊ ጉዞ ነው፡፡ ይህንን በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ የሚታይ መንፈሳዊ ጉዞ በተቻለ መጠን ተስፋ ሳይቆርጡ በእግዚአብሔር ረድኤት መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ የክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች ይከፈላል፡፡ እነርሱም፡- ወጣኒ፣ ማዕከላዊ እና ፍጹማን ናቸው፡፡

### *ወጣኒ (ጀማሪ)፡-*

በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኙ አማኞችን ወይም ገና ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውን የጀመሩትን ያመለክታል፡፡ በክርስትና መሠረተ ትምህርት ላይ እንደዚሁም ገና በትምህርተ ክርስትና እውቀት ያላደጉትን ፣ በእምነትና በምግባር ያልጸኑትን ሁሉ ያካትታል፡፡ በዚህ የመንፈሳዊ ሕይወት የሚገኙ ክርስቲያኖች የሚፈጽሟቸው ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ከዓለም መለየት፡-** ከዓለም መለየት ማለት ቁሳዊ ክብርን መናቅ፣ አሁን ከምናየው ምድራዊ እና ዓለማዊ ኑሮ በላይ ያለውን ለማግኘት ሲባል ይህን ዓለም መካድ ማለት ነው፡፡***“ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም፡፡”*** ፩ኛ. ዮሐ.፪፥፲፫

**“መለየት”** ሲባል ለአበው መነኮሳት እና ባሕታውያን የዚህን ዓለም ኑሮ በጠቅላላው መተው እና ኑሮን ከፈጣሪ ጋር ብቻ ማድረግ ነው፡፡ በአንድም በሌላም መልኩ ኑሮአችን ከቁሳዊው ዓለም ጋር ለተገናኘን ሰዎች ግን ራሳችንን ከራስ **ወዳድነት፣ ከከንቱ ድርጊቶች እና ለዓለማዊው ነገሮች ከፍተኛ ግምት** ከመስጠት መለየት እንዳለብን የሚያመለክት ነው፡፡ ***“ወዳጆች ሆይ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፡፡”*** ፩ኛ ጴጥ.፪፥፲፩

**ውዳሴ (ምስጋና) ከመሻት መለየት፡-** ውዳሴን የሚሻ ስለ ተወደሰ ብቻ እርካታ ይኖረዋል ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ምስጋናን የሚፈልግ፣ ራሱን ከፍ አድርጎ ማየት የሚሻ ሰው ስለ ራሱ ብዙ ማውራቱን በመቀጠል ራሱን በሰው ፊት ማወደስ ይጀምራል፡፡ ስለ ራሱም እውነት የሆነውን ነገር ሁሉ አይናገርም፡፡ የሚናገረው ስለ መልካም ጎኑ፣ ስለ ማሸነፉና ስለ ክብሩ ነው፡፡ ይህን በማድረጉም ጉድለቶቹን ይሸሽጋል፡፡ ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወታችን የመጀመሪያው ደረጃ ከዓለም መለየት ነው ሲባል ውዳሴ ከንቱ ከመፈለግ መለየትን ያካተተ ነው፡፡(የቅዱስ መቃርዮስ ታሪክ)

www.zeorthodox.org

***ማዕከላዊ፡-***

በወጣንያን እና በፍጹማን መካከል ያለ የክርስቲያናዊ ሕይወት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ያሉ ክርስቲያኖች መገለጫ በጎ ምግባራትን በመፈጸም የሚደረግ ተጋድሎ እና የራስ ፍላጎቶቻችንን ለማሸነፍ የምንጋደልበት የዕድገት ደረጃ ነው፡፡

***በጎ ምግባራትን መፈጸም፡-*** በመንፈሳዊ ሕይወት ስናድግ የማዕከላዊው ዕርከን መሠረታውያን በጎ ምግባራትን አብዝተን መፈጸም ነው፡፡

***መሠረታውያን በጎ ምግባራት፡-***

***ሀ. ታማኝነት፡-***ታማኝ በመሆናችን በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠንን ፍጹም ፍቅር ለመቀበል ዝግጁዎች እንሆናለን፡፡ ታማኝ ባለመሆናችን ገነትን አጥተናል፡፡ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የሚያስፈልገን ደግሞ ታማኝ መሆን ነው፡፡ "**በሔዋን ምክንያት የገነት ደጅ ተዘጋ፤ ዳግመኛ ስለ ድንግል ማርያም ተከፈተልን፡፡**" ውዳሴ ማርያም፡፡ ታማኝነት ለሕሊና፣ ለቃለ እግዚአብሔር እና ለሰዎች ነው፡፡

ታማኝነት ከበላያችን ላሉ ሁሉ፡- ***"ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን ከሁሉ በላይ ነውና፤ ለመኳንንትም ቢሆን ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣትም በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ፡፡"*** ፩ኛ ጴጥ.፪፥፲፫-፲፬

***ለ. የንስሐ ሕይወት፡-*** ኃጢአትን ማመን፣ ስለ ሠራነው ኃጢአት ማዘን፣መጸጸት፣ ዳግመኛ ወደ ኃጢአት አለመመለስ፣ እንደገና መወለድ ነው፡፡ ንስሐ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡

- ***ራስን መውቀስና መጸጸት፡-***ንስሐ የአንድ ጊዜ ቅጽበታዊ ድርጊት ሳይሆን ሁልጊዜ ከሕይወታችን እስትንፋስ ጋር ተዛምዶ ሊኖርና ሊለይ የማይገባው ነው፡፡ በልብ ማዘንና መተከዝ ከሰው ሕሊና ሊለይ አይገባም፡፡ "**ኃጢአቴም ሁል ጊዜ በፊቴ ነው**" መዝ.፶፥፫
- ***ለእግዚአብሔር መናዘዝ፡-*** የሠራነውን ለእግዚአብሔር የምንነግረው እርሱ የማያውቀው ሆኖ ሳይሆን እርሱን ያሳዘንን መሆናችንን እና መጸጸታችንን ለመግለጽ ነው፡፡ የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ሲመለስ "**አባቴ ሆይ በሰማይና በምድር በደልኩ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም**" እንዳለ፡፡ ሉቃ. ፲፭፥፲፰
- ***ለካህን መናዘዝ፡፡*** ጌታችን ራስህን ለካህን አሳይ እንዳለን፡፡ ሉቃ.፲፯፥፲፤ በካህኑ ፊት፣ ለካህኑ መናዘዝ፡፡

www.zeorthodox.org

***ሐ. ተዘክሮተ ሞት፡-*** ዕለተ ሞቱን የሚያስብ ሰው በዚህ ዓለም ከሚያደርገው ተጋድሎ የሚያርፍበት ነው፡፡ በሕይወቱ ተስፋ የሚያደርጋት መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት የሚሸጋገርባት ድልድይ ስለሆነች፤ ከኃጢአት ጋር ለሚያደርገው ብርቱ ትግል የዘወትር ብርታቱ ስለሆነች ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ተዘክሮተ ሞት ኃጢአት ምን ያህል ክፉ እንደ ሆነች በአንጻሩ በጎ ሥራ ምን ያህል የከበረ ዋጋ እንደሚያሰጥ አንድ ሰው እንዲረዳው ያደርጋል። ተዘክሮተ ሞት ለመንፈሳዊ ሕይወት ያለው ጠቀሜታ ጉልህ ነው። **"በተናገርከው ነገር ሁሉ ፍጻሜህን አስባት ሁልጊዜም አትበድል።"** ሲራ.፯፥፴፮

**ማጠቃለያ፡-** መንፈሳዊው እድገት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆን የምንሄድበት የጉዞ መስመር ነው። በተፈጥሮአችን መንፈሳውያን ነን። የክርስቲያናዊ የሕይወት ደረጃዎች ሦስት ናቸው። በእያንዳንዱ የሕይወት ደረጃ የምንፈጽማቸው መንፈሳዊ ድርጊቶች እና ተጋድሎዎች አሉ።

**ተግባር፡-** አሁን ባላችሁበት ሁኔታ በጣም የምትቸገሩበትን ፈተና በመለየት እነርሱን ለማሸነፍ የተጠቀሱትን ምግባራት ተለማመዱ።

***ጥያቄዎች፡-***

1. ሰው መንፈሳዊ ለመሆን የሚችለው እንዴት ነው? አብራሩ።
2. የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃዎች ስንት ናቸው? እያንዳንዳቸውን ግለጹ።
3. የበጎ ምግባራት መሠረታዊ የሆኑ ዐበይት ነገሮች ምን ምን ናቸው? አብራሩ።

www.zeorthodox.org

# መንፈሳዊ ዕድገት (ክፍል ሁለት)

## ሠላሳ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የመንፈሳዊ ሕይወት ሂደቶችን ይረዳሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡- "… በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፡፡" ዕብ.፲፪፥፪**

**ተጨጫሪ ምንባባት፡-** ‹‹Ascending the Hights; A Lay Man Guide to the Ladder of Divine Ascent (Father John Mark)

**መግቢያ፡-** ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን መንፈሳዊ ደረጃዎችን ተመልክተናል፡፡ የመንፈሳዊው ሕይወት ደረጃዎች ወጣኒነት፣ ማዕከላዊነት እና ፍጹምነት መሆናቸውን ተምረናል፡፡ በማዕከላዊነት የመጀመሪያውን ክፍል በጎ ምግባራትን መፈጸም አይተን በይደር አቁመን ነበር፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ቀጣዩን ክፍል እናያለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

**ከራስ ስሜቶች ጋር የሚደረግ ተጋድሎ፡-** ከራሳችን ስሜቶች ጋር የሚደረጉትን ተጋድሎዎች አካላዊ የሆኑና ያልሆኑ ብለን ለሁለት እንከፍላቸዋለን፡፡

1. **አካላዊ ያልሆኑ ስሜቶች፡-** በብዙ መንገድ ይገለጣሉ፤ ለምሳሌ እንዲሆነንም የሚከተሉትን እንይ፡-

**ሀ. ቁጣ፡-** ቁጠኝነት የእግዚአብሔርን መንፈስ ከውስጣችን እንዲሸሽ የሚያደርግ እና በአንጻሩ ሰይጣናዊ አስተሳሰቦች ውስጣችንን እንዲቆጣጠሩት መንገድ የሚከፍት፤ እኔ ብቻ ትክክል ነኝ ከማለት የሚመጣ ስሜት ነው፡፡ **"የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና፡፡"** ያዕ.፩፥፳

**የቁጠኝነትን ስሜት ለመተው፡-** ለቁጣ የሚያነሣሡንን ነገሮች ለመተው መለማመድ አለብን፡፡ በሕሊናችን የሚያስቆጣ አሳቦች ቢኖሩም በንግግር ከመግለጽ መቆጠብ (የቁጣ አሳባችንን ማሸነፍ)፡፡ ማንንም (ተቆጥቶ ለመጣ እንኳን) በቁጣ መንፈስ አለማናገርን መምረጥ ሊተኮርባቸው የሚገባ ጉዳዮች ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

**ለ. ቂመኝነት፡-**በመንፈሳዊ ሕይወታችን ከሚያጋጥሙን ፈተናዎች አንዱ ከቂመኛነት ለመላቀቅ የምናደርገው ተጋድሎ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ቂመኛ የምንሆነው በጣም ስላሳዘኑን ሰዎች አተኩረን ስናስብ ነው፡፡

**እናም ከዚህ ፈተና ለመውጣት፡-** ክፉ ባደረጉብን ሰዎች አለመናደድ እና ያደረጉብንን አለማስታወስ፡፡ ይቅር ለመባል የይቅርታ ልብ ሊኖረን ይገባል፤ ይቅር ባይነት የፍጹም ተነሳሒነት አንዱ መገለጫ ነውና፡፡ በንስሐ ሕይወት ውስጥ ነው ያለነው እያልን ራሳችንን ከቂመኛነት ካላጸዳን እየሮጠ የሚያንቀላፋን ሰው እንመስላለን፡፡ **"ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር አይላችሁም፡፡"** ማቴ.፮፥፲፬-፲፭ ይቅር ባይ ሰዎች ካልሆንን ራሳችን የክፋትና የኃጢአት ምንጮች እንደሆንን መዘንጋት የለብንም፡፡ የይቅርታ ሂደት ይቅር ለማለት ውስጣችን አልሸነፍ ያለንን ሰው በትሑት ሰብእና ***"የበደልከኝን ይቅር ማለት ስላልቻልኩ ማረኝ"*** እስከ ማለት የሚደርስ ነው፡፡ ድርጊቱ ከባድ ቢመስልም መንፈሳዊነታችን ወደ ኋላ ከሚጎትተን ከቂማችን በሲያል ከምንሆን ግን የተሻለ ነው፡፡

**ሐ. ሐሜተኝነት፡-** ስለ አንድ ሰው ድክመት እና መጥፎነት ማውራት ነው፡፡ ሐሜተኞች የሚያሙት ሰው እንዲስተካከል ብቻ ስለርሱ እንደሚያወሩ ይናገራሉ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ዘደማስቆ **"የምትወደውን ሰው የምታማው እንዲስተካከል ከሆነ በአደባባይ ከምታወራበት በሥውር ጸልይለት"** በማለት ይመክራል፡፡

***ሐሜተኝነት ግብዝ መሆናችንን ይገልጻል፦*** ሰዎችን በሌሉበት ስለ ጥፋታቸው ማውራት የራሳችንን "እውነተኛነት እና ጽድቅ" እየመሠከርን ነው፡፡ ድርጊቱን የምንፈጽመው ከፍቅር አንጻር ከሆነ ግን **"ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና"** ወዳጆቻችንን ከማማት መራቅ ይገባል፡፡ ፩ኛ ጴጥ.፬፥፰

***ሰውን ስናማ ፍርድ እየሰጠን ነው፦*** በሰው ላይ ስንፈርድ ራሳችንን ከእግዚአብሔር እኩል እያደረግን፣ በእርሱም ሥራ ጣልቃ እየገባን ነው፡፡ **"ወንድሙን የሚያማ በወንድሙም ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል በሕግም ይፈርዳል፤ በሕግም ብትፈርድ ፈራጅ ነህ እንጂ ሕግ አድራጊ አይደለህም፡፡ ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፤ እርሱም ሊያድን ሊያጠፋም የሚችል ነው፤ በሌላው ግን የምትፈርድ አንተ ማ ነህ?"** ያዕ.፬፥፲፩-፲፪ የሰውን ልቡና የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ምናልባት እኛ እየፈረድንበት ያለው ሰው በእርሱ ይቅር የተባለ ሊሆን ይችላልና የእግዚአብሔርን ምሕረት በእኛ ፍርድ መቃወም እንዳይሆንብን እንጠንቀቅ፡፡ **"ምሕረትን ለማያደርግ ምሕረት የሌለበት ፍርድ ይሆናልና፤ ምሕረትም በፍርድ ላይ ይመካል፡፡"** ያዕ.፪፥፲፫

www.zeorthodox.org

**አካላዊ ስሜቶች** /physical passions/፡-

*ሀ.* **ስግብግብነት፡-** በመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞአችን ያሉ ስሜቶቻችንና ፍላጎቶቻችን እርስ በእርስ የተያያዙ በመሆናቸው፤ አንደኛውን ካላሸነፍን ሌላውን ማሸነፍ አንችልም፡፡ እንዲሁም ደግሞ

አንደኛውን ካሸነፍን ሌሎቹን ማሸነፍ ቀላል ይሆናል። ስግብግብነት ለሌሎች ኃጢአቶች በር ከፋች ነው። በንስሐ ሕይወት ሂደት ከፍተኛ ፈተና ከገጠመህ፤ የጠገበ ሆድ እንባን ለማፍሰስ ይቸገራልና መብልህን አስተካክል። በዝሙት ምክንያት ጾር የሚበዛብህ ከሆነ፤ የሆዱን ፍላጎት እና የዝሙት ጾሩን ለማጥፋት የሚፈልግ ሰው እሳትን ለማጥፋት ጋዝ የሚጠቀም ሰውን ይመስላል።

**ለ. ንጽሕና፡-** ንጽሕና ስንል ከጋብቻ በፊትም ሆነ ከጋብቻ ውጪ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን አለመፈጸም ማለት ነው። ንጽሕናችንን ጠበቅን ማለት የሥጋ ፈቃዳችንን እያሸነፍን ለፈቃደ ነፍሳችን መኖር ጀመርን ማለት ነው። ንጽሕና ከሕሊና ይጀምራል። ስለ ዝሙት ከመስማት፣ ከማየት፣ ከማንበብ በመከልከል ፈተናውን መጋደል ይገባል። ፪ኛ ሳሙ.፲፩

***ፍጹማን፡-***

በክርስትና እውቀታቸው ይልቁንም በሃይማኖታቸው የበቁ ምግባርና ትሩፋት የሚሠሩት፤ በመንፈሳዊ ገድላቸው ከራሳቸው አልፈው ለሌላ የሚተርፉት ክርስቲያኖች በከፍተኛው የዕድገት ደረጃ የደረሱ ናቸው። ይህ የፍጹምነት ደረጃ ስለሆነ ቅዱሳንን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። በዚህ የሕይወት ደረጃ ያሉ ቅዱሳንን መገለጫ እንደሚከተለው እመለከታለን።

**ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን፡-** የፍጹማን አባቶች ሕይወት ላይ ስንደርስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ በመፈጸም እንኖራለን። በነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሆነ የምናውቅበት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ ከሚገኙት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

**መረጋጋት፡-** ርጋታ ሲባል ዕረፍተ ነፍስ፣ መንፈሳዊ ውጊያ የሚጠፋበት ፍጹም ሰላማዊ ሕይወት ማለት ነው። ከላይ የተመለከትናቸውን ተጋድሎዎች የምንፈጽመው ይህንን ፍጹም ሰላም ለማግኘት ነው። ቅዱስ ዳዊት ***"ሰላምን እሻ ተከተላትም"*** እንዳለ። መዝ.፴፫(፴፫)፥፲፬

**ጸሎት፡-** ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን አንድነት የምናጠናክረውና የምንገልጸው በጸሎት አማካኝነት ነው። ጸሎት የማድረግ የመጨረሻ ግብ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ለመመሥረት ነው። ጸሎት ራስን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረድ ነው።

በመጀመሪያ ራሳችን ለጸሎት እንተጋለን ፤ በመጨረሻ ግን የተለማመድነው የጸሎት ሕይወት ራሱ እንድንጸልይ ይገፋፋናል። የጸሎት ሕይወትን እየለመድን ስንመጣ አንደበታችን፣ ሕሊናችንና ልባችን በጸሎት ጊዜ አንድ ይሆናሉ።

www.zeorthodox.org

ምንም እንኳን በጎ ምግባራትን ሁሉ የምትፈጽም ብትሆንም አሁንም ስለ ኃጢአትህ መጸለይህን አታቁም። ቅዱስ ጳውሎስ **"ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ"** ፩ኛ ጢሞ.፩፥፲፭ በማለት እንደተናገረ እርሱን አብነት አድርግ።

**ፍቅር፡-** የመንፈሳዊነት መጨረሻው ማፍቀር ነው፡፡ **"ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው፡፡"** ፩ኛ. ቆሮ.፲፫፥፲፫ በትክክል የእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ጋር መሆናችን የሚታወቀው የፍቅር ሰዎች ስንሆን ነው፡፡ ፍቅር እግዚአብሔር ነው ፤ ማፍቀር ደግሞ እግዚአብሔርን መምሰል ነው፡፡ ፍቅር ከእግዚአብሔር ባሕርያት የሚመደብ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ እርሱ የሚያደርጋቸው ነገሮች ቅጣት፣ ቁጣም ቢሆን እንኳን ከፍጹም ፍቅሩ የተነሣ ነው፡፡

ፍቅር ከእግአብሔር የሚሰጥ ነው፤ መንፈሳዊ ሕይወት ደግሞ ይህን የእግዚአብሔር ፍቅር ለመቀበል የሚደረግ ዝግጅት ነው፡፡ ***"እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን፡፡"*** ፩ኛ ዮሐ.፬፥፲፱

**ማጠቃለያ፡-** ከላይ የተመለከትናቸው የመንፈሳዊ ሕይወት የዕድገት ደረጃዎችንና በየእርከኑ ያለውን የተጋድሎ ሕይወት ነው፡፡ በሦስቱም የሕይወት ደረጃዎች የምናገኛቸው ማዕርጋት አሉ፡፡ እነዚህም አሥሩ ማዕርጋተ ቅዱሳን የሚባሉት ናቸው፡፡

**ተግባር፡-** ሁሌም ራሳችሁን ለማሳደግ ጥረት አድርጉ፡፡

***ጥያቄ፡-***

1. ከራሳችን ስሜቶች ጋር የምናደርጋቸው ተጋድሎዎች አካላዊ የሆኑ እና ያልሆኑ ተብለው በትምህርቱ ተረድታችኋል፡፡

   *ሀ. አካላዊ የሆኑ ስሜቶች*

   *ለ. አካላዊ ያልሆኑ ስሜቶች*

በማለት የተከፈሉትን በዝርዝር እየጠቀሳችሁ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ቁርባን

## ሠላሳ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ቅዱስ ቁርባን ያውቃሉ፤ የሚሰጣቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ ለዘላለም ሕይወት አለው ፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፡፡ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ፡፡"*** ዮሐ.፮፥፶፬-፶፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳፮፥፳፮፤ ዮሐ.፬፥፲፫-፲፬

***መግቢያ፡-*** ቁርባን፡- የሱርስት ቃል ሲሆን፤ ለአምላክ የሚቀርብ ስጦታ፤ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ጥንታዊ ግብጻውያን ‹‹ኤውክሪስት›› ሲሉት ***"ምሥጋና ማቅረብ "*** ማለት ነው፡፡ በክርስትና ትምህርትም ቅዱስ ቁርባን እኛ ለአምላክ የምናቀርበው እርሱም ለእኛ የሚሰጠን አምኃ (ስጦታ) ነው፡፡ ይኸው ቁርባን የተለያዩ ስሞች አሉት፡፡ እነርሱም፡- ***"የጌታ ራት"*** ፤ ***"ምስጢራዊው ራት "*** ፤ ***"አንድ የመሆን ምስጢር"*** ፤ ***"ክቡር ሥጋውና ቅዱስ ደሙ"*** ወ.ዘ.ተ…..ተብሎ ይጠራል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ ቅዱስ ቁርባን እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

**የምስጢረ ቁርባን አጀማመር** ፡- ቅዱስ ቁርባን በጌታችን የተመሠረተ ነው፡፡

1. በትምህርት፡- ***"ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፡፡…. እኔ ከእርሱ ጋር እኖራለሁ እርሱም ከእኔ ጋ ይኖራል " " ሥጋዮ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው ፡፡ "*** ዮሐ.፮፥፶፮-፶፮
2. በተግባር፡- በምሴተ ሐሙስ ***" የመጨረሻውን ራት "*** ለደቀ መዛሙርቱ ሲያበላቸው በተግባር ያደረገውና ያስተማረው እንዲህ ተጽፎልናል፡፡ ***" ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ ፡፡ ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፡-ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡"*** ማቴ.፳፮፥፳፮-፳፰

www.zeorthodox.org

3. **ካህናት በመሾም፡-** ጌታችን ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ብቻ ሰብስቦ ነው። ይህንን ምስጢር የመሠረተው። ማቴ.፳፮፥፳፮ ንስሐንና የኃጢአት ሥርየትን እንዲሰጡም የክህነት ሥልጣን እና ትእዛዝ ሰጥቶአቸዋል። (ማቴ.፳፰፥፲፱-፳፣፩ኛቆሮ.፲፩፥፳፫-፳፮፣ሉቃ.፳፬፥፵፮፣፳፪፥፲፱-፳)

## ቅዱስ ቁርባን ምንድነው ?

1. **እውነተኛ የጌታችን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው።** *" እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም.... ይህ ሥጋዬ ነው። ጽዋንም አንሥቶ .... ደሜ ይህ ነው።አለ"* ማቴ.፳፮፥፳፮
2. ***ሥጋው እውነተኛ መብል ደሙም እውነተኛ መጠጥ ነው።*** ይህም ማለት በልተን እና ጠጥተን ነገ እንደሚርበን ሳይሆን፤ ለዘላለም ከእኛ ጋር ሆኖ ዘለዓለማዊ ምግብ እና መጠጥ የሚሆነን ነው። ***"ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰውም ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው። ... እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ ለዘላለም ሕይወት አለው፥እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና።"*** ዮሐ. ፮፥፶፩-፶፮
3. ***መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የተለየው ነው።*** የምንቀበለው ሥጋና ደም በዕለተ ዓርብ የተሠዋውን ነው፤ ጌታ በዚህች ቀን በነፍስ ወደ ሲዖል ሲወርድ በሥጋ በመስቀል ነበር። መለኮት ደግሞ ከሁለቱም ጋር የተዋሐደ ነው። በዚህ መሠረትም መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የተለየው ብለን በማመን እንቀበላለን። **ምሳሌ፡-** እስራኤል የበሉት የፋሲካ በግ ሲበሉ የታዘዙት ***" ጥሬውን በውኃም የበሰለውን አትብሉ ነገር ግን... በእሳት የተጠበሰውን ብሉት "*** ዘጸ.፲፪፥፱ ተብለው ነበር። ያም በግ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። ፩ኛ.ቆሮ.፭፥፯ እሳቱም የመለኮቱ።

ይህ ምስጢር ደም አልባ መሥዋዕት እንደሆነና ለመዳናችንም እንደሚቀርብ እናምናለን። ጌታችንም እንዲሁ ብሎናል***"ስለ እናንተ የሚሰጠው /የሚሠዋው/ ሥጋዬ ይህ ነው። ይህ ጽዋ ስለእናንተ የሚፈሰው / የሚሠጠው / በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።"*** ሉቃ.፳፪፥፲፱-፳። ቅዱስ ጳውሎስም በአሕዛብ እና በክርስቲያኖች መሥዋዕትና መሠዊያ መካከል ሲያነፃፅር (፩ኛቆሮ.፲፥፲፰-፳፩) የጌታን ማዕድ (ቅዱስ ቁርባንን) እውነተኛ መሥዋዕት መሆኑን ማረጋገጫ ሰጥቶናል። በዕብራ.፲፫፥፲ ላይም እውነተኛውን የክርስቲያኖች መሠዊያ ሲል ጠቅሶታል ።

ይህ የሐዲስ ኪደን መሥዋዕት በብሉይ ኪዳን ተተንብዮለት ነበር ።***" ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና ፤ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ ፤***

www.zeorthodox.org

***ንፁሕም ቁርባን ያቀርባሉ፣ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ።"*** ሚልክ. ፩÷፲፩ ነብዩ ስለ ሐዲስ ኪዳነ መሥዋዕት እየተናገረ እንደሆነ ግልፅ ነው፤ ይህም በወንጌል የቀረበው የጌታ ሥጋና ደም ነው። ይህን ጥቅስ የተረጐሙ የተለያዩ ተርጓምያንም ይህንኑ ነው ያረጋገጡት።

ይህ መሥዋዕትም ጌታ በመስቀል ላይ ካቀረበው መሥዋዕት ጋር አንድ ነው ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም "***ሊቀ ካህናችን እኛን የሚያነጻ መሥዋዕት አቀረበ ፤ከዚያ ጀምሮም እኛ ተመሳሳይ መሥዋዕት እናቀርባለን።"*** ሲል በመስቀል የተሠዋውን ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ሁሉ እንደምትፈጽመው ገልጿል።

እንደ ካቶሊካውያን ሥጋውን ብቻ አንቀበልም ምክንያቱም ጌታ " ***ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ"*** ዮሐ.፮÷፶፮ ነው እንጂ ያለው፤ ሥጋዬን ብቻ አላለም። ለሐዋርያት ሲሰጣቸውም ሕብስቱን ቆርሶ ብሉ እንዳላቸው ጽዋውንም ቀድቶ ***"ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ።"*** ማቴ.፳፮÷፳፯ ነውና ያለው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖችም በሐዋርያት አማካኝነት ሁለቱንም ይቀበሉ እንደነበር ጳውሎስ ***"የሚበላና የሚጠጣ ይበላልና ይጠጣልምና "*** በማለት ስለ ቅዱስ ቁርባን ሲናገር ጽፎልናል ።

ሌሎቹ ደግሞ መታሠቢያ እና ምሳሌ ብቻ ነው ይላሉ። ለመሆኑ ጌታ ለመታሠቢያዬ አድርጉት ሲል ምን ማለቱ ነው? መከራ መስቀሌን እያሰባችሁ ፈጽሙት ማለት እንደሆነ ፤***"ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው"*** ዮሐ.፮÷፶፩ ሲል አረጋግጦልናል። ለሐዋርያት ሲሰጣቸውም" ***ነገ የሚፈስ ሥጋዬ" " ደሜም"*** ማቴ.፳፮÷፳፮-፳፯ ሉቃ.፳፪÷፳፱ አለ እንጂ ምሳሌው አላላቸውም ። ቅዱስ ጳውሎስም" ***ከጌታ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን"*** ብሎ አንድነቱንና አማናዊነቱን አስተምሮናል።

**ይህን ምስጢር መፈጸም የሚችለው ማነው ?** ጌታ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ብቻ መርጦ ***‹‹ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት››*** ሉቃ.፳፪÷፲፱ ብሎም አዝዟቸዋል። ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው ጳጳሳት አስተላለፉ። ክርስትና እየተስፋፋ ሲሄድም፤ ካህናት እንዲፈጽሙት ተፈቅዷል። ዲያቆናት በመራዳት ብቻ ያገለግላሉ፤ ምእመናን ግን ቀድሶ ማቁረብ አይችሉም ።

**ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ያለበት ማነው ?** ጥሙቃን ክርስቲያኖች እንዲቀበሉ ታዟል። ቀደምት ክርስቲያኖችም "***ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።"*** ዮሐ. ፮÷፶፮ ያለውን ይዘው በየሳምንቱ ይቆርቡ ነበር።

www.zeorthodox.org

በዓመት ሦስቴ መቁረብ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ይገባል። ኃጢአት ከተፈጸመም ወዲያው ንስሐ በመግባት ልንቀበል ይገባናል። ቅዱስ ቁርባን ***ስለ ኃጢአት ሥርየት የሚቀርብ*** ነውና። ነገር ግን ከመቁረባችን በፊት ራሳችንን ማዘጋጀት ይገባናል። ***" ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው***

***ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና።"*** ፩ኛ ቆሮ.፲፩፥፳፰-፳፱ ተብሎ እንደ ተጻፈ መቀበል የሚገባቸው በንስሐ የታጠቡ አማንያን ናቸው።

- ❖ ጥምቀት የተፈጸመላቸው ሕፃናትም ይህን የነፍስ ምግብም ሊከለከሉ አይገባምና ቅዱስ ቁርባን መቀበል አለባቸው ።

**ማጠቃለያ፡-** ቅዱስ ቁርባን የጌታችን ሥጋና ደም ነው። ስንቀበለውም ከእርሱ ጋር እንሆናለን። የዘላለምንም ሕይወት እናገኛለን። ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል የዕድሜ፣ የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም የዕውቀትና ብቃት መመዘኛ አልተቀመጠም።

## ተግባር

- ከቅዱስ ቁርባን የተለየ ሕይወት ሊኖረን አይገባም።
- የሞት መውጊያ ኃጢአት በንስሐ ይወገዳል። የዘለዓለም ሕይወት የሚሰጠን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እንቀበል።

***ጥያቄዎች፡-***

1. ቅዱስ ቁርባን ምንድን ነው?
2. ቅዱስ ቁርባንን የመሠረተው ማን ነው? እንዴት መሠረተው? በዝርዝር ግለጹ
3. ቅዱስ ቁርባን፤ ‹‹እውነተኛው የጌታችን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው›› ‹‹ሥጋው እውነተኛ መብል ደሙም እውነተኛ መጠጥ ነው›› የሚሉትን ኃይለ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ እያቀረባችሁ አብራሩ።
4. የቅዱስ ቁርባንን ጌታችን ለመታሰቢያዬ አድርጉት ሲል ምን ማለቱ ነው?በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት መሠረት ግለጹ።
5. የቅዱስ ቁርባንን ምስጢር መፈጸም የሚችለው ማን ነው?
6. ቅዱስ ቁርባን መቀበል ያለበት ማን ነው? ለመቀበል ምን ማድረግ አለበት?

www.zoorthodox.org

# ጾታዊ ቀጠሮ

## ዐርባኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ጾታዊ ቀጠሮ ትክክለኛ ግንዛቤ ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**ጥቅስ፡-** *"... ይህንን ዓለም አትምሰሉ፡፡"* ሮሜ. ፲፪÷፪

**ምንባባት፡-** መሳፍ.፲፬-፲፮፣‹‹መሸኮርመምና ማሸኮርመም›› በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ - zeor-thodox.org

### መግቢያ፡-

ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ጾታዊ ግንኙነት ወጣቶች ንጽሕናቸውን እንዲያጡ ከሚያደርጓቸውን ድርጊቶች አንዱ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ፣ ካህናት፣ እንዲሁም ማንኛውም ክርስቲያን የሚመሰክሩት ነው፡፡ **የዚህ ውድቀት የድግስ ቦታው** ጾታዊ ቀጠሮ ነው፡፡ ጾታዊ ቀጠሮ በዓላማ ጥንካሬና በጥንቃቄ ካልተመራ፤ የልብና የሁኔታዎች አጥር ካልተሠሩለት ለመንፈሳዊ ሕይወታችን አደገኛ ይሆናል፡፡ ንጽሕናችንን የሚያጎድፍ ነው፤ ሥነ ልቦናዊ ጫናም ይፈጥርብናል፤ ለመንፈሳዊ ዕድገታችንም ማነቆ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. ጾታዊ ቀጠሮ ምንድን ነው?

ጾታዊ ቀጠሮን ***"ጊዜያዊ ደስታን እና መዝናናትን በመፈለግ በሁለት ፍቅረኛሞች መካከል የሚደረግ 'የፍቅር' ግንኙነት ነው፡፡"*** የሚለው ትርጉም ይገልጸዋል፡፡ ስለዚህ ጾታዊ ቀጠሮ፡- ዘላቂ ሳይሆን ጊዜያዊ ፣ የፍቅር ግንኙነት ነው፡፡ ከመዝናናት ባለፈ ለወደፊት ሕይወት ታቅዶ የሚደረግ አይደለም፡፡

### 2. ጾታዊ ቀጠሮ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ አይደለም፡፡

www.zeorthodox.org

ጾታዊ ቀጠሮ ከእግዚአብሔር ሐሳብ እና ፈቃድ ውጭ መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠ ነው፡፡ ሶምሶን ከጋብቻ በፊት ባደረገው የፍቅር ግንኙነት እግዚአብሔርን አሳዝኗል ፤ ቀሪ ሕይወቱም የተመሰቃቀለ ሆኗል፡፡ መሳፍ. ፲፬-፲፮ የያዕቆብ ልጅ ዲና ደስታን በመሻት ባደረገችው ድርጊት አሳዛኝ ሕይወት ውስጥ ወድቃ ነበር፡፡ ዘፍ.፴፬÷፩-፫

በምዕራባውያን ዘንድ ጾታዊ ቀጠሮ የተለመደና በጣም እየጨመረ የመጣ ባህል ነው፡፡ የዚህም ምክንያት፡- የሴቶች እኩልነት አመለካከት ሴቶችን ከቤተሰባቸው እቅፍ ወጥተው ተቃራኒ ጾታ

ከሚያገኙበት የሥራ ቦታ እንዲሠማሩ ስለገፋፋቸው፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተቃራኒ ጾታ ግንኙነትን በመፍቀዳቸው፣ የመገናኛ ብዙኃን (ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ድረ- ገጾች፣ ፊልም…) ተጽዕኖ፣ በከተሞች መስፋፋት የተነሣ በአንድ ሥፍራ በርካታ ማኅበረሰቦች በመኖራቸው የሚፈጠር የተቀራረበ የሕይወት ልምምድ እንዲሁም የቤተሰብ ሓላፊዎች ክትትል ማነስ ጉዳዩን እንዲጨምር አድርጎታል፡፡

## 3. ጾታዊ ቀጠሮ ስሕተት የሆነበት ምክንያት

### *ሀ. ለፈተና የሚጋብዝ በመሆኑ፡-*

ከላይ የጠቀስናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እንደሚያስረዱን ከጋብቻ በፊት ያደረጉት ጾታዊ ግንኙነት ለኃጢአት እና ለዝሙት እንደዳረጋቸው ይገልጻሉ፡፡ (ዘፍ.፴፱÷፩-፫፣ መሳ.፲፬-፲፮) ከዝሙት ለመጠበቅ ጋብቻ ዓይነተኛ መፍትሔ ሲሆን ጾታዊ ቀጠሮ ግን ለፈተና ይገፋፋናል፡፡ ወደ ሰማዩ አባታችን ስንጸልይ ***"ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን"*** እንለዋለን፡፡ ማቴ.፮÷፲፫ ***" ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው፡፡ ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት፡፡"*** ፩ኛቆሮ.፯÷፩-፪

### *ለ. ከትእዛዘ እግዚአብሔር የሚያሸሽ በመሆኑ*

ጾታዊ ቀጠሮ ስሜታችንን፣ ፍቅራችንን፣ ኃይላችንን በሙሉ ተቆጣጥሮ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከመጠበቅ ይልቅ በስሜት ተገፋፍተን ወደ ተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ይስበናል፡፡ ስለዚህ ከመንፈሳዊ ድርጊቶች ኅሊናችንን አርቆ የእግዚአብሔርን ሕግ መመልከት አስትቶ ምድራዊ ነገሮችን ብቻ እንድናሰላስል ስለሚያደርገን ስሕተት ነው፡፡ ***"… በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም፡፡"*** ቆላስ. ፫÷፪ በዚህ የወጣትነት ዘመናችን አብዝተን ልናስብ የሚገባን ስለ ፈጣሪያችን ነው፤ ***"በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡፡"*** መክ.፲፪÷፩

### *ሐ. የድርጊቱን ፈጻሚዎች ሕሊና ስለሚጎዳ*

ጾታዊ ቀጠሮ በዘላቂ ዓላማ ላይ የማይመሠረት እና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አክብሮ በጥንቃቄ ስለማይመራ ለውድቀት ይዳርጋል፡፡ በጊዜያዊ ስሜት የሚመራ እንደመሆኑ መጠን ግንኙነቱ ሲቋረጥ በድርጊቱ ተካፋይ የነበሩ ወጣቶች ሕሊናቸው ይጎዳል፡፡ ወጣቶች የብስለት ደረጃቸው ከፍተኛ ባለመሆኑ ያልጠበቁት ነገር ሲከሰት በከፍተኛ የሥነ ልቡና ችግር ውስጥ ይወድቃሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ራስን እስከ ማጥፋት ድረስ ሙከራ ያደርጋሉ፡፡ ክርስቲያን በሰዎች ጉዳት የሚደሰት ባለመሆኑ አላስፈላጊ ጾታዊ ቀጠሮን ባለማድረግ ወገኖቹን ከጉዳት ይከላከላል፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ወንድሞቻችን እና እኅቶቻችንን ከልብ የምንወዳቸው ከሆነ ከጉዳት ልንጠብቃቸው ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

### *መ. ከፈቃደ እግዚአብሔር የሚለየን በመሆኑ*

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰውነታችን ንጹሕና ቅዱስ እንዲሆን ነው፡፡ ጾታዊ ቀጠሮ ሰውነታችንን በማጉደፍ ከዘላለማዊ ሕይወት የሚያርቀን እና ፈጣሪያችን ደስ የማያሰኝ ስለሆነ ስሕተት ነው፡፡ "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ÷ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ÷" ሮሜ.፲፪÷፩-፪

### *ሠ. መንፈሳችንን የሚያጎድፍ በመሆኑ*

ሰውነታችን በክርስቶስ የከበረ ደም ፈሳሽነት የተዋጀ በመሆኑ በሰውነታችን እግዚአብሔርን ማክበር አለብን፡፡ በሰውነታችን ብቻ ሳይሆን በመንፈሳችንም እግዚአብሔርን ልናከብር ይገባል፤ መንፈሳችን የሰብእናችን ማዕከል ነውና፡፡ "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ***በእናተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ*** እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡" ፩ኛ ቆሮ.፲፱÷፲፱-፳

## ማጠቃለያ፡-

- ጊዜያችንን፣ ኃይላችንን ጾታ ዊ ግንኙነት ላይ በማተኮር አናባክን፡፡ ይልቁንም ለሥጋዊም ሆነ ለመንፈሳዊ ዕድገታችን እንጠቀምበት፡፡
- ሰውነታችንን እና መንፈሳችንን ለእግዚአብሔር ንጹሕ እናድርግ፡፡ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ከሚወስደን መንገድ እንዳንወጣ ጥንቃቄ እናድርግ፡፡
- ራሳችንን ንጹሕ በማድረግ እስከ ቅዱስ ጋብቻ ድረስ እንቆይ፡፡

## ተግባር፡-

- ምን ግንዛቤ ወሰዳችሁ፡፡ በክፍልና በቤተሰብ ተወያይታችሁ ሐሳቡን አዳብሩት፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ጾታዊ ቀጠሮ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ትምህርት መሠረት ስሕተት የሚሆነው ለምንድን ነው?
2. ወጣቶች ራሳቸውን ጠብቀው እስከ ቅዱስ ጋብቻ ለመድረስ ምን ማድረግ አለባቸው?

www.zeorthodox.org

# ቁማር

## አርባ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማዎች ስለ ቁማር አደገኛነት ግንዛቤ ያገኛሉ፤ የሚቀርብላቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"በጽድቅ የሚገኝ ጥቂት ነገር በዓመጽ ከሚገኝ ከብዙ ትርፍ ይሻላል፡፡"*** ምሳ.፲፮፥፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** በትምህርቱ ውስጥ የተሰጡትን ጥቅሶች በሚገባ አንብቡ፡፡

**የመወያያ ነጥቦች፡-** የቁማር ጨዋታ እንደ መዝናኛ ሊታይ ይችላል ? መልካም ነገርን በማሰብ ቁማር መጫወትስ ተገቢ ነው?

**መግቢያ፡-** ቁማር በትንሽ ድካም ብዙ ትርፍ እና ሀብት በማግኘት ለመበልጸግ የሚደረግ የስሕተት መንገድ ነው፡፡ በዓለማችን ላይ በርካታ የቁማር ዓይነቶች ሲኖሩ፤ አሁን አሁን ቴክኖሎጂን በመጠቀም በድረ-ገጾች ላይ ቁማርን ማካሄድ የተለመደ ክሥተት ሆኗል፤ በበርካታ ሀገራትም ሕጋዊነትን አግኝቷል፡፡

የቁማር ጨዋታ ሲጀመር ራስን ለማዝናናት በሚል ሲሆን በሂደት ግን እየቆየ ከጨዋታነቱ በማለፍ ሱስ ይሆናል፡፡ ጊዜን በከንቱ ያባክናል፡፡ በትክክለኛ ጥረት ሠርቶ ከማግኘት ይልቅ በአቋራጭ በሰው ገንዘብ መበልጸግን ቀዳሚ ምርጫ ያደርጋሕ፡፡ ለሥራ አያነሣሣም፡፡ ያሰንፋል፡፡ በርካታ ቤተሰብ በቁማር ምክንያት ተበትኗል፡፡ ይህም የሚሆነው በቁማር ያጣውን ገንዘብ ለማስመለስ በሚያደርገው ተደጋጋሚ የቁማር ጨዋታ ሀብቱን ንብረቱን ያጣል፣ ሚስቱን ያጣል፣ ልጆቹን ይበትናል በጣም ሲከፋም ራሱን እስከ ማጥፋት የሚያስደርስ ከባድ ሱስ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

www.zeorthodox.org

### 1. ከሥነ አመክንዮ /Logic/ አንጻር ቁማር ትክክል አይደለም

በአንዳንድ ሀገራት ካለው ሕጋዊነት በመነሣት ከሥነ-አመክንዮ አንጻር "ቁማር ትክክል አይደለም" የሚለውን ሐሳብ የሚቃወሙ አሉ፡፡ ነገር ግን ቁማር ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ማኅረሰቦች ዘንድ ውርጃ፣ ሲጋራ ማጨስ፣ የአልኮል መጠጦችን መጠጣት፣ አደንዛዥ ዕፆችን መጠቀም

ወዘተርፈ…. ተቀባይነት ያላቸው ድርጊቶች ቢሆኑም፤ ይህ የድርጊቶቹን ትክክለኛነት አያመለክትም፡፡ ቁማርም የሚታየው ከዚህ አንጻር ነው፡፡

- ቁማር በራሱ ሱስ ከመሆኑም ባሻገር ፤ ለበርካታ ተያያዥ ሱሶች የሚያጋልጥ ነው፡፡
- ለወንጀል መስፋፋት ምክንያት ነው፡- መቆመሪያ ሥፍራዎች ብዙ ወንጀል እንደሚፈ ጸምባቸው ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡
- ለሴተኛ አዳሪነት ሕይወት መስፋፋት ምክንያት ነው፡፡ ይህም ለፍቺ እና ለቤተሰብ መበተን ዓይነተኛ ምክንያት ነው፡፡
- ብዙዎች ራሳቸውን ለማጥፋታቸው ምክንያት ሆኗል፡፡

## 2. እግዚአብሔርን የማያስደስት ተግባር ነው

እግዚአብሔርን ደስ ከማያሰኙ ተግባራት መካከል ቁማር አንደኛው ሲሆን፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ ምድራዊና የዚህ ዓለም ሥራ ነው፡፡ *"በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ÷ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም፡፡"* ፩ኛ ዮሐ.፪÷፲፮ *"በቀረውስ ወንድሞች ሆይ÷ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ÷ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ÷ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ÷ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ÷ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ÷ በጎነት ቢሆን ምስጋና ቢሆን÷ እነዚህን አስቡ፤"* ፊልጵ.፬÷፰ ቁማር እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን መሆን የሚገቡንን ነገሮች እንዳንሆን የሚያደርገን በመሆኑ ፈጣሪያችንን ደስ አያሰኘውም፡፡

- ቁማር መንፈሳዊ ተግባር ባለመሆኑ እግዚአብሔር አይደሰትበትም፡፡ ኤፌ.፪÷፪
- ቁማር ለመንፈሳዊ ዕድገታችን ምንም የማይጠቅምና በጸጋና በዕውቀት እንዳንበለጽግ የሚያደርገን ነው፡፡ *"በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ፡፡"* ፪ኛ ጴጥ.፫÷፲፰
- ቁማር እግዚአብሔርን የሚያከብር ሥራ አይደለም፡፡ *"ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡"* ፩ኛ ቆሮ.፮÷፲፱-፳

www.zeorthodox.org

## 3. የቁማር ጨዋታ ሥጋዊ ፍላጎት ለማርካት እና ለመበልጸግ ብቻ የሚደረግ የአመጽ ጉዞ ነው

*"ከማንም ብር ወይም ወርቅ አልተመኘሁም፤ እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ…"* ሐዋ.፳÷፴፫ *"ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር*

*ነውና÷ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ።"* ፩ኛ ጢሞ.፮÷፲

ቁማር ራስን ለማዝናናት ብቻ የሚደረግ ባለመሆኑ *"ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና÷ ገንዘብን የሚወዱ ትምክህተኞች ትዕቢተኞች ተሳዳቢዎች ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ የማያመሰግኑ ቅድስና የሌላቸው.... ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ።"* ፪ኛ ጢሞ.፫÷፪

4. እግዚአብሔር ስለ ቁማርተኞች ምን ይላል?

*"ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእክቴ ጻፍኩላችሁ። በጠቅላላው የዚህን ዓለም ሴሰኞችን÷ ወይም ገንዘብን የሚመኙትን ነጣቂዎችንም ወይም ጣዖትን የሚያመልኩትን አላልሁም፤ ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር። አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጠዖት የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ፤ እንደዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ።"* ፩ኛ ቆሮ.፭÷፲-፲፩*"..ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም"* ፩ኛ ቆሮ.፮÷፲፣ መዝ.፲÷፪፣ ፩ኛ ጢሞ.፫÷፫

5. ቁማርተኝነት ለስንፍና ይዳርጋል

ቁማርተኝነት ሰዎች ሳይለፉና ሳይደክሙ የሌላ ሰውን ሀብትና ገንዘብ በማጭበርበር ለማግኘት የሚደረግ ክፉ ተግባር ነው። በማይገባ መንገድ በሰው ሀብትና ንብረት በአቋራጭ ለመበልጸግ የሚደግ ጥረት ነው። ይህ ደግሞ ሠርተን መብላት የምንችል ስንሆን ራሳችንን ወደ ስንፍና መንገድ የሚመራ ክፉ ድርጊት ነው።*"በችኮላ የተከማቸች ሀብት ትጎድላለች፤ ጥቂት በጥቂት የተከማቸች ግን ትበዛለች።"* ምሳ.፲፫÷፲፩፣፳፩÷፳፭-፳፮ *"በአሁኑ ዘመን ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለ ጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው።"* ፩ኛ ጢሞ.፮÷፲፯፣ ኤፌ.፬÷፳፰

ያለድካማችን ምንም ዐይነት ዋጋ እንድናገኝ ፈጣሪያችን አይፈልግም፤ በሚሠራ ሰው ግን ደስተኛ ነው። *"ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና።"* ሉቃ.፲÷፯

www.zeorthodox.org

6. ለመልካም ነገር ታስቦ የሚደረግ ቁማር ኃጢአት ነው

ብዙ ጊዜ መልካም ነገር አስበን የምንሠራቸው ድርጊቶች *‹‹ውጤቱ ለመልካም ከሆነ ክፋቱ ምንድን ነው?››* ልንል እንችላለን። ነገር ግን የድርጊቶች መልካምነትና ክፋት የሚመዘነው ድርጊቶቹ ባላቸው አቅዋም እንጂ ከሚፈጸሙበት ምክንያት አንጻር አይደለም። ስለዚህም ቁማርም ለመልካም ነገር ታስቦ ቢደረግ እንኳን ኃጢአትና የሚያስጠይቅ ድርጊት ነው። ‹‹ *እንዲህ አይሁን፤ እንዲህ*

*ቢሆን እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈረዳል? ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም?›*
ሮሜ. ፫፥፭-፲፡፡

## ተግባር፡-

- ❖ ቁማር ሱስ የሚሆን አደገኛ ድርጊት በመሆኑ በጨዋታ መልክ በድርጊቱ ከመዝናናት ተቆጠቡ፡፡
- ❖ ለመልካም ተብሎ የሚደረግ ቁማር ባለመኖሩ ለመልካ ነው በሚል ስሜት ከሚደረግ ቁማር ራሳችሁን ከልክሉ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ቁማር ከሥነ አመክንዮ (Logic) አንጻር ትክክል አለመሆኑን አስረዱ፡፡
2. ቁማር እግዚአብሔር የማይደሰትበት ተግባር የሆነው ለምንድነው? መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ በማቅረብ በተማራችሁት መሠረት ግለጹ፡፡
3. ቁማር ለስንፍና የሚዳርገው እንዴት ነው? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የሕይወት ምርጫ(አንድ)

## አርባ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ሕይወት ምርጫ ይገነዘባሉ፤ ጥያቄዎችን በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ "*** ዘዳ.፴፥፲፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘዳ.፴፥፱-፳ ፤ ገላ. ፮፥፯-፱፤ መዝ. ፴፬፥፲፪-፳፪

**መግቢያ፡-** ይህ በተከታታይ የምንማረው የሕይወት ምርጫ ትምህርታችን የመጀመሪያ ክፍል ነው፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

#### መሠታዊው የሕይወት ምርጫ

***የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ሕይወቱ በምርጫ የተመላ ነው፡፡*** ሰው ነጻ ፈቃድ ያለው እና ለባዊ (አስቦ አስተውሎ መሥራት የሚችል) ፍጡር ስለሆነ ሕይወቱ በምርጫ የተሞላ ነው፡፡ ይህም ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ ልዩ ጸጋ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ በገነት ሲያኖረው የሕይወት ምርጫ በማሳየት ነበር፡፡ (ዘፍ. ፪፥፲፮-፲፯)፡፡ ሰው ሕይወትን ወይም ሞትን መምረጥ በነጻ ፈቃዱ ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡

***ሰው ለዘላለም በሕይወት የመኖርና የመሞት ምርጫ አለው፡፡*** ሰው በከይሲ ምክር ሞትን መርጦ ከገነት ተባረረ፡፡ በዚህ የፍዳ ምድር ሲኖርም ይህ ምርጫው አልተገታም፡፡ ሕይወትን ያገኝ ዘንድ ሌላ ምርጫ ተሰጥቶታል፡፡ ይህም በወልደ እግዚአብሔር ማመን ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ሕይወት የለም፡፡ ***"በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም"*** ዮሐ.፫፥፴፮

www.zeorthodox.org

***ለሕይወትና ለሞት ያለን ምርጫ በዕለታዊ ድርጊታችንም ይገለጣል፡፡*** ከእግዚአብሔር ፍቃድ ውጪ፣ ኃጢአትን የሚፈጽም በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ በማለት ብቻ ሕይወትን አያገኝም፡፡ ***" በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡"*** ማቴ.፯፥፳፩ ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስም ***" አትሳቱ፤***

*እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል። ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት።" ገላ.፮፥፯-፱*
ለዚህ ነው መዝሙረኛው ዳዊት ሕይወትን እንድንመርጥ፡- *"ሕይወትን የሚፈቅድ ሰው ማን ነው? በጎንም ዘመን ለማየት የሚወድድ ? አንደበትህን ከክፉ ከልክል፥ ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይናገሩ። ከክፉ ሽሽ መልካምንም አድርግ ሰላምን እሻ ተከተላትም።"* ሲል የመከረን። መዝ.፴፬፥፲፪-፲፬

*ምድራዊ ኑሮአችንም በምርጫችን የተመሠረተ ነው።* ምድራዊ ባለጠግነት እና ድኅነት፣ እውቀትና መሀይምነት፣ የኑሮ ዘይቤ በምርጫችን በተመሠረተው ድርጊት ይወሰናል። በርትቶ የተማረ፣ ተግቶ የሠራ፣ አጋጣሚዎችን ለመልካም ያዋለ፣ የሚያስቀድመውንና የሚያስከትለውን የሚያውቅ፣ አስተውሎ የሚያደርግ ይዘገያል እንጂ ታላቅ ቦታ መድረሱ አይቀርም። ዳዊት እረኛና የምስኪን ቤተሰብ ልጅ ነው። *አስተውሎ ያደርግ ነበርና - ታላቅ ንጉሥ ለመሆን* በቃ። ፩ኛ.ሳሙ.፲፰፥፳ በተቃራኒው የጠፋው ልጅ አባካኝ ስለነበር ከአባቱ የወረሰው ኃብት አልጠቀመውም" *ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፥ ከዚያም እያባከነ ገንዘቡን በተነ። ሁሉንም ከከሰረ በኋላ በዚያች አገር ጽኑ ራብ ሆነ ፥ እርሱም ይጨነቅ ጀመር። ሄዶም ከዚያች አገር ሰዎች ከአንዱ ጋር ተዳበለ ፥ እርሱም እሪያ ሊያሰማራ ወደ ሜዳ ሰደደው። እሪያዎችም ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ይመኝ ነበር፥ የሚሰጠውም አልነበረም።"* ሉቃ.፲፭፥፲፫-፲፮
ሰዎች በሐሳብና በድርጊት የሚመርጡትን ይቀበላሉ። አጋጣሚዎችንም በአግባቡ ከተጠቀምን መልካም ምርጫ እየመረጥን ነው። ለምሳሌ እናንተ ተማሪዎች ናችሁ። ቤተሰብ አላቸው የምትማሩበት ትምህርት ቤት እና በሰላም ወጥታችሁ የምትመለሱበት ሁኔታ የተመቻቸ ነው። ይህንን ዕድል እንደ ዳዊት በአግባቡ ተጠቅማችሁ ታላቅ ሰው መሆን ወይም እንደጠፋው ልጅ ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ በማባከን መጎዳት በእጃችሁ ያለ ምርጫ ነው። መንፈሳዊነት መልካም የሆነውን ምርጫችንን ለማስተካከል አማራጭ የሌለው መንገድ ነው።

*የሚበልጠውና ተፈትኖ የታየው መልካም ምርጫ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እና መታዘዝ ነው።*

በቃሉ በመኖር የዘላለም ሕይወትና የምድር በረከት አለ። *"የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ፥ በዚህም ሕግ መጽሐፍ የተጻፉትን ትእዛዙንና ሥርዓቱን ብትጠብቅ፥ በፍጹምም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ብትመለስ፥ እግዚአብሔር በአባቶችህ ደስ እንዳለው በመልካሙ ነገር ሁሉ እንደ ገና በአንተ ደስ ይለዋልና አምላክህ እግዚአብሔር በእጅህ ሥራ ሁሉ በሆድህም ፍሬ በከብትህም ፍሬ በእርሻህም ፍሬ እጅግ ይባርክሃል። እኔ ዛሬ የማዝዝህ ይህች ትእዛዝ ከባድ አይደለችም፥ ከአንተም የራቀች አይደለችም። ሰምተን እናደርጋት ዘንድ ስለ እኛ ወደ ሰማይ ወጥቶ እርስዋን የሚያመጣልን ማን ነው? እንዳትል በሰማይ አይደለችም። ሰምተን*

www.zeorthodox.org

*እናደርጋት ዘንድ ስለ እኛ ባሕሩን ተሻግሮ እርስዋን የሚያመጣልን ማን ነው? እንዳትል ከባሕሩ ማዶ አይደለችም። ነገር ግን ታደርገው ዘንድ ቃሉ በአፍህና በልብህ ውስጥ ለአንተ እጅግ ቅርብ ነው። ተመልከት ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፥ ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ። በሕይወትም እንድትኖር እንድትባዛም፥ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባበት ምድር እንዲባርክህ፥ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ። ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ፥ ብትታለልም፥ ለሌሎችም አማልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም፥ ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ። ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባበት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም። በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ። እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፥ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ።”* ዘዳ.፴፥፱-፳፱

## ማጠቃለያ

1. የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተሰጠው መልካምና ክፉን ለመመረጥ የሚያስችል አእምሮ አለው። በዚህ ውድ የእግዚአብሔር ስጦታ ሕይወትን መምረጥ በዚህ ምድር በረከትን፣ በሰማይም የዘላለምን ሕይወት ያስገኛል።
2. በዚህ ምድር የሚኖረን የወደፊት ዕጣ ፋንታችንና ዘላለማዊ ሕይወታችን የምርጫችን ውጤት ነው።

## ተግባር

ምርጫችንን ቃሉን በመስማትና እና በማንበብ ከእግዚአብሔር ጋር እናድርግ።

### *ጥያቄዎች:-*

1. ሰው ከተፈጠረ በኋላ በገነት ሲኖር ከእግዚአብሔር የተሰጠው የመጀመሪያው የሕይወት ምርጫ ምን ነበር? ከመጽሐፍ ቅዱስ እና በተማራችሁት መሠረት ማስረጃ በማቅረብ መልስ ስጡ።
2. ሰው ከገነት የተባረረበት ምርጫው ምን ነበር ? በማን ምክር?
3. ለሕይወት እና ለሞት ሊኖረን የሚችለው ምርጫችን እንዴት ይገለጣል? በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ አብራሩ።
4. በምድር ያለው ኑሮአችን በምርጫችን ላይ የተመሠረተ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? አብራሩ።

www.zeorthodox.org

# የሕይወት ምርጫ(ሁለት)

## አርባ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች በክርስቲያናዊው ሕይወት ስላሉት የሕይወት መንገድ ምርጫዎች ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ"* ፩ኛ ቆሮ.፯፥፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የተሰጡትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡

**መግቢያ፡-** ይህ በተከታታይ መማር የጀመርነው የሕይወት ምርጫ ትምህርታችን ሁለተኛው ክፍል ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የምናየው ምርጫ፤ በክርስትና ያለውን የአኗኗር ምርጫ እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

በአርባ እና በሰማንያ ቀን የተጠመቁ እና የመንግሥተ ሰማያት ተስፈኞች ሆነው የሚኖሩ ክርስቲያኖች በክርስቶስ አምኖ በመኖር በሚገኝ ሕይወት ውስጥ ተጨማሪ የሕይወት ምርጫ ያከናውናሉ፡፡ ይህም በድንግልና (በምንኩስና) ወይም በጋብቻ የመኖር ምርጫ ናቸው፡፡

የክርስትና የመጨረሻው ግብ ርስተ መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ነው፡፡ መንግሥቱን መውረስ የሚቻለው በክርስትና  ሕይወት መኖር ሲቻል ብቻ ነው፡፡ በክርስትና ሕይወት ለመኖር ደግሞ በክርስትናው ዓለም ከሚታወቁት ከእነዚህ ሁለቱ የሕይወት ምርጫዎች/መስመሮች/ አንዱን መምረጥ ሲሆን፤ የመረጥነው የሕይወት መስመር በሚፈቅደው መንገድ መጓዝ ይገባል፡፡

www.zeorthodox.org

በዘመነ ብሉይ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ ወደ እግዚአብሔር የተወሰደው ሄኖክ እና *"አበ ብዙኃን፣ አርከ እግዚአብሔር"* እየተባለ የሚጠራው አብርሃም በተቀደሰ የጋብቻ ሕይወት ኖረዋል፡፡ ሄኖክ በረዥም ዕድሜው የሚታወቀውን ማቱሳላን፤ አብርሃምም በታዛዥነቱ የተመሰከረለትን ይስሐቅን አፍርተዋል፡፡ ዘፍ.፭፥፳፩-፳፭፤ ዘፍ.፳፪፥፩-፱

በሌላው መንገድ ለአምልኮተ እግዚአብሔር እጅግ ቀናዒ የሆነውና ዝናብ እንዳይሰጥ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ሰማይን መለጎም የቻለው ነቢዩ ኤልያስ በድንግልና ሕይወት የኖረ ነበር።

በሐዲስ ኪዳንም ከተመሰከረላቸው ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በጋብቻ ሕይወት የኖረ ሲሆን ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ድንግላዊ ነው። ማቴ. ፰፥፲፬፣ ፩ቆሮ. ፯፥፰

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋብቻንና በድንግልና የመኖርን ሕይወት አስተምሮናል። ማቴ.፲፱፥፩-፲፪ ‹‹*መጋባት አይጠቅምም?*›› ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄም ‹‹*ለተሰጣቸው ነው።*›› ሲል መልሷል። (ማቴ.፲፱፥፲-፲፩) ቅዱስ ጳውሎስም ***"ዳሩ ግን ይህን እንደ ፈቃድ እላለሁ እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም። ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ። እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው፤ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።"*** ፩ኛ ቆሮ.፯፥፯ በማለት ሰዎች የተሰጣቸው እና የአቅማቸውን እንዲመርጡ አስተምሯል። በዚህ መሠረትም ከሁለቱ አንዱን በመምረጥ ካለው መርሐ ተነሥተን እንማራለን።

## የሕይወት ምርጫ መርሖዎች

### ሀ/ በቅድመ ምርጫ መጠንቀቅ

የሕይወት ምርጫችንን እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ የምንኖርበትና የምንጠብቀው ስለሆነ ውስጣችንን በሚገባ ሳንረዳ፣የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳንጠይቅ፣ በአባቶች ምክርና ጸሎት ሳንታገዝ በስሜታዊነት እንዳንገባበት መጠንቀቅ ያስፈልገናል። የሕይወት ምርጫችን ምድራዊ ዓላማን ከማሰብ ብቻ እንዳይሆንም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

### ለ/ በመረጡት ምርጫ መኖር

ከመረጡ በኋላ በምርጫው መጽናት እንጂ ፈተና በመጣ ቁጥር ከፈተና ያመለጥን እየመሰለን ምርጫችንን መለዋወጥ አንችልም። በዓለም ስንኖር በሁለቱም የሕይወት ምርጫዎች ፈተናና መከራ አለ። ጋብቻን የሕይወት ምርጫቸው ያደረጉ ከአብሮነት የሚመነጩ ፈተናዎችን ለማለፍ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። የጋብቻ አብሮነት የራስ ፍላጎቶችን ከትዳር አጋር ፍላጎቶች ጋር በማጣጣም ራስን ለትዳር አጋር ማስገዛትን የሚጠይቅ የአንድነት ኑሮ ነው።

www.zeorthodox.org

ሰዎች አንድ ለአንድ ጸንተው እንዳይኖሩና ለትዳር አጋራቸው ራሳቸውን እንዳያስገዙ ልዩ ልዩ ፈተናዎች ያጋጥሙአቸዋል። እነዚህን ፈተናዎች ሲያልፉ ነው ሰማያዊ ክብርን ሊጎናጸፉ የሚችሉት። ስለዚህ ጋብቻ ከብቸኝነት በረከቶችና ፈተናዎች ወጥተን ወደ አብሮነት በረከቶችና ፈተናዎች የምንገባበት ሕይወት ነው።

በድንግልና /ምንኩስና/ ለመኖር የወሰኑትም ይህንን ሕይወት በመምራት የሚገኙ በረከቶችን ለማግኘት ጽኑ የብቸኝነት ፈተናዎችን ማለፍ እንደሚጠበቅባቸው አስቀድመው ማወቅ አለባቸው። ስለዚህ ያልመረጥነው የሕይወት መንገድ መልሶ እንዳያንጓን ምርጫችንን ከፈቃደ እግዚአብሔር ጋር በጥንቃቄ መመርመር እና መወሰን አለብን። በቅድመ ምርጫ ወቅት በሁለቱም የሕይወት ምርጫዎች ሊኖር የሚችል የሕይወት መርሕና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈተናዎች በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል። በማንኛውም መልኩ መርጠን የገባንበትን ሕይወት አክብረን በመያዝ ሰማያዊ ርስት ለማግኘት መጋደል ያስፈልጋል። ሁለቱም የሕይወት ምርጫዎች በተጋድሎ የእግዚአብሔር መንግሥት የምንወርስባቸው መንገዶች ናቸውና።

**ሐ/ የሌሎችን ምርጫ ማክበር**

ሁለቱም የሕይወት ምርጫዎች በእግዚአብሔር ኅብረት እንድንኖርና መንግሥቱን እንድንወርስ የሚያስችሉ ስለ ሆኑ አንዱ የሌላውን ምርጫ በማክበር የመኖር ግዴታ ይጣልበታል። ከዚህ አልፎ የራስን እያሞገሱ የሌላን እያጣጣሉ ቅድስና አይገኝም። ይልቁንም ወንድማችን ከእኛ የተሻለ መሆኑን ማሰብ እና ትሕትና እንጂ ራሳችንን በትዕቢት ከፍ ማድረግ አይገባም። ***"ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል"*** ማቴ.፲፰፥፩-፬ ***"በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤... "*** ፊልጵ. ፪፥፫-፬።

**መ/ በቂ የትምህርት እና የዝግጅት ጊዜ መኖር**

ለጠቅላላ ዕውቀታችን፣ በምንወስነው በአግባቡ ለመኖር፣ ለማስተዋል እንድንችል እና ለነገ ሕይወታችን ፍሬያማነት ዛሬ በትምህርታችን የምናደርገው ጠንካራ ዝግጅታችንና ጥረታችን ወሳኝ ነው። ወጣቶች ዛሬ በተሰጣችሁ ጊዜ ጠንክራችሁ በሚገባ ተማሩ፣ አስፈላጊውን መረጃና ዕውቀት ጨብጡ።

## ማጠቃለያ

1. እግዚአብሔር እንድንኖረበት የፈቀደልን ሁለት የሕይወት መስመሮች አሉ። እነርሱም በጋብቻ እና በድንግልና መኖር ናቸው።
2. ከሁለቱ አንዱን ለመምረጥ መሠረታዊ ግንዛቤዎችን (መርሖዎችን) አይተናል። እነርሱም፡- በቅድመ ምርጫ ወቅት መጠንቀቅ፣ በምርጫ መኖር እና የሌሎችን ማክበር ናቸው።

www.zeorthodox.org

## ተግባር

በተጠቀሱት ነጥቦች ተወያዩባቸው።

***ጥያቄዎች፡-***

1. ክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው ጸንተው በመኖር ያላቸው የሕይወት ምርጫ ምን ምን ናቸው?
2. በብሉይ ኪዳን በተቀደሰ ጋብቻ በመኖር የተመሰከረላቸውን ሁለት አባቶች ጥቀሱ? የተቀደሰ ጋብቻቸውን ፍሬዎች ገለጹ?
3. በብሉይ ኪዳን በድንግልና ሕይወት ኑሮው የታወቀ አባት ማነው? በምን ይታወቃል?
4. በሐዲስ ኪዳን በተቀደሰ የጋብቻ ሕይወት እና በድንግልና ሕይወት የተመሰከረላቸውን አባቶች፤ በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ ጥቀሱ፡፡
5. በተማራችሁት መሠረት የሕይወት ምርጫ መርሖዎች የተባሉትን በመግለጽ አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የሕይወት ምርጫ(ሦስት)

## አርባ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- *ተማሪዎች የሕይወት መንገድን ለመምረጥ ስለሚያስችሉ መመዘኛዎች ተገንዝበው፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፤ ያብራራሉ።*

**የሚጠና ጥቅስ**፡- ***"ሰው በሚኖርበት ዓለም ላይ ያዘዘውን ሁሉ ያደርግ ዘንድ ፈቃዱ ወደ መራቸው ይዞራል"*** ኢዮ.፴፯÷፲፩-፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- የተሰጡትን ጥቅሶች አንብቡ።

***መግቢያ፡-*** ይህ በተከታታይ የምንማረው የሕይወት ምርጫ ትምህርታችን ሦስተኛው ክፍል ነው። በዛሬው ትምህርታችንም የሕይወትን መስመር ለመምረጥ የሚያስፈልጉንን መስፈርቶች እንመለከታለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

### 2. የምርጫ መስፈርቶች

***ሀ/ የራስን ፍላጎት መገንዘብ:-***

ሰው ከስሜታዊነት ወጥቶ በትክክለኛው የልቡ ትርታ ምርጫውን ማከናወን አለበት። ልቡ (ውሳጣዊ ስሜቱ) በጋብቻ እንዲኖር እየገፋፋው፣ በልጅ ፍላጎት ልቡ እየነደደ፣ የምንኩስና /የድንግልና/ ሕይወትን ቢመርጥ ኋላ በከባድ ፈተና መውደቁ አይቀሬ ነው። ምንኩስናውን ጥሎ ወደ ትዳር ዓለም ለመግባትም ሊወስን ወይም በድብቅ በዝሙት ፈተና ሊወድቅ ይችላል። ልቡናው በድንግልና መኖርን እየሻተ ደግሞ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተገፋፍቶ ሕግ ቢገባ ከጋብቻ የሚገኘውን የደስታ ሕይወት ማግኘት ሳይችል ቀርቶ ዕድሜውን በመወላወል ሊጨርስ ይችላል። ከዚህ አልፎም ትዳርን ጥሎ ልጆችን በትኖ ወደ ገዳም በመግባት ሕይወቱን ሊያመሰቃቅል ይችላል። ስለዚህ ሰው ከማግባቱም ይሁን ከመመንኮሱ በፊት ወደ ኋላ የማይመለስበትን ውሳኔ ሊወስን የሚያስችለውን የልቡን መሻት ማወቅ ፈቃደ እግዚአብሔርን በጸሎት በመጠየቅና የሕይወት ጉዞውን በጥንቃቄ መመርመር እና በዛም ለመመራት መጽናት እና ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

www.zoorthodox.org

***ለ/ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅ:-***

ሰው ሕይወቱ መልካም ሊሆን የሚችለው በፈቃደ እግዚአብሔር ሲመራ ነው። *"ሰው*

*በሚኖርበት ዓለም ላይ ያዘዘውን ሁሉ ያደርግ ዘንድ ፈቃዱ ወደ መራቸው ይዞራል"* ኢዮ.፴፯፥፲፩-፲፪ ጌታችን *"እግዚአብሔርን የሚፈራ ፈቃዱንም የሚያደርግ ቢኖር ያንን እግዚአብሔር ይሰማዋል"* (ዮሐ. ፱፥፴፩) ብሎ ሲያስተምር፤ ወንጌላዊው ዮሐንስም በመልእክቱ *"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል"* (፩ዮሐ. ፭፥፲፬) በማለት ጽፏል። ስለዚህ የሕይወት ምርጫችንን ከመወሰናችን በፊት ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅ ፈቃዱን ማወቅ ያስፈልጋል። ይህም የሚሆነው ልቦናችንን ወደ በጎ መንገድ እንዲመራልን በጸሎት በመጠየቅ ነው።

**ሐ/ የአበው ምክርና ጸሎት:-**

በመግቦቱ ሁሌም የማይለየን አምላካችን የመግቦቱ መገለጫ የሆኑ በምክራቸው የሚመሩን በጸሎታቸው የሚደግፉን አበው ካህናትን ሰጥቶናል። ጸሎታቸውን መጠየቅና ምክራቸውን መቀበል ይጠቅማል። አባቶቻችን "ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው" የሚለውን የወንጌልን ቃል ሲተረጉሙ "በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖር ሰው ነው" ብለው ተርጉመውታል። ሲያብራሩትም "ልመንኩስ" የሚላቸውንም ሆነ "ላግባ" የሚላቸውን "ትንሽ ቆይ" እያሉ ትክክለኛውን የሕይወት ምርጫውን እስኪያውቅ ድረስ ያረጋጉታል። ትክክለኛ ሕይወት እንዲመራም ይጸልዩለታል። ይህ የሚያሳየን የሕይወት ምርጫችንን ለመወሰንና ለማስተካከል የአባቶቻችን ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ነው።

**መ/ አስገዳጅ ተፈጥራዊ ሁኔታዎች:-**

ምንም እንኳ የሰው ተፈጥሮ አንድ ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች ሲወለዱ በጋብቻ ሕይወት ለመኖር የማያስችላቸው ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ሊያጋጥማቸው ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ልቡና በጋብቻ የመኖር ፍላጎት ቢበቅል ልቦናቸውን በማባከን ንጽሕና ከማሳጣት ውጭ በጋብቻ የሚገኙትን በረከቶች ማግኘት አይችሉም። ስለዚህ ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ ጃንደረባ የሆኑትም ሆነ በሰው እጅ አካላዊ ጃንደረባነት ያጋጠማቸው ሰዎች ሕሊናቸውን ንጹሕ አድርገው በሚኖሩበት በምንኩስና በገዳም ቢኖሩ ይመረጣል።

**ሠ/ በቃለ እግዚአብሔር ማደግ:-**

እንደ ክርስቲያን የድርጊቶቻችን እና የእምነታችን መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ መማር፣ መመሪያ ማድረግ እና በጸሎት ማንበብ ውሳኔዎቻችን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ እንዲሆኑ ይረዳናል። ቅዱሳት መጻሕፍትን መማር ሕይወትን በዓላማ ለመምራት ያግዛል። የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ምስጢር የተረዳ፣ በእግዚአብሔር ቃል መነጽርነት ራሱን የፈተሸ ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን አይቸገርም። ከዚህም ጋር በጸሎት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ መዝሙረኛው፤ *‹‹እግዚአብሔር ለሕዝቡ፥ በውስጥዋም ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል።››* መዝ.፹፮(፹፯)፥፮ እንዳለ፤ በእኛ ሕይወት ውስጥ አምላካችን ያለውን ዓላማ እና ፍቃዱን በመጽሐፍ

www.zeorthodox.org

እንድናውቅ ይረዳናል፡፡ ታላቁ እንጦንስ ‹‹*ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንስ ቢያጎድል ምን ይረባዋል፤*›› የምትለው ቃል ማርካው ወደ ገዳም ገባ፡፡

*ረ/ ትክክለኛ ዕውቀት እና ግንዛቤ መያዝ፡፡*

ምንኩስናና ጋብቻ በእግዚአብሔር የተፈቀዱ፣ ጠቃሚና ለብቃት የሚያደርሱ የሕይወት መንገዶች ናቸው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ሰዎች አንደኛውን ሲመርጡ፣ ሌላኛው ስሕተት ይመስላቸዋል፡፡ ከዚህ ስሕተት የሚጠብቀንና መልካም ውሳኔ እንድንወስን የሚያደርገን የጋብቻን ቅድስና ከምንኩስና ቅድስና ጋር እኩል መሆኑን መረዳት፣ የሁለቱን ሕይወት አኗኗር ማወቅ፣ አርዓያ የሚሆኑትን አበው እና እማት ሕይወት እና ዓላማቸውን ማጥናት ናቸው፡፡ ይህን ማድረግ ከተሳሳተ ግንዛቤና መረጃ ወጥተን ትክክለኛውን የሕይወት መንገድ እንድንወስን ይረዳናል፡፡

## ማጠቃለያ

1. እግዚአብሔር እንድንኖረበት የፈቀደልን ሁለት የሕይወት መስመሮች አሉ፡፡ እነርሱም በጋብቻ እና በድንግልና መኖር ናቸው፡፡
2. ከሁለቱ አንዱን ለመምረጥ ዝንባሌን መረዳት፣ ጸሎት፣ ምክረ አበው እና ተፈጥሯዊ ሁናቴዎች ለምርጫችን ወሳኝ ናቸው፡፡

## ተግባር

ስለ መመዘኛዎቹ ተወያዩ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

*መምህር ተማሪዎችዎ ከዚህ በታች በተሰጠው ርእሰ ጉዳይ ላይ በተማሩት መሠረት ጥናት አድርገው ሐሳባቸውን በመግለጽ ጽሑፍ አቅርበው በክፍል ውስጥ እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡*

1. የሕይወት ምርጫ መስፈርቶች
   - የራስን ፍላጎት መገንዘብ
   - ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅ
   - የአበው ምክርና ጸሎት
   - የተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች አስገዳጅ ተፅዕኖ
   - በቃለ እግዚአብሔር ማደግ መኖር

www.zeorthodox.org

# የሕይወት ምርጫ(አራት)

## አርባ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- ተማሪዎች ስለ ጋብቻና ምንኩስና ሕይወት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠኑ ጥቅሶች**፡-*"መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን"* ዕብ.፲፫፥፬

*" እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል፡፡ የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም፡፡"* ፪ኛ ጢሞ.፪፥፫-፬

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ስለ ጋብቻ የተሰጡ ተከታታይ ትምህርቶች፤ በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ (Zeorthodox.org) ፤ የተሰጡትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡

**መግቢያ**፡- ይህ በተከታታይ ስለ ሕይወት ምርጫ የምንማረው ትምህርታችን አራተኛው ክፍል ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ጋብቻና ምንኩስና ምን መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

1. የጋብቻ ሕይወት

*"መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን"* ዕብ. ፲፫፥፬

*"እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ ልደትም ርኲሰት እንደሌለበት እንናገራለን"* አመክንዮ ዘሐዋርያት፡፡ ከሁለቱ የክርስትና የሕይወት ምርጫዎች አንዱ የጋብቻ ሕይወት ነው፡፡ የጋብቻ ሕይወት የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ተስማምተውና ተፈቃቅደው የሚመሠርቱት የአንድነት ኑሮ፣ የተቀደሰ ሕይወት ነው፡፡ እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ እና በአምላካዊ መግቦቱ የመሠረተው ይህ የአብሮነትና የአንድነት ሕይወት መለኮታዊ ዓላማ ያለው ታላቅ ምስጢር ነው፡፡ ይህን ታላቅ ምስጢር ጌታችን ኢየሱስ፤ *"ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው"* ማቴ.፲፱፥፭-፮ በማለት ሲገልጠው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ *"ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡ ይህ ምስጢር ታላቅ ነው፡፡"* ኤፌ.፭፥፴፩-፴፪ ሲል ያደንቀዋል፡፡

www.zeorthodox.org

*መፋታት አይፈቀድም። "ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።"* ማቴ.፲፱፥፱

***የጋብቻ ዓላማ - የጋብቻ ዓላማዎች ሦስት ናቸው***

***ሀ/ ዘርን መተካት፡-*** ይህ የጋብቻ ዓላማ የእግዚአብሔር *መለኮታዊ መግቦቱ* (Providence) ጥበቃና አብሮነት /Preservation and Concordance/ *መገለጫ* ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ራሱን እንዲጠብቅ /ዘርን በመተካት/ እና ከሱ በታች ያሉትን ሌሎች ፍጥረታትን እንዲጠብቅ ነው። ***"እግዚአብሔርም አለ፡ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፡ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው"*** ዘፍ.፩፥፳፮-፳፰ ***"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው"*** ዘፍ. ፪፥፲፭

***ለ/መረዳዳት፡-*** የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ያገኙት ታላቅ ሀብት ነው። ጋብቻም የዚህ ማስፈጸሚያ ዋናው ተቋም ነው። ይህንንም በሚከተሉት ማስረጃዎች ታያላችሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ፤ ***"እግዚአብሔር አምላክም አለ፡ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት"*** ዘፍ. ፪፥፲፰ በማለት ይመሰክራል። ጳውሎስም ባልና ሚስት እየተረዳዱ እና እየተፈቃቀዱ እንዲኖሩ፤ ***"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ። ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ"*** ፩ቆሮ.፯፥፫-፬ በማለት ያዛቸዋል። በመክብብም እንዲህ ተጽፏል፡- ***" ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል። ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት።"*** መክ.፬፥፱-፲

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ኦሪት ዘፍጥረትን ሲተረጉሙ የባልና ሚስትን *መረዳዳት* በአራት ከፍለውታል። አንደኛው ስሜትን /ፍላጎትን/ የመጋራት ርዳታ ሲሆን ***"በአቅልሎተ ክበደ ዋዕይ"*** በማለት ተገልጿል። ሁለተኛው ልጅን *መውለድ* ነው። ይህ መረዳዳት የመጀመርያው ውጤት ነው። እንዳቸው ከሌሉ ራስን *መተካት* አይቻልም። ሦስተኛው መረዳዳት የሥራ መረዳዳት ሆኖ ኢኮኖሚያዊ ርዳታ ተብሎ ሊገለጥ የሚችል ነው። አራተኛው ደግሞ ***"ብቻ ከመኖር"*** መዳን ነው። ብቸኝነት ከባድ መከራ ነው። ከትዳር አጋር ጋር በመኖር የሚገኝ በመጋራት መረዳዳት አለ። አበው፤ ***ብቻ መኖር ጽኑዕ ገድል ነው፤*** ሲሉ ገልጠውታል። (ኦሪት ዘፍጥረት አንድምታ) ይህም በጠቢቡ ሰሎሞን የተባለውን ያስታውሰናል። ***"አንድ ሰው ብቻውን አለ፥ ሁለተኛም የለውም ልጅም ሆነ***

www.zeorthodox.org

***ወንድም የለውም ለድካሙ ግን መጨረሻ የለውም፥ ዓይኖቹም ከባለጠግነት አይጠግቡም። ለማን እደክማለሁ፥ ሰውነቴንስ መልካሙን ነገር ለምን እነፍጋታለሁ? ይላል። ይህም ደግሞ ከንቱ ነገር ክፉም ጥረት ነው።"*** መክ.፬፥፰

የማኅበረ ሰብ ሳይንስ ምሁራን፤ ***"ሰው ማኅበራዊ እንስሳ ነው"*** ይላሉ። ይህ ማለት አብሮ እየተረዳዳ እየተጋገዘ የሚኖር ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክም ሲፈጥረው ሰው ለሰው ጠላቱ ምቀኛው አድርጎ ሳይሆን ረዳቱ አድርጎ ነው።

**ሐ/ ከፈተና ለመራቅ**

ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዲችል ከፈተና መጠበቅ አለበት። ከፈተናዎች አንዱ ደግሞ የዝሙት ፈተና ነው። ስለዚህ ሰዎች ራሳቸውን ገዝተው ንጽሕናቸውን ጠብቀው መኖር የማይችሉ ከሆነ በዝሙት ከሚመጣ ፈተና ለመጠበቅ መጋባት እንዳለባቸው መጽሐፍ ያዛል። ***"ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር፥ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው። ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት"*** ፩ቆሮ. ፯፥፩-፪ ***"ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ። እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው፤ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።"*** ፩ቆሮ፯፥፰-፱

## 2. የድንግልና /የምንኩስና/ ሕይወት

***"ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ። እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው"*** ፩ቆሮ፯፥፰

የድንግልና ሕይወት ታሪኩ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ እንደነበረ የእነ ኤልያስ ሕይወት ምስክር ነው። ይሁን እንጂ በጋራ እና በተደራጀ መልኩ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በታላቁ ቅዱስ እንጦንስ ተጀምሮ በቅዱስ መቃርስ/መቃርዮስ/ እና በቅዱስ ጳኩሚስ ተስፋፍቷል።

ድንግልና /የምንኩስና/ ሕይወት መላእክትን የሚመስል የትሩፋት ሕይወት ነው። ***"መነኮሳት ምድራውያን መላእክት ሰማያውያን ሰዎች ናቸው። ... Monks are earthly angels and heavenly humans "*** ይህም የሆነው ተገደው ሳይሆን ወደው ከሴት /ከወንድ/ ርቀው ንጽሕ ጠብቀው ፈቅደው የሚኖሩት ሕይወት ስለሆነ ነው። የምንኩስና መነሻው ***"ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ"*** (ማቴ.፲፱፥፳፩) ያለው የጌታችን ቃል ነው።

www.zeorthodox.org

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በድንግልና/ሳያገቡ/ መኖር መልካም እንደሆነ እና ያላገቡ ሰዎች እንደ እርሱ በድንግልና እንዲኖሩ፤ ***"እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው"*** ፩ቆሮ.፯፥፰ ብሎ ከመከረ በኋላ፤ ምክንያቱን ***"ነገር ግን ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል፤ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፥ ልቡም ተከፍሎአል። ያልተጋባች ሴትና ድንግል በሥጋም በነፍስም እንዲቀደሱ የጌታን ነገር***

***ያስባሉ፤ የተጋባች ግን ባልዋን እንዴት ደስ እንድታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች"*** (፩ቆሮ. ፯ ፥ ፴፪-፴፬) ሲል ገልጦታል። ለመንፈስ ልጁ ለጢሞቴዎስ የመከረውም ይህንኑ ነው። ***" እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል። የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም።"*** ፪ኛ ጢሞ.፪ ፥፫-፬

የምንኩስና መርሖዎች /Principles of Monasticism/

ሀ/ ከጋብቻ መራቅ /Celibacy/

ለ/ መታዘዝ ወይም እሺ ማለት/Obedience/

ሐ/ ለብቻ ሆኖ መመሰጥ/Meditation in Seclusion/

መ/ የእጅ ሥራ መሥራት /Manual Labor/

ሠ/ ራስን ድሀ ማድረግ(የግል ሀብት አለመሰብሰብ) /Self chosen poverty/

በተጨማሪም በመጽሐፈ መነኮሳት የሚከተለውን የምንኩስና አኗኗር የውዴታ ግዴታ አለ። ***"እስመ ሥርዓተ ምንዅስና በኀበ አበው ለኀበ ሠለስቱ ክፍል። ኀድዓት ምስለ ተጋድሎ፣ ወደዌ ምስለ አኰቴት፣ ወተልእኮ ምስለ ፍስሐ ወጥብዓት - በአባቶች ዘንድ ያለች ሥርዓተ ምንኩስና በሦስት ክፍል ናት ብቸኝነት ከተጋድሎ ጋር፣ መከራን ከምስጋና ጋር መቀበል፣ በደስታና በትጋት መታዘዝ"*** (ፊልክስዩስ ክፍል ፩፣ ተስእሎ ፩፣ ገጽ 5)

## ማጠቃለያ

❖ ጋብቻና ምንኩስና ፣ መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ግዴታና በረከት አላቸው

## ተግባር

❖ በትምህርቱ ዙሪያ ተወያዩ።

***ጥያቄዎች፦***

1. የጋብቻ ሕይወት ምንድነው? በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ አብራሩ።
2. የጋብቻ ዓላማዎች ስንት ናቸው? ምን ምን? እያንዳንዱን አብራሩ።
3. የድንግልና (የምንኩስና ሕይወት) ምንድነው? በማብራራት መልሱ።
4. ድንግልና በተደራጀ ሁኔታ ሥርዓት ይዞ የተጀመረው መቼ ነው? ማን ጀመረው? ያስፋፉትስ እነማናቸው?
5. የምንኩስና ሕይወት መርሖዎች ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት

# አርባ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ራስን ለእግዚአብሔር ስለ መስጠት ግንዛቤ ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትፈልጉ ዘንድ ልባችሁንና ነፍሳችሁን ስጡ"*** ፩ዜና.፳፪፥፲፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ምሳ.፳፫፥፲፯ ፣ ሮሜ.፲፪፥፩

## መግቢያ

ሰው ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አርፎበት በራሱ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠረ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው ሰው ሁሌም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈጸመ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲኖር ነው፡፡ እግዚአብሔር ኤልሻዳይ (ከሐሌ ኵሉ) መሆኑን በመረዳት ሰው ፈጽሞ ለእግዚአብሔር መታዘዝና መገዛት አለበት፡፡

### ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ምንድን ነው? ሀብታችንን ወይስ ራሳችንን ?

ከእኛ አንዳች ይቀበል ዘንድ እግዚአብሔር ድሀ አይደለም፤ ቁሳዊ ስጦታችንን ይመኝ ዘንድም ቁሳዊ አይደለም፡፡ ***"ሕዝቤ፥ ስማኝ፥ ልንገርህ እስራኤልም፥ ስማኝ፥ ልመስክርብህ አምላክስ እኔ አምላክህ ነኝ፡፡ ስለ ቍርባንህ የምዘልፍህ አይደለሁም፤ የሚቃጠል መሥዋዕትህ ሁልጊዜ በፊቴ ነው፡፡ ከቤትህ ፍሪዳን ከመንጋህም አውራ ፍየልን አልወስድም፣ የምድረ በዳ አራዊት ሁሉ በሺህ ተራራዎች ያሉ እንስሶችም የእኔ ናቸውና፡፡ የሰማይን አዕዋፍ ሁሉ አውቃለሁ፥ የምድረ በዳ አራዊትም በእኔ ዘንድ ናቸው፡፡ ብራብም ለአንተ አልነግርህም፥ ዓለምና ሞላው የእኔ ነውና"*** መዝ. ፵፱፥፯-፲፪

በዛሬው ትምህርታችንም ራስን ለእግዚአብሔር ስለ መስጠትና ምሳሌ ስለሚሆኑን ቅዱሳን እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

ወደ ቤተ እግዚአብሔር ስጦታችንን ይዘን የምንሄደው የመታዘዛችንና ራሳችንን ለእግዚአብሔር የመስጠታችን ማረጋገጫ /መግለጫ/ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እንድንሰጠው የሚፈልገው ራሳችንን ነው፡፡ ***"አባቶቻችሁም እንደ ነበሩ አንገተ ደንዳና አትሁኑ፤ እጃችሁንም ለእግዚአብሔር ስጡ፥ ለዘላለም ወደ ተቀደሰው ወደ መቅደሱም ግቡ፥ ጽኑ ቍጣውም ከእናንተ እንዲመለስ አምላካችሁን***

*እግዚአብሔርን አምልኩ።”* ፪ዜና.፴፥፰ *“አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትፈልጉ ዘንድ ልባችሁንና ነፍሳችሁን ስጡ”* ፩ዜና. ፳፪፥፲፱

*ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት የአምልኮ መገለጫ* ነው። ሰው እግዚአብሔርን የሚያመልክ ከሆነ ራሱን ለእግዚአብሔር መስጠት አለበት፤ ሰው ግን ራሱን ለእግዚአብሔር መስጠት ካልቻለ አምልኮተ እግዚአብሔር በውስጡ የለም ማለት ነው።

*ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ሐሳብንና ፍቃድን ለእግዚአብሔር ማስገዛት* ነው። ሐሳብንና ፍቃድን ስለ መስጠት፤ *“ልጄ ሆይ፥ ልብህን ስጠኝ፥ ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ።”* ምሳ.፳፫፥፳፮ በማለት ያስተምረናል።

*ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት* በንስሐ እና በአገልግሎት *መቅረብ* ነው።*“እንግዲሁ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።”* ሮሜ.፲፪፥፩

*ራስን ለእግዚአብሔር የመስጠት መገለጫዎችና ፍሬዎችም* አሉ። ኃጢአትን ድል ማድረግ መቻል፣ ትዕግሥት፣ በመከራ መጽናት፣ ያለንን በእምነት ማካፈል፣ ትሕትናና የመሳሰሉት ራስን የመስጠት መገለጫዎች ናቸው።

**ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ**

**አቤል፡-** አቤል ከሚጠብቃቸው በጎች መርጦ ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት ሰማየ ሰማያት ሊደርስለት የቻለው አስቀድሞ ራሱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ስለ ነበረ ነው። ለዚህ ነው መጽሐፍ *“እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ”* (ዘፍ. ፬፥፬) ብሎ የመሰከረለት። የወንድሙ የቃየን መሥዋዕት ቅድመ እግዚአብሔር ሊደርስ ያልቻለውም አስቀድሞ ቃየን ራሱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ስላልነበረ ነው። *“ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም ”* (ዘፍ.፬፥፫) ተብሎ እንደተጻፈ።

**አብርሃም፡-** “አበ ብዙኃን” እየተባለ የሚጠራው አብርሃም ፍጹም ራሱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ነበር። እግዚአብሔር ይፈትነው ዘንድ፣ *“የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው”* (ዘፍ. ፳፪፥፪) ባለው ጊዜ ሳይሰስት በፍጹም እምነት በመታዘዝ የሚወደው ልጁን በልቡ ሠውቷል። ቅዱስ ጳውሎስ *“አብርሃም በተፈተነበት ጊዜ ይስሐቅን በእምነት አቀረበ፤ የተስፋን ቃል የተቀበለው፣ በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል የተባለለት እርሱም አንድ ልጁን አቀረበ፤ እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው*

www.zeorthodox.org

***እንዲቻለው"*** እንዳለ፤ አብርሃም አባታችን በፍጹም እምነትና መታዘዝ እንዲሁ ነጭ በግ በዕፀ ሳቤቅ ታስሮ ከሰማይ እስኪወርድለት በመታገሥ ራሱን ለእግዚአብሔር ማስገዛቱን አሳይቷል።

**ድንግል ማርያም፡-** እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት ከሚታወቁ ቅዱሳን ቀዳሚ ምሳሌ ናት። እመቤታችን ፍጹም ራሷን የሰጠች መሆኗን መልአኩ ባበሠራት ጊዜ ሕገ ተፈጥሮን መሠረት በማድረግ ***"ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል?"*** ብትለውም ***"ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም"*** በማለት መልሶላታል። እመቤታችንም ***"እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ"*** (ሉቃ.፩፥፴-፴፰) በማለትዋ በፍጹም ቀናነትና ታዛዥነት ራሷን ለእግዚአብሔር በመስጠቷ ቀዳሚ አርአያችን ሆና ትጠቀሳለች። ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት የመጨረሻው ደረጃ ነው።

## ማጠቃለያ

- "ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት እግዚአብሔር በእኛ እንዲሠራ እና ሕይወታችንን እሱ እንዲመራው ራስን አሳልፎ በፍጹም እምነት ለርሱ መስጠት ማለት ነው" እናም ከጊዜአችንና ከገንዘባችን እኩል ቀድሞ እኛነታችንን ለእርሱ እንስጠው።
- ራሳቸውን የሰጡ ኃጢአትን ድል ለማድረግና ያላቸውን ለመስጠት አይቸገሩም።

## ተግባር

- ራሳችሁን ለእግዚአብሔር መስጠትን ተለማመዱ።

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ቀዳሚ ስጦታ ምንድነው? ማረጋገጫውስ ምንድነው?
2. በተማራችሁት መሠረት ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ሁለት አርአያዎቻችንን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ ጻፉ።
3. ከአቤል እና ከቃየን መሥዋዕት ሰማየ ሰማያት ደርሶ እግዚአብሔር የተቀበለው የትኛውን መሥዋዕት ነው? ለምን?

www.zeorthodox.org

# ትዕግሥት

## አርባ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ትዕግሥት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።"* ያዕ. ፩፥፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የተሰጡትን ጥቅሶች አንብቡ። የማቴ.፬፥፩-፲፩ ትርጓሜ ወንጌል።

***መግቢያ፡-*** አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ *"ትዕግሥት"ን በቊሙ፣ መታገሥ፣ መቈየት፣ ታጋሽነት፣ አንዋ መንፈስ"* የሚል ፍቺ ሰጥተውታል። ብዙውን ጊዜ ወጣቶች በትዕግሥት ማጣት ይፈተናሉ። በዚህ ምክንያትም ነገ ሊመልሱት የማይችሉትን ስሕተት ይሠራሉ። ሆኖም በክርስትናችን በሚገባ መረዳት ካለብንና ከምንፈጽማቸው ጉዳዮች አንዱ እና ዋናው ትዕግሥት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበረሐ ሰይጣንን ድል የነሳው በትዕግሥት ነው። ከእኛም ትዕግሥት ይጠበቃል። የዛሬው ትምህርታችንም ስለዚህ ይሆናል።

### የሳምንቱ ትምህርት

ትዕግሥት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። አምላካችን እግዚአብሔር ከሚታወቅባቸው መገለጫዎቹ አንዱ ታጋሽነቱ ነው። ሁሉን ማድረግ ሲችል ዝም ይላል፤ ፈጥኖ መቅጣት ሲችል ይራራል። ሰው እንደሚቸኩል እግዚአብሔር ቢቸኩል ኖሮ ከቅጣት የሚያመልጥ ሰው ባልተገኘም ነበር። *"እግዚአብሔር ታጋሽና ምሕረቱ የበዛ፥ አበሳንና መተላለፍን ይቅር የሚል"* ዘኍ.፲፬፥፲፰ *"እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ ነው፥ ኃይለኛም ታጋሽም ነው፥ ሁልጊዜም አይቈጣም"* መዝ.፯፥፲፩ *"አንተ ቸርና ይቅር ባይ፥ ታጋሽም፥ ምሕረትህም የበዛ ከክፉው ነገርም የተነሣ የምትጸጸት አምላክ እንደ ሆንህ አውቄ ነበርና"* ዮና.፬፥፪ *"የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ"* ሮሜ.፲፭፥፭ *"ጌታም ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ወደ ክርስቶስም ትዕግሥት ልባችንን ያቅናው"* ፪ተሰ. ፫ ፥ ፭ *"ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም።"* ፩ጴጥ. ፫፥፳

www.zeorthodox.org

**ቅዱሳን ለክብር የበቁት በመታገሣቸው ነው፡፡-** ቅዱሳን መላእክት የቅድስናን መዓርግ ያገኙት እግዚአብሔር ፈጥሮ በተሰወራቸው ጊዜ፤ ***"ንቁም በበሕላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ"*** በማለት በትዕግሥት ስለጸኑ ነው፡፡ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት የክብርን አክሊል ሊቀዳጁ የቻሉትም በትንቢት፣ በስብከት፣ በገዳም፣ በተጋድሎ፣ በትዕግሥት ስለጸኑ ነው፡፡ ***"እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትሕትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ፡፡"*** ቆላ. ፫፥፲፪ ***"ወንድሞች ሆይ፥ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ፡፡ እነሆ፥ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፥ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና፡፡"*** ያዕ. ፭፥፲-፲፩

### *መቼ ነው የምንታገሠው?*

**ሀ/ በመከራ ጊዜ**

የትዕግሥት አባት እየተባለ የሚጠራው ኢዮብ መከራ ቢደራረብበትም እሱ ግን ሳያቋርጥ በማመስገን እግዚአብሔር የሚያደርገውን በትዕግሥት ይጠብቅ ነበር፡፡ ***"እነሆ፥ ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ ነገር ግን መንገዴን በፊቱ አጸናለሁ፡፡"*** ኢዮ. ፲፫፥፲፭

ከሐዋርያት ሁሉ አብዝቶ መከራ የተቀበለ ቅዱስ ጳውሎስ መከራና ፈተና እንዲያልፉ ተስፋ እያደረገ በመታገሥ በደረሰበት መከራ ይመካ እንደነበረና የወንጌል አገልግሎቱን መከራን ፈርቶ እንዳላቋረጠ፡፡ ***"ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፣ ትዕግሥትም ፈተናን፣ ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን"*** ሮሜ.፭፥፫-፬ በማለት ሲነግረን እኛንም ***"በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ"*** ሮሜ.፲፪፥፲፪ እያለ መከራን እንድንታገሥ ይመክረናል፡፡

**ለ/ በተበደልን ጊዜ**

በደል በደረሰብን ጊዜ ከመማረር እና ለበቀል ከመነሣሣት ይልቅ በትዕግሥት እንድናሳልፍ መጻሕፍት ይመክሩናል፡፡ ትዕግሥት የይቅርታ ልብ እንዲኖረን ታደርጋለች፡፡ ***"እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ፡፡ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፡፡"*** ቆላ.፫፥፲፫

www.zeorthodox.org

**ሐ/ የእግዚአብሔር መልስ የዘገየ በመሰለን ጊዜ**

እግዚአብሔር ምን እንደሚያስፈልገንና መቼ እንደሚያስፈልገን ያውቃል፡፡ ለእያንዳንዱ ሥራውም የሚሠራበት ጊዜ አለው (መዝ.፻፲፰፥፻፳፮)፡፡ አዳም ስሕተቱን አምኖ በተጸጸተ ጊዜ ወዲያው እንዲድን ፈልጎ የነበረ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን 5500 ዘመን አስጠበቀው፡፡

***መታገሥ ለምን ይጠቅማል ?***

*ሀ/* **ፍጹማን ምሉዓን ያደርገናል፡-** *"ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።" ያዕ.፩፥፬*

**ለ/ ከፈተና ለመውጣት፡-** *"ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።" ፩ቆሮ.፲፥፲፫*

*ሐ/* **ምኞታችንን ለመቆጣጠር፡-** *"ልባሞች ስለምትሆኑ በደስታ ሞኞችን ትታገሣላችሁና፤ ማንም ባሪያዎች ቢያደርጋችሁ፥ ማንም ቢበላችሁ፥ ማንም ቢቀማችሁ፥ ማንም ቢኮራባችሁ፥ ማንም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ ትታገሣላችሁና።" ፪ቆሮ. ፲፩፥፲፱-፳*

*መ/* **በእግዚአብሔር ለመመስገን፡-** *"ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፥ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል።" ፩ጴጥ. ፪፥፳*

*ሠ/* **ነፍሳችንን ለማግኘት፡-***"በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ"* ሉቃ. ፳፩፥፲፱

## ማጠቃለያ

- ❖ የትዕግሥት መምህራችን እግዚአብሔር ነው። ቅዱሳን ለክብር የበቁትም በዚህ ነው።
- ❖ ክርስቲያን ሁሌም ትዕግሥተኛ መሆን አለበት።
- ❖ መታገሥ፡- ምሉዕ ያደርገናል፣ ከፈተና በድል ያወጣል፣ ክፉ ምኞቶችን ድል ማድረጊያ መሣሪያ ነው። ይህንን በማድረግም ከእግዚአብሔር ክብርና ምስጋናን እንቀበልበታለን።

## ተግባር

በአራት ቡድን በመከፋፈል የትዕግሥት ፍሬ የሚያሳዩ ታሪኮችን አቅርቡ።

***ጥያቄዎች፡-***

1. ትዕግሥት ማለት ምን ማለት ነው?
2. አምላካችን እግዚአብሔር የባሕርይው በሆነው በታጋሽነቱ ይታወቃል። እንዴት? ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ በተማራችሁት መሠረት ግለጹ።
3. ቅዱሳን ለክብር የበቁት በምንድነው? ምክንያቱን በማብራራት ግለጹ
4. ትዕግሥት ለምን ይጠቅማል?
5. መታገሥ የሚገባን መቼ ነው?

www.zeorthodox.org

# ትሕትና

## አርባ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የመንፈስ ፍሬ ስለሆነው ስለትሕትና ግንዛቤ ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ትምህርት ነው፤ ትሕትናም ክብረትን ትቀድማለች"*** ምሳ.፲፭፥፴፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** የተሰጡትን ጥቅሶች አንብቡ

***መግቢያ፡-*** የአማርኛ መዝገበ ቃላት "ትሕትና" በቁሙ፣ ትሑትነት፣ ዝቅታ፣ ውርደት፣ የልዕልና አንጻር የሚል ፍቺ ይሰጡታል። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትም፤ ራስን ዝቅ ማድረግ ፣ ሌላው ሰው እንዲጠቀም መፈለግ፣ ከራስ ይልቅ ሌላ ሰው እንደሚሻል መቊጠር፤ በማለት ይፈታዋል። ዛሬ ስለትሕትና እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### ትሕትና በእግዚአብሔር ፊት

ሰው የራሱ የሆነ ምንም ነገር የለውም፡፡ ስለዚህ ሁሉም ነገር ካለውና ለሁሉም እንደሚያስፈልገው ከሚሰጥ ጌታ ፊት ራሱን ሊያዋርድ ይገባዋል። በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን በትዕቢት ከፍ ያደረጉ እነ ፈርዖን እነ ናቡከደነፆር ተዋርደዋል፡፡ ኃይላቸው እግዚአብሔር መሆኑን እየመሰከሩ ራሳቸውን ያዋረዱ እነ ዳዊት ግን በእግዚአብሔር ፊት ከብረው ከፍ ከፍ ብለዋል። ***"ሰው ሆይ፥ መልካሙን ነግሮሃል እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ... ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?"*** ሚክ.፮፥፰ የተባለው ለዚህ ነው፡፡

ራሱን በትሕትና ከእግዚአብሔር በታች የሚያዋርድ ከፍ ይላል፡፡***"እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ"*** ፩ጴጥ. ፭፥፮ በሌላም ቦታ ***"በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል"*** ያዕ.፬፥፲ ተብሏል፡፡

www.zoorthodox.org

### ትሕትና በሰው ፊት

ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን አዋርደው በሰው ፊት ትሑት መሆን ያቅታቸዋል፡፡ ነገር ግን ***"እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ"*** ፩ቆሮ. ፲፭፥፱ ከሐዋርያው ቃል በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል በተፈጠረው በሰው ፊትም ትሑት መሆን እንደሚገባን እንማራለን፡፡ አዋቂ ከእርሱ በላይ የሚያውቅ

እንደሌለ እያሰበ በዕውቀቱ ሊታበይ አይገባም፡፡ ካወቀው ይልቅ ያላወቀው ነገር እንደሚበዛ እያሰበ፣ ይልቁንም በባሕርዩ አዋቂ የሆነው እግዚአብሔርን እያሰበ ራሱን ዝቅ ያደርጋል፡፡ ባለጸጋም በሀብቱ ከመመካትና ከመታበይ ወጥቶ በባሕርዩ ባዕል የሆነውን እግዚአብሔርን እያሰበ ሰውነቱን ትሑት ሊያደርግ ይገባዋል፡፡*"እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ፤ የትዕቢትን ነገር አታስቡ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ"* ሮሜ.፲፪፥፲፮

## ትሕትናን ከክርስቶስና ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም እንማር

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *"ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና"* ማቴ.፲፩፥፳፱ ብሏል፡፡ በዕውቀታቸውና በጽድቃቸው የሚመኩትን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ሲገሥጽም *"አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ፡፡ ሊቃችሁ አንድ እርሱም ክርስቶስ ነውና፡፡ ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ፡፡ ከእናንተም የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል፡፡ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፥ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል"* ማቴ.፳፫፥፱-፲፪

ሐዋርያት በአንድ ወቅት ስለ ታላቅነት ተከራክረው ጌታችንን፤ *"በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን?"* ማቴ. ፲፰፥፩ ሲሉ ጠየቁት፡፡ ጌታችን ግን *"እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም፡፡ እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው፡፡"* ማቴ. ፲፰፥፫-፬

በተግባርም ጌታችን ሥጋን ነሥቶ ሰው መሆኑ ፍጹም ትሕትናውን ያሳያል፡፡ ኃያል አምላክ ሲሆን በለበሰው ሥጋ በመስቀል እስከ መሞት ድረስ ትሕትናውን አሳይቶናል፡፡ *"በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን፡፡ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ፡፡"* ፊልጵ. ፪፥፭-፰

ጌታችን በዘመነ ስብከቱ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ካስተማረባቸው በዕለተ ሐሙስ ያደረገው ቀዳሚ ምሳሌ ነው፡፡ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ እነሱም እንደርሱ እንዲያደርጉ አዟል፡፡ *"እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንሥቶ ዳግመኛ ተቀመጠ፥ እንዲህም አላቸው፦ ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ፡፡ እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፡፡ እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና፡፡"* ዮሐ. ፲፫፥፲፪-፲፭

www.zeorthodox.org

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በትሕትናቸው ከታወቁ ፍጥረታት ቀዳሚዋ መምህርት ናት፡፡ ትሕትናዋ በንግግሯና በሥራዋ ብቻ ሳይሆን፤ በሕሊናዋም ነበር፡፡ መልአኩ *"ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ"* ብሎ ሲያመሰግናት *"ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?"* ብላ ታስብ ነበር፡፡

### የትሕትና መገለጫዎች

ሀ/ ወንድማችን ከእኛ እንዲሻል ማሰብ፡- *"ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር"* ፊልጵ. ፪፥፫

ለ/ በአንድ ሐሳብ መስማማት፡- *"እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ፤ የትዕቢትን ነገር አታስቡ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ። ልባሞች የሆናችሁ አይምሰላችሁ"* ሮሜ.፲፪፥፲፮

ሐ/ ለሌሎች መታዘዝ (መገዛት)፡- *"እንዲሁም፥ ጐበዞች ሆይ፥ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።"* ፩ጴጥ.፭፥፭

## ማጠቃለያ

- ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር እና በሰው ፊት በትሕትና ራሳቸውን ዝቅ ሲያደርጉ ፣ ይከበራሉ። ትሕትና መንፈሳዊና ሥጋዊ ክብርን ያሰጣል። በተቃራኒው ትዕቢት ያዋርዳል።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የትሕትና አርዓያዎቻችን ናቸው።

## ተግባር

- በጸሎት እና በሕሊናችሁ የሚኖራችሁ ትሕትና በሰው ፊትም ሊገለጽ ይገባዋል።
- ትሕትና ራስን የማወቅ ማሳያ ነው።

### ጥያቄዎች፡-

1. የ‹‹ትሕትና››ን ትርጉም ግለጹ።
2. በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን በትዕቢት ከፍ አድርገው የነበረና በታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀሱ ምሳሌዎች እነማን ናቸው? መጨረሻቸው ምን ሆነ?
3. ራሳቸውን አዋርደው በፍጹም ትሕትና ኃይላቸውና መመኪያቸው እግዚአብሔር መሆኑን የመሰከሩ ምሳሌዎችን ጥቀሱ? ምን ሆኑ?
4. ጌታችን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትሕትናን በተግባር ያስተማረበት ዕለት መቼ ነው? በዚህ ዕለት ምን አደረገ? ምንስ አዘዘ?
5. ስለ እመቤታችን የትሕትና ቀዳሚ አርአያነት እና መምህርነት በማስረጃ ግለጹ።
6. የትሕትና መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ደብረ ታቦር - ግርማ መለኮት የተገለጠበት

## አርባ ዘጠነኛ ሳምንት

**ዓላማ**፡- ተማሪዎች ጌታችን ግርማ መለኮቱን በደብረ ታቦር እንደገለጠ ያውቃሉ፤ መምህሩ የማሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ** ፡- "የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ " ፪ኛ.ጴጥ.፩፥፲፮

**መግቢያ፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን ዮሐንስንና ያዕቆብን ደብረ ታቦር /የታቦር ተራራ/ ወደ ተባለው ሥፍራ ይዞአቸው ወጣ፡፡ በዚያም አንድ አስደናቂ ነገር ተከሠተ፡፡ የጌታችን ፊት እንደ ፀሐይ ሲያበራ ልብሱም እንደ መብረቅ ብርሃን አንጸባርቆ ነጭ ሆነ፡፡ በዚህ ክብሩ ጌታችን በደቀ መዛሙርቱ ፊት ሲገለጥ ፣ ሙሴና ኤልያስ ተገልጠው ስለ ክርስቶስ ይመሰክሩ ነበር፡፡

ሦስቱ ሐዋርያት ባዩት ነገር ተደነቁ፤ ጴጥሮስም እንዲህ አለ፡- ***" ጌታ ሆይ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ፣ አንዱንም ለሙሴ፣ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ፤ "*** ጴጥሮስ እየተናገረም ደመና ጋረዳቸውና ከደመናው ድምፅ ወጣ፡፡ ***"የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ ወጣ፤"***

ደቀ መዛሙርቱ ይህን ድምፅ ሲሰሙ በግንባራቸው ተደፍተው ወደቁ እጅግም ፈሩ፡፡ ጌታችንም ቀርቦ ***"ተነሡ አትፍሩ"*** አላቸው፡፡ ከክርስቶስም በቀር ማንንም አላዩም፡፡ በየዓመቱ ነሐሴ ፲፫ ቀን ‹‹ደብረ ታቦር›› ብለን በዓሉን እናከብራለን፡፡

## ትምህርቱ

1. **ጴጥሮስ ዮሐንስ እና ያዕቆብ፡-** ከላይ በመግቢያ ታሪክ እንደተማርነው ጌታችን ከተከታዮቹና ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ሦስቱን ብቻ መርጦ ወደ ተራራ ይዞአቸው ወጥቶል፡፡ እነዚህ ሐዋርያትም የምስጢር ሐዋርያት ይባላሉ፡፡ በተያዘበት ሐሙስ ምሽት ጌቴ ሴማኒ በተባለ ቦታ ሲጸልይም ሦስቱን ሐዋርያተ ብቻ ይዞ ነበር የሄደው፡፡
2. **ደብረ ታቦር፡-** በምሥራቃዊ የኢይዝራኤል ሸለቆ ጫፍ ከገሊላ በስተ ምዕራብ 17 ኪ.ሜ. ርቆ የሚገኝ 562 ሜትር ከፍታ ያለው በምድረ እስራኤል የሚገኝ ተራራ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

3. ኤልያስ እና ሙሴ፡- በዚህ ታሪክ የተገለጡት ሁለቱ ነቢያት ሙሴና ኤልያስ ናቸው። ሙሴ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ አውጥቶ የመራ ነቢይ ነው። ኤልያስ ደግሞ ከሙሴ በኋላ የተነሣ ነቢይ ነው። ወደ እግዚአብሔር የተወሰደውም በእሳት ሰረገላ ነበር። ስለዚህ ጌታ በሞት ካለፉት ነቢያት እና በሕይወታቸው ከተሰውሩት መርጦ አምጥቶአል።

4. ግርማ መለኮት፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***"እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚኣብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም። ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ። በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ÷ "*** ፊልጵ.፪÷፮-፰ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ በዚህ ምድር ሲመላለስ ፍጹም ሰው ሆኖ በደካማ አካል ያየነው ክርስቶስ ማንም ከፊቱ ሊቆም የማይቻለው የክብር ጌታ ነው።

ግርማ መለኮቱን ለመጀመሪያ የገለጠውም በደብረ ታቦር ነበር። ይህን የተመለከተው ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲህ ሲል ጽፎልናል ፡-***" የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ ከገናናው ክብር ፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና ፤ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን። "*** ፪ኛጴጥ.፩÷፲፮-፲፰

ጌታችን ሙሉ መለኮታዊ ኃይሉን ቢገልጥ ማንም ማየትና በፊቱ መቆም የሚችል የለምና በደብረ ታቦር የተገለጠውም ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር ነበር።***"እርሱ ብቻ የማይሞት ነው ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻልም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን አሜን።"*** ፪ኛ.ጢሞ.፮÷፲፮ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም ያየውና በተግባር የተረጋገጠውም ይኸው እውነት ነው። ***"በመቅረዞቹም መካከል የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ ÷ እርሱም እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰው ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር። ራሱና የራሱ ጠጉርም እንደ ነጭ የበግ ጠጉር እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ። ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ። እግሮቹም በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር። ድምፁም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበረ። በቀኝ እጁም ሰባት ከዋክብት ነበሩት፤ ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ወጣ፤ ፊቱም በኃይል እንደሚበራ እንደ ፀሐይ ነበረ። ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ። አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ። እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።"*** ራዕ.፩÷፲፫-፲፱

www.zeorthodox.org

5. እንዴት እናከብረዋለን ? ፡- ከዘጠኙ የጌታችን በዓላት አንዱ ደብረ ታቦር ነው። በቅዳሴ ፤ በመዝሙር እና የተገለጠልንን ብርሃነ መለኮት ለማስታወስ ችቦ በማብራት እናከብረዋለን።

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በመለኮታዊ ክብሩ ሲገለጥ ይህ የመጀመሪያው ነበር፡፡ ከእርሱም ጋር ሁለት ታላላቅ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ነበሩ፡፡ ሐዋርያት ቅዱሳንን ያከብሩና ይወዱ ስለነበረም ነው ቅዱስ ጴጥሮስ ለአንተ ለኤልያስ እና ለሙሴ ሦስት ድንኳን እንሥራ ያለው፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን የቅዱሳን ድንኳን፣ የጌታችን የአምላካችን የእግዚአብሔር ማደሪያ ናት፡፡ ለዚህም ነው እግዚአብሔርን በቤተ ክርስቲያን የምናመልከው፡፡ ቅዱሳንንም በሚገባቸው ክብር እናከብራለን፤ እንዲረዱንም እንማጸናለን ፡፡ ***"ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም፡፡"*** ማቴ. ፲÷፵፪

ጴጥሮስ ድንኳን ለመሥራት የፈለገው ከእግዚአብሔር ጋር እና ከቅዱሳን ጋር ለመኖር ስለፈለገ ነው፡፡ እኛም ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ከእግዚአብሔር ጋር፤ ኅልቆ መሳፍርት ከሌላቸው ቅዱሳንና መላእክት ጋር ለመኖር መዘጋጀት አለብን፡፡

## ተግባር

በመንፈሳዊ በዓላትና በትውፊታዊ አከባባራቸው ተሳትፎ ይኑራችሁ፡፡ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘትም መምህራንን ጠይቁ፡፡

### *ጥያቄዎች፡-*

1. ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙሮቹን ጴጥሮስን፣ ዮሐንስን እና ያዕቆብን ይዞአቸው የወጣበት ቦታ ማን ይባላል? የት ይገኛል? በዚያ ቦታ ምን ተደረገ? በዚህ ታሪክ ከነቢያት የተገለጡት እነማን ናቸው?
2. ይህ በዓል በቤተ ክርስቲያናችን ማን ተብሎ ይጠራል? የሚከበርበት ዕለት መቼ ነው?
3. የምስጢር ሐዋርያት ተብለው የሚታወቁት እነማን ናቸው?
4. ጌታችን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግርማ መለኮቱን ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጠው የት ነው? ይህንን አስመልክቶ ቅዱስ ጴጥሮስ የጻፈልን ምን ብሎ ነው?
5. ይህንን ዕለት በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት እንዴት እናከብረዋለን?

www.zeorthodox.org

# ሥርዓተ ማሕሌት

## ሃምሳኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ማሕሌት ግንዛቤ ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤"* ኤፌ.፭፥፲፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ‹‹ያሬድና ዜማው›› በጥዑመ ልሳን

### መግቢያ፡-

ማሕሌት "ሐለየ" ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ነው። ትርጉሙም አሰበ፣ አመሰገነ፣ የብዙ ሰው ዜማ ማለት እንደሆነ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ በተባለው መጽሐፋቸው ተርጉመዋል።

በሥርዓተ ያሬድ ‹‹ማሕሌት›› የሚባለው በበዓላት እና በዕለተ ሰንበት የድጓና የአቋቋም ሊቃውንት በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና ነው።

በዛሬው ትምህርታችን ስለ ማሕሌት እንማራለን።

### የሳምንቱ ትምህርት

አብዛኛውን ጊዜ ማሕሌት የሚባለው በሦስቱ ንዋያተ ማሕሌት ማለትም በከበሮ፣ በጸናጽልና በመቋሚያ ተቀነባብሮ የሚቀርበውን ነው። ያለ ከበሮና ያለ ጸናጽል በመቋሚያ ብቻ የሚፈጸመው አገልግሎት ደግሞ የስብሐተ ነግህ የጾመ ድጓ ቁመት እየተባለ ይጠራል። ይህም በየምዕራፉ ውስጥ የሚገባውን ድጓ ከምዕራፉ መጀመርያ ወይም መጨረሻ ጋር በማያያዝ በመቋሚያ ዝማሜ ስለሚፈጸም ነው። ማሕሌት በሦስቱ የማሕሌት ንዋያት (ማለትም ከበሮ፣ መቋሚያና ጸናጽል) ተቀነባብሮ የሚቀርብ ሲሆን ማሕሌቱ በሚቀርብበት ጊዜ መሠረት በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል።

www.zeorthodox.org

**1/ ዋዜማ/መኃትው/፡-** ዋዜማ የበዓሉን ታላቅነት የሚያበሥር ከዋናው በዓል በፊት የሚውለው ቀን ነው። የዋዜማ አገልግሎት /ማሕሌት/ ሊከናወን የሚችለው (ዋዜማ ዘሠርክ ስለሚል) ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ ነው። ሆኖም በዓሉ በጾም ወቅት ከሆነና በዋዜማው ዕለት ቅዳሴ ካለ እንዲሁም በታላላቅ ገዳማትና አድባራት ቀለሙ ስለሚረዝም ከቅዳሴ በፊት ሊከናወን ይችላል። ሥርዓተ ዋዜማው ደግሞ እንደሚከተለው ይከናወናል።

**የዋዜማ ደወል**:- ዋዜማው ከመጀመሩ በፊት የዋዜማውን መጀመር የሚያበሥርና ሊቃውንት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ የሚያነቃቃ ደወል ይደወላል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ተከፍቶ ማሕሌት ከመጀመሩ በፊት የሚሰማው የደወሉ ድምፅ የተለየና የራሱ የሆነ ዜማ ያለው ነው፡፡

**አስርቆት**:- ደወል ተደውሎ ሊቃውንት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደገቡ ከሊቃውንቱ ወይም ከካህናቱ መካከል በዕድሜ ተለቅ ያሉት አስርቆት በማድረስ ማሕሌቱን በጸሎት ይከፍታሉ፡፡

**ጸሎተ ኪዳን**:- ከአስርቆቱ በኋላ ደግሞ የሰርክ ጸሎተ ኪዳን ይደረሳል፡፡

**የዋዜማ ቀለም**:- ኪዳን ከተደረሰ በኋላ የዋዜማው ቀለም ተቃኝቶ ይጀመራል፡፡ እንደ ሥርዓቱም በዓሉን የተመለከቱ ቀለሞች ተራ በተራ ደርሰው ዋዜማው በሰላምታ (ሰላም ተብሎ) ይጠቃለላል፡፡

2/ **የሌሊት ማሕሌት**:- የሌሊቱ ማሕሌት አገልጋዮቹ ከዋዜማ በኋላ ትንሽ ዕረፍት አድረገው እንደተመለሱ ጀምረው ሌሊቱን ሙሉ የሚያከናውኑት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ አገልግሎትም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ሌሊቱን ሙሉ ያለ ድካም እንደ ቅዱሳን መላእክት አምላካቸውን ሲያመሰግኑ ያድራሉ፡፡ በሌሊቱ ሥርዓተ ማሕሌት የሚከናወኑ ይትበሃሎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**የሌሊቱ ማሕሌት ደወል**:- አፈጻጸሙ እንደ ዋዜማው ደወል ነው፡፡

**የሕብረት ጸሎት**:- ይህ ጸሎት ማሕሌት ከመጀመሩ በፊት በታላቅ አባት የሚከናወን የመክፈቻ ጸሎት ነው፡፡

**ሚካኤል**:- በመሪ/አንሺ/ ወገን "ሚካኤል ሊቀ መላእክት ሰአል በእንቲአነ" ይባላል፡፡ ይህ መቅድመ ማሕሌት ተብሎ ይታወቃል፡፡

**ስምዓኒ**:- በትልቁ አባት ወይም በአንሺው "ስምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ" የሚለውን የዳዊት መዝሙር ተመርቶ በግራና በቀኝ በመቀባበል ይደረሳል፡፡

**ስቡሕ**:- "ስቡሕ ወውዱስ ዘሣረረ ኵሎ ዓለመ በአሐቲ ቃል" የሚለው ከሲኖዶስ የተወሰደ የምስጋና ቃል በቁም ዜማ ተብሎ እንዳበቃ በጸናጽል በቁምና በመረግድ ይደረሳል፡፡ እነዚህ መርገፎች ከተደረሱ በኋላ በዓሉን የተመለከቱ የዕለቱ ቀለም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ደረጃ በደረጃ የሚጸነጸለውን እየተጸነጸለ የሚመረገደውም እየተመረገደ እስከ ፍጻሜው ይደርሳል፡፡(ማሕሌት በስቡሕ ተጀምሮ "ተሣሃልከ እግዚኦ ምድረከ" ተብሎ በሰላም ይፈጸማል፡፡ ተሣሃልከ መስመሩ ሃያ ሰባት ሲሆን ሃያ አራት የአመስጋኞቹ የካህናተ ሰማይ ምሳሌ ሲሆን፤ ሦስት ደግሞ የተመስጋኞቹ የቅድስት ሥላሴ ምሳሌ ነው፡፡) ጥንት ግን ማሕሌት የሚጀመረው ኦሪት ዘፍጥረት የመጀመርያው ምዕራፍ በማንበብ እንደነበረ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡

www.zeorthodox.org

**አመላለስ/ለዘብ/**:- የሌሊት መዝሙርና እስመ ለዓለም ተጸንጽሎ፣ ተመርግዶ እና ተጸፍቶ ካለቀ በኋላ የሚዘመር የማሕሌቱ ክፍል ነው፡፡

**ወረብ:-** መልክ ወይም ዚቅ በአግባቡ ተጸንጽሎና ተመርግዶ ካለቀ በኋላ የሚዘመረው የማሕሌቱ ክፍል ነው። ያለ ከበሮና ጸናጽል ለተወሰነ ጊዜ ከተባለ በኋላ አስረጋጮቹ ካህናትና መርጌቶች /ደብተሮች/ ወደ መካከል ገብተው፤ በከበሮና በጸናጽል አስማምተው፤ መቋሚያቸውን በትከሻቸው አድርገው፤ በአጽሕሶ/በሽብሸባ/ አምላካቸውን ያመሰግናሉ። ምእመናንም ደስታቸውን በዕልልታና በጭብጨባ እየገለጡ ከሊቃውንቱ ጋር አብረው ያመሰግናሉ/በረከቱን ይካፈላሉ/። በዚህ አኳኋንም ከጣዕመ ዝማሬውና ከማሕሌቱ ድምቀት የተነሣ ካህናቱም ሆኑ ምእመናኑ ድካመ ሥጋና ድካመ ሕሊና አይሰማቸውም። የቀኑ ትኩሳት የሌሊቱ ርዝመት ሳይገታቸው በአርያም ያሉ መላእክትን መስለው መላ ሕይወታቸውን የተቀደሰ መሥዋዕት አድርገው ለአምላካቸው ያቀርባሉ።

**አጽሕሶ/ሽብሸባ/:-** የጣዕመ ዝማሬ እንቅስቃሴ ሆኖ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀሉን የሚያስታውሰን እንቅስቃሴ ነው። በአጽሕሶ ጊዜ የሚታየው የካህናቱ አለባበስ (መታጠቂያቸው)፣ የመቋሚያው አያያዛቸው፣ የእግራቸው እንቅስቃሴ፣ ወደ ፊትና ወደ ኋላ መንቀሳቀሳቸው፣ የከበሮው አመታት ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ የደረሰበትን መከራ የሚያሳይ ነው።

## ተግባር

በቤተ ክርስቲያን በሚደርሰው የማሕሌት አገልግሎት ቀርባችሁ በመስማት (በድምጫ) እና በትምህርት ራሳችሁን በማሳደግ በአገልግሎቱ በምስጋናው ተሳተፉ።

***ጥያቄዎች:-***

1. ‹‹ማሕሌት›› ማለት ትርጉሙ ምን ማለት ነው?
2. በቅዱስ ያሬድ ትምህርትና ሥርዓት መሠረት ‹‹ማሕሌት›› ምንድነው?
3. የ‹‹ማሕሌት›› ሦስቱ ንዋያት የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
4. ያለ ከበሮ እና ያለ ጸናጽል በመቋሚያ ብቻ የሚፈጸመው አገልግሎት ምን ይባላል?
5. ማሕሌት በሚቀርብበት ጊዜ መሠረት ሁለት ክፍሎች አሉት? ማን ማን ይባላሉ? በማብራራት ግለጹ።

www.zeorthodox.org

# በንጽሕና መኖር ይቻላል!

## ሃምሳ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከዝሙት ርኩሰት ራሳቸውን ጠብቀው በንጽሕና በመኖር ቅድስናን መካፈልን እንደሚችሉ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ትዕግሥት ታላቁን ኃጢአት ጸጥ ያደርጋልና" መክ.፲÷፬

**ምንባባት፡-** ‹‹ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ›› ፤ በአቡነ ሙሳ የተዘጋጀና በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ።

**መግቢያ፡-** አንዳንዶች ከዝሙት በመራቅ ሕይወታቸውን በንጽሕና የሚመሩ ወጣቶችን እንደ አላዋቂ፣ ዘመናዊነት እንዳልገባቸው ኋላ ቀሮች በመቁጠር እያገለሉ ወደዚህ ሕይወት እንዲገቡ ይገፋፋሉ። በዚህም ምክንያት ብዙ ወጣቶች በዕድሜ እኩዮቻቸው በመገፋፋት ወደ ዝሙት ሕይወት ሳያስቡት ይገባሉ። በሕይወታቸው ከእግዚአብሔር እንዲርቁ፣ ከማኅበረሰቡ በጎ ወግና ባህል እንዲጋጩ ይሆናል። ውጤቱም ለብዙ ችግር እየዳረጋቸው ለጋ ዘመናቸው የተመሳቃቀለ ይሆንባቸዋል።

ወሲብ ተፈጥሯዊ ቢሆንም ጠቢቡ ሰሎሞን "**ለሁሉም ጊዜ አለው**" እንዳለ ፤ በጊዜውና በሰዓቱ የሚፈጸም ነው። ወጣቶች ከፊታቸው የሚጠብቋቸው በርካታ ሓላፊነቶች አሉ። ስለዚህ ሕይወታቸውን በሰከነ መልኩ ሊመሩ ይገባል። በዚህ ትምህርታችን ንጽሕና የምንለውም ከትዳር ውጭ ከሚፈጸም ሩካቤ ሥጋ መጠበቅን ነው።

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. በንጽሕና መኖር ይቻላል!

ሰው በመጀመሪያ ሲፈጠር በውስጡ ካለከፍተኛ ፍላጎት /desire/ ጋር ነው። በዚህ ፍላጎት አማካኝነትም መልካም ድርጊቶችን ይፈጽማል። የኃጢአት ሥራዎችንም እንዲሁ ያደርጋል። አምላክ እስከ መሆን የተመኘውም ይኸው ፍላጎቱ በውስጡ ስላለ ነው። ስለዚህ ሩካቤን የመፈጸም ፍላጎትም በተፈጥሮ የሰው ልጅ ከሚሰማው ስሜቶች አንዱ ነው፤ ጤናማ ፍላጎትም ነው።

www.zeorthodox.org

ነገር ግን በተፈጥሮ ሰው ሩካቤን የመፈጸም ፍላጎት ቢኖረውም፤ ይህንን በመቋቋም ሕይወቱን መምራት እንደሚችል "**ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ።**" በማለት ጌታችን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ራሳቸውን ከሩካቤ ሥጋ በመጠበቅ ስለሚኖሩ ቅዱሳን መነኮሳት /ደናግላን/ ተናግሯል። ማቴ. ፲፱÷፲፪

ሩካቤ *ሥጋ* ምንም እንኳን ተፈጥሮአዊ ቢሆንም፤ በተፈጥሮ ለሰው ልጅ ህልውና እንደሚያስፈልጉት እንደ አየር፣ ውኃ እና ምግብ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ ሰው አየር በማጣት ይሞታል፡፡ ሩካቤን ባያደርግ ግን ይፈተናል እንጂ አይሞትም፡፡ ስለዚህ ከወሲብ በመቆጠብ በንጽሕና መኖር የማይቻል ተደርጎ መወሰድ የለበትም ፤ ውድቀት የሚጀምረው "አይቻልም" ብሎ ከማሰብ ነውና፡፡

ክርስትና ***በሰው የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል፤*** ብሎ ማመን ነው፡፡ ሉቃ.፲፰፥፳፯ በክርስቶስ በማመናችን ኃጢአት፣ ዲያብሎስና ክፉ የሥጋ ምኞትን ድል የማድረግ ኃይል አግኝተናልና፡፡ ከሐዋርያው ጋር ***"ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን "*** ፩ኛ.ቆሮ.፲፭፥፶፯ እንላለን፡፡

የሥጋ ምኞትም ሆነ የሰይጣን ፈተና እንደጥላ ጊዜያዊ ነው፡፡ ጥቂት በመታገስ ያልፋል፡፡ ኃጢአትን በመፈጸም ከሚገኘው ደስታ ይልቅ ድል በማድረግ የሚገኘውን ደስታ በእምነት ተለማመዱት፡፡ ይህን በማድረግም ‹‹***በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል፡፡*** ፩ኛ ጴጥ.፭፥፲

## 2. ንጽሕናን በማጣት የሚከሠቱ ችግሮች

### ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ያሳጣናል

ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከሚያሳጡን የኃጢአት ሥራዎች በመጀመሪያ ያስቀመጠው ዝሙትን ነው፡፡ ***"የሥጋም ሥራ የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት÷ ርኵሰት…እንደነዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡"*** ገላ.፭፥፲፱

የእግዚአብሔርን መንግሥት ከመውረስ በፊት ቀዳሚው ነገር ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ነው፡፡ ስለዚህ ሰማያዊ ኅብረትን ከሚያሳጠን ሥራ በመቆጠብ በጥምቀት ከአምላካችን ጋር የመሠረትነውን አንድነታችንን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ "…**ብልቶቻችሁን የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ አታቅርቡ÷ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ**" ሮሜ. ፮፥፲፪

www.zeorthodox.org

### ለ. ከማኅበራዊ ሕይወት ይለያል

ከጋብቻ በፊት ከተራክቦ መጠበቅ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን አንድነት ማጠንከር ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰባዊ ተቀባይነት ያለው ሕግ ነው፡፡ ሰለዚህም በቤተሰባችን ብሎም በአካባቢያችን ንጽሕናን ጠብቆ እስከ ጋብቻ መቆየት የሚያስመሰግን ምግባር ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ንጽሕናቸውን ያጡ ሰዎች ደግሞ የተናቁ እና እንደ አመንዝራ የሚታዩ ናቸው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ "በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል፤ የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ ነው... ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ።" ፩ኛ ቆሮ.፭፥፩-፪ በማለት ዝሙት ከክርስቲያን ኅብረት እንደሚለይ ሥርዓት ሠርቶአል።

በመጽሐፍ ቅዱስም በነበሩበት ማኅበረሰብ ተቀባይነት እና ተፈላጊነት የነበራቸው ሰዎች በንጽሕና የኖሩ አባቶች ናቸው። ነቢዩ ሳሙኤል በወጣትነት ዕድሜው ራሱን በመግዛት እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘ ከራሱ አልፎ እስራኤልን ለመምራት ተመረጠ። ፩ኛ. ሳሙ. ፪

ሐ. ክርስቶስን ማሳዘን ነው።

*"ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም።"* ፩ኛ ቆሮ.፮፥፲፭ *"ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን ? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።"* ፩ኛ ቆሮ.፮፥፲፱-፳ ዝሙት መስራት በክርስቶስ እና በመንፈስ ቅዱስ ላይ ኃጢአትን መሥራት ነው።

መ. የጤና ቀውስ ያመጣል።

ለአካላዊ እና ሥነ ልቡናዊ የጤና ችግሮች ያጋልጣል፡- በሩካቤ ሥጋ የሚተላለፉ በሽታዎች በዚህ ዓይነቱ በቅድመ ጋብቻ እና በችኮላ በሚፈጸሙ ሩካቤዎች ይብሳል። ከዚሁም በተጨማሪም አብዛኞቹ ሩካቤን ቀድመው የሚጀምሩ ሰዎች አግባብነት ያለውን ደስታ ያጣሉ። ይህም ራሳቸውን በማደንዘዝና ለሰው ወደማይገባ ግብር ይገፋቸዋል። ጤናማ እርካታ ስለማያገኙም ለሥነ ልቦናዊ ችግሮች ይጋለጣሉ።

## 3. በንጽሕና ለመኖር ምን እናድርግ?

ሀ. ወደ ዝሙት ከሚያመሩን ማንኛውም ድርጊቶች መከልከል፡-

ራስን ለኃጢአት በሚዳርግ መንገድ እየተጓዘን እግዚአብሔር ያድነኛል ማለት እግዚአብሔርን በክፉ መፈታተን ነው። ስለዚህ ወደ ዝሙት ከሚያመሩን ፊልሞች፣ ድረ-ገጾች፣ ጓደኞች፣ ቦታዎች ወዘተ መከልከል፤ ራሳችንን በንጽሕና ለመጠበቅ ይረዳናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዲያብሎስ "የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ፥ ወደ ታች ራስህን ወርውር" ሲለው ፤ ክርስቶስ ከመቅደሱ ጫፍ መውረድ ይችል ነበር። ሆኖም ለፈተናው የሰጠው ምላሽ፤ ራስን ወደ ፈተና እየከተቱ እግዚአብሔር ያድነኛል ለሚሉ ሰዎች ትምህርት ይሰጣል። *"ኢየሱስም ፡- ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል አለው"* ማቴ.፬፥፮-፯

www.zeorthodox.org

ለ. ሕሊናን ከኃጢአት ንጹሕ ማድረግ

ሕሊናን በሥራ መያዝ፡-"የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን፤ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን" ፪ኛ ቆሮ.፲፥፭

እንደሚል በሐሳብ የሚመጡ ኃጢአቶችን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ፣ በመጸለይ፣ በመጾም፣ በማጥናት፣ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ድል ማድረግ ይቻላል፡፡

***ብቸኝነትን አለማዘውተር፦*** ሕሊናን ለኃጢአት የሚጋብዘው አንደኛው ብቸኝነት ማብዛት ነው፤ ሰው ብቸኛ ሲሆን ለኃጢአት አሳቦች ይጋለጣል፡፡ ስለዚህ ጊዜያችንን በአግባቡ ለመጠቀም መርሐ ግብር /Schedule/ ነድፈን በሥራ የተሞላ ጊዜ ሊኖረን ይገባል፡፡

***ከኃጢአት ምክንያቶች መሸሽ፦ ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል፡፡*** መዝ.፩፥፩ እንደተባለ ዝሙትን የሚያወሩ ጓደኞች ካሉ መራቅ ያስፈልጋል፡፡ ዝሙት ቀስቃሽ ከሆኑ ቦታዎች፣ ፊልሞች እና ድረ ገጾች ራስን ማሸሽ መልካም ነው፡፡ ዝሙትን መጋፈጥ ትዕቢት ነው፡፡ መሸሽ ድል ይሰጣል፡፡***"ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሹ፥ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል"*** ፪ኛ ጢሞ.፪፥፳፪

## ማጠቃለያ

- ንጽሕና ራስን የመግዛት ውጤት ነው፤ "ራስን መግዛት" ደግሞ ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ በመሆኑ ራሳችንን በመጠበቅ የነፍሳችንንም የሥጋችንን ደኅንነት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡
- "አይቻልም" የሚለው አመለካከት ለውድቀት መንደርደር በመሆኑ፤ ይህንን ክፉ አሳብ "***ለሚያምን ሁሉ ይቻላል"*** ማር.፱፥፳፫ በሚለው የእግዚአብሔር ቃል መሠረትነት ራስን ለእግዚአብሔር ንጹሕ አድርጎ ማቅረብ ለክርስቲያን ተገቢ እና አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡

## ተግባር፡-

- ለዝሙት የሚገፋፉአችሁን ነገሮች ለይታችሁ እወቁ፣ ብትችሉ ማስታወሻ ያዙ ካልሆነም በድንብ ጊዜ ሰጣችሁ ተረዱት፡፡
- ከላይ በተጠቀሱትና እናንተ በምትረዱት የተሻለ እና መንፈሳዊ መንገድ የዝሙትን ጦር ሽሹ በሩንም ዝጉበት፡፡

www.zeorthodox.org

### ***ጥያቄዎች፡-***

1. ራስን ከዝሙት ጠብቆ በንጽሕና መቆየት ይቻላል? እንዴት? ሐሳባችሁን ግለጹ፡፡
2. በንጽሕና ራስን ጠብቆ ለመኖር ምን ማድረግ ይገባል?
3. ከተቀደሰ ጋብቻ በፊት በሩካቤ በመውደቅ ንጽሕናን በማጣት የሚከሠቱ ችግሮች ምን ምን ናቸው?

# በንጽሕና ያሉ ወጣቶች መገለጫ

## ሃምሳ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ንጽሕና ትልቅ ዋጋ ያለው መዝገብ እንደሆነና ለሥጋችንም ሆነ ለነፍሳችን የደስታና የመረጋጋት ምንጭ ስለመሆኑ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ።"* ዘፍ.፴፱፥፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ‹‹ቅድመ ጋብቻ››፤ በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ - zeorthodox.org

**መግቢያ፡-** ከዚህ በፊት በንጽሕና ስለመኖር ተምረናል። በንጽሕና መኖር ማለትም ከዝሙት ርኩሰት ተጠብቆ መኖር መሆኑን ተረድተናል። ይህ እንዴት እንደሚቻልም ከመንፈሳዊው አስተምህሮ አንፃር ተምረናል። በዛሬው ትምህርታችንም የመንፈሳዊው ሰው መገለጫ የሆኑትን እናያለን።

**የሳምንቱ ትምህርት፡-** በወጣትነት ዕድሜ የኃጢአት ማዕበል በከፍተኛ ደረጃ የሚያናውጠን ጊዜ ነው። በመሆኑም የእግዚአብሔር ምሕረት እንዲጎበኘን፣ ቅድስናን፣ ንጽሕናን እንዲያድለን ዘወትር ለእኛም ሆነ ለፍጥረት ሁሉ መለመን አለብን።

በተጨማሪም በረከትን ከፈጣሪ ከዚህ ቀደም እንደ ተቀበላችሁና ፍጹም የደስታ ስሜት ተስምቷችሁ እንደምታውቁ እርግጥ ነው። ይህ አጋጥሟችሁ ካልሆነም በዚህ ዙሪያ ሊያስተምሩን የሚችሉትን የቅዱሳን አባቶቻችንን ገድል በማንበብ ስለ ጉዳዩ ለመረዳት ሞክሩ። ይህን ስታደርጉም የምትረዱት ንጽሕና ለነፍስም ሆነ ለሥጋችን ምን ያህል የደስታ ምንጭ መሆኑን ነው።

**በንጽሕና ያሉ ወጣቶች መገለጫ፡-**

www.zeorthodox.org

1. ስኬታማ ናቸው፡-

በንጽሕና ያሉ ወጣቶች አካላዊ ኃይላቸውን በመጠበቅ አእምሮአዊ ኃይላቸው እንዲዳብር ያደርጋሉ። ይህም ለነገሮች ትኩረት እንዲሰጡ እና ለሚያደርጉት ጥናት ይረዳቸዋል። አካላዊ እና አእምሮአዊ ኃይላት ለትምህርታዊ እና ሙያ ነክ /professional/ ስኬቶች መሠረታዊ ናቸውና። **"እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ።"** ዘፍ.፴፱፥፪ እንደሚል፤ ዮሴፍ ስኬታማ የሆነው ንጽሕናውን ባለማጉደፉ ነበር።

በንጽሕና ያሉ ወጣቶች ጥንካሬያቸው ያልተፍረከረከ እና ዘወትር ምሉዕ፣ ጤናማ፣ በአእምሮ ንቁና ውጤታማ ሆነው የሚገኙ ናቸው። ንጽሕናቸውን በመጠበቅ ጠንካራ ሰብእናን የገነቡ ሆነው ይገኛሉ። በሁሉ ነገር ቁጥብና ራሳቸውን ጊዜያዊ ለሆኑ ፍላጎቶቻቸው ስለማያስገዙ ስሜታዊነት የማይነበብባቸው በረጋ መንፈስ በማስተዋል የሚመሩ ሚዛናዊ ናቸው።

## 2. ግርማ ሞገስን የተላበሱ ናቸው

ኃጢአትን ማዘውተርና መለማመድ ውሳጣዊ ዝለትን (በመንፈስ መዛልን)፣ እውነትን ለመጋፈጥ አለመቻልንና ፍርሃትን ያመጣል። "**ኃጥእ ማንም ሳያሳድደው ይሸሻል፤ ጻድቅ ግን እንደ አንበሳ ያለ ፍርሃት ይኖራል።**" ምሳ.፳፰÷፩ በንጽሕናና በቅድስና ሕይወቱ ከሴት ከተወለዱ ሁሉ በላይ እንደ ሆነ የተመሠከረለት ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ የእውነትን ቃል ንጉሥ ሄሮድስን ሳይፈራ "**የወንድምህ ሚስት ለአንተ ልትሆን አልተፈቀደም**" በማለት ይገሥጸው ነበር። ነገር ግን ምንም እንኳ በሥጋዊ ዕይታ በንግሥና ከፍ ብሎ የሚታየውና የሚከበረው ሄሮድስ ቢሆንም በዘማዊነቱ ምክንያት ያ የንግሥና ሞገስ ከእርሱ ጋር አልነበረም። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን "**ሄሮድስ ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው እንደ ሆነ አውቆ ይፈራውና ይጠባበቀው ነበር።**" ማር.፮÷፲፰-፳ በሕይወቱ ሁል ጊዜ በዕድገት መስመር ላይ ነው፤ ጥፋተኝነት ስለማይሰማው የሚያስፈራው ነገር የለም።

## 3. በነጻነት የተመሉ ናቸው

ኃጢአት ነፍሳችንን በባርነት ቀንበር እንድትያዝ ያደርጋታል። ጌታችን "**ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባርያ ነው።**" እንዳለ ዮሐ.፰÷፴፬፤ ንጹሐነ ልብ ከልማድና ከማንኛውም እስራት የተፈቱ ናቸው። መንፈሳቸውን ንጹሕ በማድረግ የጠላትን ወጥመድ አልፈው በነጻነት ስሜት ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ጉዞአቸውን ያቀኑ ናቸው። በአንድ ወቅት ጌታችን "**ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።**" በማለት እንደ ተናገረ፤ እውነተኛ ነጻነት ከኃጢአት በመላቀቅ የሚኖር ሕይወት ነው፤ ኃጢአትን ለመረጠ ግን በባርነት ቀንበር ለዘላለም እንደተያዘ ነው። ዮሐ.፰÷፴፮

## 4. ደስተኞች ናቸው

www.zeorthodox.org

ፍጹም በእርጋታ የተሞላ፣ ቀጥተኛ እና ያልተወሳሰበ ሰብእና የተላበሱ ናቸው። በኃጢአት መውደቅን ተከትሎ ከሚመጣው እንደ ድብርት /depression/ ያሉ ነገሮች አይታዩባቸውም። ይልቁንም አካላቸው፣ ልቡናና ድርጊታቸው በሙሉ ተስፋን የሚረጩ ናቸው። ደስተኝነታቸው እና ሰላማዊነታቸው ከእነርሱ ጋር ለተገናኘ ሁሉ የሚዳረስ በመሆኑ ከእነርሱ ጋር መሆን ደስተኞች የሚያደርጋቸው ብዙዎች ናቸው።

በንጽሕና ያሉ ወጣቶች ፍጹም ሰላማዊና በእርጋታ የተመላን ሕይወት የሚመሩ ናቸው፡፡ የዚህ ምክንያትም ኃጢአታቸው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም እንደ ተሰረየላቸው ዘወትር ስለሚያስቡ እና አካሄዳቸውን ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት ስለሚያደርጉ ነው፡፡

በተቃራኒው ንጽሕናችንን ካለመጠበቃችን በጭንቀት የተሞላን፣ በውስጣችን ያለውን መክሊት እዳንጠቀም ሰነፍ፣ ለተለያዩ ሥነ ልቡናዊ እና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ሊያውኩ የሚችሉ የተሳሳቱ ድርጊቶችን ባርያ እንድንሆን ያደርገናል፡፡

### 5. መልካም ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው

በኃጢአት ያለ ሰው መልካም ፍሬን ማፍራት አይቻለውም፡፡ ***"እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ነበራችሁ?"*** ሮሜ.፮፥፳፩

ንጽሐ ነፍስ ያደረበት ሰው የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ያፈራል፡፡ በሕይወቱም ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡ "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር÷ ደስታ÷ ሰላም÷ ትዕግሥት÷ ቸርነት÷ በጎነት÷ እምነት÷ የውሃት÷ ራስን መግዛት ነው፡፡"

**ማጠቃለያ፡-** በንጽሕና መኖር፡- ስኬትን፣ ነጻነትን፣ ግርማ ሞገስንና መልካም ፍሬን የሚሰጠን ከሆነ፤ እኛም ለራሳችንና ለሌላው ታምነን በንጽሕና እንኑር፡፡

## ተግባር፡-

❖ በጎ ልምድ ያላቸውን አርዓያ በማድረግ ራሳችሁን በንጽሕና መጠበቅን አስለምዱ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. በንጽሕና መኖር ማለት ምንድነው?
2. በንጽሕና ራሳቸውን የጠበቁ ወጣቶች መገለጫዎቸው ምን ምን ናቸው?
3. የመንፈስ ፍሬዎች ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኝኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፩፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኅሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም።


www.zeorthodox.org

- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት። 2000 ዓ.ም። የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም። አዲስ አበባ ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )። 2000። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ። አዲስ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር። 1996 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት።
- ጎርጎርዮስ(ብፁዕ አቡነ)። 1996 ዓ.ም። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ። አዲስ አበባ። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት)። 19 ዓ.ም። የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው። አዲስ አበባ።
- ዳንኤል ተሾመ። 19 ዓ.ም። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች። አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
-
- Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.
- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)። አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ። የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ።

www.zeorthodox.org

- ጎርጎርዮስ (በብፁዕ አቡነ):: 1981 ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ:: አዲስ አበባ::
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር ):: 2001:: የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ:: አዲስ አበባ::
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን):: 2001ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት:: አዲስ አበባ:: ባናዊ ማተሚያ::
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮፕያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያረጋል አበጋዝ (ዲ/ን):: ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር):: 1997 ዓ.ም:: የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን):: 1998ዓ.ም:: የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች:: አዲስ አበባ:: ሜጋ ማተሚያ ቤት::
- .........:: አዋልድ መጻሕፍት:: ሐመረ ተዋሕዶ::
- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology: Holy Trinity College module/ unpublished./
- Malaty T.Y( Father)Patrology ;


www.zeorthodox.org

- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.
- ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የማዕረግ ቃል ማተሚያ ቤት፡፡
- ነገረ ማርያም
- Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጎሜ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)፡፡ መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 200 ዓ.ም፡፡ መሽኮርመምና ማሽኮርመም፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ቅድመ ጋብቻ፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡፡ 1988፡፡ መጽሕፍተ መነኮሳት፡፡ አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፡፡
- ጥዑመ ልሳን፡፡() ያሬድና ዜማው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)፡፡ ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ፡፡ በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ፡፡


www.zeorthodox.org